
እኛ የጭንቅ ዘመናቶች!!
ጃዩ
፲፱፻፹፱-፳፻፲፬ ዓ. ም

# መቅድም

የሰውን ልጅ ከችግር በላይ የሚንቀው የለም እና ማንም በማንም ላይ ሳይዘባበት መጥፎ የሆነውን ጠላት በታላቁ ሥራው ታትሮ ሊያስወግደው ይገባል፡፡ ሲቀጥል የማከብራችሁ እና የምወዳችሁ በዓለም ላይ ላላችሁ ህዝቦች በሙሉ ታላቅ የሆነውን የሕይወት ማንነቴን ስሰጣችሁ መልካሙን ነገር በማሰብ የተሻለውን ለመጪው ትውልድ ብሎም አሁን ላይ በሰው እስር ውስጥ ያለ ፍላጎቱ የተቀመጠን ፍጥረት ነፃነቱን ባለመውረስ (ባለመሻማት) ለተሻለ የነገ ህይወቱ መርህ እና ዐርዓያ እንድትሆኑት ልባዊ ምኞቴን ለእናንተው ለመቸር ነው፡፡

የደከመ የመሰለኝን የራሴን ሰውነት ሁሌም እንደ  ነስር  እያደስኩ እንደ አበቦች እያፈካሁ እንድኖርበት የዘወትር ሥራዬ በጠጣሩ አለት ላይ እንኳን እኔ ከልፈቀድኩለት ማንም ምንም ሊያደርግ እንደማይችል ከኔ በላይ ከፈጣሪዬ ውጪ ለእኔ ማንም ምስክር የለም፡፡ ይህንን ፍልቃቂ የህይወት ታሪኬን ለምወድህ/ሽ ወንድም ና እህቴ ከትልቁ መዝገቤ ትንሹዋን ዳራዬን ቀንጨብ አድርጌ ሳቀርብልህ/ሽ አንድም ራስህን/ሽን ከእንደዘህ ዓይነቱ የድክመት በሽታ አስቀድመህ/ሽ እንድትድን/ኚ በማሰብ ነው፡፡

ሌላኛው እና ሁሌም ማንም ሊዘነጋው የማይገባው ታላቅ ቁም-ነገር ቢኖር ማንም ሰው ያለጥረት ና ወዙ ሰላሙን ሸምቶ እንደማይኖር በዚህም አውድ የቀረበ የሌላውን ሰብስቦ ከመጨነቅ ላይበሉትም ተመልካአች ከመሆን የራስን ጥቂት የልፋት ውጤት መልካም በሆነው ፍቅር መጠቀም ከተቻለም ላይደረስበት መንገድ ላይፀዳ የልብስ እድፍ ምንም ዋስትና የለውም እና እናንተም የዚሁ መርህ ተሸካሚ ኃያል ሰው እንድትሆኑ በማሰብ ለእናንተው ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው፡፡

የሰው ልጅ ካዳመጠው ከድንጋይም ይማራል እና ከዛም ሳይሆን ባስም ሲል ትውልድ በሥነ-ምግባር፤ በእውቀት ለያዘው ነገር በህይወት እስካለ ድረስ ራሱን አጉል አጉል በሆነ የማይጠቅም አስተሳሰብ እና ድርጊት ሳይጎዳ ጠንክሮ በመሥራት ራሱንም ከፈጣሪው ውጪ ለሌላው ባርያ ሳያደርግ ሌላውንም በባርነት ሳይጨቁን ከተፈጥሮው ውጪ ከምንም ሳያንስ ሳያሳንስ ከብሮ ና አስከብሮ እንዲኖር በማሰብ በጥቂቱ አሐዱ የተባለች ቅንጭብ የህይወት ውጣ ውረድ ተሞክሮ ነች፡፡

የነገሮች ሁኔታ ኮምጨጭ ሲልብህም/ሽም ‹‹ምስማር ሲመቱት ይጠነክራል›› እንደሚባለው ለያዝከው/ሽው ማንኛውም እውነት እስከ መስዕዋትነት ድረስ ብዙ አጋንኜ የኔ ህይወት ሌላ ብርቱ ፈተና ለወደፊቱ ቢጠብቃትም ላለፈው ማንነቴ እንደ እኔ መክፈል እንዳለብህ ነገር ግን እያንዳንዷን ውጣ ውረድ ማሳያህ/ሽ እንዲሆን አዕምሮህ የተዘጋበት በር ባለፉት ጊዜያቶች በቁጭት ተሰባብሮ አንተም ኃያል የራስህ ንጉስ እንድትሆን በዛ የስቃይ ና የሞት መጨረሻ ከሚመስሉት ቀናቶች ውስጥ ተጨንቄ በመጠኑም ቢሆን ተጠብቤ ያቀረብኩልህ/ሽ የተስፋ ሥራዬ ጅማሮ ሆኖ አንተም ካሰብክበት መቻልህን በማሰብ ለውድ እህት ና ወንድሞቼ የቸርኳችሁ የእውነት ስጦታዬ ነው፡፡

ተርፎ ሲሞላህም አስብ፤ አስተውል ግልፅ በሆንክ ቁጥር ነገሮች ላንተ ከሰማይ ፀሐይ እንኳን ላታገኘው የምትችለው ብርሃን ያጎናፅፍሓል ብሎም ነገሮች ሁሉ ማብራሪያ የማይፈልጉ በእሳቱ የተነጠረው ወርቅ ሆነው ወዳንተ ይመጣሉ፡፡ ይህንንም ስልህ ዝብት የመሰለውን ትዝብት ሁሌም ራስህን ገንብተህበት ልትቆምበት መሬት እንዲሆን ግድ ያሻዋል እና የህሌና አስተሳሰብ እንዲሁም ታላቅ የሆነው ትዕግስት ቁጭት ከሆነው ሥራ ጋር እንድታበረታው ልትወድቅ ስትል እንድትደገፍበት በማሰብ የቀረብ የኔው ላንተ/ቺ የይድረስ እጅ መንሻዬ ነው፡፡

## *እኛ!! የጭንቅ ዘመናቶች*

*ቴክኖሎጂ አይተህ እንደምትጠቀምበት በአንዴ ተወልዶ አንዳየኸው አይደለም፡፡ ዓለም ገነት እንኳን ብትሆን ሳታስበው እርጋታን እና ማስተዋልን ከተነጠክ ልክ እንደ ቀድሞ መላዕክቶች እንዳሁኑ ሲኦላውያን ኒፍሌሞች እርኩስ መናፍስቶች ሳታውቀው ከጉርንዱ ሰምጠህ ትቀራለህ፡፡ ይልቁንም ቀስ በቀስ በጠበበ ምርምር ከጥቃቅን ነገር ተነስቶ ትልቅ መሆን መቻል በትልቅነት ትንሽ ነገር የማይረታው መሆኑን ሁላችንም የምናውቀው ሀቅ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ለሁሉም ጊዜ ይፈልጋል እና የሰው ልጅ በነገሮች ላይ በምንም ተገፋፍቶም ይሁን ስሜታዊ ሆኖ በመቸኮል ወደ ውሳኔ ከመብረሩ በፊት አስተሳሰቡን ለአትኩሮት ለግሶ ሺሕ ጊዜ ራሱን ቆሞ እንዲመለከትበት የቀረበ የአትኩሮት ሥራ የድካሜ ውጤት ነው፡፡*

*ከፀሐፊው አብነት ሲራጅ*

# መግቢያ

የሰው ልጅ በመወለድ ውስጥ የሚያተርፋቸው በርካታ ነገሮች አሉት። ከነዛም ውስጥ ዋናው እና ትልቁ ሰው ህይወት ነው። በዚህ ዓለም ውስጥ የራስህን ህይወት በፅኑ ለመምራት የምትሻ ከሆነ የሰውን ማንነት ክብር ልትጠብቅ ግድ ይልኃል። ይህ ሌላኛው የመኖርህ ማፅኛ ሰው ለሆነው የአካልህ ህይወት ታላቅ ንግስና ነው።

በህይወት ጎዳና ሰው ለሆነው ህይወትህ በ*ርግጥ ብዙ ክፋትን እና ደግነትን ልታስተናግድ ወዴታም ግዴታም ሆኖ ትችላለህ፤ ያ! ደግሞ ቆም ብለህ ካስተዋልከው ሰው ያልሆነችው የዓለም ከፊሏ በፈጣሪዋ አንተን ለበጎ ነገር ልታጭህ ከስለት በላይ እንድትሆን በፈተናዋ ልትሞርድህ ላንተ ብቻ የሰጠችህ ሳይሆን ለሌላውም የተሰጠ የበጎ ነገር እጅ መንሻ ሊሆን ይችላል። እንደ እውነቱ ከሆነ አንተ መቼም የህሌናን ሰውነት በህይወትህ ውስጥ ከተሸከምክ አትጠራጠር የአንተ መፈተን ለበጎ ብቻ ነው።

አስተውል በዓለም ላይ አያሌ ድንቅ ነገሮችን የሠሩ ታላላቅ ሰዎች ተፈጥረው ነበር። በ*ርግጥ አሁን ላይ እነዛ ሰዎች አንድ ተክለው ሌላም ነቅለው ውርሳቸውን ባደባባይ አስጥተውልኃል። ስለዚህ አንተ ዛሬ ላይ ስለታላላቆችህ ስታስብ ውስጥህ ምን ይነግርህ ይሆን?! መቼስ ለክፋም ለደጉም ሁሉም በአትኩሮት ዕይታህ የሚወሰን ሆኖ ከእኔ በተቃራኒው ከሆንክ እመነኝ ልንገርህ በህይወት የለሙ። መንፈሳዊ የራሳቸው የእምነት ፅናት ሆኖ ሀሳባቸው እና ሥራቸው ከእኛ ጋር እስከ ዓለም ፍፃሜ ሊደርስ ይችላል። ይህንን ስላችሁ እናንተ ስለምን እንደ ታላላቆቻችሁ ይቺን ዓለም እየኖራችኃት እንደሁ ታውቁትን ይሆን?! አስተውላችሁ አስቡ እያንዳንዷ የምጠት ቀን ስለ እናንተ መስዕዋትነት እየከፈለ ነው። እናንተስ ሰው ስለሆነው ህይወታችሁ ምን እያደረጋችሁለት ይሆን? ወደ ፋሲካው በመሄድ ፋንታ ሁሌም ፋሲካን እየጠበቃችሁ ነውን? ስለምንስ ያልኖርክበትን በሰውነት ሕይወት ያለበስከውንስ ፋሲካ ትመኘውስ ይሆን?!

ዓለም አንተ እና መሰሎችህ መልካምነት ከሌላችሁ ከምኑም ተፈቶ ከመታሰር የምትጠብቁት መበዓ ባይኖራችሁ በደከመው ክፋታችሁ ብቻ ሰነፍ ስለሆናችሁ ምንም ባትጠብቁ ስለሌላው በጎነት ብቻ ኖራችሁ ሳትኖሩ ስለራሳችሁ ትሞታላችሁ። በ*ርግጥ ሰው የሆነውን ሕይወትህን ተላበሰው አልኩህ እንጂ ህይወትን ከተራራ አክብደህ ከሰማይ አርቀህ ስቀለው አላልኩህም። ህይወት በጣም ቀላል እና ሲበዛም ጫጪትዬ ነች። ውበት እንዲኖረው ግን ካላሰብከው ቦታ ጥለኃት ስትፈልግ ከመዋተት ዕድሜህን በከንቱ ከአውላላው ሜዳ በእንቶ ፈንቶው አሳብቀህ አትጨርስ እያልኩህ ብቻ ነው።

ሕይወት ገንዘብ አይደለም። ከፍ ሲልም ከምንም ቦታ የምንሸምተውም ሸቀጥ እንዲሁ አይደለም። ብቻ አንተ እመን እንጂ ህይወት ከህይወትነቱ ውጪ ምንም ሊገዛውም ሆነ ሊሸጠው የሚችል አንዳችም ነገር የለውም። ነገር ግን ቆንጆውን ጠረን ከእፍኙ አውጥቶ መልካሙን መዓዛ ከእውነት ከማንኪያው እየጨለፉ የሚመገቡት ታላቅ መና ብቻ ነው። አስበህ አስተውል የሰው ልጅ ህይወት እስከ ዘላለሙ በዚህ ዓለም አይኖርም እና ዓለምን ተሰናብተህ ለመሄድ ሞት ስታጣጥርህ እሷን ዐይኖችህ እስኪከደኑ የምታስታውስበት አንድ ትንሽዬ ስጦታ ይኑርህ። ስጦታህ ካንተ ውጪ ማንንም አይሻ። ምክንያቱም ሳታስበው የማያስፈልግህ የፈለከው ማንነት የማጥፊያ ማራገቢያው ሊሆንብህ/ሽ ይችላል። በ*ረግጥ ይህንን ስልህ ፈፅመህ ራቀው ሽሸው እያልኩህ አይደለም። ምናልባት የተሸከምከው በስጋ የታጀለ ሆድ ነው እና ደክሞ ሲያለግምህ እንዳትወድቅብኝ በማሰብ ነው። ካልሆነማ አንጀትን ቆንጥጠህ እትሬዎችህን ካጠነከርካቸውማ ጭለማው አስግጎ ጭላንጭሉን ካልጋረደብህ/ሽ ማራገቢያውን እንደ ማንደጃ ላይ ከሰል ማቀጣጠያው ንፋስ ተጠቀምልኝ/ሚልኝ።

## *እኛ!! የጭንቅ ዘመናቶች*

*ዓለምን ናቃት ግን አደራ እንዳትዳፈራት፡፡ ምክንያቱም እሷ ያላንተ የሆነች አንተ ግን ላፍታ እንኳን ያለ እሷ መሆን የማትችል ስትቀር የምትረሳህ አንተም የማታስታውሳት የስጋዊው መንፈስህ ደጅ ብቻ ናት፡፡ በ*ርግጥ ታላቋን ዓለም ስትተኛ፣ ስትነሳ፣ ስትቀመጥ ና ስትሄድ መቼም ቢሆን አንተ ግን በህይወት እስካለህ የስጋህን ምርት አሳዝላ ወደ ላይኛው ስለምትልክህ በአትኩሮት በጥንቃቄ አይተህ አስተዋላት፡፡ ምክንያቱም አንተ ስትሄድ እስከ ዓለም መጨረሻ እሷ ልትዘልቅ ትችላለች እና፡፡*

*እኔ *ምልህ መሬትን ባፈራህባት ሃብቷ ገዝተኃት መኖር እንደቻልከው ሁሉንም በግዞት እንደምትኖር ቢፈረድብህ ስለእውነት እልኃለው/ሻለሁ ከሌሎቹ የዱር አራዊቶች የምትለይ/ዪ ይመስልኃል/ሻል?! አየህ/ሽ ወዳጄ ትልቁ በሽታችን የተሸከምነው ያልከበደን ግን ተደብቆ ሚሳኤሎቹን በሌላው እና በራሳችን ላይ እያስገመገመ ሊያጠፋን የተነሳ ስውር ጠላታችን ትዕቢት እና ትምክተኝነት ነው፡፡ ዕየኝ/ዪኝ ወዳጂ እሱን የበሽታ ባህሪህን/ሽን ሳትረሳው/ሺው በገንዘብህ/ሽ እንኳን የምትገዛው/ዢው ሰው በሆነው የህይወት መንገድ ተገዝቶ ካልተሰጠኽ/ሽ ካንተ/ቺ ድንጋይ እንኳን የከበረ እንቁ ነው፡፡*

*በተለይ እኔ እንደ ወዳጄ የምነግርህ/ሽ የህይወትህ/ሽ ጠላት የሆነውን ወሸት፣ መልካም ያልሆነ ቅናት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ ዘማዊነት፣ ከንቱ ናፋቂነት፣ ትዕቢት፣ ንቀት ና ሥውር ደባዎች ጅርባህ/ሽ መተኛ አልጋቸው እንዳይሆን ሳትቀርብ በሩቁ ሽሻቸው/ሺያቸው፡፡ ከመጡም ላታኖር/ሪ አንቅረህ/ሽ ጣላቸው/ያቸው ይጎዱኃል/ሻል እንጂ አይጠቅሙህም/ሽም እና፡፡ አስተውል/ይ ወዳጄ እነዚህ መጥፎ ሽክሞች የሚመጡት አንድም ገንዘብ ስላገኝህ/ሽ (ስላላገኝህ/ሽ)፣ መልክ ስላለህ/ሽ (ስለሌለህ/ሽ)፣ ራስህን/ሽን ከሌሎች ስላሳነስክ/ሽ (ከፍ ስላደረክ/ሽ) እንዲሁም አልሸነፍ (እሸነፍን) ብቻ በግትር ማንነትህ/ሽ እንደ ፀጋ አድርገህ/ሽ ስለምትቀበል/ይ ነው፡፡*

*ሕይወትህ/ሽ ፈጣሪዋ አንድ ብቻ ቢሆንም የአንድ መንገድ ውጤት ብቻ አይደለችም፡፡ ይልቁንም የብዙ ነገር ውጤት ጥርቅም ነህ/ሽ፡፡ እስኪ ልጠይቅህ/ሽ ምግብ ተበልቶ ውሃ ሳይጠጣ፣ ውሃ ተጥቶ አየር ሳይማግ ታላቋ ሕይወትህ/ሽ ስለ ዓለም ትርጉሙ ይኖራትን ይሆንን?! እሺ ስጋስ ኖሮህ/ሽ ውበት ታክሎበት ነብስያ በደም ውስጥ ተዘርታ ልብ ኩኩሉ… ብላ መንገዷን ሳትጀምር ኩላሊት አቤት ብላ ሳታስተጋባ ተኝታ ብትለግም ስለበድንህ/ሽ ምኑን ታውቀው/ቂው ይሆንን?! በኩሬ ሆይ ምን ዘመድ ወዳጅ ቢኖርህ ላንተ የተሰጠውን/ሽን ሰማያዊ ህመም ቀርቶ *ምድራዊውንስ ቢሆን የሚሸከምልህ/ሽ የለም፡፡ በቃ ህይወትም በህመምህ/ሽ ጊዜ እንደነበረው ስቃይ በድህነተ ለመነሳት እንደበቃኸው/ሽው ሁሉ የምትኖራትም/ሪያትም የራስህን/ሽን የልፋት እና የመከራ ውጤት ናት፡፡*

*አትፍራ/ሪ፣ አተክዝ/ዢ፣ አትሸማቀቅ/ቂ ብሎም አትደናገር/ሪ ወደ ፊት በሕይወትህ/ሽ ዘወትር ሺሕ እልፎችን ተራመድ/ጂ ግን አንድ ነገር አትዘነናጋ/ጊ ማብሰያ ማገዶ የሆነውን ድካም፣ ውጣ ውረዱን፣ሜዳው ሲያልቅ የሚፈጠረውን ዳገት፣ ተራራው ሲታለፍ አስቀያሚው የማይደረስ የሚመስለውን መንገድ፣ ከመንገዱ ላይ ተጥለው የሚዋጉትን ተዋግተውም ሰውነት የሚያስመረቅዙትን እሾሆች፣ የጠጠሮች እንቅፋትን ብቻ አደራ ካንተ በልጠው ስለማያንሱ አትፍራቸው/ሪያቸው ብሎም አትሸሻቸው/ሺያቸው፡፡ አንተ/ቺ በነፍሰ ስጋቸው ላይ እየተረማመድክ ስትሄድ ድንጋውም ሲፈነገል እሾሁም ተሰባብሮ ከጭቃው ውስጥ ብን ያለ አፈር ሆኖ ይቀራል፡፡ ዳገቱም በተራራው የአሸናፊነትህ/ሽ ማብሰሪያ ማማህ/ሽ ይሆናል፡፡*

*በስተመጨረሻው ከምክሬ የምለግስህ ነገር ቢኖር ይህ መፀሐፍ የአዕምሮህ ትንሸዬ የመና ምግብ ነው እና እስኪጠግብ ውስጥህ ሥራዬን ከአቦሉ ‹‹ፉት›› እንድትለው በጥሞና ጋብዤሃለሁ፡፡ ከፋትንም ከውስጥህ አውጥተህ አርቀህ ቀብረኸው/ሺው መልካሙን ፍሬ ታፈራበት ዘንድ ከልብ ወድጄህ ተመኝቼልኃለው/ሻለሁ፡፡*

*ደራሲ፡- አብነት ሲራጅ*

# *ምዕራፍ አንድ*

## *በማድጋ የተነነተው የእንጀራ ማር!!!*

*መወለዴ ሳያንስ ነገሮች ሁሉ ለበጎ ሊሆኑ እኔ ተጨነኩ። ስለራሴም ልሆን ሌላውን በመከራ ዘመኔ አስጨንቅ እንዲጠበቡ አደረኩኝ። ብቻ ህይወት ጣዕም ብቻ ሳይሆን መራራውንም ስቃይ በኔው ላይ አጥምዳ ግታ እስትንፋስ አጥሮኝ እስክቃትት አሳይታኛለች። በዓለም ላይ ሺህ አልጋ ቢነጠፍ ምንም ፍቅር ካጣን በቆዳ ተወጥሮ እንደሚጮኽ ከበሮዎች ነን። ታድያ ሰውነታችን ሁሌም ከእንቅልፍ ሲነቃ በንጋት ሲታወድ እሱም እንደ ንጋቱ ሊሆን ይገባዋል። የህይወት ንጋት ለማምሻው ውበት እንዲኖረው በበጎው ሀሳብ የተሳለጠ ጎዳና መሆን መቻል አለበት። እኔነቱ በእሾህ የታጠረ ጥቅጥቅ ደን ነው። ከገባሁ ላብብበት፤ ከጠፋኝ ልከስምበት የራሴው ፍቃድ እና ብቃት ነው። ታድያ በ’ምድር ላይ በህይወት የሌላ ሰው ሀሳብ ተሸክሞ እንደ መዝለቅ ትልቅ ድክመት የለም።*

*መቼስ ከመግቢያው ስምህ ማነው? የት ተወለድክ? ቀኑ፤ ወሩ ’ናስ ዓመተ ምህረቱ ስንት ነው? ትሉ ይሆናል! በ’ርግጥ ጥያቄያችሁ ሁሉ ይሄንን አስቀድማችሁ ከሆነ ልክ ናችሁ ’ና ስሜ አብኔዘር ኤርሚያስ ይባላል። የተወለድኩት በጥር /7/1989ዓ.ም ከአባቴ ኤርሚስ ዮቶር ’ና ከእናቴ ህሌና ጥበብ ከበረራ ዘጠና ዘጠኝ ኪሎ ሜትር በስተ-ሰሜን ’ና ከደብረ-ኤባ ሠላሳ አንድ ኪሎ ሜትር በስተ-ደቡብ በምትገኝ የገጠር ከተማ በሰሜን ሸዋ ስር በምትገኝ ሰ.መ በምትባል ትንሽዬ የገጠር ከተማ ነው። ተወልጄ የእናቴን ጡት መጥባት ስላልቻልኩ ወንድሜ አላዛር ከኔ ተከትሎ በአንድ ዓመት ልዩነት ውስጥ እንደተወለደ ህሌና ’ና ኤርሚያስ ይነግሩናል።*

*ታድያ የሰውኛ እጣፋንታ ሆኖ ጉንጮቼ ለጡት ሳይታደሉ ቀርተው በተሻለው ፋንታ ያነሰውን ሸንኮራ ሆኖ እንድመጥ አላዛር ከአፌ ተዋደደ። ጥቅሙን ’ና ጉዳቱን በወጉ ባያውቁትም ባሻቸው ልጅ ማሳደግን የተካኑበት እናት ’ና አባቴ ሁሉንም በወጉ ያደርጉት ነበር። ብቻ በጤና-ባለሙያ ቢታይ ለኔ የሚከብደውን የሚጠቅም ቢመስላቸው አቅም እና ሀሳብ መልካም ነው ብሎ ከኪሱ መንዝሮ ያስረከባቸውን ሁሉ አደረጉ። እንደ እውነቱ ከሆነ ራሴን በመጠኑ እያወኩ የመጣሁት አራት ዓመት ገደማ ነበር። ከዛ በፊት ባለው ህይወት ከኤርሚያስ አና ከህሌና እንደ ሰማሁት ከሆነ በጣም ሲበዛ ዝምተኛ ’ና የምጠቀመው የአጥሚት ምግብ ካልቀረበ አልቃሻ ብሎም ተነጫናጭ እንደነበርኩ ያወጉኛል። እንደ ሀቁ ከሆነ የሚገርመው ነገር በሕጻንነት የተፃፈብህ የትኛውንም እትም መቼም ልትረሳው አትችልም እና ብዙውን ነገር በደንብ መከታተል የጀመርኩት ከዚህ ዕድሜ በኋላ ነበር። ብዙኋኑ ወላጅ የሚያስደንቀው ነገር ግን ለሚያደርገው ማንኛውም ነገር በተለይ እንደዚህ ላሉ ልጆች ምን ሰጥቶ ምን መጠንቀቅ እንዳለበት በፍፁም አለማወቁ ነው። ክፉ ነው ባይባልም እንደ ሕጻን ሊቀበሉት የማይችሉትን ስድብ፤ ግልምጫ እና ’ርስ በ’ርስ ለመጎዳዳት የሚደረጉ የድንጋይ ፍንቀላዎችን በመገንዘብ እመለከተው ነበር።*

*ኤርሚያስ እና ህሌና በፍቅር ህይወት ሲገናኙ የህሌና ፍቃድ ግን ፈፅሞ እንዳልነበር አሁን የሚያሳዩት ባህሬ በደንብ ያሳብቅባታል። ቤቱ ተገብቶ እስኪወጣ በቁጣ ብሎም በሁለቱ ጥል የተናወጠ መዐበል ነው። በ’ርግጥ ከዚህ በፊትም ሆነ በዚህ ወቅት የእናት እና አባቴ ፍቅር በቋፍ ተጀምሮ በዳገት ላይ ሊወድቅ አንድ ሐሙስ እንደቀረው ቋጥኝ ስለሆነ ብዙም መግባባት አልነበረውም። ከደስታ አስቀድሞ ሀዘንን የሚጠራ፤ ከመኖር ተግደርድሮ ሞትን በፀጋ እንደ መበዓ የሚመኝ፤ ከመፋቀር ተበታትኖ ክፋትን በመዝራት መለያየትን ገነት የሚያደርጉበት ነበር። ለሰው ልጅ ሁሉም ከቤት ሞልቶ ከደፍ እየፈሰሰ ፍቅር ከሌለው ምንስ ዋጋ ኖሮት? በወጣትነትስ ላይ ክፋት እና መቀናናት ተደርቦበት*

የትስ ሊያደርስ? ብቻ የትዳር ኖሯቸው እንደዚህ ነበር። ማደግ አይቀርም እና ከዛች የመከራ ጎጆ በፈጣሪ ፍቃድ ሁለታችንም አዳድገን በር በሩን እየወጣን መግባት ጀምረናል። መቼስ ልጅነት ያየውን የሚጎመጅበት ዘመን ሳይሆን መውሰድ ካልቻሉ ሞተው የሚገኙበት ሁኔታ መሆኑ መቼስ ለሁሉም አይጠፋውም እና እኛ ጋር የነበረው በተገላቢጦሹ ነበር ማለት ቢቻል እውነት ስለሆነ ግነት 'ና ቁልጽፃ አያሻውም። የሁለቱ አለመግባባት ይባስ ብሎ ቃላቶች እንደ ጠላት ሀገር መወራወራቸው በሕጻንነት አእምሮ አምኖ መቀበል እጅጉን ይከብድ ነበር። እኔም ከዚህ አሰቃቂ ድምፅ ለመሸሽግ ስል በተቻለኝ መጠን ከበራፍ በተደለደለ አመድ ውስጥ ከአላዛር ጋር እየተሽቀዳደምን ተከምረንበት እንጫወታለን።

እናቴ በወቅቱ የደረጃ ተማሪ ነበረች። አባቴ ደግሞ ከመሠረተ ትምህርት እና ከአንደኛ ክፍል የዘለለ ምንም የገፋ Academic knowledge አልነበረውም። እሷ የወታደር ልጅ እንደመሆኗ መጠን እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ ደርሳ አባቷ ሲመለሱ ለጋብቻ በሽምግልና ተጠይቃ አሻፈረኝ ብታበዛም በመጨረሻ ያለፍላጎት የተከሰተው ትዳር ውስጥ ገብታለች። በ'ርግጥ እንደነገሩኝ እና እንዳየሁት ከሆነ የፍቅር ጅማሮው ከአባቴ ስለሆነ በእናቴ ዘንድ በዚህ ወጥመድ ውስጥ ገብቶ መቆየቱ ዳግም እንዳያጣት ይሳሳል። ስለእውነት ነው የምላችሁ "አብራችሁ ካልኖራችሁ ገነት አትገቡም" የተባሉ ነው የሚመስሉት። ይሁን እንጂ ዓመታቶች ተወልደው ዘመናት በነጎዱ ቁጥር የእናቴ የበላይነት በኤርሚያስ ላይ እያጋደለበት መጣ። ለዚህም ይመስል ጠጣ መቀመጫዬን እንድትል ሁለት ወንድ ልጆች በተከታታይ ዓመት የተወለዱት።

ህሌና ከሚገባው በላይ ተቆጪ ስትሆን ለምትናገረው ንግግር ጥንቃቄ እና የሀሳብ ምርጫ የላትም። ኤርሚያስ ነገሮቹ ሁሉ ግልፅ ባይሆኑም ካለው የሽውሻዋ እና የማፍቀር ስሜት የተነሳ የምትለውን ከመስማት ብሎም ለስድቧ ጥቂት ምላሽ ከመስጠት የዘለለ እንብዛም አይታገለም። በቤት ውስጥ አንዳንዴ የሚላስ የሚቀመስ ይጠፋና ሁለቱ ሲገናኙ የቤተሰቡ አባል ይዘነጋ እና እኛ በምንቁለጨለጭበት መታደያ ይዘባበታሉ።

ኤርሚያስ አባታችን በግብርና፤ በእርባታ 'ና አንዳንዴም በንግዱ ዘርፍ የሚሰማራ ሲሆን እናታችን ህሌና ደግሞ እርባታውን በመንከባከብ እንዲሁም የግሮሰሪ የንግድ ሥራ በመሥረት የሚተዳደሩ ነበሩ። ይሁን እንጂ የግሮሰሪው ሥራ ዘርፍ ከሌላው የሚመጣው በህሌና ድክመት ምክንያት የሚጎዳ ነበር። ምክንያቱም ተጠቃሚዎች ደግመው ደጋግመው በመመላለስ ትውውቅ እየበዛ ሲሄድ አንዳንዱ አንድ መለኪያ ይዞ አነሰ ቢባል ለሁለት ሦስት ሰዓት ይቀመጣል። ይባስ ሲለውም እሱኑ ዱቤ ያደርገው እና በማግስቱ መሄጃ መንገድ እያማረጠ ላለመታየት ይሽሎከለካል። ብሎትም መምጣት ሲሻው ወር ሁለት ወር ቆይቶ ይመለስ 'ና ያለፈውን ከፍሎ ድጋሜ ከከፈለው በ'ጥፉ ጠጥቶ ሌላ ቀን ሊከፍል ዳግም ወሽክቶ ይሄዳል።

በዚህ ምክንያት ህሌና የመጠጥ ዓይነቶችን ለሌላው ደንበኛ ማምጣት ስለሚጠበቅባት ቤት ያፈራውን የግብርና 'ና እርባታ ውጤት ሽጣ ታሟላለች። ኤርሚያስ በሷ ዘንድ ብዙም ክብር የለውም። ጠዋት ከወጣ ከግብርናው ውሎ ሲመጣ ቁርስ፤ ምሳም አይኖረውም። ይባስ 'ራተም ራሱ ስርቶ ካልሆነ በዛውም ወደ መኝታ ሊያመሩ ግድ ይሆናል። ህሌና ከጠጪዎቹ ጋር አንጌ ወሬ ከያዘች እኛም እንዘነጋና አመሻሽ አደካክሞ ያገናኘናል።

እሱንም አልፎ አልፎ 'ራት ለመሥራት ያለው ልምምጥ 'ና ግልምጫ ደም ያስቀምጣል። በ'ርግጥ ይሄ የሚሆነው ቤት ራቁቱን ቀርቶ ሌላኛው ማራቀቻ የሆነው ሰነፉ አስተሳሰብ ማንነቱን በነሱ ላይ ሲያነግስ ነው። በዛ ላይ ቁጠባ አይሉት ስስት ለሌላው ቸር ለራስ እንደ ቀደመው የናይል ወንዝ ባዳ

መሆኑ ላይ የሚፈጠር የአጉራሽ ታዛቢነትም ችግር ነበር፡፡ ሰው የሚኖረው ከሰው ጋር በሰው ነው፡፡ በሰውነት ላይ ግን የሚፈነጭ ደሃዊ አስተሳሰብ ሰውነትን ቢያጎድፍ እንጂ አዝልቆ በፅናት አያቆምም፡፡

አንድ ቤተሰብ እንደ አስተዳዳሪነቱ ሌላ ተጨማሪ እንከኖች ሳይፈጠሩ በፊት አስቀድሞ ሊያስብበት ይገባል፡፡ በወቅቱ አግባብ ያልነበረው ቤተሰብ እኔ እና ሌሎቹን በመፍጠር የድርሻውን ተወጥቶ በመገኘት ፋንታ ምንም ከማያውቁ ጨቅሎች የድርሻውን ዳገቱን ጉልበቱ መውጣት በለገመ ጊዜ የሚጠይቅ ምሲኪን ነው፡፡ ቤት ያፈራውን በወግ ማዕረጉ አድርጎ ወደ ማማው መጓዝ የመልካሙ መንገድ ጅምር ነው፡፡ ነገር ግን በእንደዚህ ዓይነቱ ቤተሰብ ውስጥ የማይታሰብ የድህነት ምልክት ተደርጎ ያልነበረው ሲኖር አሰር በአሰር ተደግሶ ከሰውነትነት ጥቅም አውጥቶ ለአደገኛው በሽታ አስጥቶ ይሰጣል፡፡

እኛ ቤት ውስጥ አንድ ነጭ እና ዶባ ላሞች አሉ፡፡ በ'ርግጥ ላሜ ቦራንም በደንብ የማስታውሳት ከነዚሁ ላሞች እየመነጨ ተንጦ የምጠጣው አጓት እና Buttermilk በደከመ አንጀት ውስጥ እንደ ባእድ ነገር ሲርመሰመስ ነው፡፡ በተለይ Buttermilk በባህሪው እሳት ስለማይነካው በውስጡ ያሉ ባክቴሪያዎች ለህመም ይዳርጋሉ፡፡ ሆድንም በጣም በመንፋት ትንፈሳንም ጭምር ያግዳሉ፡፡ የከፋ የሚሆነው ደግሞ ምንም ቁርሶ ሳያምስ በዋለ ሆድ ላይ አሳቻ እራት ላይ ሲጠቀሙት የሚፈጠረው ችግር አጀብ ብቻ ነው፡፡ የመናጥ ሥራውም ቢሆን ሌላኛው የመፎካከሪያ በር ነበር፡፡ አንዳንዴ ኤርሚያስ ከሥራ መልስ እሷን ላለማማረር 'ና ላለማስቀየም ሲል እንቅልፍ ጣል መለስ እያደረገው በዛ ትልቅ የሸክላ እንስራ እስኪወጣ ፊት ኋላ መወዛወዙ ይቀጥል እና እርጎው ተበጥብጦ ቅቤው ከButtermilku ተለይቶ እስኪወጣ ይቀጥላል፡፡ እንደ ህሌናዊ ፍርድ ከሆነ ይኽ ሥራ ዛሬ ዘመናዊው የቴክኖሎጂ አሰራር ከመፈጠሩ በፊት በዙኋኑ ስለሚጠቀሙበት ሲበዛ አሰልቺ እናም አድካሚ ነበር፡፡ ህሌና ለሥራ የሚሆን ብቃቱ ቢኖራትም አብዛኛውን ጊዜ የመስነፍ ባህሪያቶችን ስለምትላበስ ይኽን ሥራ ለመሥራት ፍቃደኛ አይደለችም፡፡ ታድያ ይህም ሆኖ መበጣጠስ ወደሚባለው ደረጃ የሚደርስ ከሆነ የግዴታዋ ውዴታ ነው እና ተሠርቶ ማደሩ ግድ ሆኖ እየወሰደ ከሚመልሰው ከስመናዊ እንቅልፍ ውስጥ እየናኘች የድርሻዋን ትወጣለች፡፡ ታድያ ትርፉ ምንድነው ቢባል ውሃ ይቀዱታል እንጂ ቢወቅጡት ምን ያደርጋል መባሉ አውን ነው፡፡ የሀገሬ ሰው "ይችውም እንጀራ ሆነች እና ሚጥሚጣ በዛባት!" ይላል 'ና በዚሁም ቅጣት እና የቁጣ ድግሱ አቅልን ከረታትፎ ጨጓራ እየበጣጠሰ ሐሞት ያስቀምጣል፡፡

ጥጃ አይደለህ በሬ፤ ላም አትሆን ጊደር፤ በግ አይደለህ ፍየል ጠፍተህ በዛው አትቀር ወዴት ተብሎህ?! ተሽጠህ ከሌላው ተጠግተህ ‹‹ልኑር›› ብትል ሰውነት አንድ ሆኖ ያልወለደ አንጀት ይባስ ይበረታ እና  የማይሆን እዳ ነው፡፡ ለማን አቤት አይሉት ነገር ልጅ ሆነህ ማንስ አስተውሎ አንተን ከሰው ቆጥሮ ሊዳኝህ?! ብቻ ፈጣሪ ሳያኖር ካለምንም ምንም ጋር አይፈጥርም 'ና ማንም ሳይመርጠው ለጭቆና በተሾመ ንጉስ ሥር ያለምንም ድካም እና መሰላቸት የጨቅላነትህን ዕድሜ በከንቱ ትገብራለህ፡፡ ደግነቱ  አልገብርስ ብትል ትፅቢት አንግሶት በወለደው ቤተሰብ ውስጥ ምን ልታመጣ?! መልሱ ቤተሰብ ነው እና ዓለምን ለመኖር ስትል ምንም ሆኖ እስክታይ ድረስ ምንም አታመጣም፡፡

በዚህ ቤተሰብ ውስጥ ህይወት ቀጥላ ቤት በርዶት ሳይሞቀው ልጅ በድሉ ያድጋል የተባለ ይመስል ሶስተኛ ልጅ እህታችን ጣይቱ ተወለደች፡፡ በርከት ብለን ቤቱ የጫጩቶች ጩኸት የነገሰበት መስፈሪያ መሰሏል፡፡ ምንም እንኳን በፈጣሪው ቃል መኖሩ 'ርግጥ ቢሆንም ይበላው እና ይቀምሰው ጥሪኝ ካጣ ሆድ ሀገር ሆኖ ከአብዛኛው የውሃ ይዘት የተገነባውን ሰውነት አፈራርሶ ከአጥንቶቹ ላይ እንደ ፀሐይ 'ና ብርድ እንደሚፈራረቅበት አያውቅምን? ሌላኛው መቼስ ዶሮ እንኳን ልጆቿ እንዲያድጉላት በሙቀቷ ካስፈለፈለቻቸው በኋላ ከብርድ በክንፎቿ እየከለለች ትንከባከባቸዋለች፡፡ የእኛ ዓይነቱ ህይወት እንደ እውነቱ ከሆነ ለዶሮዋም ሆነ ለጫጩቶቹ አይሆንም፡፡ ይታረሳል፤ ይገባል ምንም

*መቀኖ ያለው ህይወት የለም። በቦታው የግብርና ባለሞያ ስላልነበረም ጭምር ዘመናዊ 'ና ወቅት የጠበቀ የአዘራር ዘዴን መጠቀም ኤርሚያስም አልተካነበትም። ባካበተው የዘመናት ልምድ እንኳን ዓመት ሲሰጥ ምርት አልባ ዘር በትኖ ሰብስቦ ቢያስገባውም ከግሮሰሪዋ መደጎኛ 'ና ከአሰር በስተቀር ምንም ምርት አልነበረውም።*

*ያንንም ህሌና በሥነ-ሥረዓቱ አዘጋጅታ ቀናቶችን በሴትነት ጥበብ ማራዘም ሲኖርባት ሲገኝ አሰር ባሰር ሲታጣ ረሃብ በሰቆቃ ይሆን እና ክረምትም ሳይገባ ከወዲሁ ተገባዶ ብድር ብሎም ሌላ የማይወጡት ዓይት ጣጣ ውስጥ ገብተው ይባክናሉ። ቀድሞ አማራጫቸው ሊያደርጉት የሚገባቸው ከቤት ያለውን ሀብት 'ና ንብረት ሲሆን ላይወጡት ሌላውንም ጨምሮ ከሚያጠፋባቸው የአንድ ለአምስት በዝባዥ፤ ብሎም የሰው ደም እንደ መዥገር እያለበ በየወሩ መጥጦ ከሚመገባቸው የብድር ተቋማት ውስጥ ገብተው ያለ ዋናተኛ የባህር ሰርጓጅ ሆነው ከዛው ሲዳክሩ ይገኛሉ።*

*የህሌና 'ና ኤርሚያስ ህይወትም ሆነ ቤተሰብ በእቅድ የሚመራ አይደለም። በዘፈቀደ ብሎም በፈጣሪ ችሮታ እንጂ። በእዳ የነገሱ የመከራ ቀናቶች ይበረቱ እና መገቢያ መወጫው ይጠፋል። ታድያ በዚህ ጊዜ የራሳቸውን የወለድ መክፈል ያቅታቸው ብሎም የክፍያ ወቅት ወዲያውኑ ደርሶ እምጥ ይግቡ ስምጥ ያስጨንቃቸዋል፤ በዚህም ምክንያት የማይቀርለት የመንግስት እዳ ነው እና ቤት ያረባውን በወቅቱ ቢሸጥ ሊጠቅም የሚችል መንጋ ተሸጦ ሊከፈል ሲኬድም ከቡድኑ አባል ሁለት ወይም ሶስት ሰዎች ሳያዘጋጁ ይቀር እና ሌላ እዳ ይጨመርባቸዋል።*

*በዚህም ምክንያት ያለውን ንብረት ሻሽጠው ከፍለው ከባለ እዳው ገንዘቡን ለማስመለስ ከቀበሌ እስከ ፍርድ ቤት ሲመላለሱ ይውላሉ። በ'ርግጥ ኤርሚያስ ምንም ባይማርም ማገናዘብ እና ነገሮችን አስቀድሞ የሚተነብይ ቢሆንም ከህሌና ትዕዛዝ ስለማይወጣ ከመቀበል ውጪ አማራጮችን አይጠቀምም። ህሌና ት/ቷን በዚሁ ጋብቻ ምክንያት ያቋረጠች ቢሆንም ካላት የመማር ቁጭት የተነሳ የራሷን ህይወት ስለምትንቅ ሌላው ታይቷት ኑሮ መሆኑንም የዘነጋችው ይመስላል። አንዳንዴ ደግሞ መለስ ስትል የምታቀርበው ሀሳብ ከኤርሚያስ ጋር ይስማማ እና ወደ መስኩ ሲገቡ የተሳለጠ እንዲሁም የተዋጣለትን በርካታ ሥራዎች ይሰራሉ።*

*በ'ርግጥ እንደዚህ ዓይነት ሀሳብ ሲመነጭ ከቤት ሥራ የዘለለ ሌላ አላማም ሆነ የወደፊታዊው ሁነት 'ና ማገባደጃው በደንብ ታስቦበት የሚሰራ አልነበረም። ታድያ ኤርሚያስ ይሄንን ለማስፈፀም ሲል የሰው ጭቃ አንጀቱ እጥፍ ዘርጋ እያለ አቡክቶ፤ አብስሎ፤ አግዞ እና መርጎ እንዲሁም ለስኖ አላማውን ከግብ ቢያደርሱም እኛን በዛ አሰር ባሰር በሆነ ወቅቱን ባልጠበቀ የአሳር ምግብ የረሃብን ጥግ አሳይተው ራሳቸውን በእሳታማው የገጠር መጠጥ (አረቄ) ለብልበው ማየት እንኳን እስኪቃተን ቀርቡ ሩቅ ሆኖባቸው ያደርጉት ነበር።*

*ይህም ሆኖ ፀባይ የገዛ ቤት ቢሆን ኖሮ ሆሉም ጥጋብ በሆነ ነበር እና ሳይሆን ቀርቶ እኔ፤ አላዛር እንዲሁም ጣይቱ በሰቀቀን ያለማንም ሀይ ባይ እንደ መጠጥ ጠጥተን፤ እንደ ሙዚቃ አጣጥመን ልምድም ሆኖን ቀኑ መሽቶ ዐይኖቻችን ሲርገበገቡ እንተኛለን።*

• * *

ዕድሜም ከፍ ሲል ምንም ክትትል የሌለው ሆድም እግር አውጥቶ ይሰፋል እና ከየመንደሩ ጎራ እያሉ ዐይን ማቁለጭለጭ ግድ ሆኖ ጎረቤት እስኪመረር ድረስ ደርሶ መመላለሱ አላቆም አለ፡፡ ከመጠን የሰለቸነው ለማየት እንኳን የሚጠላን ሰው በእጁ ቀርሶ ለሚሰጠን ቁራሽ ጉርሻ እንኳን ተፀይፎ እያቋደሰ ይሸኘናል፡፡ ለነገሩ ባለቤቱ የናቀውን ጨው ማን ሊያከብረው ሆኖ ህሌና ያላየችውን ልጅ ሌላው ቢያመናጭቀው የሚገርም ነገር አልነበረው፡፡ ያንንም እነሱ ሆነው እንጂ ሌላው ከኛ ቤት ሲመጣ ቢስተናገድም የሚሆነውን እኛው እናውቅ ነበር፡፡

ከፊታችን የፋሲካ ዓመት በዓል እየመጣ እንደመሆኑ መጠን ከቤት ውስጥ የሚደረገው ሽር ጉድ ለኔ የመጀመሪያ እና የተለየ የሚያስደምም ነገር ስለነበረው ደስታ በጣም ውስጤን አስክሮ የማደርገው ቢጠፋኝ ከአላዛር ጋር ከቤት ገብተን እስትንፋስ እስኪያጥረን እንዘል፤ እንቦርቅም ነበር፡፡ ዋዜማው ላይ የኢትዮጲያ ሬድዮ በዓመት በዓል ሙዚቃ ቤቱን ሽብ-ረብ አድርጎት ኤርሚስ እና ህሌና ሳይቀሩ ሳቅ ጫወት ይሉ ነበር፡፡ ይህንን ሀሴት በሁለቱ መሐል ተፈጥሮ ሳየው ምነው ‹‹ሁሌም ፋሲካ በሆነ›› እያልኩ ተመኘሁ፡፡

በዋዜማው እንዲህ አምሽተን ማግስቱን በድካም የተጫነው ሰውነት እንቅልፍ ከአላጋ አጋድሞን በማለዳው ጠዋት ስንነቃ ቤቱ በጉዝጓዝ አብዶ፤ የሲኒው ማስቀመጫ ተውቦ፤ ዳቦው በሚያምር ዳንቴል ተሸፍኖ ስመለከት አላዛርን ቀስቅሼ አስነሳሁት፡፡ ኤርሚያስ በአላዘር መቀስቀስ ቢቆጣም በዓመት በዓል መልካም አለመሆኑን ህሌና በምክር ብጤ ከቁጣው አስቆመችው፡፡ እሱም ከኩሽናው ባሞቀው ውሃ ገላችንን አጥቦ አዳዲስ ቱታዎችን አልብሶ ከለሲቱ የፆም መፍቻ የዶሮ ወጥ በአይብ እያላወሰ አጎረሰን፡፡

እኔ እና አላዛር ትልቅ ዳቦ ሲጋገር ‹‹እናንከ›› ነው የምንለው፡፡ ይህንን ስንል አንድ ትልቅ ቡሬ በሬ ቤት ውስጥ አባታችን ኤርሚያስ ከደጅ ሲያርስ ‹‹ና..ና…ናክ›› ሲል እንሰማ ስለነበር በመደመም ትልቅነቱን ለመግለፅ ዳቦውን ‹‹እናንክ ሊቆረስ ነው›› እንላለን፡፡ ዳቦው ተቆርሶ በላልተን ትንሽ ሆዳችን ቆዘር እንዳለች ሬድዮ አስከፍተን የማናልሞሽ ዲቦን የዓመት በዓል ዘፈን እየኮመኮምን ቋጫት እንደበላት ፍየል ስንዘል ቆይተን አጎታችንን እና ጎረቤት እንድንጠራ ታዘዝን፡፡

ሰው መጥራት ደስ ይለን ስለነበር እኛው እየተሽቀዳደምን ትዕዛዛችንን በምንችለው ቋንቋ መጠን አስተጋብተን ተመለስን፡፡ ሰው ሲበዛ ደስታችን ጨምሮ ትንሽ ቀልጠጥ ስንል ህሌና እያጉረመረመች በቁጣ አስቀመጠችን፡፡ ወድያውኑ የተገዙ ሁለት ፍየሎች ኤርሚያስ እና ወንድሙ ዘራይድረስ ሲያርዱ እኛ የተሰጠንን ፍሬ ህሌና እንድትጠብስልን ብናደርግም ብዙም ሳንበላው አንገሽግሾን ረሃቡም ተረስቶ ለእንግዳ ከተገዛው የእንቁላል ቅቅል ላይ ተማስን፡፡

ጎረቤቱ ተጫውቶ፤ በልቶ ጠጥቶ ዓመትን ለዓመት እንዲደግመው እየመረቁ ሲሄዱ እናንኩ እና ሌላው ወደ መጠናቀቁ ደርሶ አመሻሹ በጥሪኝ ታድሮ ማግስቱ ገነት እና ገሃነም ሆነ፡፡ የፍየል ስጋ በአልጫ እየተሰራ ለጥቂት ቀን ቢቆይም ጉዝጓዙ ደክርቶ፤ ሳህኑ ተጣጥሎ እና ቤቱ ተዝረክርኮ ተቃራኒውንም ውሎ አድሮ እዛው አየነው፡፡

ህሌና ሌላኛውን እናንክ ስትጋግር ሌላኛውን ፋሲካ ልትደግመው መሆኑን ተስፋ አደረግን፤ ከዛም ትንሽዬ ቢጥሌ አስበጥለን እየበላን ሌላኛውን ብንጠብቅም ሳይሆን ቀርቶ ጣይቱ ታዝላ፤ አላዛር በእንኮኮ ተይዞ እናነኩ በአህያ በትልቅ እንቅብ ተጭኖ መንገድ ጀመርን፡፡

የምንሄደው የህሌና ቤተሰቦች ወደ ሆኑት አያቴ ጥበቡ ዘውድዓለም ነው፡፡ ትንሽ መንገድ ለመሄድ ብሞክርም ከወንዙ መሻገሪያ ማዶ እስክንድር የህሌና ወንድም በፈረስ ደርሶ ከፈረሱ ላይ

አስቀምጦ አቅፎ አሻገረኝ፡፡ እስክንድር ቆንጂዬ ልጅ ሲሆን ከገጠሩ ደርሰን ከቤት እስክንገባ እየደጋገመ ይስመኛል፤ ከከረሜላ ብቻ የእጅ ማበሻውን አቅሙ ከፈቀደው ይሰጠኛል፡፡ መኖሪያቸው ትልቅ የሳር ቤት ሲሆን ጭስ በተከመረበት የብር ገለባ ውስጥ ‹‹ትንንን…›› እያለ ወደ ሰማይ ይወጣል፤ ከውስጥ ስንገባ አጎቶቼ እና አያቶቼ ቆመው ተቀበሉን፡፡

ሴት አያቴ አበባ ገ/መስቀል ስትባል ወንዱ አያቴ ጥበቡ ዘውድዓለም ሲሆኑ ረዘም ያለው አጎቴ ናስቶሲን፤ ከሱ አጠር ብሎ ዶርቸም ያለው ደግሞ ነጋድረስ ይባላሉ፡፡ ሌሎችም ከውስጥ በኩል ከምድጃው በስተጀርባ እየተነሱ ሰላምታቸውን ችረው አስቀመጡን፡፡ ከጠላው፤ ከወተት-ከአይቡ፤ ከስጋው-ከወጡ ብቻ ምንም ያልቀረበ አልነበረም እና ሁሉም ቀርቦ የየችሎታችንን በላልተን አዋቂዎች ጨዋታ ሲጀምሩ ናስቶሲን እና ነጋድረስ እንደ ወጡ እስክንድርም ከብቶች እየጠበቀ ሩር ከሚጫወትበት ‹‹ፉራ›› ሲሮጥ መጥቶ ህሌናን አስፈቅዶ ይዞኝ ወጣ፡፡

ሜዳው በአረንጓዴው ሳር የተጥለቀለቀ ነው፡፡ በዛ ላይ መንጋው በውስጡ ሲርመሰመስ፤ አጋጋጡ እና ህብረ ቀለማቸው በጣም ሌላኛው አስደማሚው ፋሲካዬ ነበር፡፡ እስክንድርም ሩር መጫወቱን ትቶ ከበግ ጀርባ ላይ እያስቀመጠ ያስፈነድቀኛል፡፡ በዚህ ሁኔታ ቀን ለአመሻሽ ተራውን እየለቀቀ ብርዱም እየከፋ ስለነበር እንድገባ መንገድ አድርሶኝ መንጋውን ሊያመጣ ሲመለስ ከደጅ ደርሼ የማላውቀው ውሻ ከግቢው እየዘለለ ወጥቶ ወደ እኔ ይጮህ ጀመረ፡፡ ለቅሶ በርትቶ ‹‹እትዬ አበባ፤ ህሌና ኤርሚስ፤ ነጋድረስ፤ ናስቶሲን …… ›› የሚሰማኝ ጠፍቶ እስክንድር ደርሶ ከውሾቹ እየተከላከለ አስገብቶኝ ተመለሰ፡፡

ማታ ላይ እንደወጉ ተደርጎ አያቴ ጥበቡ ከተረቱም ከቀልዱም ሲያስቁ፤ ሲያጫውቱ ከቆዩ በኋላ ነጋድረስ ዘፈን ጀምሮ ከጓደኞቹ ጋር ጭፈራውን አቀለጠው፡፡ ህሌናም በግዴታ ከማህላቸው ስትጨፍር ሲላት ስትሽኮረመም ተመልሳ ጣይቷን ከአበባ ላይ ትወስድ እና ተቀምጣ ትመለከታለች፡፡ ኤርሚያስ ቤት የሚጠብቅ ሰው ስላልነበረ ቀን ላይ ቀደም ብሎ ሄዶ ነበር እና ብፈልገው ስላጣሁት አበባን እና እስክንድርን ስጠይቅ መሄዱን ነገሩኝ፡፡

ነጋድረስ ጓደኞቹን ሸኛኝቶ ሲመለስ አብሬው እንድተኛ የኔን እና የህሌናን ፍቃድ ጠየቀ፡፡ ህሌና እሺታዬን ተጠራጥራ ሊያለቅስ ይችላል በሚል ግምት የኔን ምላሽ ጠበቀች፤ እኔም ፈቅጄ ለመሄድ ስነሳ አንድ ድምፅ በትስማ ልትቀጣኝ እንደምትችል አስጠንቅቃ እንድሄድ ፈቀደችልኝ፡፡ ነጋድረስ ኮረኮንቹን ድንጋይ አቅፎ እያሳለፈኝ ከፎቁ ደረጃ ላይ ደረሰ፡፡ ከመዐድ ቤቱ ኩራዝ ነበር እና ያንን ረጅም ደረጃ ወጥተን ከጭለማው ስንማስ ጨነቀኝ፤ ፍራሹን ከመታደያው አንጥፎ ጋደም ከማለታችን ከተነጠፈው መኝታ ፊት ለፊት በጭላንጭል ወደ ታች ሳይ ደንግጬ ጮኹኝ፡፡ የመሬቱ ርብራብ በደንብ አልተደለደለመም ነበር እና በቀዳዳው የመንጋው እበት ወደ ላይ እየተነነ አስጠልቶ በጣም ያስፈራ ነበር፡፡

እሱ ግን እኔን ለማባበል ቢሞክርም ስላልተቻለው ከንግግር ወደ ቁንጢጥ ተሸግሮ ዝም አስባለኝ፡፡ በጣም ከመናደዴ የተነሳ የፎቁ ቀዳዳ ቦታዎች ተረስተውኝ ሽንቴ እንደመጣ ሰው አስመስዬ ለመሄድ ውጪ እንዲያወጣኝ አደረኩት፡፡

እሱም ሶስት ሜትር ርዝመት ባለው ደረጃ ላይ እንድሸና ቢያዘኝም ከመሬት ካልወረድኩ መሆን እንደማይችል ለማሳመን በመሞከር አሻፈረኝ አልኩት፤ ነገር ግን ካልሆነ እንደሚያስገባኝ አስፈራርቶ እጁን ሊዘረጋ ሲል ከዛው ልሸና ዘንድ ተማምቼ ፊቱን እንዲያዞርልኝ አደረኩ፡፡

ነገር ግን ብልጠት አብዝቼ የሳንሳ በሁለት እጁ አቅፎ አስገባኝ፡፡ አበባ፤ ህሌና የተባለው አልቀረም እና ሆኖ እነሱም በዝምታ እኔም በለቅሶ ጩኸት እንቅልፍ ይዞኝ ነጎደ፡፡

• * *

ጠዋት ከእንቅልፌ ስነቃ 'ርግብ ከፎቁ ሥራ ‹‹ጉጉ..ኡ.. ጉጉ…ኡ›› ስትል ሰማሁ፡፡ ድምጧ በጣም ያምር ስለነበር መቀያየሙም ተረስቶ ነጋድረስ እንዲያሳየኝ ጠየኩት እሱም መስኮቱን ከፍቶ ከጎጆዋ እየነካ ሊያሳየኝ ሲሞክር እርግቧ ‹‹ፉር›› ብላ ስትሄድ አየኋት፡፡ ከፎቁ ማዶ ብዙ መንደሮች አሉ ሜዳው የመሰኖ ወቅት ስለነበር አረንጓዴ ሲሆን የበቀለው የነጭ ሽንኩርት ቅጠል፤ እንጭጭ ገብስ፡ ስንዴ ባቄላ፤ አብሽ፤ ምስር፤ ጓያ፤ ካሮት፤ ጎመን፤ የባህር-ዛፍ አፈላሾ ….. ሁሉም ወለል ብሎ ይታይ ነበር፡፡ በዛ ላይ የጠዋቷ ፀሐይ በመስኩ ላይ ብርሃኗን ጥላ ውስጥን ፍክት የሚያደርግ ስሜት ፈጥራል፡፡

አሞራ፤ ወፍ፤ ዳክዬ፤ ጋጋኖ፤ ነጭ 'ርግብ፤ ሰማያዊ 'ርግብ፤ ቢጫ 'ና ጥቁር ቀለም ያለው ቡሬ ወፍ ….. ጩኸታቸው አስደምሞ ልጅ አይደለም ደስታው አዋቂ ያሰክራል፡፡ ከአንደኛው መስኮት ወደ ሌላኛው መስኮት ስንዞር ‹‹ካካ….›› እያለች ሌላኛዋ አእዋፍ ቆቅ ስታስካካ በዛፍ የተንቆጠቆጠውን ጋራ በዐይን ዳሰን ወደ መዐድ ቤት ህሌና ጠርታን ተጓዝን፡፡ ቁርስ ቀርቦ ከበላላን በኋላ ነጋ ድረስ ከእስክንድር ላይ የወፍ ጥበቃ ተራው ስለነበር በአያቴ ጥበቡ አምካኝነት እንዲሄድ ተደረገ፡፡

አበባ እና ህሌና አፍ ለአፍ ገጥመው ከምድጃው ሲያወሩ ናስቶሲን ተቀላቅሏቸው አንድ ሁለት እያለ ሲጫወት እስክንድር መጣ፡፡ ህሌና በዚህ ጊዜ ለመሄድ እያኮበኮበች ስለነበር ከአበባ ጋር ምን እንደተነጋገሩ ባላቅም እስክንድር እያታለለ ይዞኝ እንዲወጣ አደረጉ፡፡ እስክንድር ናስቶሲን መንጋውን እየለቀቀ ስለነበር ከሱ ተቀብሎ ወደ ተራራው እየነዳ ካንድ ጥግ ስር ደርሰን ከዛው መላፋት ጀመርን፡፡ ነገር ግን ይሄም ስለበቃኝ ለመሄድ አሻፈረኝ ስል አቅፎ ከጋራው ቁልቁል ይዞኝ ከነፈ፡፡

ከፊታችን ቁልቋል 'ና ቀጋ አለ፡፡ ከቁልቋሉ ብስሉን እየቆረጠ ሲሰጠኝ ለመብላት ጠንቃቃ ስላልነበርኩ ጣፋጩን ብቻ አስተውዬ ከላው ላይ የሚቦነው እሾህ በምላሴ እንዲሁም በመላው ሰውነቴ ላይ ተሞጀረ፡፡ እስክንድርም ለእገዛ ቢታትር ሳይሳካለት ቀርቶ ከእጁ ላይ ይባስ እያራገፈብኝ ስቃዬን አበዛው፡፡ በስተመጨረሻ ምንም ዓይነት መፍትሄ ስላጣ መንጋውን ካለበት ለናስቶሲን ጥሎ ከቦዩ ይዞን ወረደ፡፡ የሰላሳ ሜትር ርቀት አልነበረውም እና ደርሰን በትንሽዬ ቦይ ውስጥ ከምትፈስ ኩልል ያለች ውሃ ውስጥ ታጥበን ከዛው ስዘላልል ቆይቼ ናስቶሲን እየተቆጣ መጣራት ጀመረ፡፡

እስክንድርም በፍጥነት በትሩን እየሸከፈ ባንድ እጁ ከትከሻው ላይ ታቅፎኝ ከጋራው ማማ ላይ ደረስን፡፡ መንጋው በርካታ ስለነበር አባባ ጥበቡ ወደ ወፎቹ ሄደው ነጋድረስን ላኩት፡፡ ወዲያውኑ አበባ መጥታ እኔን ከእስክንድር ላይ ስትቀበለኝ ናስቶሲን፤ ነጋድረስ እና እስከንድር ሆነው መንጋውን እየነዱ ከመምጫችን ፊት ለፊት ባለው ጎዳና መንጋውን ይዘው ነጎዱ፡፡

እኔ እና አያቴ አበባ ከቤት ስንደርስ የጠበቋትን ህሌና ከቤት ላገኛት አልቻልኩም ነበር እና ከአያቴ ጋርም ብዙ ስላልቆየሁ በቤቱ እንቧ ከረየሁ ቀጥሎ የአበልጆቻችን ልጆች ተጠርተው ከስንት ማባበል እና ልምምጥ በኋላ ጨዋታ ተጀመረ፡፡ በዚህ መሐል የምሳ ሰዓት ደርሶ መንጋው ከበረቱ ሲጎርፈፍ በጎቹን እያባረርኩ ከጎለቱ እስኪገቡ በዛ ክምር ድንጋይ ላይ እየሮጥኩ እከተላቸው ነበር፡፡

እስክንድር ገና ከመቀመጫው አርፎ ምሳውን አጠዳድፎ በላልቶ ወደ ውጪ ይዞኝ ሊወጣ ሲል አበባ ቡና እያፈላች ስለነበር ካላትም ባዕዳዊ አምልኮ የተነሳ በሰዓት መልካም አለመሆኑን ለመግለፅ

ቁጣዋን አስቀድማ አዘነበች፡፡ ‹‹ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል፡፡›› ሆነ እና ነገሩ አባባ ጥበቡ ስለዲቃላነቴም በቁጣ ነግረውት ለማስቆም ሲሞክሩ እኔ ሳይሆንልኝ ቀርቶ ከሱ ስንጠለጠል ናስቶሲን የቁጣ መብረቁን ለቀቀብኝ፡፡ በዚህ ጊዜ ሌላኛውን ዕድል ያገኘ የመሰለው ነጋድረስ በእስክንድር ላይ ለዝበታ ሲነሳ እትዬ አበባ እና አባባ ጥበቡ አስቆሙት፡፡

እስክንድር ቡናው እንዳከተመ ከሱ ሌላ ሰው ስላላስፈለገኝ ተያይዘን ከግቢው ወጣን፡፡ ሰፈሩን ዙሪያ ገባውን ከቃኘን በኋላ ከጋራው ስር ወርደን ቀጋ እየፈለፈልን መብላት ጀመርን፡፡ ቀጋው የመኮሳኮስ ባህሪ ቦኖረውም እሾሁ እንደ ቁልቋሉ እሾህ ጠንካራ ስላልሆነ በምራቅ ተሰባብሮ ይወርዳል፡፡ ከዛው ባብለን ትንሽ ከቆየን በኋላ ተያይዘን ከሚጠብቁት የወፍ መስክ ደረስን፡፡ ‹‹ዎሼ ቡሬ!! ዎሼ……..›› እያለ በየድንበሩ እየሮጠ በያዘው የገመድ ወንጭፍት እያምዘገዘገ ሲወረውር በህብረት ከውስጡ ተመስከው የነበሩት አመድማ እና የቢጫ ጥቁር ቡሬ ወፎች በአናታችን ላይ ይብራሉ፡፡

በዛ ሰፈር ሁሉም ‹‹ዎሼ … ቡሬ›› ጋራው ስለሚያስተጋባ ደስ ይል ነበር፡፡ የነእስክንድርን ማሳ ከላይ እንስተን ከጫፍ ስንደርስ ትልቅ ወንዝ አገኘን፤ እኔ ፍርሃት ቢሰማኝም እሱ ግን በቁርጥሚ እና ውስጡ በሚበቅሉ ማንኪያ መሰል ቅጠሎች ያስደምመኝ ተያይዟል፡፡ ውሃውም ቢሆን ‹‹ሹዋ..ቆረረ..ር›› እያለ ሲሄድ በእጄ እየመታሁ እንቦጫረቅበታለሁ፡፡

ማታ ማታ እስክንድር ከዛ ሁሉ ስራ ሲመለስ መፀሐፎቹን ይዞ ሥዕሎችን እያሳየ ስማቸውን ይነግረኛል፤ ‹‹ይሄ ቀንዱ ተጠላልፎ የምታየው በሬ መሰሉ እንሰሳ ጎሽ ይባላል፤ ይሄ ደግሞ ሰውነቱ ቡራ ቡሬ ፊቱ ኮስተር ያለው ነብር ይባላል፤ ይሄ ደግሞ እንደ ውሻ ጆሮው ወደ ላይ የቆመው ቀበሮ ይባላል፡፡ ይቺ ደግሞ ጆሮዋን ጥላ እንደ ድመት ጭብጥ ያለችው ጥንቸል ትባላለች፡፡ ይቺ ደግሞ (ይሄ ደግሞ)›› እያለ ከህብረተሰብ መፀሐፉ የማያሳየኝ ታሪክ አልነበረም፡፡ አንዳንዴም እንደ ቆሎ አምረው ‹‹ዝገኑኝ ዝገኑኝ›› የሚሉትን ፊደሎች ቅሞ ለማስቀረትም እሞክር እና ‹‹በድምፅ ጨ ና ጀ፤ ረ ና ለ፤ ከ ና አ፤ ሰ ና ሸ፤ ጸ ና ጸ በቅርፅ ደግሞ ሸ ና ሾ፤ ሀ ና በ፤ መ ና ወ፤ ሐ ና ጠ/ጨ፤ ፈ ና ፈ፤ ተ ና ቸ፤ ደ ና ጀ፤ ከ ና አ፤ ሰ ና ሸ፤ ጸ ና ጸ፤ ዐ ና ፀ …›› ተመሳሳይ እነታቸው እና የድምፅ አጠቃቀማቸው ትንሽ ከበድ ስለሚል ችላ እለዋለሁ፡፡

በስተመጨረሻም ፋሲካውም አልቆ በጋውም ራሱን ሰውቶ ለክረምት እያስረከበ ሌላኛው ወቅት መጣ፡፡ ኤርሚያስ ብዙ ጊዜ ቢመጣም ‹‹ካልሄድን!!›› እያልኩ ስለማስቸግረው ወደ እኛ ሰፈር ድርሽ አይልም፡፡ ቢመጣም በሩቁ አይቶኝ ቢሄድ እንጂ ወደኔ አይቀርብም፡፡ እስክንድር ያንን ክረምት ከፊታቸው ከሚታየው ተራራ መንጋውን እየነዳ ሲያበላ ስለነበር መሬቱ ጠገግ ሲል ይዞኝ ይሄድ ጀመረ፡፡ ጋራው ውስጥ ጦስኝ፤ ጤነዳም፤ ጉራ-ሃሬ፤ ሰማያዊ አበባ፤ አደይ አበባ፤ ዛይላፎን የሚመስለው ጣፋጭ አበባ….. ብቻ ብዙ ነገር ስላለ ቦታው በጣም ደስ ይላል፡፡

ከዛይላፎኑ አበባ ጣፋጩን እየመጠጥን ስንጥል አንዳንዱ ውስጥ ንብ ሌላው ደግሞ ትልም ልናገኝ እንችላለን፡፡ እስክንድር ታድያ የዚህን አበባ ጥራት እና ብስሉን የሚያውቅበት የአስተውሎት ዘዴ አለው፡፡ እሱም መብሰሉን የሚያረጋግጠው ከቢጫነት ቀላ ወዳለ ብርቱካናማ (ሮዝ) መልክ ሲቀየር ሲሆን ንፃቱን ደግሞ የሚያጣራው ዙሪያውን ምንም በትል ያልተቦረቦረ የአካል ክፍል መኖር አለመኖሩን በማየት ነው፡፡

በጋራው ላይ እየተንቆረቆረ የሚወርደው የፏፏቴ መልክ ያለው ውሃ ከጥራቱ የተነሳ ከማንቆርቆሪያው ዳገት ስር ሲቆም አቤት ደስ ማለቱ፡፡ እስክንድር ታድያ ሌሎች ጓደኞቹም አብረውት ስለነበሩ ከጋራ ውስጥ የሚያስካኩ ቆቆችን በማደን ላይ ተሰማርተዋል፡፡ ቆቆቹ ሊያዙ የሚችሉት ከሶስት

ጊዜ የበረራ ድካም በኋላ ነው፡፡ ማን ቀድሞ ይያዝ ማን ይወሰድ ቀድሞ በያዘ ወስነዋል እና በረራቸውን ቀጥለው እኔ ከመንጋው ጋር እየተከተልኩ ቁልቁል ተምዘገዘኩ፡፡

እጅግ በጣም አፉን የከፈተ ጎሬ ከፊቴ አገኘሁ፤ ከዛም ተቀምጬ ለመጫወት ብፈልግ አንድ የቀይ ነጭ ቡሬ በሬ ከአጠገቤ ሳይለይ አብዝቶ መጮህ ጀመረ፡፡ አጎቴ እስክንድር ግን ከዛ ሁሉ የግስጋሴ ድካም በኋላ እኔን ከቦታው ቢፈልገኝ አጥቶ በሬው ከሚያጓራበት ጎሬ የበደነፍሱን እየሮጠ ደረሰ፡፡ በሬውን በንዴት ቢቀጠቅጠውም እሱን ሲያሸሽ እኔን ከዛው አግኝቶ በመደንገጥ በበሬው ላይ ባደረገው ድርጊት ተፀፅቶ ያጨደውን ሳር ከመንጋው ለብቻው ለይቶ እያሻሸ እንዲበላ ሰጠው፡፡

እኔም በመጨረሻ ለምን እንደሆነ ብጠይቅ ጎሬው የጅብ መኖሪያ እንደሆነ ነገረኝ፤ ታድያ ይሄንን ሲነግረኝ ጅብ ለሊት እንጂ ቀን አለመባላቱን ስጠይቀው መቼም እንደማይምረኝ ነግሮ ሳቀብኝ፡፡ አንድ ቆቅ ይዞ ስለነበር እኔን ለጓደኞቼ ሰጥቶኝ ሲበር ከቤት አስገብቶ ተመልሶ መጣ፡፡

መንጋውን በርካታ መኖ ወዳለበት ስናበላላ አመሻሽ ቀኑን ወርሶት ወደቤት ልናመራ መንገድ ጀመርን፡፡ በዚህ ጊዜ ለማታለያ የምታበራ መስቅል እስክንድር ከአንገቱ ላይ አውልቆ ሰጥቶኝ ስለነበር እሷን እያቀሻበልኩ ሳለሁ ፈረስ ሊያስቀምጠኝ መሆኑን ነግሮ ቀይ በጣም የጋማ ፀጉሮቿ ሲይዙት እንደ ለምለም ሳር ደስታን በሰውነት ውስጥ ከሚዘራ ጀርባዋ ላይ አውጥቶ ከመረኝ፡፡ በጣም ያስፈራ ስለነበር አንቂ ብይዘውም ያ! ሁሉ መንጋ የሰው መስክ ውስጥ እየገባ ስላስቸገረው በሥነ-ሥረዓቱ መቀመጥ ከቻልኩ መስቀሏን ከነጭራሹኑ ሊሰጠኝ ተስማምተን እሱም ወደ መንጋው ሲሄድ ከእጄ ላይ ስትሽከረከር የነበረችው መስቀል ወድቃ ፈረስ ላይ መሆኔን ዘንግቼው ለመቅለብ ባየር ላይ ስንሳፈፍ እኔ እዛ ማዶ ፈረሷ እዛ ማዶ ሆነን መስቀሉም ላይገኝ የእንግጫ ሳሩ ግንባሬን ትንሽ ፋር አደረገኝ፡፡ ነገር ግን ፈረሷም ደንግጣ ስለነበር ፈርጥጣ ከደጅ ቆማ ትጠብቀን ነበር እና እኔን ስታይ የቆሙ ጆሮቿ ‹‹ተመስገን›› በሚመስል መልኩ ጋደም ጋደም ሲሉ አየኋቸው፡፡

ለመንጋው መኖው በየፈርጅ በየፈርጁ ተደርጎ ከተመገበ በኋላ ላሞች ጥጆቻቸውን እየተገናኙ ወተት ሰጥተው በየቦታ ቦታቸው ታስረው ወጋገኑ በጭለማ ተውጦ ወደ ቤት ገባን፡፡ ምድጃው በጀበና፤ በገበታ ፤በሲኒ ረከቦት፤ በእጣን ማጨሻ ገል እና በቁሳቁስ አብዷል፡፡ የቆቋ ወጥ እንደ ዶሮ ሽታ ገና ከመግቢያው በር ያውዳል፡፡ ብቻ ከምድጃው በየተርታው ተኮልኩለን ተቀመጥን፡፡ ወንድ አያታችን ሰፊውን ቦታ ይዘዋል፤ ከምድጃው ወጣ ብሎ ከአያታችን ጎን ደግሞ አጎቴ እስክንድር ተቀምጧል፤ ከወንድ አያቴ ፊት ለፊት ሴት አያታችን ከነሲኒዋ ተቀምጣለች እኔ እና አጎቴ እስክንድር ደግሞ ከጎን በኩል በተከታታይ ተቀምጠናል፡፡

አስቀድሞ ድርቅ ያለ ጥሮሾ ሴት አያቴ ለወንድ አያቴ ሰጠቻቸው እሳቸውም ቆራርሰው ጉማጁን ከእጅ አፍ እያሉ ሰው መኖሩንም ዘነጉት፡፡ እሳቸውን ጎልባ ከሚማረው አጎቴ ናስቶሲን በስተቀር ማንም ሰው ስለምንም ነገር መገላመጥም ሆነ ደፍሮ ማናገር አይቻለውም፡፡ በዚህ ጊዜ ተስፋው የተሟጠጠው እስክንድር ከጎናቸው ቁጭ ብሎ ድመት የዘረፈች እያስመሰለ እሳቸው "ችፍ" ሲሉ እሱ ጉማጆቹን ያከፋፍል ጀመረ፡፡ እሳቸውም የኋላ ኋላ ነገሩ ገብቷቸው የቆራረሱትን ጉማጆች በእጅ እጆቻችን ላይ አደረጉልን፡፡ ቡናው ተጠጥቶ፤ ጥሮሾውም ተበልቶ የቀረው የ’ራት ሰዓት ብቻ ነበር፡፡ እናም በገበታው፤ በእርቦው እና በትልልቅ ትሪዎች ቀርቦ ከመረቁ ለልጆች ሲቀዳ ስጋው ግን የአንድ ሰው ብቻ ሆነ እስክንድር በጣም ስሜታዊ እንደሆነ ያወኩት ያን እለት ነበር፡፡ በጣም እየተቆጣ የተሠራውን ምግብ ከሴት አያታችን ላይ ነጥቆ ከፊቷ ከአመድ ጋር ለወሰው፡፡

ሴት አያቴ ባደረገው ነገር ተራግማ እየተበሳጨች ሁሉንም ነገር ትታ እሳቱን በኩበት አዳፍና ወንድ አያቴም ጉዟቸውን ወደ ፎቅ አድርገው ተኛን።

- * *

ከወትሮ በተለየ ሁኔታ በማግስቱ ጠዋት በማለዳው ስለተነሳሁ ለመጀመሪያ ጊዜ የተላመዱኝን ውሾች አስከትዬ ከግቢው ስወጣ አባባ ጥበቡን ከውጪ ሲንጎራደዱ አገኘኋቸው። እኔን በጣም ከመውደዳቸው የተነሳ "ጉቼ" ብለው ይጠሰሩኛል። እናም አወጣጤ ግራ ስለገባቸው እንደ እሳት እጅ ቆላልፎ ከሚያቃጥለው የጉም ብርድ እያጫወቱ እጅ ለእጅ ተያይዘን አብረን ገባን።

እንደተለመደው ቤቱ በጠዋት የኩበት ጭስ ታፍኖ 'ምድጃው ወግ ማዕረጉን እንደያዘ ጠበቀን። ማለዳ እንደመሆኑ መጠን ሁለቱ አጎቶቼ ጠዋት ቡና እስኪጠጣ ከቤት ቁጭብለው አይጠብቁም እና አባባ ጥበቡን ጠዋት ጠዋት ሁል ጊዜ እጃቸውን የማስታጥበው እኔው ሆንኩ። እሳቸውም "የዘሊላው ሚካኤል አንተ በሰላም ያሳደርከኝ አምላክ በሰላም አውለኝ......" ብለው ከፀለዩ በኋላ መርቀው "እንትፍትፍ" ይሉብኛል። ብቻ ቡናው ተጠጥቶ፤ ቁርሱ ተበልቶ ሲጠናቀቅ አጎቶቼ ከሰፈር ቅኝቱ ተመልሰው ቁርሳቸውን ከበሉ በኋላ ታላቅየው ወደ አዝመራ ሲሰማራ ታናሽዬው ወደ እረኝነት ተሰማርተው እኔ እና እስክንድር ተያይዘን ወደ ጋራው ነጎድን።

ይህ ቀን ሌላ አዲስ ነገር ያየሁበት እለት ነበር። የአባቴን ቤተሰቦች ቤት ከተራራው አናት ሲወጣ ወለል ብሎ ከሌላኛው ተራራማ ሜዳ ይታያል። በቃ ያ! ሁሉ ስፍራ የዘመድ አዝማድ ነው። እስክንድር ይሄንን እያሳየ ቁልቁል አስመልክቶ በሥዕል የተሳሉ ከሚመስሉ ቤቶች ውስጥ ስለምንኖርበት ቤት አቅጣጫ ጠየቀኝ። እናም እየዘላበድኩ ብዙ ለማሳየት ብሞክርም ነገሩ ሳይሳካልኝ ቀርቶ በጥያቄ ስረታ በእጆቹ ከፍ አድርጎ የኛን ግቢ እየጠቆመ ፍክት አድርጎ አሳየኝ።

የኤርሚያስ ቤተሰቦች ጋር ለምንም አንሄድም። ፋሲ ጋና ቡሄንም ቢሆን ከነሱ ጋር ትውውቅ የለንም። እሱም እናት እና አባት እንዳለው ያወኩት ከዛን ጊዜ በኋላ ነበር። ምክንያቱም ከዮቶር ውጪ ብዙኃኑ ወደኛ ቤት ቢመጡም ዘመዶቻችን ስለመሆናቸው አናላውቅም። ብቻ ታሪኩ አስጠሊታ ነበር። የህሌና የኑሮ መዛባትም ከዚህ ጋር ይጀምራል። የኤርሚያስ እናት በአንድ ወቅት ህሌናን በአራስነት ለመጠየቅ ትመጣለች፤ ከዛም ለመጠይቅ ተሰናድቶ የቀረበው እጅ መንሻ የማይሆን ነው ሲሉ እሷ ያለች በማስመሰል ለሌላው ሲያወጉ የዮቶር ባለቤት ይሰማሉ።

በዚህ ጊዜ እግራቸው ወደ ለመደው ባዕዳዊ አምልኮት ወደ ሆነው ‹‹አዋቂ›› ወደሚሉት አካል ይሄዳሉ። እውነቱ ግን አዋቂ ከተባለው ሰውዬ ንግግር በተቃራኒው ይሆን እና አማት 'ና ምራት ጭድ እና እሳተ ሆነው ነገሩ በጦርነት ድምዳሜውን ያገኛል። አማት ከምራት ጋር ምራትም ከአማት ጋር በአንድ ገበታ ተቀምጠውም ሆነ ተቋድሰው መብላት አይችሉም። ከነሱ ጋር የማንሄደውም ለዚህ ነው።

ከፊታችን አዲሱ ዘመን 1994ዓ.ም ሊመጣ በጣት የሚቆጠሩ ቀናቶች ቀርተውታል። የአያቶቼም ጉድ ጉድ እና ዝግጅት በጣሙን ከሯል። እህል በአህያ ከከተማው ተወስዶ ይፈጫል፤ ልብስ ለመላ ቤተሰቡ ጭምር ሲገዛ አባባ ጥበቡ ሄደዋል። ሌላውም በየፊናው ተሰማርቶ እኔ ና እስክንድር ከመንጋው ቀርተናል።

በዚህ ሁነት ቀን ቀንን እየወለደ ክረምቱም ተገባዶ የበጋው ወር ሊመጣ "ዶሮ ከጮኽ የለም ለሊት፤ ቡሄ ካለፈ የለም ክረምት" እንደሚባለው ሆኖ ነሐሴ ጊዜውን ለቆ ለቀጻግሚ ሊሰጥ ጥቂት ቀናቶች ብቻ ናቸው የቀሩት። ቴጵ ሁሉ ተረስቶ ፀሐይ በወጣች ቁጥር አያቴ የሚያዳምጧት ሬድዮን በለምለሙ ሳር

ብርሃን ሲያንጃብብ ለቀውት ድምፁ በአየር ሲንሳፈፍ በ’ርግጥ በሀሳበ የተሳለውን ገነት ይመስላል። በወቅቱ ከብት እረኝነት ላይ ጎበዝ የምባል አይደለሁም እና በትሬን ጥዬ ወደ መንጋው ስሮጥ "ልትነክሳቸው ነው?!" በሚል ተግሳጽ "እረኛ ያለበትር፤ ተማሪ ያለ ብዕር እና ክታብ፤ ወታደር ያለ መሳሪያው ምንም አይደለም።" ሁሉንም እስከነ ትንታኔው በሥነ-ሥርዓቱ ይነግሩኛል። በተቻለኝ መጠን ለማስተካከል ብጥርም የልጅነት እና በቤተሰብ ውስጥ የነበረ መልካም ያልሆነ የንግግር ግብረ መልስ አፍዝዞኝ መልሼ እዘነጋዋለሁ።

በ’ርግጥ እንደ ትልቅነታቸው ትልቅ እውቀት መግበውኛል። ማለትም መሆን ያለብህን መሆን ትችላለህ እንደ ማለት ነው። ነገር ግን የሕጻንነት አእምሮ ይህንን ተቀብሎ ማገናዘብ ባይችልም በወቅቱ ግን ከውስጤ ሆኖ እስከ ዛሬም ድረስ ሥራውን ይረሳል። አያቴ ጎበዝ አሽሙረኛ እና ቁምነገረኛ እንዲሁም የተግባር ሰው ናቸው። ሁለቱ አጎቶቼን ወደ አረም የላኳቸው አያቴ የመጀመሪያ ቀን የእረኝነት ውሏችን በዚሁ ተጠናቀቀ።

አባባ ጥበቡ ባለፈው ሳምንት ለግብይትት ወደ ገበያ ሲሄዱ ለኔ የተገዛልኝ ሙሉ ነጣ ያለ ሰማያዊ ሙሉ ልብስ፤ ቆንጆዬ እና በመጠኔ የሆነች ትንሽዬ ጫማ ሲሆን ለሌላውም በየፍላጎቱ እና አቅሙ እንደፈቀደው ተገዝቶላቸዋል። እንቁጣጣሽ (ቅዱስ ዮሐንስ) ደርሶ ኮረዳው ያዘጋጀውን እንግጫ ለቤቱ እያዳረሰ በጭፈራ እና ረገዳ አቅልጦ እማወራዋ እትዬ አበባ ቅር ካላት ትንሽ አልጎምጉማ ዳግም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ጎረቤት ለጎረቤት ጉድ እስከሚል ድረስ ተጨፍሮ ቤት ያፈራውን ቀማምሰው መርቀው እና ተመርቀው ይሸኛል።

በ*ርግጥ የአምስት ዓመት ልጅ ብሆንም የአያቴቼ ቤት ስለተመቸኝ ቤተሰቤን ረስቻቸዋለሁ። መኝታውንም ተላምጄ የገጠሩን ገፀባህሪም ተላብሼዋለሁ። በቃ ምርጥ የገጠር ልጅ ነበርኩ። ላልወደው የማልመኘውንም ወተት እትዬ አበባ ስታልብ እንደ ድመት ካጠገቧ አልለይ ሆነ። እንቁጣጣሽ አልፎ ሌላኛው ዓመት በዓል መስቀል ደርሶ ዋዜማው በችቦ ማቀጣጠል እና ‹‹የቅንጬ ፈጫሳ›› ተጀመረ።

በመስቀል በዓል እርድ በአከባቢው በማህበረሰብ ብዙም የተለመደ አይደለም። ይሁን እንጂ አባባ ጥበቡ ቤት ሳይታረድ ዓመት በዓል መልክም መዓዛ እና ለዛ አይኖረውም። ማግስቱን በግ ታርዶ ተጠባብሶ ከበረቱም፤ ከቤቱም ሥጋው ’ና ቅንጬው እየተፈነጣጠቀ አባወራው እና እማዋራዋ ቀማምሰው እማወራዋ ጨሌዋን ቅቤ እየቀባች በሁለት እጇ ትጎርስ እና ለመላው የቤተሰቡ አባላት ይቋደሳል። ከዛ በተረፈ ጎረቤት በራሱ ፍላጎት እና ጊዜ ስለሚመጣ መጥራት ብሎ ነገር በፍፁም አልነበረም።

አባባ ጥበቡ የቀ/ኃ/ሥ የጎበዝ አለቃ ሲሆኑ የደርግ ደግሞ የሚሊሻ ወታደር ነበሩ። እናም ‹‹ ከሰው ቤት መሄድ ቀላዋጭነት ነው።›› ስለሚሉ ከማንም ቤት ሳይጠሩ ድርሽ ማለት አይፈልጉም። የሚሄዱ ልጆቻቸውንም ከመጥላት ውጪ አይወዷቸውም።

የመስቀል በዐል በነሱ ዘንድ የሚከበረው በኮረዶች እና በወጣቶች ጭፈራ ነው። ቀኑን ሙሉ ቦታ ተቀጣጥረው የዓመት ናፍቆታቸውንም የሚወጡበት በዐይን ተግባብቶ በልብ የተፈላለገው ለጋብቻ የሚተጫጭበት ሲሆን በሀገሩ ደንብ መሰረት ግን ሁሉም ከከናፍር ወዳጆቻቸው ጋር ተገኛኝተው ከንፈር ወዳጅ የሚሳሳሙበት በዓልም ነው። እኔ እና አባባ ጥበቡ እያደር በተረታቸው እና በቀልዳቸው መግባባት ከጀመርን ወራቶች አልፈው መንፈቃት ሰርበውልናል። ብዙ ጊዜ ስለ አለቃ ገብረሃና እና አንዳንድ አሲቂኝ ቁምነገር አዘል ሥነ-ቃሎችን ከምድጃው አስቀምጠው አፌ ተከፍቶ ጉሮሮዬ እስከሚታይ በሰመመን ያስናኙኛል።

## *እኛ!! የጩንቅ ዘመናቶች*

በወቅቱ የተሻሉ የተባሉ የኢትዮጲያ የከተማ ክፍሎች የአፀደ ሕጻናት ት/ት የጀመሩበት ወቅት ቢሆንም ገና በመዳረስ ላይ የነበረ በግል ድርጅት ስምም የሚሰጥ ስለነበረ እኛ ጋር ተደራሽ አልነበረም፡፡ ይሁን እንጂ ከዚህ በፊት ያቅቱኝ የነበሩት ፊደላቶች በእስክንድር ጥረት እና ኃይል 32ቱን ፊደላት እስከነ ዝርያቸው በአግባቡ ጠንቅቄ አውቂያለሁ፡፡ ነጋድረስም አንዳንዴ ጎልማሶችን ሲያስተምር ስለነበር ጠዋት ጠዋት ይዞኝ ይሄዳል፡፡ እሱ በጥያቄ የተካነ ስለነበር ለነኚህ የፊደላት እውቀት መጠናከር ታላቁን ሚና በአግባቡ ተወጥቷል፡፡

ወራቶች ገስግሰው ህዳር ሲደርስ ሌላኛው የባህል በዓል በጥሮሾ እና በበግ ስጋ ከከብቶች ጎለት ውሥጥ ተከበረ፡፡ እስክንድርን ስለዚህ ጉዳይ ብጠይቀውም አምላክን እየተማፀኑበት እንደሆነ እና ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑበት እንደሆነ ነገረኝ፡፡ እኔም ከእትዬ አበባ ጋር ቆሎውን፣ ሱፉን፣ ጭብጦውን፣ ፈንዲሻውን እና የቀረቡትን መአት ቆላ ቀቁልቶች እየበተንኩ ‹‹አሜን አሜን …›› እያልኩ ከዛ ተነስተን ከቤት በስተጀርባ ከተሰራች አነስ ያለች፣ ውስጧ ወርቃማ በሆነው ምንጣፍ እና መጋረጃ ባበደው ኩሽና ቤት ውስጥ ገባን፡፡ በዚህ ጊዜ አባባ ጥበቡ ወደ ማድቤት አልገቡም ነበር፡፡ እትዬ አበባ፣ እስክንድር፣ ናስቶሲን እና እኔ ብቻ ነበርን፡፡

እትዬ አበባ ከመጋረጃው ውስጥ ገብተው ሲቀመጡ የተቀረነው ከመጋረጃው ፊት ለፊት ተቀምጠን ከሙዙ፣ ከቡርቱካኑ፣ ከቡናው፣ ከዳቦው እና ከቆሎው እንበላለን፡፡ በቃ የኛ አምላክ መመስገን ስላለበት ሁሌም ማታ ማታ ከጀርባ እየዞርን ‹‹እግዚኦ… አሜን… አሜን›› እያልን እናመሰግናለን፡፡ ዋናው ትልቁ ገልማ የሚባለው አበልጃችን ጋር ስለነበረ፡፡ በተለይ አንዳንድ ቀን ከበሮ እየተመታ ‹‹ዝየራ›› ነው እየተባለ ሲያመሰግኑ ከኛ ቤት ቁጭ ብለን እየሰማን እናመሰግናለን፡፡ እዛ ቤት የማይመጣ የሰው ዘር የለም ብቻ ከየት እንደሚመጡ ባይታወቅም ይጎርፋሉ፡፡ በተለይ የመስቀል ማግስት ኢሬቻ እየተባለ የሚጠራው የአምልኮ ወቅት አንዳንዱ ሰው አማቻችን ላይ ያለው መንፈስ ሳይፈቅድ አይሄዱም፡፡

በዚህ ሁነት ሌላኛው በዓል ገና ተጨምሮ በሩር ጨዋታ ታልፎ ፋሲካም ተደግሞ የግንቦት አንድ የማላውቀው አዲሱ ክብረ በዓል መጣ፡፡ ይህ በዓልም ከህዳሩ ብዙም የሚለይ አይደለም፡፡ የተለየ የሚያደርገው አንዳንዱ በህብረት ተሰባስበው አባት አባት የሆኑ ሰዎች ቀጠሜ ይዘው ወንዝ ዳር በግ አርደው ደሙን ወደ ወንዝ ውስጥ አፍስሰው ስጋውን እዛው ጠባብሰው ፈነጣጥቀው ትልልቆቹ አባወራዎች ከቀመሱ በኋላ ለሌላው በአመራሮ ቅጠል በቅቤ እየተለወሰ ይሰጣል፡፡ ልላው ደግሞ ጋራ ወይም አድባር ብለው በአንፍር ስር በግ አርደው ሁሉም ከየቤቱ ጥሮሾ እያመጣ ሴቶቹ በጨሌ ተንቆጥቁጠው የተዘገጃጀው ስጋ እየተጠባበሰ ይበላል፡፡

ግንቦት መሐል አከባቢ ወርልድ ቪዝን ኢትዮጵያ በሕጻናት ላይ የሚሰራ የተራድኦ ድርጅት ስለነበር በማህበረሰቡ የሥራ አባላቶች ቅስቀሳ ያካሄድ ነበር፡፡ ቅስቀሳውም የገጠር እና የአከባቢውን ሕጻናት በመርዳት ት/ት እንዲማሩ ማድርግ ነበር፡፡ እናም ቅስቀሳው የኛ ሰፈር ቀጠና ደርሶ ቀስቃሽ ወደ እኔ አያቶች መጥታ እኔን ታገኛለች፡፡ ያልጠፋችብኝ ሁሌም የማልለያት የማወቃት የሣህ-ለወርቅ ነበረች፡፡ በእጇቷ ፀጉሬን እያሻሸች ካዋራችኝ በኋላ የተለየ ፍቅር በማሳየት ፎቶ አንስታ ሥሜንም መዝግባ በማስጠንቀቂያ ጭምር መማር እናዳለብኝ በማስገንዘብ እና ከበድ ያለ ቅጣት ሊኖረው እንደሚችል አባባ ጥበቡን አሳስባ ሄደ፡፡

• * *

# ምዕራፍ ሁለት
# የስቃዩ ወጨፍ በቤትም የሚያስጠልል አይደለም!!

በማግስቱ ወንድሜ አላዛር ታሞ ስለነበር ‹‹ወንድሜ ና! ና! አብረን ዛሬን እንጫወት›› የሚለው ንግግሩ ህሌናን ስለጨነቃት በእስክንድር እንድመጣ መልዕክት ተላከ፡፡ እሱም በፈረሱ ይዞኝ ከቤት ደረሰ፡፡ አላዛር እንጥሉን ታሞ ነበር፡፡ ኤርሚያስ እና ህሌህ የሚያደርጉት ጠፍቷቸው ቤቱን በጭንቅ እርምጃ ያምሱታል፡፡ በዚህ ጊዜ የኤርሚያስ ወንድም ሚስት ሁኔታቸው ስላላማራት ዘራይድረስን አስከትላ አላዛርን በባሕላዊ ሀኪም የወረደችውን ጉሮሮ አስቆርጠው ተመለሱ፡፡ አላዛርም እያደር ተሸሎት ጨዋታውን ቀጥሏል፡፡ ጣይቱም የሶስት ዓመት ከአምት ወር ስለነበረች ከመራመድም አልፋ በደንብ መናገር ጀምራለች፡፡ ነገር ግን ሁሉም የኔ ካልሆነ ሞቼ እገኛለሁ ስለምትል አንዳንዴ ከአላዛር ጋር ስም እየሰጠን እናስለቅሳታለን፡፡

ቤተሰብን በድንጋይ በር ስታዘጋ እኛ ግን እየቆነጠጥን ስንመልሳት ለቅሶዋ ማባሪያ ያጣል፡፡ ህሌና እና ኤርሚያስ እኛ በእሷ ላይ ያደረግነውን እኛ ላይ በማስመሰል እያደርጉ እሷ ዝም እንድትል ያደርጋሉ፡፡ ቤቱ ከበፊቱ ምንም የተለወጠ ነገር የለውም ይባስ ብሶበት የተበላበት ሰሀን በየስራቻው እና ሳሎኑ ዝም ተብሎ ተጣጥሏል፡፡ የጥል ዙሩም ከበፊቱ ከሮ አይቶ ለመስማትም ይዘገንናል፡፡ ገጠር ላይ አባባ ጥበቡ ሲቆጡ እትዬ አበባ ከማልጎምጎም ውጪ ደፍራ የምትመልሰው ክፉ ምላሽ የላትም፡፡ እሳቸው ትንሽ ሞቅ ሲላቸው በጣም ጥያቄ ያበዛሉ ነገር ግን እትዬ አበባ መልሰው እያቃለዱ እስከሚሄዱ መታገስ እንጂ እንደ ኤርሚያስ ጭብጥ ኩርምት እስኪሉ ድረስ እንደ ህሌላ አያደርጉም፡፡

ህሌና ስድቦቿ ሁሉ አፀያፊ ቃላትን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ዕድሜዋም ሃያ ስድስት ስለነበረ የጉርምስናም ሊሆን ይችላል ቢባል በዚሁ ቀጥሎም በአርባዎቹ ዓመታት ውስጥ መታረም አልተቻለውም፡፡ ብቻ ካለመውደድም የተነሳ ይመስለኛል በቤት ውስጥ ምንም ታጥቶ ቢኖር ሰላም የለም፡፡

ዘራይድረስ ዮቶር የኤርሚያስ ወንድም ነው፡፡ ሲበዛ ብልጣ ብልጥ እና ህይወቱን በትንሽዬ ነገር በጥበብ የሚመራ ነው፡፡ አሁን ላይ የሚሰራው ከአጎቱ ወፍጮ ቤት ሲሆን አንዳንዴም የራሱን ሱቅ ጀምሮ ያዝ ለቀቅ እያደረገ ይተዋል፡፡ ታድያ ግንቦት አጋማሽ ሰላም ልለው ከሚሠራበት ቦታ ብሄድ ሰላምታ ተለዋውጠን ኮቾሮ እየበላሁ ለምን እንደመጣሁ ሲጠይቀኝ እኔም ያላንዳች ዝንፊት ስነግረው ተገርሞ ለመፈተሽ በሚመስል መልኩ ከሚሸጠው ሱቅ የተበጫጨቀ ደብተር እና እስኪርቤቶ ሰጥቶ ወደ ት/ቤት ላከኝ፡፡

ት/ቤቱ በሶስት መቶ ሜትር ላይ የሚገኝ ስለነበር ያለምንም ፍራቻ ከአንድ ክፍል ሰተት ብዬ ገባሁ፡፡ ክፍሉ ስድስተኛ ክፍል ነው፡፡ ልጆች የሬድዮ ትምህርት ያዳምጣሉ፡፡ መምህር በክላሱ የለም፡፡ አለቃ የጥያቄ እና ምላሽ ሰዓት ሲሰጥ እንደ መምህር ሆኖ በሥነ-ሥርዓቱ ያስተናግዳል፡፡ የሚረብሽም ተማሪ ካገኘ በያዛው ልምጭ ከመቀመጫው እና ከጆርባው ሰትሮ ያስተካክለዋል፡፡ በዚህ ቅፅበት የሥነ-ዜጋ መምህር ዐይነ-ስውር ስለነበረች በዝግታ ማቋሚያዋን ይዛ ከወንበሩ አልፋ ተቀመጠች፡፡

## *እኛ!! የጨንቅ ዘመናቶች*

የሬድዮ ት/ት አልቆ ሙዚቃ ሲጀምር ሲል አለቃው ዘግቶ ከቦታው እንደተቀመጠ መምህርቷ ተነስተው ሰላምታ ሲቸሩን እኔም ብድግ ስል አንዳንድ ተማሪዎች በአግራሞት ሳቁ፡፡ በዚህ ጊዜ ምክንያቱን ከመጠየቅ ያልቦዘኑት መምህር ጥያቄያቸውን ሲያቀርቡ አንድ ትንሽዬ ልጅ በመሐላቸው እንዳለ ነገሯቸው፡፡ መምህርትም በመገረም ካናገሩኝ በኋላ ቀድመው ከውጪ አጎቴ ዘርይድረስን አግኝተውት ስለነበር ከዛው ከወንበራቸው የቁጥር ፒዝሎች እና በክብሪት ቀፎ ውስጥ የተቀመጡ በተለያየ ቀለም የተዋቡ ቁጥሮችን ሰጥተውኝ ወደ ዕለት ሥራቸው ተሰማሩ፡፡

በመጨረሻም ክፍለ ጊዜው ስላለቀ መምህርት ይዘውኝ ሊወጡ ስሉ ከሬድዮ የሰማሁትን ሰላምታ እንዲህ ስል ስጠኂቸው ‹‹ደህና ሁኑ ተማሪዎች!›› ድምፁም ጮክ ያለ ስለነበር ሁሉም ‹‹ዋህ!!›› ብሎ ሳቀ፡፡ አጎቴ ዘራይድረስም ከክፍሉ ስንወጣ ከበሩ ጠብቆ ተሸክሞ እየሳቀ ይዞኝ ወደ ቤት ተመለሰ፡፡

• * *

ዳግመኛው ክረምት 1995ዓ.ምን ይዞ ሊመጣ እያስገመገመ ከወቅቱ ደረሰ፡፡ ከገጠር እስክንድር ጋር ከብት ጥበቃውን በትንሹም ቢሆን ለምጃለሁ፡፡ እናም ከኛ ቤት ለመንጋ ጥበቃ የገባው ዘብ ቤል ይባላል፡፡ ብዙ ጊዜ ከሜዳ ይዞኝ ይሄድ 'ና እሱ ከመንጋው በሌላኛው ወገን ሲሆን እኔ በሌላኛው በኩል እጠብቅ ነበር፡፡ ታድያ ጩኸቱ ብሎም ትዕዛዙ እያሰለቸኝ ስለመጣ ላለመሄድ ጠዋት ጠዋት ከመኝታ ቀን ቀን ከሰፈሩ ራቅ እያልኩ እውላለሁ፡፡

ቤል አባት የሌለው ልጅ ሲሆን ሲተዳደር የነበረው በዚሁ ሥራው ነው፡፡ በወቅቱ እኔ እንደ ወንድሜ አይቼ በችግሬ ጊዜ እያለቀስኩ ወደ እሱ ብሄድም አንዳንዴ ሌላ በደል በድሎ እንጣላ እና ቤተሰብ ይደኘናል፡፡ ህሌናም ከሚገባው በላይ ስለምትወደው ከኛ ለይታ አታየውም፡፡ በመጨረሻ ግን የቤል እናት የተሻለ ቦታ እንዳገኘችለት ለኤርሚያስ ነግራ ልትወስደው ወሰነች፡፡ እኔ እና አላዛር ቤል ሲሄድ እየተከተልን ብናለቅስም እናቱ ጨክና ይዛው ከመሄድ ልትቆጠብ አልቻለችም፡፡

ክረምቱ ማገባደጃ ላይ ልጆች እየቦረቁ ከቤት ቤት በጭለማው እየዞሩ የሚጫወቱት የቡሄ ጨዋታ ነበር፡፡ የቡሄ ጨዋታ በመላው ኢትዮጲያ ነሐሴ አስራ አንድ ጀምሮ  እስከ ፍልሰታ ፆም መፍቻ ይቀጥላል፡፡

በአማርኛ ‹‹መጣና ባመቱ እንዴት ሰነበቱ (2)

ክፈት በለው በሩን የጌታዬን /የመቤቴን/ (2) እያሉ ወደ ማወዳደሱ እና መማፀኛ እንጌርጉሮ ይገባሉ፡፡

ሆያ ሆዬ ሆ (2)

-----------------

በኦሮምኛ ‹‹ደወና! ደወና! DHUፍኔ ጋ ከረ ኑበና፧ (2) እያሉ እነሱም ወደ ማወዳደሱ እና መማፀኛ እንጌርጉሮ ይገባሉ፡፡

ጎቤ ጎቢለ ሆ!

ጎባ አሃሬ

ብሪ አማሬ

## እኛ!! የጭንቅ ዘመናቶች

----------------- እያሉ ከተሰጣቸው መርቀው ካልተሰጣቸው በእንገርጎሮው ተራግመው ይሄዳሉ፡፡ ብቻ በጣም ደስ የሚል የወጣቶች ጨዋታ ነው፡፡ ክረምቱ በእንዲህ መልኩ አልፎ 1995ዓ.ምትን ተቀበልን፡፡ አዲሱ ዓመት ትምህርት ከአላዛር ጋር የምንጀምርበት ስለሆነ ከሚገባው በላይ ያስደሰተን ነበር፡፡ የት/ት ምዝገባ ነሐሴ 22 ቢደረግም አላዛር እጁን አዙሮ ጆሮውን መንካት ስላልቻለ ላለመመዝገብ መዝጋቢያን እና መምህራኖች አሻፈረኝ ብለው የነበረ ሲሆን ህሌና ዕድሜው መድረሱን እነሱ አብረዋት አለመውለዳቸውን በመንገር በጥል ጦርነት አስመዝባዋለች፡፡

አውነታው አላዛር የስድስት ዓመት ልጅ ነው፡፡ እኔ ደግሞ የሰባት ዓመት የትምህርት ካሪኩለሙ የሚፈቅደው ለአንደኛ ክፍል ሰባት ዓመት 'ና ካዛ በላይ ለሆኑ ልጆች ነው፡፡ ታድያ እኔ እና አላዛር ያ'ስራ ስድስት ሉክ ደብተር ተገዝቶልን ወደ ት/ቤት ከህሌና ጋር ስንሄዴ የጠበቁን ልጆች ሳይሆኑ በዕድሜ ጠንዝተው በቁመት ዛፍ የሚያካክሉ ናቸው፡፡ በዛ ላይ የገጠር ልጆች ስለሆኑ ከዛ የሚመጡት ከ15ዓመት በላይ የሆኑ ናቸው፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ ከት/ቤት እንደ መገኘታችን አላዛር ከህሌና ላለመለየት ቢፈልግም በማባበል እና ባስ ሲልም በማበሻሸቅ ከኔ ጋር አንድ ክፍል እንድንገባ ተደርጎ ህይወታችን ከት/ት ሆነ፡፡ ታድያ ከመነታረክ እና ከችግር ያለወጣው ህይወት በችግር ላይ ሌላ የችግር ሰንኮፍ ሲጨምር ሴት ልጅ ፍለጋ ሌላ ልጅ ተጠነሰሰ፡፡

አላዛር ከት/ት መውደቅን የሚያስበው በሰውነት እንደመውደቅ ዓይነት አድርጎ ነው፡፡ እኔ ደግሞ ቅላትን መሰረት አድርጌ ሲሆን እሱ በሄደበት ሁሉ መምህራን እያዩት ወድቆ ሰነፍ መባልን አይሻም፡፡ ከወደቀም በፍጥነት ተነስቶ ለማስተባበል ትልቅ ጥረት ያደርጋል፡፡ እኔም መምህራችን ለምን ወደ ት/ቤት እንደመጣሁ ሲጠይቁኝ እነሱንም አትኩሮት ኖሮኝ የነሱን ቀለም እና የራሴን ቀለም በደንብ ለይቼ ባላውቀውም ‹‹ቀይ እንድሆን›› አላቸው ነበር፡፡

ታድያ ብዙ ጊዜ አስታፍ ላይ እያቀፉ ጉንጭ ጉንጫችንን እየሳሙ ስለሚጠይቁን በምላሻችን ተደመው ይስቃሉ፡፡ በተለይ በ'ረፍት ሰዓት ከክላስ እንደወጣን ሌላው እየተሯሯጠ ሲጫወት እኛ ከነሱ ጋር በሳቅ ተፍነክንከን ተመልሰን እንገባለን፡፡ ታድያ ነገሩ እያደር የመወደቅ እና የማለፉ ነገር ገብቶን በት/ችን ላይ ፈጣን እየሆንን ብንመጣም ድግግሞሽ እና ተመሳሳይነት ያለው የተንዛዛ ት/ቸው አንገሽጋሽ እና ለኛ የማይመጥን ነበር፡፡ በዛ ላይ በእንግሊዘኛ ፊደላት ላይ ያለው የተዛባ አስተምህሮት በድግግሞሹ ላይ ተጨምሮ ምንም ትርጉም የሌለው ት/ታዊ ዳራ ያልነበረው ነው፡፡ ጥሬ ቃሉን ከመስጠት እና የቁጥር ቃላት እየመሰረቱ ሲያስጮሁ ከመዋል ውጪ ምንም የፊደሎችን ድምፅ እነሱም የሚያውቋቸው አይመስልም፡፡

የመንግስት ት/ት ቤት እንደ መሆኑ መጠን ክትትልም ስለማይደረግበት እና ሁሉም በሚመለከተው የተመረቀበት ዲፓርትመንት ስለማይሠራ እንብዛም ትውልድ የማይፈለግበት ወቅት ነበር፡፡ በሂሳብ የተመረቀው አምስቱንም የትምህርት ዘርፍ ያለምንም እውቀት በግዳጅ ይዞ ይሰራል፡፡ ይህ ደግሞ ለውትድርና እንጂ ሀገርን ለሚረከብ የዛሬ እንቦቃቅላ የነገ ሀገር ተረካቢ ባለዳ ትውልድ አያስፈልግም ነበር፡፡

## *እኛ!! የጭንቅ ዘመናቶች*

እንደ እውነቱ ከሆነ አሁን ላይ ወደ ት/ቤት ጠዋት ቁርስ ሳንበላ የቤተሰብ ንትርክ እንደ ወተት ተግተን የምንመላለስበት ቀናቶች እየተበራከቱ ናቸው። ከክፍል ገብተን እንደ ሰይጣን መስለን የምናየውን ጥቁር ሰሌዳ እንኳን ባግባቡ የሚያዩ ዐይኖች በብዥታ ታጥረው፤ በትዕዛዝ የተወጠረውን አእምሮ ሆድ እያስጨነቀው ሁሌም የሚያስበው የኩሽና ቤት ህይወትን ከሆነም ሰነባብቷል። እጆቻችን ለተው እስኪንቀጠጡ እስከ ሁለት ሰዓት መቀመጥ የጀመሩ መቀመጫዎች ተርገብግበው 'ረፍትን ጠብቀው እግርን ከቤት ቢያሮጡም መለኪያ የሚያንቃርሩ ተሳፋ ቢስ ሰዎችን እና የህሌናን ስንፍና ተግቶ ከመመለስ ውጪ ምንም ቁብ ምላሽ ሳይገኝ ዕዝ ወደሆነው ት/ቤት ለሌላኛው አጋማሽ ሰዓት ውሎው ተጠናቆ እንመለሳለን።

መምህር ቀለም እንጂ ምግብ ላይመግብ ይችላል። ነገር ግን ከስሙ ብንነሳ የታመመ ልጅ ቢኖረው ወደ ሐኪም ቤት ወስዶ መንስኤውን ከነምክንያቱ አረጋግጦ በመድሃኒት ማዳን እንደሚቻለው ስለምን ዐይኑ ያየውን በሽተኛ መድሃኒቱ በእጁ ሆኖ አክሞ ማዳን አቅቶት ይሆን?! ነገሩ ወዲህ ነው ለራሱ ተጠቅሞ ሊድን ያልቻለበትን መድሃኒት ከእጁ ላይ እያለ አለማወቁ ነው።

በወቅቱ ከሬድዮን ውጪ የተለቪዥን ተደራሽነቱ ብዙም አልነበረም እና ይህንኑ የድካም መንፈስ ለማስታገስ እንዲሆን መምህር ‹‹ሑሱ›› ብለን በቀልድ ስማቸው የምንጠራቸው ከት/ቤቱ ቴሌቪዥን አስር አስር ሳንቲም እየተቀበሉ ያሳዩናል። ልጅነት በዚህ ቢታለለል ሆኖ ማታ ያየነውን ከመንጋ ጥበቃ መስክ ተሰብስበን እየጠበቅን ገፀ-ባህሪዎቹን እየተላበስን ከት/ት መልስ ስንተውን፤ ኳስ ስንጫወት እናመሻለን። ህይወት በዚሁ ቀጥላ ከመጀመሪያው ክፍል በሞተ ውጤት መስኮት ብለው ብዙዎቹ በሚጠሩት ት/ት ወደ ቀጣዩ ክፍል ከገፋትም ቋጥኝም ቢሆን ይንከባለላል እና ከክፍል ወደ ሌላኛው ክፍል ተዘዋወርን።

እሁድ እና ቅዳሜን ኤርሚያስ እና ህሌና ረሃብን በመለኪያ አረቄ እንደሚያስታግሱት ሁሉ መንጋውን ከሚዳ ይዘን እንወርድ እና የጭቃ ዋንጫ እያዘጋጀን ከፌስታል እና ከጨርቅ ጥርቅም በተሰፋ የካልሲ ጨርቅ ኳስ ስንጫወት እንውላለን። ከቤት ተመልሰን ከማለዳው ዕድል ሳትቀና ቁርታ ተመሳሳ ከሆነ ከሰዓት ስንመለስ ‹‹ሲዲሳ›› የሚባለውን ነጭ ስራ ስር ቆፍረን በወንዙ ውሃ አጥበን ጣፋጩን መጠን ከዛው ውሃ እየጠጣን ስሩን እንጥላለን።

ትንሽ ቀማምሰን ጠገብ ስንልም ሰው ያደረው እንዳይቀረን ከወንዝ እየገባን ገላችንን ታጥበን እንዋኛለን። በቻ ዋናው ቅርበት ካለው ወንዝ ገብቶ መቦናቸት ነው። ከዛ የዘለለ ግን የዋና ምስልም ሆነ ተግበር የለውም። ሁለተኛ ክፍልም በጭለማው ህይወት ውስጥ አልፎ ወደ ቀጣዩ ክፍል ጋሪ ካላሰበው በሰው ሊደርስ ሆኖ ወደ ቀጣዩ ክፍል ተዘዋወርን። አላዛር ትንሽ እንደመሆኑ መጠን ብዙም ጫና አይደረግበትመም። እኔም ከገጠር ከመጣሁ በኋላ ለት/ት እንብዛም ትኩረት ስለማልሰጥ ለዚህም በቢመስል መልኩ እሱ ከኔ በት/ት ትንሽ ሻል ያለ ነበር። በዛ ላይ ከህመም ስላዳኑት የሚኖረውም ካጎቱ ዘራይድረስ ስለነበረ ባለቤቱ በት/ቱ ዘርፍ በደንብ ትከታተለው ነበር።

ህሌና ለዘጠኝ ወር በማህፀኗ ተሸክማ ስትጠብቀው የነበረው ፅንስ ሴት ሳይሆን ያማረ ቆንጆ ወንድ ልጅ ሆኖ ተከሰተ። በምጡ ወቅት እኔን ተከታትሎ የሚያስተናግደኝ ስላልነበረ ከቤት የነበረውን የሽሮ ዱቄት እየቃምኩ ከሚመለከተኝ ለመሰወር ከድንክ ስር እወሸቅ ነበረ። ይሄንን ያዩ አዋላጆች ሌላውን መፍትሄ ከመፈለግ ይልቅ ለህሌና ተናግረው አስቆነጠጡኝ። በዛ ምጥ ውስጥ እሷስ ምን ዓይነት እጅ እንደያዘላት ባላውቅም በቅጣቱ መጎዳት ክፉኛ አለቀስኩ።

በዚህ ጊዜ እውነቱ የገባት አያቴ አበባ ህሌናን ስታርስ ቆይታ በመጨረሻም ይዛኝ ወደ ገጠር ሄደች። እስክንድር እና ነጋድረስ ጎርመስ ብለው ስለነበር መንጋ መጠበቅን ይፀየፉ ጀምረዋል።

የመንጋው ብዛትም እንደበፊት አይደለም፡፡ በዛ ላይ የተጋባበት ይመስል አባባ ጥበቡ ከሌሉ ናስቶሲን እና እስክንድር በጭቅጭቅ እና ስድብ አበባን ቁም ስቅሏን ያበሏታል፡፡ ነጋድረስ ብዙ ጊዜ ከቤት አይቀመጥም ወደ ስራ ይሁን ወደጓደኞቹ ባላውቅም ቤት ሲውል አላየውም፡፡ እሱ አንዴ ከጓደኞቹ ጋር መጫወት መቀለድ ከጀመረ አመሻሹዋ በእሱ ትደምቃለች፡፡ በዛ ላይ አንዱ ሌላውን ሲሸኝ ወንዝ ወንዙን የሚግጠውን ፈረስ ፈልገን ስናስገባ ምሽቱ ከቤት ደምቆ ይጠብቀናል፡፡

ነጋድረስ ከዚህ በፊት ከእስክንድር ጋር መንጋ ስንጠብቅ ከጎሬው ደርሼ ካፉ ያመለጥኩትን ጅብ በድምፁ ብቻ የማውቀውን በአካል እየተከታተለ በጋራው ላይ ውሃ ሊጠጣ ቀበሮ ከጀርባው እየፈነጨችበት ሲሄድ አየሁት፡፡ አንድ እግሩ አጭር ስለሆነች ሲሄድ ያነክሳል፡፡ በምፈልግ ሰዓት አንዳንዴ ነጋድረስ ያሳየኛል፡፡ እስክንድር እያደር ለኔ ያለው ቦታ እየተሸረሸረ ነው፡፡ ምክንያቱም ካስያዘኝ ውጪ ሌላ ነገር ምንም እንዳልጨበጥኩ ከመጠይቁ ተረድቷል፡፡ ለዚህም ማስታረቂያ ይሆነን ዘንድ በርካታ የተረት መፀሀፎችን እያመጣ እንድተርክለት ያደርጋል፡፡ በ'ርግጥ የማንበብ ክህሎቴንም በዛው አጠናከርኩ፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኛውን ጊዜ ከናስቶሲን ጋር ስለማይስማሙ ከቤት መሰነባበቱም እየቀነሰ መጥቷል፡፡

የተለመደው የስኒ ረከቦት እስከነ ማዕረጉ በያለበት ተቀምጧል፡፡ ለየት የሚያደርገው ዛሬ ወንድ አያቴ የሚካኤል ፅዋ ስለነበር በቦታቸው አልነበሩም፡፡ ሲቀጥል ደግሞ ይመጣል ብዬ የምጠብቀው ነጋድረስ ዱካውም የለም፡፡ እንደ አጋጣሚ ሆኖ ዛሬ እስክንድር ከቤት መጥቷል የተለመደ የማስጠናት ሥራውን አጠናክሮ ቀጥሏላ፡፡ እኔም ከሙዚቃ መፅሐፉ ላይ አንዳንድ ግጥሞቹን በዜማ ስለሚልልኝ በጣም እወደዋለሁ፡፡ "ነይ ብራ ነይ ብራ"፤ "እቴሜቴ የሎሚ ሽታ"፤ "ውሽታሙ እረኛ"፤ "ውሻው ተራመደ"፤ "ሆያ ሆዬ /ጎቤ ጎቢለ ሆ/"፤ "አበባየሆሽ" እንዲሁም ከሬድዮ የሚሰማቸውን ሙዚቃዎች "ጮቀርሲ ሎሌ ሎሌ....፤ ሀምቱ መሌ ቆቶን ጣፊ ሙሩ....፤ መላዬ መላዬ መላዬ፤ እሸቱ ሌላው ሌላ ሌላው ኮረሪማው.... ብቻ ብዙውን እያደረገ ያዝናናኛል፡፡

የሱ ማጫወት መቀለድ በዚህ ብቻ አያበቃም ሌላም ነገር መቅሰም እንድችል ስለሚፈልግ ከፎቅ ይወስደኝ እና አንዳንድ በግርግዳ ላይ የተፃፉ የአባባል ዐ.ነገሮችን እንዳነብ ያደርገኛል፡፡ "ከሰው ሀገር መሔድ ያደርጋል ደንቆሮ፤ ውሺትን ዘልዬ ነከሰችኝ ዶሮ፤" ይሄንን ግጥም ከስነቃል ሰምታ የኔው እናት ነጭ አፈር በጥብጣ በግርግዳው ላይ እንደፃፈችው ነገረኝ፡፡ ብቻ እሱ እኔን ለማስደሰት ሁሉ ነገር አያልቅበት ነው፡፡ ዛሬ ከሌላው ቀን በተለየ አንድ ነገር አቦል ጀባ ተብያለሁ፡፡ ሌላ በጣም ደስ የሚል ትልቅ የተረት መፅሐፍ ነው፡፡ በውስጡ የያዛቸው ርዕሶች "ላሜ ቦራ፤ ብልጧ ጦጢት፤ ጉንዳን እና የውኃ እናት፤ሁለቱ ሞኞች፤ ቀበሮ እና አሞራ፤ ከባህር የተጣላው አንበሳ፤ ኤሊ እና ጥንቸል ........" ብቻ ብዙ ናቸው፡፡ ይሄንን መፅሐፍ ማንበብ የእኔ ሥራ ነበር እና በደስታ ማንበቤን ወድጄ ተገበርኩት፡፡

አባባ ጥበቡ እና እትዬ አበባም ያላቸው ጥብቅ ግንኙነት በ-ናስቶሲን ት/ት 'ና በእህቱ ከአያቶቹ መምጣት እንዲሁም ሽክም መሆናቸው ምክንያት ሻክሯል፡፡ በዚህ መሐል አንዱን ከሌላው አግባብቶ ለማኖር ነጋድረስ መከራውን ይበላል፡፡ ነገር ግን እንደ በፊቱ መኮን አልተቻለም ነበር፡፡ እትዬ አበባ ሁሌም ሲከፋት ወደ እናቷ ነበር እና የምትሄደው ቤቱን ለነጋድረስ ትታ ነጉዳ ነበር፡፡ እኔ ከት/ቤት ስመለስ ማንንም ላገኝ ሳልችል ከዛው ተቀምጬ ሳለሁ ነጋድረስ እና ጓደኛው ተያይዘው መጡ፡፡

ነጋድረስ እንደራበኝ ስላወቀ ከግቢው ይዞኝ ገብቶ የሚበላ ቢፈልግም ስላላገኘ በጥብቅ ከሚከለከለው እና ሊያጣላው ከሚችለው እርጎ ቀድቶ ሰጠኝ፡፡ እሱንም ጠጥቼ ነገሩ የበረደ ስላልመሰለው ከጓደኛው ቤት ይዞኝ ሄዶ የጓደኛው እናት ከምትጋግረው እንጀራ እያግባባ እንድትሰጠኝ አደረገ፡፡ እኔም እሱን ስበላ ጋብ ብሎልኝ ከአባባ ጥበቡ ጋር መንጋውን እንድጠብቅ ሰዶኝ እሱ ወደ ሥራ ሄደ፡፡

ማታ ላይ እትዬ አበባ መጥታ ቤቱ ውስጥ በኃይል እየተቆጣች ስታልጎመጉም በጣም ያስፈራ ነበር እና በዛ ቁጣዋ ላይ አባባ ጥበቡ ተጨምረው ሰውነቴ እስኪንቀጠቀጥ እያካለቡ ሊተውኝ አልቻሉም፡፡ በመጨረሻም ቁጣው ወደ በትር ሊቀየርብኝ ሆኖ ባልበላው እዳ እንደበላው በማስመሰል ነጋድረስ ላይ ከመርኩት፡፡ ነጋድረስ አስጠንቅቆኝ ስለነበር በጣም ደንግጦ ለማስተባበል ቢሞክርም በሱላይ ቁጣው በርትቶ እጅግ አዘነ፡፡

ታድያ ሰላም ያልፈለገው የአባባ ጥበቡ ቤት ጥቂት ወራቶችን አብሮ ቢሰነብትም- በናስቶሲን ምክንያት ወደ ንብረት መከፋፈሉ ውስጥ ገባ፡፡ ከዛም ልቆ እያለ እያለ ወደ መለያየት ደረጃ ደርሶ በወሰን እና በቤት ተከልለው ኑሮን ጀመሩ፡፡ እትዬ አበባ በተለይ ስትናደድ እና ዝናብ ጀርባዋን ሲነካት በጠና ትታመማለች፡፡ ነጋድረስ በዚህ ጊዜ ካንደኛው ቤት ሌላኛው ቡና እያፈላ ቤት ያፈራውን ለሁለቱም እያቀማመሰ ለማስታረቅ መታገሉን ታይዞታል፡፡

ከግብርናው በሬ ጠምዶ ሲያርስ የቆየ እልሁን መወጫ ሊያደርግብኝ በሚመስል አኳሁን ሰላሙን ሥራ ያበላሸሁ በማስመሰል የያዘውን ጅራፍ በሰውነቴ ላይ ደጋግሞ አጋደመው፡፡ ልመና አልበግር ብሎት በስተመጨረሻም የአባባ ጥበቡ መምጣት አስደንግጦት እያስፈራራ ዝም አሰኘኝ፡፡ ‹‹ይበለኝ የጄን ነው ያገኘሁት›› ማለት ይሄኔ ነው፡፡ በ’ርግጥ ከጓደኞቼ ጋር ማታ ላይ ተጣልቶ ስለመቱትም በጣም ተናዶ ነበር፡፡ በመጨረሻም እናት እና አባቱን ማስማማቱ ቢሳካለትም ሰላም ሊሰጡት ስላልቻሉ ጥሏቸው ወደ ደብረአ-ሌባ ተጓዘ፡፡

• * *

ከቤት የቀረነው ልጆች እኔ እና እስክንድር ነን፡፡ እስክንድር ደግሞ የነበረ ባህሪው ጠፍቶ ሌላ ሰው ሆኗል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ከዚህ በፊት የተለያዩ ሥራዎችን ለመስራት ቢሞክርም አባባ ጥበቡ በቅዝምዝም እያባረሩ አሰቃይተውታል፡፡ ይህን እያደረጉ አንጀት አልችል ሲላቸው በጣም ሰለሚወዱት ካላቸው ነገር በግዳጅ ገፍቶ ሲጠይቃቸው ይሰጡታል፡፡ ታድያ በዚህ መሐል ከነጋድረስ ቀጥሎ አንድ ያደረጋቸው እሱ ሲሆን ቤቱም ባይጎል ብሎ ከእርሻው ብሎም ካዝመራው ለፍቶ ጥሮ ያመረተውን ምርት ህሌና እና ኤርሚያስ ወደ ’ራሳቸው ጭነው ወስደው እንዲያስቀምጡ እኔውኑ ላኩ፡፡

ነገሩ እንዲህ ነው እስክንድር በእንቢተኝነቱ ከምሰሶ ታስሮ ከዚህ በፊት ቢቀጣም ሳያርመው ቀርቶ ብዙ ጊዜ ከሚውልባቸው ጓደኞች ጋር ከዘሩ ቆንጠር እያደረገ ይጠቀማል፡፡ በ’ርግጥ ጓደኞቹ ተሰጥቷቸው አይደለም ዘርፈው አረቂ ሲጠጡ ውለው ቢያድሩ ዴንታቸው አይደለም፡፡ እሱ ግን የየዋሕነቱን ምንም ያደርግላቸው ነበር፡፡

ሁነቱ ወደ ሌብነት በአባባ ጥበቡ ተቀይሮ እስክንድርን በወጣ በገባ ቁጥር ማደን ሆነ፡፡ ከእትዬ አበባ ጋርም ያለው ጥል ተሸሮ ሁለቱም ሰላም ሆኑ፡፡ እሱ ግን ከቤት ሲመጣ ላይበላው ለጓደኞቹ ሊሰጥ ሁለት ሶስት እንጀራ በፊታቸው እየዛተ ይዞ ይወጣ ጀመር፡፡ በዚሁ ያላበቃው የንዴት መወጫው አባባ ጥበቡን ለመበቀል ኮታቸውን እና የውትድርና ማዕረግ ያለበትን ልብሳቸውን ከነመታወቂያቸው ሳይቀር በጫጭቆ የሚሸጠውን ሸጠው፡፡

እስክንድር ናስቶሲንን አክብሮ ይፈራው ስለነበር በማስፈራሪያው ኮቱን ለመመለስ ቢሞክርም ሌላው ሳይሆን በማስጠንቀቂያ አለፈው፡፡ እኔም ከቤት እትዬ አበባ ስትሄድ የመንጋውን በረት አፅድቼ ውሃ ከጅረት አምጥቼ ዕዳጄን ጠፍጥፌ፤ ቡና አፍልቼ ስለምጠብቃት የምወደውን ሙዝ እና በወቅቱ ብርቅ የነበረውን ‹‹ፉርኖ›› ዳቦ ገዝታልኝ ትመጣለች፡፡

ከአራተኛ ክፍል ወደ አምስተኛ ክፍል የምዘዋወርበት ክረምት ከፊቴ እየመጣ ነው፡፡ አባባ ጥበቡ በዛ ግዙፍ ዕድሜያቸው ሲያርሱ እኔ በሮቹን በማብላት፤ በማጣመድ እና መንጋቸውን በመጠበቅ አግዛቸዋለሁ፡፡ እንዲህ እያልን ክረምት ገብቶ እስክንድርም እንደ ወንድሙ ከበረራው ከተማ ነጎደ፡፡

ህሴና እና ኤርሚያስ ክረምቱን መንጋውን ይዘው ከዛው አረም አርመው እያበሉ ከርመው መስከረም ደርሶ አዲሱን ዓመት ምክንያት በማድረግ አብሬያቸው ሄድኩኝ፡፡ መስከረም መገባደጃ ከነሱ ጋር አልፎ ት/ት በዛው ተጀመረ፡፡ ከገጠራማው ክፍል ከሶስት ወደ አምስት የተሸጋገሩት ተማሪዎች ስማቸዋን እንኳን የሚፅፉበትን ፊደል ከነመፈጠራቸው አያውቋቸውም፡፡ ከዛ የበቁ ተብለው የተላኩ ሲሆን ይሄን መሆናቸው በ'ርግጥም ያበቋቸው መምህራኖቹ ሳይሆኑ ተማሪዎቹ ናቸው ቢባል መምህራኖቹን ማተለቅ ቢሆን እንጂ ማሳነስ እንዳማይሆን እገምታለሁ፡፡

በ'ርግጥ ትክክለኛው መረዳትን የሚፈልገው እና ህግን ልንሸከምበት ብሎም ሳይንስን ልንማርበት የሚገባን ት/ት እዚህ ጋር ነው የሚጀምረው እና የሂሳብ፤ የሳይንስ፤ የፒዚክስ፤ የስፖርት እና የአማርኛ ት/ት አስተማሪዎች ከመቃብር ውስጥ እንደ ነበር አሬሳ የሚያነቃ የመንፈሱ ብቃት ነበራቸው፡፡ እኔም ራሴን እንደ ነስር እያደስኩ ሳይንሳዊ የሆነውን ት/ት በብቃት ደረጃውን እየተቆናጠጥኩት መጣሁ፡፡

አያቶቼ ረዳት ስላልነበራቸው ከዛው እየተመላለስኩ ስማር ስለነበር አንዳንዴ እስክንድር ከበረራ እየመጣ ሰላም ፈጥሮ ሊቀመጥ ሲሻ ሁለቱም በነገር አረንቋ ወግረው መልሰው ይሸኙታል፡፡ እስክንድር ከዚህ በፊት አባባ ጥበቡ የተናቁበት ቢመስለው የመስኖ ውሃ በጉልበት ወስዶ ከሚያጠጣው አበልጃቸው መልሶ ሲያጠጣ ሊመታው ህብረት ሲያዘጋጅ እሱ ቀድሞት ከሞት አፈፍ ተመልሷል፡፡ ታድያ በዚህ ጊዜ አባበ ጥበቡ በደካማ ጎኑ ተጠቅመው እሱኑ ጥፋተኛ አድርገው ለራሳቸው ካበልጃቸው ጋር ሰላም ፈጥረው መኖር ጀመሩ፡፡ በዚህ ምክንያት ነበር ትልቁ መቃቃር በቤተሰቡ እና በእስክንድር መሐል የተፈጠረው፡፡

ከዛ በፊትም አበልጃቸው በኔ ምክንያት ትንሽ ተተናኩሰው ነበር፡፡ ምክንያቱ ደግሞ በወረወርኳት ጠጠር የስድስት ዓመቱን ሕጻን ሁለት ጥርስ ገጨት ሳደርጋት ተነቃንቃ ነበር፡፡ ይሁን እጂ ከዛ ቀደም ‹‹ብር ሰርቀሻል›› በሚል እነሱ ‹‹ጌቶቹ›› ከሚሏቸው ሰዎች እየተመላለሱ ነበር እና ይሄንን አጋጣሚ በመጠቀም ዝምድናውም ምኑም ሳይታይ የልጁን ጥርስ በበቀል ለመመለስ በመሮ ነቅለው ማግስቱን ክስ ጀምረው ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ሌላኛው ፍትጊያ ስለነበረ እስክንድር ከዛ ተቀምጦ መኖር ሳይችል ወደ በረራ ተመልሶ ሄዶ ነበር፡፡

እኔ ከዛው እየተመላለስኩ ከማጨዱ፤ ከማጋዙ እና ከውቂያው አባባ ጥበቡን አግዛቸው ጀመርኩ፡፡ እነሱም ምርቱን ሲያስገቡ ግርዱን አዝርቼ ሽጬ በአንድ ብር አራት ብስከት ገዝቼ በተቀረው ገንዘብ ቡና እና ስኳር እየገዛሁ እገባለሁ፡፡ በዚህ የአገልግሎት ምልልስ ላይ እያለሁ ት/ት ጠንከር ብሎብኝ ስለነበር ራሴንም በደንቡ እያወኩ ስለመጣሁ ከቤተሰብ ጋር ሆኜ ለመማር ወስኜ ሲ.መ ተመለስኩኩ፡፡ ውጤት እና መረዳት ቢኖረኝም የእንግሊዘኛ እና መምህራኖቹ ነገር ግን አነጋጋሪ እና አስጊ ጉዳይ ነበር፡፡ ከኤ-ዜድ ያሉ ፊዳላቶችን መቁጠር እንኳን ይከብድ ነበር፡፡

ዓመታት ወራቶች እየከነፉ አምስተኛ ክፍልን በእውቀት እና በመረዳት ቀስቃሽ የሆኑትን ት/ቶች አጠናቅቂያለሁ፡፡ ዘንቦ የማያባራው የቤተሰብ ችግር ግን ልላ ልጅ ተደግሞ ተደራራቢ ቤት ተሰርቶም ሊያቆም አልቻለም ነበር፡፡ ይባስ በማሕላቸው አሉባልታ ገብቶ የህሌና አስተሳሰብ ሁሉ ኤርሚያስን መግደል እንደሆነ ንንግሯ ያሳብቃል፡፡ ኤርሚያስ ግን አምስት ልጆችን በተስፋ ይጠብቅ ስለነበር ይሄንን ውጦ በችግር ወቅት የኛን ጎሮሮ ለመዝጋት ከማያውቀው ሀገር ተቀጥሮ አጨዳ አጭዶ ገንዘብ ይልካል፡፡ ከዛ መልስ ግን የሚነግረን ያሳለፋቸው ቀናቶች አንዳንዱ ለሞት ዳርገውት ፈጣሪ እንዳተረፈው ሌላው አዝኖ ደግሞ ወዶት እንዳከበረው ይግረናል፡፡ ይህን የሚያደርገው የራሱ አዝመራ ደርሶ ለቤት እስከሚውል ድረስ ነው፡፡

አሉባልታው ብዙ ጊዜ የሚጎርፈው ከኤርሚያስ ቤተሰብ ነው፡፡ ማለትም ለህይወቱ አቃቂር ከሚያወጡ የቤተሰብ አባላት፤ በዛ ላይ አብዛኛው የዮቶር ቤተሰቦች እኛን ከነመፈጠራችን አይወዱንም ነበር፡፡ ሲበዛም ለራሳቸው እንጂ ለሰው ዴንታ የሌላቸው ትንሽ ደከምከም ያለ አስተሳሰብ ብጤ ያላቸው ናቸው፡፡ ታድያ ኤርሚያስ ዘር በፍሬው ያምራል እና ለሥራ እንዲሁም ለሌላ ነገር ከዛው ይዞን ሲሄድ የሚወራውም ሆነ የሚነገረው ነገር በሁለቱ መሐል መልካም ህይወት እንዳይኖር መበታተን ነው፡፡

ከዚህ በፊት ከህሌና በሰማሁት ታሪክ ከሆነ ኤርሚያስን ራሱ ባካበተው ንብረት ምክንያት ሲገሉት እንደነበረና አባቱ ዮቶር እስከነ ንብረቱ እንዳስመለጠው ለመረዳት ሞክሪያለሁ፡፡ በ'ርግጥም አሁን ላይ የሚያሳዩት ባህሪም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ዛሬ ኤርሚያስ የሶስት ቤት እና የንብረት እንዲሁም የመሬት ባለይዞታ ባላባት ሆኗል፡፡ ለዛም በሚመስል እሱን ሲቀርቡት በሚበላ ምግብ ላይ እንኳን የእኛን እጆች ለመያዝ ይቃጣቸዋል፡፡ ብቻ አንዳንዶቹ ከሚባለው በላይ ከባድ እና መጥፎዎች ነበሩ፡፡

በዚሁ ቤተሰብ ወሬ እና በአሉባልታ የተበረዘው ኑሮ በ'ርግጥ አሁን ላይ ምስቅልቅሉ ወጥቷል፡፡ በመቀናናት የተጠመደው ግንኙነታቸውም ያንን ገሎ ቀባሪ ግሮሰሪ እንኳን አፈራርሶ ምስቅልቅሉን አውጥቶታል፡፡ ታድያ በዚህ መሐል ህሌና አሉባልታ በደስኳሪው ውስጧን አብግኖት፡፡ ከሌላ ሰው ጋር ግንኙነት መጀመሯ ታወቀ፡፡ ኤርሚያስ ይህንን ወሬ ከሌላ ሰው ሊሰማው ቢችልም እውነቱን ግን እስኪሰማው ምንም ማለት አልቻለም ነበር፡፡

ታድያ አዝመራው ሰፍቶ ሰው ጉድ ጉድ በሚልበት ወቅት ኤርሚያስ ለመሰንበቻ የሚሆን የውቂት እህል ይዞ ሲመጣ እኔ ዐይኔን አሞኝ ከት/ቤት ቤት እንዳለው ሰው መጥቼ ከበር ስደርስ ቤቱ ከውስጥ ተቀርቅሮ አገኘሁት፡፡ ባንኳኳ ባንኳኳ ሊከፈት ስላልቻለ የአባቴ ኤርሚያስን ድምፅ ከአራት መቶ ሜትር ላይ ስሰማ በሩን ትቼ ስሮጥ ሄድኩኝ፡፡ ዐይኔን አሞኝ ሲያይ ለምን እንዳልተኛሁ ሲጠይቀይ ከት/ቤት መጥቼ ከቤት ልገባ ስል በሩ ከውስጥ ተቀርቅሮ እንደነበር ነገርኩት፡፡

ከግቢው ስንገባ በሩ ክፍት ሆኖ አገኘነው፡፡ በአህያዋ ላይ የጫነውን ነዶ ከዛው አውርዶ ወደ ውስጥ ሲዘልቅ ህሌና የመለኪያ አረቄ እየቀዳች ከሌላ ሰው ጋር ተቀምጣ አገኛት፡፡ ሁለቱም አላማቸው ይሄ ስለነበር ነገሩ ከተነቃ እና ኤርሚያስ የሚያመዝን ከሆነ በመጥረቢያ ሊመቱት ተዘጋጅተዋል፡፡ በዛ እንኳን ያልቆረቆረው ቅጥረኛ ገዳይ ካለበት ምንም እንዳላደረገ ተቀምጧል፡፡ ህሌና ባጋጣሚ ከቤት ስትወጣ ኤርሚያስ ስላገኛት ከእጇ ይዛው የነበረውን ማሰሮ ለሁለት ከፈለው፡፡ ሊገድል የተቀጠረው ሰው በዚህ ጊዜ ለዱላ ሲጋበዝ ህሌና ከፊት ሆና ኤርሚያስን ከመሐል አደረጉት፡፡

የአሉባልተኞች ወሬ በእልህ እና ንዴት ተጠምቆ ህልሟም አላማዋም ከጅምር እሳካሁን ይህ ነበር እና ከመሐላቸው በፍላጎቷ መሆኑን ሲያረጋግጥ ለሚኖርላቸው ልጆቹም ጭምር ሲል ጥሏቸው

*ፈንጠር ሲል ነገሩ ያልተመቸው ፈሬ ገዳይ ጥሎ ሄደ። በዚህ ጊዜ በበሽታ የሞቀሞቀ ዐይኔን ይገፔ ስጮህ ህሌና እናቴ ከተኛሁበት ድንግት አጠገቤ ቆማ ከትራሴ የተኛሁበትን ድንክ በቡጢ እየነረተች ‹‹እስኪ ያ'ባህ እሱ ያድንህ!!.....እስኪያ'ባህ.......›› እያለች ትዝትብኝ ጀመር።*

*ዐይኔ በጣም እየለበለበኝ መተናፈሻ እንኳን አሳጥቶኛል በዛ ላይ እሷ እንደዛ እያለች ስትደረብ ሞት አንጋሽ ሆነችብኝ። ኤርሚያስ ግን ይሄንን አጠገቤ ስላልነበረ ሊከላከልልኝ ሳይችል አመሻሽ ላይ መድሃኒት አምጥቶልኝ በስንት የእንፍዳ ስቃይ ዐይኔ ድኖ ት/ቴን ቀጠልኩ። ከት/ት ውጤቴ የተነሳ በጣም የምትወደኝ የአማርኛ መምህት አስቴር ልትጠይቀኝ ብትሻም ከክፍል ስላጣችኝ ምንም ማድረግ ሳትችል ቀን እየቀጠረች ሳለ ነበር የሄድኩት።*

*አንዳንዴ መንጋወን ከት/ቤት ግቢ አየለቀኩ ሳጠና እና ሲለኝም ተማሪዎች በሰሯት ክራር ስጫወት ስለምታይ እንዲሁም አኗኗሬን ስለምታውቅ እንዳንድ ቀላል ሥራዎችን እያዘዘች ቤት ካፈራው በትብቆዬ አሲዛ ትሸኘኛለች። የቤተሰብ ህይወት ከህሌና ጥላቻም በላይ አልፎ ከቤት ቤት ለዘር የተቀመጠ በችግር ጊዜ የተጠራቀመ ገብስ እንዲሁም ዱቄት ሳይቀር ይዛ ጠፋች። ከቤት እኔ፤ ጣይቱ እና ሁለቱ ታናናሾቼ ቁጭ ብለን ኤርሚያስ ከሥራ እስኪመጣ ጠበቅነው። እሱም የዛች ቀን ያለቀሳት እንባ መቼም አትረሳኝም። መንገድ ላይ ሲገሉት እንደነበረ እና እንደዛም ሆኖ እሷን ዳግም እንደሚፈልጋት እየተናገረ ያነባል። እኔ እና ጣይቱ ከፍ ብለን ስለነበር ረሃብንም ለምደነው ቻል ብናደርግም ሁለቱ ግን አለቀሱ። በዚህ ጊዜ ከየት እንዳመጣው ባላውቅም አንባሻ እና የምትበጠበጠዋን ጁስ ገዝቶ አመጣልን።*

*ማግስቱን ምንም ስላልነበረው የጭቃ ኮንትራት ይዞ ሲሰራ ህሌናን ታናናሾቻችን ሲያዩዋት እያለቀሱ ተከትለዋት ሄዱ። እውንም ተበድላ፤ ተቸግራም ሊሆን ይችል በሚል አስተሳሰብ ከአጠገቧ ደርሼ ‹‹እናቴ ነገ እኮ ሌላ ቀን ነው። እኛም እውነት ብሎ ፈጣሪ ከፈቀደ ያልፍልን ይሆናል። አውቃለሁ ባለመስማማታችሁ ቡዙ ክረምቶችን በአጥሚት እና በመንተርፌ (በሜዳ ጎመን) አሳልፈናል። ታድያ እኔ እኮ ዛሬ የስድስተኛ ክፍል ተማሪ ነኝ። እና ከዚህ በኂላ ቢቀረኝ እኮ ከጠነከርሽ አስር ዓመት ብቻ ነው።›› አልካት ቀሚሷን ይገፔ እጇን እየደባበስኩ ዐይኔ ከዐይኗ በፀፀት ተፋጦ።*

*እሷ በሀሳቡ ውስጧ ቢሸነፍም ከኤርሚያስ ላለመሆን የወሰነች በሚመስል መልኩ ክስ ጀምራ ከዳኞች ሌላኛው ምክር እና የልጆች ሁኔታ ታይቶ በማስተዛዘን እንዲታረቁ በሽምግልና ቀጠሮ ተይዞ እርቁ ሰምሮ ዳግም አንድ ላይ ተመለሱ። የኤርሚያስ ስቃይ ግን አላበቃም። አንዳንዴ አባይ ጠንቋዮች ‹‹ከሱ ብትለዩ ትልቅ ህይወት ይኖርሻል።›› እያሉ መንታ መንገድ ላይ ሆና ሌላውን ጎድታ ራሷንም እንድትትጥል ያደርጋሉ። የገዳይ መቀጣጠሩ አሁንም ቢሆን ህበረት ሆነ እንጂ ሊቆም አልቻለም። እንደ ነገሩ የምትሠራ የነዚህ ተስፋ ቢስ ገዳዮችም መምጫ ምንጩ ይቺው ጠላ እና አረቂ ስለነበረች እሷ እንድትቆም ተደረገች።*

*በዚህ ጊዜ ትንሽ እስትንፋስ ተገኝቶ ተስፋ ቢሶቹ እርኩሳኖች ቢቀሩም ጭቅጭቃቸው እና ችግራቸው ሊያባራ ስላልቻለ ማታ ማታ ከማውቀው ሻይ ቤት በህንድ እና ሌሎች የአሜሪካ ፊልሞች ውስጥ ራሴን አሰምጥና ጭቅጭቃቸውንም ረሳቼ እመለሳለሁ። በዚህ ጊዜ እነሱም ተኝተው ከቤት ስለምደርስ ኤርሚያስ ተቆጣጥቶ የተዘጋጀ ምግብ ካለ ወስጄ እንደበላ ቦታውን ይጠቁመኛል። በልቼ እስክጨርስ ግን እንቅልፍ አይዘውም።*

*እኔም ከበላሁ በኂላ እንቅልፍ እስኪጥለኝ አነባብብ እና ተነስቼ እተኛለሁ። የማይለመድ የለም እና ያንን ሁሉ እንክን እስከነ ችግሩ ለምጄው ት/ቴ ላይ አትኩሮት አድርጌ ከዛ ሻይ ቤት እየተመላለሱ*

ራሴን በማደስ ተክኜ መልካም ውጤት ይገፔ ወደ ሰባተኛ ክፍል አለፍኩ፡፡ በዚህ ጊዜ ከሌሎቹ ጉልበትም አውጥቼ ስለነበር፡፡ አባቴ ከርቀት ቦታ ሄዶ አጭዶ የተሰጠውን ነዶ ወቅተን አምርተን ይዘን እንመለሳለን፡፡ ልፋቱ ከባድ ነው፡፡ እሱ ላጨደው እሱ ለወቃው አግዞ መጫን እንኳን ይከብዳል፡፡ በዛ ላይ ከቤት የሚቋጠር አንዳች ነገር ስለማይኖር ከዛው አበሳስለው እስኪሰጡን መጠበቅ ብቻ እጅግ ከባድ ነበር፡፡

ያም ሆኖ ከቤት ሲደርስ አሰራሩ ተራ የግብር ይውጣ ስለሚሆን ሌላ ቧገታን ከመጨመር ውጪ ምንም ፋይዳ አልነበረውም፡፡ እኔም አንዳንዴ ሻይ ቤት ውሃ በመቅዳት እና እቃ በማጣጠብ ሥራ እየሠራሁ አንዳንዴ ለቤት ሳይሆን ደግሞ ለሆዬ እያደረኩ ራሴን ገለል ለማድረግ ሞከርኩ፡፡ ሰባተኛ ክፍል ብዙኂኑ መምህራን ት/ት ሲያስተምሩ የሚያስተምሩት በመሽምደድ እንጂ በእውቀት ላይ ተመስርተው በእምቅ የተፈጥሮ እውቀታቸው አይደለም፡፡ ለእያንዳንዷ የትርጉም ፍቺ ከተረዱት አንግል አንፃር እንጂ በአውነተኛ ፍቺው ላይ መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡

እኔ እና መሰሎቼም ብንሆን በዚሁ የነሱ መር ተከትለን ከመማር ውጪ አጋዢ ሊሆንልን የሚችል ተጨማሪ መፀሐፍ ግን ማግኘት አልተቻለንም ነበር፡፡ ለአላማው የታተረ ወላጅ ለልጁ የሚያስፈልገውን መፅሐፍ ሲገዛ እኛ ግን አዳማጭ እና ሽምዳጅ ከመሆን የዘለለ ያተረፍነው ነገር አልነበረም፡፡ ህይወት በዚህ ቀጥላ ኤርሚያስ እና ህሴና ራሳቸውን ፍለጋ የከፋፈሉትን ንብረት ሲያገባድዱ ካገኟት ነገር ወደ ጎነ ማለት ከጀመሩ በርካታ ዓመታት አስቆጥረዋል፡፡ እኛ በዚህ ቤተሰብ ውስጥ የፊልም ተመልካች እንጂ አክተር ልንሆን ልምዱም አቅሙም አልነበረንም፡፡ ዕድሉ ኖሮን እናድርገው ብንልም ላይሆን ይሆን እና ከምንም ሳትሆን ወድቀህ ከመሰባባር ውጪ ምንም አማራጭ አይኖርም፡፡

ከሞላ ጎደል ያልዘነጋሁት የትምህርት ህይወትም አንድ ሁለት እያለ ስድስት ዓመታትን አስቆጥሮ ሌላኛውን ዓመት አሐዱ ብለን ጀምረንዋል፡፡ ብቻ የመጣሁበት መንገድ በጠንካራ መምህራኖች ትጋት ትኩረት ተገንብቶ በፅኑ እውቀት ላይ የቆመ አለመሆኑ ለእነሱ የእንጀራ ህይወት ሆኖ ቢያለፋቸውም ለህሌናቸው ግን ማስመሰል አግዞ አልረዳቸውም፡፡ ስድብ እና ልምጭ የተመረቁበት አንዱ የትምህርት ዓይነታቸው ነው የሚመስለው፡፡

ስለ ተማሪ ነገሮችን በመረዳት እና በመገንዘብ መማሩ ለነሱ የቅንጣት ቁም-ነገር የለውም፡፡ ከመቶ ዘጠና ዘጠኝ በማምጣት ተማሪ እገሌ እገሊት አንደኛ ሁለተኛ ወጣች፤ ወጣ እያሉ ያልተገነባ ጭንቅላትን በነጥብ ክምር ይዘው ለማለፍ ሲሞክሩ በ'ርግጥ እንደ ሰው ለሚያስብ ሰው የራስ ምታት በሽታ ብቻ ነው፡፡

በመረዳት ውስጥ የተገነባ በፅናት የሚቆም የአለት ላይ እውቀት ያለው ሲሆን፤ በሥነ-ምግባር የታነፀ ሲሆን፤ ችግር ከመፍጠር ይልቅ ችግር የሚፈታ ሲሆን በመማር ውስጥ የሚገኝን መረዳት የራሱ ንጉስ ማድረግ ይቻለዋል ማለት ነው፡፡ ከአስር አስር አሳስሮት ካለበት ሆኖ በራሱ መሞት እንዲመፃደቅ አደረገው እንጂ አፍሮ ዝቅ ብሎ ይቅርታ እንዲጠይቅ እና ሰውነትን እንዲረዳ አላደረገውም፡፡

በተለይ የቋንቋ መምህራን ትምህርቱን ሲወስዱት በመስኮት ጥግ በሽውታ ብቻ የተማሩት ነው የሚመስለው፡፡ የአንድን ተማሪ የእውቀት ልክ መዝኖ ድክመቱን ከጥንካሬው ለመለየት እና እገዛ ለማድረግ እንኳን እውቀቱ ያስፈልጋል፡፡ ይህን ግን ከኛ ዘመን ትውልድ ‹‹አዋቂ ነኝ!›› ከሚል ዜጋ ውስጥ አንድ እንኳን እውቀት ለመረዳት ቁም ነገር አልተገኘም፡፡ ሁሉም በአርባ ደቂቃ ውስጥ "የከበረ

ቀን የሰጠው ቅል የድንጋይ መስበሪያዎች ናቸው።" ሁሉም በያለበት አእምሮው ደቋል። የጠነከረው ከተለያዩ አጋዥ መፀሐፊ በጠንካራ ቤተሰቦቹ ብርታት ሲደበቅ ሌላው ባልደረሰበት የፍቅር ህይወት ውስጥ ገብቶ ትንሽ ትልቁ የሚዳክርበት ጊዜ ሆነ።

በአንድ ወቅት እንደለመደው በማያቁ ተማሪዎች ላይ ማፏጨት የለመደ መምህር የተሳሳተ አረዳድ ለተማሪው ሲበትን ከውስጥ በኩል እውቀት በተፈጥሮ የተካነ ከውትድርናው ዓለም በእውቀት በሁሉም ነገር ተገንብቶ የተመለሰ ምጡቅ ወታደር ሊያስቆመው በትህትና ያናግረው ጀመረ። ነገር ግን መበለጡን አምርሮ የጠላው ጀማሪ መምህር ተማሪ እንደሆነ እና ቁጭ ብሎ ከመማር የዘለለ ምንም ነገር ማድረግ እና ማለት እንደማይችል ለማስጠንቀቅ ሞከረ በዚህ የቀጠለው እሰጣ ገባ አቅጣጫው ከፍ ወዳለ ደረጃ ላይ ይደርስ እና ወደ ፀብ ይቀየራል።

መቼስ በጉልበት ወታደርን አንድ ተራ የምንም አካላዊ እንቅስቃሴ የሌለው ሰው ገጥሞ ያሸንፋል ማለት የህልም ምኞት ሆኖ ወታደሩ በስሜት ተነሳስቶ የልቡ እስኪደርስ በሚገባው ቋንቋ አናግሮት በፖሊስ ተይዞ ያለ ጥፋቱ ሁለት ዓመት ጥቃት በመፈፀሙ ብቻ ከትምህርቱ ታገደ። ብቻ ስንማር የነበረው ከእንደዚህ ዓይነቱ ትምህርት ቤት ነው። ጥቁር ሰሌዳ እስኪጨንቀው ጠመኔዎች በላው ላይ ይረግዳሉ። ሰላሳ ደቂቃ ፅሁፍ ሲበዛ አስር ደቂቃ ሲያንስ አምስት ደቂቃ የሲበሉ ላኩት መልዕክተኛ ወሬ እንጂ አዲስን ነገር አዲሱ ትውልድ የሚረዳበት የመማር ማስተማር ሂደት አልነበረውም።

እንደ እርኩስ መንፈስ ጣኦት አምላኪዎች የወጉ እንዳይቀር ያለምንም መረዳት እና ማወቅ የቤት ሥራ እና የማስታወሻ ፅህፈት እንደ ግብረኛ ያሸክፉናል። የሚገርመው ብዙዎቹ ለማርክ ሲሉ ሌላውን ያፅፉታል። ከዛም የባለ ሳምንት እቁብተኛ ይመስል አስር፤ ዘጠኝ፤ አስር፤ ዘጠኝ እንዳሻ ሥራ ለማቅለል ይሞላል። እቁብተኛ እንኳን ተመሳሳይ የገንዘብ መጠን ቢያስመዘግብም ሰርቶ ያመጣው ነው። የነዚ ብቻ በትዝብት አይቶ ላስታወሰው ምን ያሕል የትውልድ ክህደት ትውልድ እንደሠራ ሌላ ምስክር አያስፈልገውም።

ሰባተኛ ክፍል ነገሮች ሁሉ ከላይ የተዘረዘሩት እንዳሉ ሆነው የቋንቋው ተቀይሮ መምጣት የፊደሉን ቅደም ተከተል በቅጡ ማንበብ ለማይችል ተማሪ ሳይንሳዊ የሆኑ ነገሮችን በትርጉሙ ውስጥ ማስተማር ማለት ምን ያህል አሰልቺ እንደሆነ መገመት የሚከብድ አይደለም። በዚህ ጊዜ ነበር የት/ት አለሙ አክትሞለት የመጀመሪያው የረሃብ ደውል ረሃቡን ከሆድ ከፍ አድርጎ ልብ ላይ መርፌዎቹን ቸክችኮ የተደወለው። በአስራ ሶስት ዓመቴ የማላውቀው የሰውነት አካል ክፍሎች አንድ ሰው ባዩ ቁጥር ይርዱብኝ ጀመር። ከክፍሉ መሐል ዐይኔ ሲያነብ ውሎ ተምሮ የሚገባው ከልብ ተሰንቅሮ አልወጣ ያለውን ሰው ነው። አይነገር ነገር ሰውነት ኮስሶ በኖሮ አቧራ ተኮሳምኗል። ብቻ ሁሌ ልብ በደረት ሾልካ እስክትወጣ ደም የነበረው እርጨት እሳት በሰውነት ውስጥ እየተፋ አሽቆጥቁጦ ያዝለፈልፋል።

ለሚኒስትሪ ፈተና ለማጠናከሪያ በሚል ሰበብ እሁድን ጨምረን ስንማር ስለነበር ከክላስ ማገባደጃ በኂላ ከሁለት ዓመት ቅጣት በኂላ የተመለሰው ወታደር አንዳንድ መሳጭ ታሪኮችን ይጀምር እና ለቀጣዩ እንድንመጣ በእንጥልጥል ይሸኘናል። ብዙኂኑ ተማሪ የዚህ ጎልማሳ ሀሳብ ለመቋጨት የሚመጣ አለ። በክላስ ጊዜ ድባቴ ጥሎበት ሲያዛጋ የነበረው ሁሉ አፉን ከፍቶ ያዳምጠዋል። ብዙ ጊዜ የሚያወራው ስለችግር እና የመውጫው መጨረሻ ስለሆነው ኃያሉ ፍቅር ነው።

በውስጡ ካሉ ገፀ-ህሪያት ሁሉ ከመነሻው እስከ መጨረሻው ጎልቶ የሚታየው መስዕዋት አስከፋዩ ውበቱ ታይቶ የማይጠገበው ፍቅር ነው። እኔም ከዚህ ታሪካዊ ትረካዎቹ በኂላ ነበር እንደ ክብሪት ቀድሞውን ሲፍር የነበረው ፍቅር እሳቱን ለኩሶ ማንነቴን ማንነቱ አድርጎ በላዬ ላየ የነገሰው።

• * *

# *ምዕራፍ ሶስት*

## *ዕድሜ ያልበገረው የፍቅር ነበልባል!!*

ነገሩ ህይወት ነው እና ለመኖር ዓለም የምትሰጥህን የእውነት ክስተቶች ተቀብለህ ማስተናገድ የግድ ሆኖ የኑሮ ማንነቱ <<በደንባራ ፈረስ ቃጭል ተጨምሮ>> ቢሆነም አንዳዴ ምንም ሁነት ላትቀበል የሚሆን ምንም ዓይነት ምክንያትም ሆነ ማሳበሪያ መንገድ የለህም። በተለይ ፍቅርን የመሰሉ አጋጣሚዎች በራሳቸው አቅም እና ጉልበት በአዕምሮህ ላይ ምህዋር ሰርተው ላፍታ የሚሆን እንኳን ’ረፍት እንዳይኖርህ ያደርጋሉ።

እኔም ከኒካውላ ዮሳፍጥ የዐይን ፍቅር ከያዘኝ ሰንበት ብሎ መቆዘሜ ከዕለት ሳምንታትን፤ ከሳምንታት ወራትን እያስቆጠረ በእውን እንደ ህልም ያቃዥ ከጀመረ ይኸው መንፈቅ ዓመት እጅ ነስቶ መስክሯል። በቃ የማይታወቅ አይቼው እና አስተናግጄው የማላቀው ሰው በውስጤ ደስታን፤ ጭንቀትን፤ ፍርሃትን እና የሚወደድ ማንነትን ፈጥሮ ዐይን ባማተረ ቁጥር ማዕበሉን እየቀሰቀሰ ፀጥ ያለውን ወጀብ ከግራ ቀኝ እያማታ ያናውጠዋል።

ኒካውላ ዮሳፍጥ ማለት ረዘም ብላ የቀይ ዳማ ስትሆን ቀጠን ያለች የማለዳ ፀሐይ ዓይነት ፍካት ከፈጣሪዋ የተቸራት መልከ-መልካም ቆንጆ አትቀመስ ሆኖ እንጂ እንደ ወተት እና ማር የምትጣፍጥ የሆነች የህይወቱ ወጥ ማጣፈጫ ቅመምዬ ነገር ነች። እንደ እውነቱ ከሆነ ኒካውላ በዚህ ብቻ የተካነች አይደለችም። በእርጋታ ተጠምቆ በአስተውሎት እንደ ምንጭ ውሃ የሚፈልቀው እሸት ያበቀለበት ንግግሯ ተዳምሮ ሲሰራት ውሎ ሲሰራት ያደረ የፍቅር አበባ ፅጌ ረዳ ነች።

ከኒካውላ የምንተዋወቀው ከዛ ከመንጋው ሥፍራ ባውላለው ሜዳ ተራ እየተሰጣጠን መንጋ ስንጠብቅ ብሎም “ብይ" እየተነጣጠቅን ተሯሩጠን በድካም ስንኮራረፍ ነው። ታድያ በዚህ ጊዜ ቀኝ እጇን በአገጯ ላይ አሳርፋ ስርጉድ ጉንጯ ወተት ከመሰሉ ዐይኖቿ ጋር በንዴት ሲርገበገቡ ውስጥን አስረብሾ ከልብ ደም እያጠለቀ ከውስጥ በሀዘን ፍካት እንባ ያራጫል። አንዳንዴ ቁጣዋ ገንፍሎ ከተቀመጠችበት ተነስታ ከኔ ለመራቅ መንገድ ስትጀምር ልቤ ተፍነካክቶ ቀድሜ ከፊቷ ስደርስ ዐይኖቿ እንባ ያቀሩ እና ሆድ አስብሶ ከእጇ ደርሰው እጆቼ የወሰዱትን እቃ እስኪመልሱ በላብ ተጠምቀው መንቀጥቀጥ ይጀምራሉ።

ኒካውሊ በዕድሜ ትበልጠኛለች። እሷ ማራኪ እንጂ ለመማረክ ጊዜ የማትሰጥ ማርሽ ቀያሪ ብልህ ናት። እኔ ከት/ቤት አዘውትሬ ያማልቀር ቢሆንም አሁን ላይ ቀኑን ሙሉ እሷን እያጠኑ ከመመለስ ውጪ ሌላ ሥራ አልነበረኝም። ውሎ አድሮ በዐይን ብቻ አልዘልቅ ያለው ፍቅር እያደር በሱ ግኖ ልብን በጦር እየሰበቀ ውስጤን እንደ ጎመራ እሳት እያፈነዳ ፍቅርን በውስጤ ያቀጣጥለው ጀመረ።

ይባስ የነደደው ቀዝቅዞ እንዳይዳፈን አንድ ቀን ከገጠር ለሥራ ተልዕኮ ስንሄድ የልጅነት ህይወቷን በሀዘን እያዋዛች አጫወተችኝ:: እኔም ነገሩን ሳስጀምረው በሰው አሉ ባልታ ወሬ ስለነበር እሷ ግን እውነት እንዳልሆነ አስረድታ እንዲህ ስትል ቀጠለች «እኔ እናት የለኝም::

በአካልም ስላላየኋት ፍፁም አላውቃትም:: ያደኩት የእናቴ እናት ጋር (አያቴ) ጋ ነው:: አያቴን እንደ እናቴ ስለማያት ከዚህ እየመጣሁ ካላየኋት እንብዛም ደስተኛ እና ጤነኛ ሆኜ አልውልም:: ምክንያቱም እናቴ እኔን ስትወልድ በወሊድ ችግር ስትሞት ትንሽ የዐይን ችግር ስለነበረብኝ በማሪያም ተስላ ፅዋዋን እየጠጣች ያዳነችኝ እሷ ናት:: አክስቴ ጋር ከእህቴ ከመምጣቴ በፊትም ቢሆን ያደኩት እሷ ጋር ነው:: ግን አደራ ላንተ እንደነገርኩህ ለማንም እንዳትናገር::» ብላ አስጠነቀቀችኝ::

እኔም ሚስጥሯን ሚስጥሬ አድርጌ ብቀጥልም መቀራረብ ጭራሽ ዐይን-ዓፋር አድርጎኝ ፍቅሯ ህመሜ ሆኖ በውስጤ ተከድኖ መተንፈሻዬን እስትንፋስ ያሳጥረኝ ከያዘ ሰንበትበት ብሏል:: እሷም ከነገርኳት ችግር አንፃር ከቤተሰብ ለማቃለል ሌላ ሀሳብ ይዛ ከቤት ብትመጣ ከህሊና ጋር ጓደኛሞች ሆነው በልጅነቷ ምክር ብትለግሳት ኤርሚያስን ከነዘርማንዘሩ እየጠራች ማንቋሸሹን በሚገባ ተካነችበት:: ህሊና እናቴ ብትሆንም አንዳንዴ ከምታደርገው ነገር አንፃር ጤነኝነቷ አስፈርቶ እያስጨነቀ ያጠራጥረኛል:: ነገር ግን ህይወትን በመልካሙ መንገድ እንድትኖር ገንዘብ በእቁብ መልክ እንድትጥል ካቋቋመችው የእቁብ ድርጅት ብታስገባትም ሲወጣ አንዳንድ ንብረቶችን እያሸሸች ከመደበቅ የዘለለ ምንም ልትፈይድ ሳትችል ኑሮ በህይወት ላይ የሚቀጣጠል ጋዝ ሆኖ ባለበት ቀጠለ::

ኒካውላን ከህሊና ማገናኘቴ ትልቅ ጥፋት መሆኑ የገባኝ ኤርሚያስን ይበልጥ እያሰቃዩ ለመግዛት ባጠራቀመችው የእቁብ ብር  እየተመካች በመጠኑም ቢሆን የያዘችውን ቤት ለመደርመስ በምትጥርበት ጊዜ ነው:: ይባስ ብሎ እኛው እንዳንናገር የሱን በደል ከምራ እንድንጠላው ራሷን እያሶደደች እኛውኑ የእቁቡ ብር ክፍያ አመላላሽ አድርጋን አረፈችው::

እኔ ግን በኒካውላ ፍቅር ተነድፌ ስለነበር ከቤት ስትመጣ ዐይን ዐይኗን እያየሁ በሰመመን ከመናኘት ውጪ ምንም መፍትሄ አልነበረኝም ነበር:: በተለይ አሁን ላይ በንግግርም ከበፊቱ ቀልጠፍ ብላለች:: በዛ ላይ ከገጠር ከሰል እያመጣች በፌስታል ቆነጣጥራ በየሱቁ እየሸጠች ስለነበር ምርጥ የቢዝነስ ሰው ሆና የምትለብሳቸው ልብሶች በዛ ውበት ላይ ተጨምሮ በዕምድር ላይ ሰዓሊ ሊስላት የማይችለው ቆንጆዬ ንግስት መስላለች::

በዚህ መሐል የአጎቴ ልጅ ከኛው ጋር ትኖር ስለነበረ ተመሳሳይ ክፍል አንድ አርቦሽ አድርጓቸው ከኛ ሰፈር መጥፋት ተሳናት:: ሁለቱም ሲያሻቸው እኔ እና አላዛር እንዲሁም ጓደኞቻችን ከሚጫወቱበት ስፍራ መጥተው ከእግሩም ከመረቡም ኳስ ይጫወታሉ:: ከኒካውሊን ገጥሞኝ አብሬ ልጫወት እጀምር እና ካጎጠጎጡ ትንንሽዬ ጡቶቿ ዐይኖቼ ፈዘው እጆቼ ዝለው ጨዋታው በሷ አሸናፊነት ይጠናቀቅ እና እኔ እወጣለሁ::

ከዛው ስለምትውል መሰለኝ ኒካውሌን በየቀኑ ካላየኋት ምንም ነገር አስጠልቶኝ እያነጫነጨ ራሴን እና ጆሮዬን ያመኛል:: እጅግ ብሶ ሳያስጨንቀኝ ቴፕ ለብቻዬ እወስድ እና ከፍቼ በተዘጋ ቤት ውስጥ እያለቀስኩ የንሰሀ መዝሙር ከፍቼ እያዳመጥኩ ፈጣሪ ከዐይኔ እንዳይለያት በምችለው አቅሜ እፀልያለሁ:: «ፍቅር ካንቺ ይዞኛል!» አልላት ነገር አጠገቧ ስደርስ ፍራቻው ሰውነቴን እንደ ደረቀ እንጨት አስግጎ ይገትረው እና ጉሮሮዬን አንቆ እየያዘ ልቤን በፈንጂ እንደተመታ ቋጥኝ ያፈነዳው እና ደረቴን እንደተበታተነው ድንጋይ ቀጥቅጦ አንደበቴን እንዳይናገር ለጉሞ ይዘጋዋል::

## እኛ!! የጨንቅ ዘመናቶች

በዝምታ የቀጠለው የፍቅር ነበልባል አንደኛ ዓመቱን ጨርሶ ሁለተኛ ዓመቱን ይዟል። ት/ትም ቢሆን የተሻለ ነገር ቢኖረኝም ደብተር ይዞ ከመመላለስ ውጪ የተለየ እና ቀስሜው የምመጣው እውቀት አልነበረኝም። ሁለታችን ስንገናኝ ስለ ህይወት እና ራስን ሆኖ ስለመገኘት በደንብ እናወራለን። በተለይ በዚህኛው ዓመት ላይ ራሴን ከሚገባው በላይ ስለጣልኩ ችግሬን ብትጠይቀኝ ሌላ እያወራሁ ለመሸፋፈን ከመሞከር ውጪ ልነግራት የምችልበትን ድፍረት አጥቼ ዝም እላለሁ።

አያቷ ጋር ብዙ ጊዜ ስለምትመላለስ ሲታመሙ በጣም ትጨነቃለች። ከዛም የተነሳ ከነሱ ጋር አድራ ወይ ውላ ልትሄድ ስትል ስለማገኛት የመንጋ መኖ ጭነን ጨዋታችን ደርቶ መንገድ እንጀምራለን። ጭነቱ ሲያጋድል በሥራው የተካነች ስለነበር ወደ ሌላኛው ጎን ተጭና ታስተካክለዋለች። እኔም በሷነት ህይወት ውስጥ ራሴን ከትቼ ስለነበር ከሻይ ቤት ሰርቼ ባጠረቃቀምኳት ብር ስኳር እና ቡና በመግዛት አያቷን እጠይቃቸው ነበር።

ውሏችንን ያዩ አንዳንድ በሰፈር ያሉ ባልተኛ ልጆች «አፈቀርካት አሉ» እያሉ በሳቅ ሲደሽቁ ቅስም ይሰባብራሉ። ግን እኔ ለሱም ዴንታ ስላልነበረኝ «ምስማር ሲመቱት ይጠነክራል።» እንደሚባለው ሆኖ 'ርግጡን ነግሬያቸው አስደምሞ አፍ ከማስያዝ በዘለለ ጉንተላቸው ጨንቆኝ ከቁብ አልቆጥረውም። እውነት የሆነውንም ቢነግሩኝ ፍቅር ነው እና በኒካውሌ ላይ በዐይኔ ካላየሁ አላምናቸውም።

ታድያ በዚህ የሰመመን ፍቅር ታላቁ ሚኒስትሪ ደርሶ «እረ መላ በሉኝ ዘመድ ወዳጆቼ..» የሚለውን ዘፈን ከማዳመጥ የዘለለ ምንም ፍንጭ ያለው መላ ጠፍቶኝ ለሚኒስትሪ ፈተና ያለምንም ዝግጅት ተቀመጥኩ። መጪው ክረምት ነው። ሚኒስትሪ ደግሞ ጥሎ ወይም ደግሞ ተሸክሞ የሚያልፈው እንዴት እና ማንን እንደሆነ አይታወቅም እና ሁሌም ማስታወሻ እንዲሆነኝ ብዬ ከደብተሬ ልባድ ላይ ሁሌም የማይጠፋውን ፎቶዋን ከክፍል ያለፍቃዷ ወሰድኩባት፤ እሷም ያለኔ ማንም እንደማያደርገው ስለምታውቅ ደብተሬን ሰብስባ ይዛው ወደ ቤቷ ሄደች። በመጨረሻም ተማምነን ደብተሬን እንድትሰጠኝ ብጠይቃት ነገሩ ያለ ፎቶው የማይሆን ሆኖ ለኤርሚያስ ነገረችው።

ኤርሚያስም በአምልኮ ጉዳይ ጠንቃቃ እና ሁሉንም የሚያውቅ ስለነበር የተደበቀ የማላውቀውን የነሱነት ታሪክ ነግሮ ፎቶዋን መልሼ ደብተሬን እንዳመጣ በቁጣ አስጠነቀቀኝ። እኔም የተባልኩትን ባደርግም ምንም ቢነገረኝ በኒካውሌ ላይ የሚቆርጥ ልብ ግን አልነበረኝም እና ህመሜ ብሶ በጭለማ ላይ ሌላው ክረምት ላያገናኘን መሆኑ ሲገባኝ የዘራይድረስ ባለቤት ፅፎ ያስቀመጠውን አንድ ግጥም ልሰጣት ወስኜ ይዤ ሄጄ ሰጠኋት። አስፈሪው እና መጥፎው አንድ ቃል ብቻ ለመጀመሪያ ጊዜ ከአፏ ወጥቶ መቆራረጫ ሆነን።

## *እኛ!! የጭንቅ ዘመናቶች*

*ያልተመረመረው የግጥም ርዕስ ‹‹**ልብ-----**›› የሚል ሲሆን እኔ ከሀሳቡ አንፃር እንዲህ ለማስታወስ ሞክሪያለሁ፡፡*

***ኃያሉ ማንነት በፍቅር ታውሮ፤***

***አንደበት በስቃይ ሉጓም ታስሮ፤***

***ዐይኔ ካይኖችሽ በሰመመን ወስልቶ፤***

***ልቤ ባዳ ሆነ ከመላው ሰውነት ተጣልቶ፤***

***በወላፈኑ ውስጤ እያረረ ቀን በቀን ተወልዶ፤***

***በጎመራው እሸት እንቡጥ ካገዳው ተጋምዶ፤***

***ያረገዘው ግርግር በእሳት ግሞ፤***

***መች ይሆን ያንቺ ቀን ከእኔ አቅምሞ፤***

***በአንጎል ቅሉ ብጥብጥ አላምኖ፤***

***ላይዘለቅበት ነገር በፍቅር መንኖ፤***

***ልብ ላይገባ ከመቃብር ፈንቅሎ፤***

***እንዴት ሊዘለቅ ራሱን ቆርጦ ቀጥሎ፤***

***መውደድ በደም ስር ታልቦ፤***

***ስጋ በነፍስ አቅል ተገልቦ፤***

***ድንገት ልብ በልብ ተማርኮ፤***

***እስከመቼ ይሆን በፍቅር አስታኮ፤***

**አንጀት ከጅማት ገልብጦ፤**
**የአፍላ አጥንት አግጦ፤**
**አይድንበት ውበት አቆሳቆሶ፤**
**እስከመቼ ድረስ ከራስ ተፈራርሶ፤**

**በሀሳብ አናኝቶ ከቤት ደጅ ፈልቅቆ፤**
**ሌቱ በእንቅልፍ ላያስተኛ ሰብቆ፤**
**ቃል በምድር በሰማይ ተለጥፎ፤**
**ለማን ይሆን ፍቅሬ የሚቀረው ግፎ፤**

**ብሸሸው ላይተወኝ በምናብ አስሎ፤**
**በውሎ ትዝታ ጭንቅን ቆልሎ፤**
**ዛሬማ ካልጠፋሽ መንገዱ ሊሆንልሽ ድልበድል፤**

**ልቤማን ይኸው ያሰረውን ውል ላይፈታ ወዶሻል፤>>** የሚል ዓይነት ይዘት ያለው ሲሆን በ'ርግጥ ገጣሚው ልቤ ባዶ ሆነ፤ ልቤ መልስ አጣ፤ ልቤ ግራገባው እና ልቤ ድፍረትን አጣ፤ አፍቅሮሻል ለማለት የተጠቀመው እንጂ እሷ ጥሬ ቃሉን ብቻ ተርጉማ እንደተረዳችው ዓይነት ትርጉም ያዘለ ሀሳብ ያለው አልነበረም:: ውስጤ አዝኖ የወደዳትን ያህል ልቤ ባይቆርጥ አምርሮ ተቀየማት:: በ'ርግጥ ከዛ በኋላ ባገኘሁት አጋጣሚ ሁሉ የአፀፋ ምላሽ ልሰጥ ይቃጣኝ እና ነውርነቱ ኮርኩሮ አንደበቴን ያስረዋል:: በዚህ መሐል አብሮን የዘለቀው የሲፓራ እና ሙሴ ልጆች ባህሪ በዛ በክረምት ተወግዶ ሳለ የኒካውሊ አያት ማረፊቸውን በህሌና አማካኝነት ሰማሁ:: ስለሷ ደህንነት ለማጣራት ስሞክር እንደምታለቅስ እና በጣም አዝና እንደነበረች ተረዳሁ:: ስለተጣላን እና ያለሁበት ሁኔታ እግር አንስቶ የሚያራምድ ስላልነበረ አዝኜ ዝም ከማለት ውጪ ላመጣ የቻልኩት መፍትሄ አልነበረኝም::

በመጨረሻም ክረምቱ ተገባዶ ሚኒስትሪ ተለቀቀ:: አላዛር ቀድሞ አይቶ ማለፉን ሲያረጋግጥ እኔ ግን ከሱ በት/ትም በደረጃም ከ5ኛ ክፍል ጀምሮ በምንም የተሻልኩኝ ስለነበርኩኝ ያለምንም መጠራጠር አልፌያለሁ ብዬ በድምዳሜ ለቤተሰብ በልበ ሙሉነት ልናገር ብችልም ሳይዋጥላቸው ቀርቶ እንዳይ ግድ ሆኖ ማለፌ 'ርግጥ ቢሆንም ውጤቱ ግን የማለፊያ ብቻ ነበር:: የኒካውላንም ውጤት እግረ መንገዴን ስመለከት መውደቋን አረጋገጥኩ:: እኔም ከዚህ በኋላ እንደማላገኛት ስለተረዳሁ ተስፋዬ ተሚጦ የፍቅር ነበልባሉን ከስንት ስቃይ በኋላ ውሃ ቸልብሼ አቀዘቀዝኩት::

# ምዕራፍ አራት

## መቅኖቢሱ የህይወት ውቅያኖስ!!

በ’ርግጥ በፍቅር ዓለመ ውስጥ ድምዳሜ ያገኘ የመስለው የውስጥ ላይ እሳት ላይነድ ያያያዘውን ረመጥ እንዳሻው ሊያዘው ይቃጣዋል፡፡ አንድ አካሉ እነደተጣለ ቅሪት ከቀን ቀን ሰውነቴን እየመዘመዘ እስትንፋስ ቢያሳጣኝም የመጨረሻውን መለያያ እንዲሆነን የትምህርቱ ዓለም ሁለታችንንም አራንባ እና ቆቦ አድርጎን ዳግም ሳንገነኝ ቢመስል ከኒካውሌ ተለያየን፡፡

የመለያታችን ዋናው ምክንያት በአከባቢያችን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በአቅራቢያ ያለመገኘቱ ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ለዚህ የፍቅር ግንኙነት መቀጠል ሁለት አማራጮች ነብሩ፡፡ እነሱም አንደኛው የእሷ ከእኔ ጋር መግባባቱ የተጠናከረ መሆን መቻል ነበረበት፡፡ ሌላኛው እና ሁለተኛው ደግሞ በአስር ኪሎ ሜትር ላይ ከሚገኘው የአ/ጠ ት/ቤት መማር ነበረብኝ፡፡

ነገር ግን ይህ ሳይሆን ቀርቶ ከሁለቱም መካን ሆኖ ራቅ ከሚለው የጎልባ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከታናሽ ወንድሜ አላዛር ጋር ገባን፡፡ ከመኖርያችን ሃያ ኪሎ ሜትር ይርቃል፡፡ በየቀኑ እየተመላለሱም ሆነ እየሰነበቱም ለመቆየት አቅም ፍፁም ሆኖ አይፈቅድም፡፡ በዛ ላይ በጣም ትንንሽ ልጆችም እንደመሆናችን መጠን ብቻችንን ለመተው ቤተሰብ ስላልፈቀደ ከዛው ሆኖ እህቱን ከሚያስተምረው አጎታችን ጋር ናስቶሲን ቤት ተከራይቶልን ት/ቱን አቦል ጀባ ካልነው ብዛት ያላቸው ቀናቶችን አስቆጥረናል፡፡ ብቻ ፈጣሪ ሁሉንም ለበጎ ስለሚያደርገው እኔም የተሰጠኝን ሁሉ በፀጋ ተቀበዪ አጉል አጉል የሆነውን ት/ት ማስኬድ ከጀመርኩ ቀናቶች ነጉደው ወር ቆሞ ቀድሶላቸዋል፡፡

የራሴን ማንነት ከሰውነት ጎዳና አውጥቼው ብቸኝነትን በፀጋ ተቀበልኩት፡ ብቻ ወይ አያስፈራ ወይ አያስደስት ግራ ሲሉት ቀኝ፤ ቀኝ ሲሉት ግራ እያለ ወስዶ የሚመልስ መጥፎ በሽታ ውስጥ ክፉኛ ሰመጥኩኝ፡፡ በ’ርግጥ ከቤተሰብ በምኖርበት ወቅት ሁሌም ብቸኛ ስለሆንኩ ከየትኛውም ወንድም እህቴ እንዲሁም ከዘመድ አዝማዶች ጋር ለመነጋገርም ሆነ ለመጫወት ፍቃደኛ አልነበርኩም፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው ደግሞ ቤተሰብ ለኔ ከሚያደርገው እንክብካቤ እጥረት እና ክብር ንፉግነት ብሎም የፍቅር እጦት ነው፡፡

ብቻ አምኛቸው የኔ መስለውኝ አያውቁም፡፡ በነሱ የተነሳ ሰው ሁሉ እንደ እነሱ ስለሚመስለኝ ፈፅሞ ባልቀርባቸው ውስጤ ደስታውን አይችለውም፡፡ ሰው ለኔ ባዳ ወይም ሌላ ፍጡር ብቻ ነው መስሎ የሚታየኝ፡፡ ሁሉም ሰው አጫውቶ አቃልዶ ሊግባባኝ ይሞክራል ነገር ግን ለኔ እንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች ጊዜያቸውን በራሳቸው ላይ እየተደበሩ የሚያሳልፉ ከንቱ ፍጥረታቶች እንጂ ሰው መስለውኝ ግብረ-መልስ መልሼላቸውም ይሁን ሰጥቻቸው አላውቅም፡፡

የሆነው ሆኖ ሁሉም ካለቀ በኃላ እነሱ ሰልችቷቸው ዝም ሲሉ እኔም የተገላገልኳቸው ስለሚመስለኝ አምላኬን እያመሰገንኩ ጥያቸው እሄዳለሁ፡፡ የሚገርመው ነገር እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ብዙ ጊዜ ስለሚመረሩኝ ከኔ ጋር መቀመጥን እንኳን አይፈልጉም፡፡ በቃ የበረሃ አውሬ እሆንባቸዋለሁ፡፡ አንዳንዴ መስሏቸው በሚያደርጉት መጥፎ ነገር እኔም ውስጤ እኔ ብቻ ስለነበርኩኝ አልታገሳቸውም፡፡ ታግሼ ካቃተኝ ማለት እና ማድረግ ያለብኝን ሁሉ በሥነ-ሥረዓቱ አደርጋለሁ፡፡ ታድያ ጉዳቱም ጥቅሙም የግሌ ብቻ ነው፡፡ ለማንም አልሰጥም ከማንም አልቀበልም፡፡ ብቻ ምንም የማይገባበት የማይከፈት በር ልቤን ከርችሞ አደንድኖታል፡፡

ይባስ ብለው ናስቶሲን እና አክሰቴ ከታናሽ ወንድሜ አላዛር ጋር በነገር አለንጋ ይጠብሱኝ ጀመር፡፡ እኔን በክፋት ምስል በመሳል እሱን አሞጋገሱት ብቻ ማንንም ሰለማልሰማ ያሉትን ይበሉ ብዬ በዝምታዬ ፀንቼ ሁሉንም የሚያጉረመርሙ ዶፎች ሲያባራ ፀሐይ ሊወጣ ሆኖ ውስጤ እየበገነ፣ ባዶነት እየነገሰብኝ በእንባ ወጨፉን ታግሼ ዝናቡን በትዕግስት አሳልፈዋለሁ፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ ለዓለም አዲስ እንደ መሆኔ መጠን አዲስ የሆነውን ክፋት አና ደግነት ለመቀበል መቻል አስፈሪ ገደል ውስጥ እንደመወርወር ነዉ፡፡ ምክንያቱም ያለ ልምድ የመጣ ጡጫ ተሸናፊ ቢያደርግ እንጂ ልምድ ካለው ጋር የሚያቧቅስ ስላልሆነ ነው፡፡ የሰው ልጅ በተወለደ በሁለተኛው ቀን እንጀራ አይበላም፣ የዶሮ እንቁላል በአንዴ ጫጩት አይሆም፣ጥጃ ስለተወለደ ብቻ በአንዴ ቆሞ አይራመድም፣ ጭቃ ወይም አንጨት ብቻውን መኖሪያ አይሆንም፣ መብረር የሚፈልግ ሁሉ በአንድ ጊዜ መብረር አይችልም፡፡ ብቻ አንድ ነገር ያስፈልገዋል፡፡ እሱም ልምድ እና ብቃት ነው፡፡

ወራቶችን እንኳን በፅናት ያልቆመው የአጎት እና የአክስት ፍቅር በወንድሜ አላዛር ላይ ተገልብጦ ወዳሴው ወደ እኔ ሊዞር ዳዳው፣ ነገር ግን እኔ ያው የምታውቁኝ አብኔዘር ነኝ እና የነገሮች መበላሸት በክፋት ላይ እንድጣመም እንጂ ቀንቼ ቀና መሆን የተሰጠኝ ስጦታ አይደለም፡፡ አላዛር የት/ት መጀመሪያ ሰሞን ከቤተሰብ መለየት የመጀመሪያው ስለነበር አመሻሽ ሲመጣ በብርድ-ልብስ ውስጥ ሆኖ እንባው ጎርፍ ሆኖ እስኪወስደው ያነባል፡፡ ብቻ የልጅነት ዕድሜ ሆኖ ክብር ባይሰጠኝ እና እንደ ታናሽነቱ አለመሆኑ ብዙ ጊዜ ቢያናድደኝም ይህንን በማየቴ እኔም ተከፍቶ ማዘኔ የግድ ሆነ፡፡

ፊቱ ብስቁል ሲል ዐይኖቹ እንባ ሲያቀሩ ምንም እንደማልበድለው እና የፈለገውን ነገር ከእኔ አስቀድሜ ላደርግለት እንደምችል እየነገርኩ ላፅናናው እሞክራለሁ፡፡ ከላይ ሰውነቴ በፀጥታ ታጅሎ የሚያስፈራ ቢመስልም ለሰው ልጅ ግን ውጤ ብዙም ጨካኝ አይደለም፡፡ የት/ቤት ውሎ በዛላይ የችግር ህይወት በሰው ሀገር ላይ ተጨምሮ ግትር ባህሪዬ በመጠኑ እየተገራ የመጣ ይመስላል፡፡

የአንደኛ ሴሚስተር ትምህርትም እየተጠናቀቀ ስለነበር ከውድቀት በኋላ የመጀመሪያ የመነሳሻ ውጤቴን ለማት ጓጓሁ፡፡ ከብዙ የመርሳት ዘመን በኋላ ሁሉንም ለማስታውስ ሞከርኩ፡፡ የመጣሁት መንገድ መልካም ባይሆንም ቢያጠነክረኝ እንጂ አድክሞ እንድቆም የማያደርገኝ መሆኑን በአንክሮ ለራሴ አስረድቼ ነገርኩት፡፡ ዓለም የፈተና ውጤት ነች፡፡ መራራውን በፀጋ የተጎነጨት የደስታን ጣዕም በተድላ ያጣጥሟታል፣ ከዛ መልስ ግን ሌላው ከአፉ ያደረሰውን ጉረሻ እንኳን ሲጎርስ ተሸማቆ በገባበት ቤት ውስጥ መግቢያ ሳጥን ይጠፋዋል፡፡

አሁን ትኩረት ማድረግ ያለብኝ እና የቀረኝ ተስፋ በቃ አንድ እና አንድ ት/ት ብቻ ነው፡፡ ከዛ ውጪ ያለው በሙሉ ናፋቂነት ነው፡፡ በ’ርግጥ ወቅቱን ያልጠበቀ ፍላጎት ቢመስልም ላይደረስ የሚጀመር መንገደ የለም እና ሁሉንም አድርጌ ለመነሳት ለራሴ ቃል ገባሁ፡፡

በዚህ ሁነተት ውስጥ እያለሁ የአንደኛ ሴሚስተር ውጤት ደረሶ የሁሉም የክፍሉ ተማሪ ውጤት ተነገረ፡፡ በክፍል ውስጥ ዘጠና አምስት ተማሪዎች አሉ፡፡ ዘጠነኛ ክፍል ብቻ አስራ ዘጠኝ ሴክሽን አለው፡፡ በጣም ትልቅ የፋሲሊቲ እና የአስተምህሮት ችግርም በተጓዳኝ ሁኔታ ያለበት ነበር፡፡ ከዛ ሁሉ ተማሪ ውስጥ ያልጠበኩት ውጤት መጣ፡፡ ይህም ሊያጠነክረኝ አስቀድሜ ለራሴ ቃል ገብቻለሁ፡፡

የሰው ልጅ ንዴቱን ገልፆ የሚወጣበት የራሱ የሆነ የመገለጫ ባህሪ ይኖረዋል፡፡ እኔም ከእነዛ ባህሪዎች ውሰጥ ማልቀስ እና መቆጣትን ብሎም ውስጥን አቁስሎ በማድማት ማንም የሚተካከለኝ ያለ አይመስለኝም፡፡

እንባዬ በልጅነት ንዴት ላይ ተጨምሮ ተፍነከነኩ፡፡ ለራሴ ማንነቴ ገርሞ እያበሳጨኝ የት ነበርኩ?! አልኩኝ፡፡ ያለፈው ማየቴ ውስጤን እያራቆተው ከአላማዬ ወደ ኋላ ሊመልሰኝ ብዙ አያሌ ምክንያቶችን በየቀኑ እያመጣ ይደረድርልኝ ጀመር፡፡ ብቻ ሥራ የበዛበት ጭንቅላት መሳሳቱ እውነት ሆኖ የግድ ነው እና ከዚህ አድካሚ አስተሳሰብ ትናንትን ቀብሬ ዛሬን እና ነገን ኖሮ ለማሳየት ራስን ከመፀሐፍ ውስጥ ከቶ መገኘት የግዴታ ውዴታዬ ሆኖ ውሎ እና አዳሬ ከመፀሐፍ ዓለም ሆነ፡፡

ት/ቤቱ በመጠኑም ቢሆን በርካታ አጋዥ መፅሐፍቶች አሉት ነገር ግን የመንግስት ት/ቤት እንደመሆኑ መጠን የመምህራኖች በወቅት አለመቀጠር እና በጊዜ በስሥራ ገበታ ላይ ተገንቶ አግባብ አና በእውነት እውቀት ላይ የተመሰረተ ስልጠና መስጠቱ ላይ ትልቅ ችግር ነበር፡፡ ሁለት ሳምን ክላስ ቀጥቶ ከሚመጣ ተማሪ ጋር ለፉክክር በሚመስል መልኩ እየዘበተ የሚመጣ መምህርም አለ፡፡ በ'ርግጥ ይህ ሰው ለራሱ ባለሞያው ስለመሆኑ ራሱን ሊጠራጠርው ሲገባ ራሱን ኮፍሶ ስድብ እና ግልምጫው አጀብ ያስብላል፡፡

አንዳንዱ መምህራን ዲቪ ሞልቶ እድሉ እስኪደርሰው በማስተማር ፋንታ ሲሞላፈጥ እና የእንግሊዘኛ ስብርብር አነጋገሩን ማቃኒያ አድርጎ ያለወቅት ብሎም ያለ ትክ መምህርት/ር የሚሄደውም የትዬ-ለሌ ነው፡፡

በክፍላችን ውስጥ ብዙ የሀብታም እና ት/ቸውን በግል ት/ቤት በረራ ውስጥ ያጠናቀቁ ተማሪዎች አሉ፡፡ በእውቀት ዙሪያ ተሳክቶላቸው ከሌላው የገጠር ተማሪዎች የደረጃ ውጤት ባይኖራቸውም በመከተል ከኋላቸው አይቀሩም፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ብዙኃኑ ተማሪ ስልጠናውን ከታች ጀምሮ በላቲን ፊደሎች የወሰደ ቢሆንም እንግሊዘኛን አቀላጥፈው አግባቡን ጠብቀው ለመናገር ባይታደሉም አወላክሶ ለመናገር ከመምህሩ ጀምሮ ቋንቋ የተቸገሩ አይደሉም፡፡ ከበረራ የመጡት ግን ከነዚህ ተማሪዎችም ሆነ መምህራኖች የተሻለ የቋንቋው ክህሎት ስላላቸው ያስቸግሯቸው ነበር፡፡

አንዳንዱ መምህር እስፔሊንግ እንደ ኢሊጎሬ ሲስት አይጣል ብቻ ነው፡፡ በ'ርግጥ እዚህ ውስጥ የሚያሳዝነው ነገር ቢኖር ልክ ናቸው ብሎ ዶከመንተሪ ፅፎ ላያነበው የሚያስቀምጠው ተማሪ ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ከዘጠና አምስት ተማሪዎች ውስጥ ለምን አላማ ትምህርት ቤት እንደመጣ አንድም ተማሪ አያውቅም ማለት ይቻላል፡፡ የእነሱ አላማ እና ግቡ ለራሳቸው የአንደኝነትን ደረጃ ይዘው ተሸልመው ቤተሰቦቻቸውን በስጦታቸው እንዲደሰቱ ማድረግ ብቻ ነው፡፡ እውነት እና እውቀት ግን በዚህ መሐል እንደ ጉም በና ተናለች፡፡

ይህ የትምህርት ደረጃ መምህር እንደ ታችኛው ክፍል እያባበለህ የምትማርበት ት/ቤት አይደለም፡፡ ሳይንስን እና ህጎችን በማዳበር እና በተግባር ለራስህ ስትል እራስህ ለራስህ በእጅህ የምትመገብበት ብሎም ሌላውን ለመመገብ የምትዘጋጅበት ነው፡፡ አንድ ክፉ ሰርገኛ ድግስ ሊደግስ ይችል ይሆናል፡፡ ነገር ግን መብላትም ሆነ መተው የተጠሪው መብት እና ፍላጎት ነው፡፡ ነገር ግን የእጅ መንሻ ሳይከፍሉ መውጣት ግን ህሌና ለሌለው ሰው አይቻለውም፡፡

በ'ርግጥ ለዚህ መብት እና ግዴታ እንኳን ይህ ት/ቤት የታደለ አይደለም፡፡ የተሰጠውን ይቀበላል፡፡ ካልሆነ ግን በሥነ-ምግባር ግድፈት ችግር ኢን-ኮምፕሌት አሰፍስፎ ያጠብቀዋል፡፡ ይህ ነገር እንደ አዝማሪ ተቀበል በሚባልበት ት/ቤት ውስጥ መሆኑ እጅግ ያበሳጫል፡፡ ሀቁ እዚህ ጋር ነው፡፡ ንዋይ ደበበ ‹‹ሀገሬ ሰው አጣሽ ወይ›› የሚለውን ዜማ ደርሶ ከመበተኑ በፊት ሊያሰማው የሚገባው ድንቅ ዜና ነበር፡፡

## *እኛ!! የጩንቅ ዘመናቶች*

ብዙውን ጊዜ የደከመ አዕምሮዬን አሙቆ ለማስነሳት ቶፑ፣ ጋላክሲ፣ ኤክስትሪም፣ የመምህሩ መምሪያ መፀሐፍ፣ የመማሪያ መፀሐፍቶች፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ማዳበሪያ መፀሐፎች ሜጋ፣ ኩራዝ፣ ስፖክን፣ ኮይን፣ ኦክስፎርደ …… ፣ የልብ ወለድ እና ታርካዊ ድርሳናት…..ለማንበብ አቅሜ መያዝ በሚችለው መጠን እሞካክራለሁ፡፡ ይህንን ያዩ አንዳንድ ተማሪዎች ጎበዞች ቢሆኑም ‹‹ብዙ ባነበበ ሳይሆን በገባው ነው፡፡›› ይላሉ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ እነሱ ያሉት ልክ ነው፡፡ ችግሩ ግን ሰው ማበድ አለማበዱን ለማረጋገጥ ራሱ ጤነኛ መሆኑን አስቀድሞ በመስፈረቶቹ መሰረት መመዘን አለመቻሉ ነው፡፡

እነዚህ ተማሪዎች የትም አያመልጡም፡፡ እውነቱም ብርቱው ፈተና ሲደርስ ውሃ እንደገባች አይጥ ተኮማትረው መገኘታቸው ላይ ነው፡፡ ፈተናው ፅሑፍ ቀርቦ ነጭ ወረቀት የሰሌዳውን መልስ ሲያጣበት አንበሳ እንደመጣበት መንጋ አንደኛው ከደብተሩ፣ ሌላው ከመፀሐፉ እንዲሁም የበረታው ከአጤረራው መሸጎጡ ነው፡፡ እጅ ከፈንጅ ሲያዝ ‹‹ለሚቀጥለው የት/ት ዘመን የመማር እድል እንዲገጥመኝ ነው፡፡ በዛ ላይ ያኔ ልጎብዝ እና አዕምሮዬም በስሎ ብዙ ነገር እሰራ ይሆናል፡፡›› ይላል፡፡ ብቻ ማሳበቢያ እንከኖችን ምን ጊዜም ቢሆን አናጣም እና ሰበቡ ትውልድ ነበር እኔን እንደዛ ሲለኝ የነበረው፡፡

ሌብነትን ትውልድ አዲስ እንደ መሆኑ መጠን ከየትም አይማረውም፡፡ ሰው መጥፎ ነገሮችን ማዳበር ብሎም ማዘውተር ከጀመረ በቃ እሱ ሌባ ነው፡፡ መዳበሩ ግን የሚጀምረው ከቤት፣ ከት/ቤት፣ ከጎረቤት እና ታሪካዊ ዳራ ካላቸው መጥፎ የሥነ-ቃል አረዳድ እና ዘመናዊ አስተምህሮቶች ነው፡፡ ሀገርም ሆነ ትውልድ ቀና እንዲሆን ቢቻል ድንጋዩ የሚናገረውን መስማት አለብን፡፡ ምክንያቱም 1225ዓ.ዓ በፊት በንጉስ ስብታህ የኢትዮጲያ የስነ-ፅሁፍ ታሪክ በቦርኜ ተንቆ በችግሩ ጊዜ በልጁ ኤልዛቦር ሲጠቀመው በአንድም በሌላ አክብሮ ማንገሱ መከበሪያውን አውቆ ስለጠቀመው ነው፡፡

እኔም ‹‹ያም ከማደር ድፎውን መቀርቀር›› እንዲሉ ከብዙ የድካም እና የትጋት ወራት በኂላ ውጤቴን ለእውቀት በመጠን አሻሽዬ ወደ ቀጣዩ ክፍል ከአስር ወራቶች በኂላ ተዘዋወርኩ፡፡ ክረምቱ ደርሶ ወደ ቤት ስንመመለስ ወንድሞቻችን እና ቤተሰቦቻችን የኑሮው ቅጡ ጠፍቷቸው ‹‹ሎቱባን ሲልጉ›› ይባባላሉ፡፡ ሰውነታቸው ክፉኛ ተጎድቷል፡፡ ሁለቱም ጋር ’ርስ በ’ርስ መከፋፋቱ ከበፊቱ ይበልጥ ጨምራል፡፡ ነገር ግን ሁለታችን ስንመጣ ህሌና እና ኤርሚያስ እንዲሁም ወንድሞቻችን አቀባበላቸው የስሰስት እና የፍራቻ ይመስል ነበር፡፡ ቤት ያፈራውን ጎንበስ ቀና ብለው አስተናገዱን፡፡ ትንንሽ ወንድሞቻችን ቦርሳ እና ይዘን የመጣነውን ሸቀጥ ይፈትሻሉ፡፡ ፊታቸው ከኛ ባይብስም ነጭ ሆኗል፡፡

ፍላጎታቸው ሰው ከከተማ መጣ ሲባል የሚታወሰው ከረሜላ ወይም ገንዘብ እና ሌላ ጥቅማጥቅም ነው፡፡ በወንድሞቻችን ብቻ ያላባራው ፍተሻ በህሌና ተደገመ፡፡ በ’ርግጥ ተማሪዎች ነን፡፡ ሥራ ወይም ሌላ የገንዘብ ማግኛ ምንጭ የለንም፡፡ መሳፈሪያ እንኳን ቸግሮን የአከራያችንን የጓሮ አትክልት ቆፍረን ነበር አስራ አምስት አስራ አምስት ብር ከወንድሜ አላዛር ጋር የተካፈልነው፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ በጣም ’ርቦን እና ደክሞን ስለነበር የመሳፈሪያ አስር አስር ብር አስቀርተን አምስት አምስት ብሯን አንድ ላይ አጋጭተን አንድ በየዓይነት እና አንዳንድ ብስኩት በላንበት፡፡ በቃ ያ! ብር ዳግም የሚመለስ ቢሆን መልሼ ቡና እና ከረሜላ ብገዛላቸው ምንኛ ደስ ባለኝ ነበር፡፡ ነገር ግን ላለፈ ክረምት ቤት አይሠራ ሆኖ ሁሉም በምኞት ቀርቶ በሥራው ዓለም በግብርናው፣ በረኝነቱ፣ በአጨዳው ሽር ጉድ ስንል በዝናቡ ወቅት አልፎ መስከረም ሲጠባ አደዩን አሽትተን፣ ቤት ያፈራውን ተቋድሰን፣ እንግጫውን ተንተንበት፣ ጭፈራውን ለአዕምሮ ማደሻ ዳንስ እና ዳንኪራውን ለጥርስ ማፍለቅለቂያ ችረንበት ወደ ቀደሞ ቤታችን ጓዛችንን ሸክፈን ተመለስን፡፡

መስከረም ከት/ቤት ወደ ቤት የሚመላለሱበት እንጂ ብዙውን ጊዜ ት/ት የለም፡፡ ብቻ በአረንጓዴ ተፈጥሮ ልምላሜ የተዋበውን ግቢ ሲሻን አንብበንበት ሲለን ደግሞ ተዝናንተንበት እንመለሳለን፡፡ ቀድመንም የቤተሰባችንን የኑሮ ደረጃ ስለምናቅ አንዳንዴ ከመነኻሪያ እስከ ከተማው የሆነ ቦታ ድረስ አንዳንድ እቃዎችን እያመላለስን የሻይም የዳቦም እናገኛለን፡፡ በ'ርግጥ ካለፈው ዘመን ጀምሮ ለቤተሰብ በጣም ስንጨነቅ ስለነበረ የሚላክልንን የገንፎ እና የአጥሚት እህል መልሰን እንልክላቸዋለን፡፡ እነሱ ከዛ ለኛ እኛ ከዚህ ወደዛ ለእነሱ እንጨነቃለን፡፡

ወርልድ ቪዠን ኢትዮጵያ የተለያዩ እገዛዎችን በከተማው ያደርግ ስለነበረ ከፍተኛ በሚባል ደረጃ አንዳንድ ድጋፎችን አድርገዋል፡፡ ለሁለት ዓመት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተገኝተን ለመማራችን ከፍተኛውን ሚና ሲጫወቱ ቤተሰብም እኛን በአቅሙ ለማገዝ ያላደረገው ጥረት አልነበረም፡፡ እናታችን እኛን ለማየት ስትመጣ መቀነቷ ያፈራውን በትናልን ትሄዳለች፡፡ ከጥሮሾው፤ ከእንጀራው፤ ከሽሮው፤ ከበርበሬው እና ከቅመማ ቅመሙ አንድም የሚቀራት የለም፡፡ ሌቱን ተጫውታ፤ አጫውተን፤ ስቀን አሳስቀን ከማህላችን አስተኝተን ቀድሞ ያላገኘነውን የእናትነት እና የልጅነት ፍቅር ሰጥተን ተቀብለን እንሸኛታለን፡፡

አባታችን ሁሌም ለኛ ያለው ፍቅር እንኳንስ ተለይተነው አጠገቡም ሆነን አያምነንም፡፡ ብቻ ወር ባልሞላ ቀናቶች ውስጥ የጉዝጓዝ ሳር እያጨደ፤ ቤት የተዘጋጀውን ሁሉን እያስቀመመ ይዞ ይመጣል፡፡ መጀመሪያ ሳሩን ከአስፋልት ለሰው ያስረክብ፤ ስንቃችንን ይዞ ይመጣ እና ከእኛው ጋር ተመልሶ የጉዝጓዙን ሳር ለመሸጥ ይዞን ይወጣል፡፡ ያገኛትን በሙሉ ግማሹን ስጋ በመግዛት የተቀረውን ለትራንስፖርት እና ለአንዳንድ ወጪዎች ሰጥቶን ይሄዳል፡፡

ታድያ በዚህ መሐል ችግር ከቀን ቀን እየበረታ ሄዶ የቤት ክራይ ለመክፈልም የሚሆን አቅም እየታጣ መጣ፡፡ የአንድ፤ የሁለት፤ የሶስት፤ የአራት ወር አከራያችን ይህ ሁሉ ሲሆን ከቤተሰብ ጋር ከመነጋገር ውጪ እኛን ያለን ነገር አልነበረም፡፡ እኛ ግን በገባን በወጣን ቁጥር መሸማቀቃችን ብርቱ ሆነ፡፡ ‹‹አረ!!›› ሰርቶ መታሰር እንዴት ቀላል ነበር?! ይባስ ብሎ አከራያችን ሁሉንም ነገር ስለተረዳ የከብት እርድ እንድናግዘው እያደረገ የመሄጃ ብር ከራሱ ይሰጠን ጀመር፡፡

በ'ርግጥ ችግሩ በቤት ክራይ ብቻ የፀና አይደለም፡፡ ይልቁንም በአስቤዛም ጭምር ራሱን ክፉ ያደረገበት ወቅት ነበር፡፡ የሚላክልን ስንቅ በሳምት ለአንድ ሰው እንኳን በአግባቡ የምትበቃ አይደለችም፡፡ ይሁን እንጂ እሷውኑ እያብቃቁ ለመዝለቅ ጥረት በምናደርግበት ወቅት አላዛር አንዳንድ የሰፈር ሥዎችን በማገዝ ገንዘብብ ያገኝ ጀመረ፡፡

ሁለታችንም ከቤተሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ ስንለያይ ቃላችን አስረኛ ክፍልን ጨርሰን ለመመለስ ነው፡፡ ከዛ ውጪ ግን የማንፈልገው መሆኑን ከአንድ ዓመት በፊት የደመደምነው አጀንዳ ነው፡፡ ሀቁ ግን እኔ ጋር የነበርው ይህ ዓየነቱ አስተሳሰብ አሁን ላይ ተወገዷል፡፡ በወንድሜ ዘንድ ግን እውን ስለነበረ ራሱን ካገለለ በወራቶች ጭብጨባ የተሸኘው ዓመት መስክሮለታል፡፡

እሱ የተሰጠው የራሱ የሆነው ነገር ይህ ነው እና በተደጋጋሚ ከጥናቱ ለማሰናከል የማያደርገው ጥረት የለም፡፡ ‹‹ክፉ ጎረቤት አይግጠምህ፤ ክፉ ዘመን ያልፋል እና!›› ሲባል በ'ርግጥም አይቶ ሳላወቀው ቀልድ ይመስላል፡፡ እውነቱ ግን እራሱ ዋዘኛው ቀልድ ነው፡፡ አሌ በነዮዲት እና በባለቤቷ ቱትሞሲስ ምክር ሳላስበው እያነበብኩ የነበረውን ደብተር ከእጄ መንጭቆ ከጣራው ላይ ወረወረው፡፡ በጣም ተናድጄ ስለነበር እግሮቼን የፊጥኝ አንፈራጥጬ እያነሳሁ ከመቀመጫው ላይ ነረትኩት፡፡ እጆቹ አንገቱ ላይ ተንጠለጠሉ ቡጢዬ በርትቶ እጆቹ ሲፈቱ ማንም ሳየየኝ ደብተሬን ሰብስቤ ወደ ቤት ተመለስኩ፡፡

ብቻ የጎረቤቱ ምክር ለኔ ግልፅ ባይሆንም ይህን አድርግ ብለው መላካቸው ካለኝ ያለመቀራረብ ሁኔታ የመነጨ ይመስለኛል፡፡ ነገር ግን የግዴታ በእነሱ ለመወደድ ስል አሽርጋጃቸው መሆን እንደነበረብኝ የመጀመሪያው ማሳያቸው ነበር፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ አሌ ሠርቶ የሚያገኘውን ለራሱ ይጠቀማል እንጂ በፍፁም ወደ ቤት ይዞ አይመጣም፡፡

በነገራችን ላይ ሥራ መሥራቱን ያወኩት ከአንድ የችግር ወቅት በኋላ ነበር፡፡ ከሚላክልን ስንቅ ብዙ ጊዜ አይጠቀመም ነበር፡፡ እናም አሞት ይሆን ብዬ በመጨነቅ በተለያዩ ማባበያዎች ልጠይቀው ሞከርኩ ነገር ግን ላይሆን ነገር ለፍቼ ጭንቀት ላተርፍ ምንም እውነት ሳላገኝ ጤነኛ እንደሆነ ነገረኝ፡፡ ግን አላመንኩትም ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ቤት ላፀዳ ከመኝታችን ስር ስገባ የተለያዩ የምግብ ዓይነቶችን አገኘሁ፡፡ በወቅቱ በጣም አዘንኩ ሰውነቴ እርቃኑን እስኪቀር በችግር ደርቆ እሱ እንደዚህ ዓይነት ነገር ማድረጉ በጣም አናደደኝ፡፡ ጭንቀቴ ለራሱ ነው፡፡ ታሟል፤ ተከፍቶብኛል፤ ተቸግሯል ….. ብቻ ይሄንን ሳስብ ነበር ሁሉም ነገር ገሓድ ወጥቶ ሥራ እንደሚሰራ ያወኩት፡፡

ይህ ሁሉ ደባ ሢሠራ የነበረው በጣም ከፉ በነበረች የኑሮ ውጣ ውረዱን በቅጡ የማታውቅ የሰባተኛ ክፍል አቋራጭ ተማሪ ባለትዳር እና የአንድ ልጅ እናት ወ/ሮ ዮዲት ናት፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡፡ ይች ልጅ የመጀመሪያ ልጇን ከርስትና በምታነሳበት ወቅት እንጀራ ማንኛውም ሰው እንደሚጠቀመው እጠቀም ነበር፡፡ ታድያ ረሃብ በመኖሪያዬ ነግሶ የምቀምሰው ባጣ እንደ ለመድኩት አንድ ቀን መሶቧን መሶቤ አድርጌ አንድ እንጀራ ወሰድኩ፡፡ ነገርየው ተደባልቆ ክፋት እና ማሸማቀቅ እና ማጥላላት የተጀመረው ከዚህ ጊዜ በኋላ ነበር፡፡

ዮዲት ብቀላው እንደ እውነቱ ከሆነ ይህንን ችግር መሠረት ያደረገ ነበር፡፡ የሚያስጠላው እና የነገሩ አቅጣጫ ከባድ ያደረገው በማይመጣበት ቦታ በወንድማማችነት መሐል መሆኑ ነው፡፡ አስበው የአስራ አምስት ዓመት አፍላ ሕጻን ላይ ይህንን ማደረግ ምንኛ የሚከብድ አፀያፊ ነገር እንደሆነ ለራስ መገመት ነው፡፡ በነገራችን ላይ እንዲህ ዓይነት ነገር መጥፎ እና አስጠሊ እንደሆነ ለራሴ የነገርኩት ከዛን በኋላ ነው፡፡ ምንም ነገር የሰው በሆነ ነገር ላይ መወሰንም ሆነ እርምጃ መውሰድ እንደሌለብኝ ለራሴ በመንገር አራግፌ ከአእምሮዬ ውስጥ አሶገድኩት፡፡

ይህን ክፋት ያየችው ከግቢያችን ውጪ የነረችው ወ/ሮ ትሬዛ ለነገሩ ትኩረት በመስጠት በአጥር መሹዋለኪያ መዐድ ቤቷ ሞቆ ቤት ያፈራውን ስትዘራበት ከእንጀራው፤ ከዳቦው እና ከጥሬው ታቀብለኛለች፡፡ ወ/ሮ ትሬዛ የአራት ልጆች እናት ስትሆን  ለኔ ያላት ነገር በሙሉ አዘኔታዋ እና ተግባቦቷ እንደ እናት ነበር፡፡ ጥሩነት በኔ ዘንድም መወለድ የጀመረው በዚሁ ወቅት እና ትህትናዋ ነበር፡፡ ታድያ እኔም በዚህ የተነሳ ከግቢያቸው እየገባሁ የሚሠራሩ ሥራዎችን አግዛት ነበር፡፡

የቤት ክራይ ክፍያው ከዛሬ ነገ እየተባለ አምስተኛው ወሩ ደርሶ፡፡ የማትሪክ መፈተኛውም ቀን እየተቃረበ ነው፡፡ ከቤተሰብ ጋር ምንም ዓይነት ፍንጭ ጠፋ፡፡ በስተመጨረሻ ወርልድ ቪዢን ኢትዮጲያ የገዛልኝን ከአንድ ገጠራማ የግብይት ቦታ ሽጬ የአራት ወር የቤት ክራይ ከፈልኩ፡፡

የምትቀረው የአንድ ወር ክፍያ ስለነበረች በማጠናበት ወቅት ከነዮዲት የተላከው አላዛር ወደኔ መጥቶ አንድ የቁፋሮ ሥራ አግኝቶ እንደነበር አወጋኝ፡፡ እናም ተያይዘን ችግር ባቆሻመደው ገላ ላልተወው ነገር ችግር ላለቀው ነገር መከራ ሆኖ ላብ ሰውነቴን አጥምቆ እያንቀጠቀጠኝ ጨርሰን የመጨረሻዋን ክፍያ በራሳችን ደመ-ወዝ አገባደድን፡፡

ታላቁ ወድቆ የመነሻው የማሪክ ፈተና ከፊታችን ቀናቶችን እያስቆጠረ ከች አለ፡፡ ሁሉም ተማሪዎች በውስጣቸው የመረበሽ ስሜት ግኖ በፊታቸው ላይ እንደ አብሪ ኮኮብ ይንፀባረቃል፡፡ ግማሹ ሩሙን ፍሊጋ ሲኳትን እንደ ቁምጣ ተለክታ የተሰጠች ሰዓት ትጋመስ እና ፊደሎችን እንዳይከፋቸው ካሬዎቹ እንዳይቀየሟቸው አደማምቀው ይወጣሉ፡፡ በ'ርግጥ አስቦ ለሚሠራ ሰው የሚሰጡት ደቂቃዎች ከሚገባው በላይ አስጨናቂዎች እና አስፈሪም ጭምር ነው፡፡ አስቀድሞ ስለ አንሰር ሺት ኦረንቴሽን ቢሰጥበትም ከሥራው ላይ ሲኮን እንደታሰበው ቀላል አይሆንም ነበር እና ወይ ሥም ካልሆነው ኮድ ነበር አንዳንዴም የከፋውን እና የካሬ ምስል ትክክለኛውን የጥያቄ ምላሽ በተራ ቁጥሩ ላይ ላትሞላ ትችል እና ሁሉም ተዛንፎ ልትሳሳት ትችላለህ፡፡

በዛ ላይ አንዳንድ ቀጣዩን ክፍል በጭብጨባ እንደለመዱት ሊያጅቡ የተዘጋጁ ከንቱ መንገደኞች ከጀርባ ከፊት እንድትሰራላቸው ሲያሻቸው በብህራቸው ጫፍ ጀርባህን ያደነቁሩታል ካልሆነም ሲዝቱብህ ሌላኛው ደግሞ ፈጣሪው ትመስል በተማፅኖ ይወተውትኃል፡፡

በዚህ ሁነት ውስጥ 'ርግጠኛ ባልሆንም እኔ ግን በደንብ እና በትኩረት እንደሰራሁ ባለ ሙሉ ተስፈኛ ነኝ፡፡ ፈተናውም ተገባዶ የንብረት ምልልስ በሚደረግበት ወቅት ታድያ ከጎኔ ሆኖ ሲያስጨንቀኝ የነበረው ተማሪ ከሌሎቹ በተለየ ሁኔታ ሲንቀዠቀዥ ስለነበር ቦታ እንደተቀየረለት አስታውስ ነበር፡፡ ታድያ ከዛ በፊት በርካታ ፈተናዎችን ብሰራለትም ሌላውን ስላላገኘ ‹‹እናንተ የተፈጥሮ ሳይንስ ወይም የማህበራዊ ሳይንስ እያላችሁ ቁርጥ ከሻኛው ስታማርጡ እኛ እንደ ፈረደብን ወደ ኮብልስቶናችን ጋር እንጋባለን፡፡›› አለ ራሱን አሻሽቶ ጭንቀት በሚመስል መልኩ፡፡

እኔም መልካም እንደሚሆንለት ተስፋ እንዲያደርግ እውነቱን እያስረዳሁት የአስራ አንደኛ ክፍል የሳይንስ መፀሐፍ ይዤ ሌላኛውን የበጋ ማዳረሻ ክረምት ከቤተሰብ ጋር ልከርም ከአላዛር ጋር ጓዛችንን ሸክፈን ሄድን፡፡

• * *

ክረምቱን ከቤተሰብ ጋር እንደተለመደው ብናሳልፍም መስከረም ደርሶ ውጤታችንን አይተን እስክናውቀው እኔ እና አላዛር ከልብ ቸኩለናል፡፡ ከዘጠነኛ እና ካስረኛ ክፍል ጀምሮ የኮምፒውተር ቲዎሮቲካል የሆነ ት/ት አልፎ አልፎ ቢሰጥም ኮምፒውተርን ግን በዐይናችን አይተን በእጃችን ለመንካት አልታደልንም እና ውጤታችንን በበየነ-መረብ ለመመልከት ከዚህ የተነሳ የሚሆን እውቀቱ አልነበረንም፡፡ ስልኮችንም ቢሆን ከሰው እጅ በዘልማድ እየተቀበልኩ ለማስተካከል ብሞክርም የራሴ የሆነ ስልክ ግን አልነበረኝም፡፡ በዚህ ምክንያት ሌላውን ብንጠይቅ አለማወቅ ሆኖ ወርደት አድርገን ስለተገነዘብነው በመፍራት ከት/ቤት መጥቶ በካርድ እስከምናየው በትዕግስት መጠበቅ ግድ ሆኖ መስከረም አጋማሽ ተገባደደ፡፡

ሁሌም የማይሞላለት በርቶ የማይነጋለት የነህሌና እና ኤርሚያስ ቤት ግን ከቀንቀን ራሱን እየገደለ ወደ ገደሉ ማማ መሮጡን ተክኖበት የትራንስፖርት ሃያ ብር እንኳን ህልም ሆና ጥቅምት ጠባ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ቁርጡ ይታወቅ ተብሎ እንጂ ወርልድ በምፅዋት በሥሜ የለገሳቸው ጥቂት በጎች እና የምትታለብ አሜሪካን ላም ተሸጠው መማሩ የማይቀርለት ሀቅ መሆኑን አስጠንቅቄ ነግሬያቸዋለሁ፡፡ በዚህ መሐል የማይፈነከት አለት ሆነውብኝ ቀድሞ ከተላመድኳት የሰፈራችን የሻይ ቤት ባለቤት ውሃ እየቀዳሁ፤ የለስላሳ ካሳ ከመኪና እያወረድኩ እና የሚያዘኝን እየታዘዝኩ ያጠራቀምኳትን አስራ አምት ብር ይዤ ለመሄድ ተነሳሁ፡፡

ታድያ አስሩን ብር ከፍዬ ከዛ ብደርስም ሰዓት አልፎ ስምንት ሰዓት ተረኛ እሲኪገባ ከዛው ሆኜ መጠበቅ ነበረብኝ እና የራሴን ችግር ለራሴ እስከነ ህመሙ ተሸክሜ በጥበቃዬ ተካንኩበት፡፡ ር/መራችን ከግቢው በራፍ ሲገባ ምክትሉ ከኋላ ኋላው እተከታተሉ እኔው ከተቀመጥኩበት ቢሯቸው ደርሰው ሰላምታቸውን አጥበቀው ችረው ወደ ክፍሉ ይዘውኝ ዘለቁ፡፡

ቅድሚያ የአላዛርን ውጤት ነበር ያየሁት፡፡ ምክንያቱም የኔ የተስተካከለ ውጤት ሊሆን ካልቻለ የሱን ሳላይ ጥዬ እንደምሄድ ጠንቅቄ አውቅ ስለነበር፡፡ አላዛር ከማለፊያው ውጤቱ 0.64 ነጥብ አንሶ አለማለፉን አረጋገጥኩ፡፡ ነገር ግን የኔም ተራ ደርሶ ስለቸኮልኩ ተስፈኛ የሆንኩበት የማትሪክ ውጤት ካንድ ሁለቴ ተደምሮ ከማለፊያው ውጤት 0.21 ቀንሶ አለማለፌን ላምን ሳልችል ከዛው ፈዝዤ ደጋግመው እንዲሰሩት በተዘበራረቀ ማንነቴ ውስጥ የተዘበራረቀ ውጤት ደምሬ አካፍዬ እያመጣሁ ታገልኳቸው፡፡

በመጨረሻም የሆነው ህልም እየመሰለኝ ብዙ የአማርጭ ት/ቤቶች በተለያዩ የት/ዘርፎች እንድማር ሊያመቻቹልኝ ምክረ ሀሳባቸውን ሊለግሱኝ ቢሞክሩም ስሜት ገዝቶኝ እነሱም እያዘኑ ከክፍሉ እንባ በዐይኖቼ ሽፋሽፍት ሞልተው እየፈሰሱ ከግቢው እንዴት እንደወጣሁ ሳላውቀው ራሴን ከመኪና ውስጥ አገኘሁት፡፡

መኪናው የሚጓዘው አስራ አራት ኪሎ ሜትር ብቻ ነው፡፡ ከሰፈሬ ለመድረስ ደግሞ የሚቀረኝ ስድስት ኪሎ ሜትር ነበር እና ያለችኝን ከፍዬ ተራምዶ በሰውነት ውስጥ ቁስል አዝሎ ቤት ለመድረስ ሁለት ነጥብ አምስት ኪሎ ሜትር የቀረው እግሬ ከመንገድ ዳር አዝለፍልፎ ራሴን እንደ ሉል እያሽከረከረ ጥሎ በእንቅልፍ ካለሁበት አስምኖ አነጎደኝ፡፡ አመሻሽ ያለሁት ከመኝታዬ ቢመስለኝ ዐይኖቼን ስገልጣቸው ፀሐይ አዘቅዝቃ መንጋ ወደቤቱ ሲየጎረፈ ጋደም ካልኩበት የድንበር ጎዳና ስነቃ ከቤት አለመሆኔ 'ርግጥ ሆኖ መንገዴን ቀጠልኩ፡፡

ከምሽቱ አንድ ሰዓት ገደማ ስደርስ ህሌና ቀድሞውኑ ከሁነቴ ነገሩን ተረድታ ስለነበር የደስተኝነት ስሜት አልተሰማትም ነበር፡፡ ይሁን እጂ የበሰለውን የብረት ምጣድ ቂጣ ለመቅመስ ብንሰፈሰፍም ቁጣዋ ግሎ እንዳልነበር ሆነች፡፡ እውነቱን ባላውቅም ለጊዜው ቦግ ያለው ንዴት ከት/ት ውጤት ጋር የተያያዘ ሳይሆን ሌላኛውን ድክመቴን አበጥሮ የሚያውቅብኝ እና የሚቀራመተኝ አካል መጣብኝ ዓይነት መልዕከት የበነረው ነው ቢባልም ከምታደርገው ድርጊት አንፃር ገላጭ ከግምትም ያለፈ ትክክለኛ ነበር፡፡

በ'ርግጥ ማንነቴ ከሚገባው በላይ ተናግቷል፡፡ በዛ ላይ የህሌና ንዝንዝ እና የጭቅጭቅ ቃሯ አጀብ ሆኖ ያሳብዳል፡፡ ምክሯ ስድብ ነው፡፡ ተግሳፁዋም ቢሆን ተመሳሳይ ነው፡፡ ወንድነትም አብዝታ ረጋሚ ዓይነት ፍጡር ነች፡፡ ነገር ግን በሥራም ሆነ በትዕዛዝ በኩል የሚጠበቅብንን ከማድረግ ወደ ኋላ የማንል መሆናችንን ቤት ቆሞ ፀሐይ የመሰከረው እውነት ነው፡፡ እያደር ከበፊቱም በባሰ የኤርሚያስ እና የህሌና አመለካከት በኛ ላይ ተቀይሯል፡፡ ያልተቀየረ እና ያልተለወጠ ነገራቸው ከሄድን በኋላ ያዳበሩት የጋራ የውርጅብኝ ስድባቸው ነበር፡፡

ነግር ግን ምን አለበት ይህንን እንደ ጥሩ ነገር አዳብረው ከሚጠብቁን ለተሻለ ማንነት የሚያበቃቸውን መልካምነት ወርሰው ቢጠብቁን መልካም በሆነ፡፡ ህሌና እዚህ ጋር ሁሌም ጥፋት ትሰራለች፡፡ እሱም ምንም የማያውቁ ምስኪን እንቦቃቅላ ታናናሾቻችንን ከጎኗ አሰልፋ በነገር መርፌ ቆስሎ ያረገዘውን ቁስል እንዲብስ ታወጋጋለች፡፡ ሥርዓት ለማስያዝ እኔ አላዛር ብንነካቸው ጮኸው ሰፈር ይያዝልን ሲሉ ሳናበላቸው፤ ሳናጠጣቸው አባት እናት አይደለን፡፡ ለምንስ ካልሆናችሁ በሚል

የትዕቢት ንግግር ዐይናችን ቀና ብሎ ማየት እስኪያቅተን እየተንቀጠቀጥን ካላፈራው ቤቱ ምሳ፤ ቁርስ እና ራት ሆኖልን ውለን እናድራለን፡፡

ህሌና ነሐሴ ስላሴ ሁሌም ደ/ኤባ ትሄዳለች፡፡ ስትሄድ ታድያ ኤልያስን ወይም እኛን አስከትላ አይደለም፡፡ በዛ ላይ እኛ ከቤት ያላገኘነውን ማዕድ ባገልግል በሽኖ-ለጋ የአትክልት ቅቤ ከሽና ትሄዳለች፡፡ እውነቱ ከደብረ ኤባ ብዙ ዘመዶች ቢኖሩንም በውል አውቀን የሚኬድበት ዘመድ ያለ ግን አይመስለኝም እና እሷ ግን ለበረከት በሚመስል ዲስኩር ይዛ ትሄዳለች፡፡ ታድያ ዘንድሮ ጉዞ ብታደርግም ቀኑን ውላ ማታውን አድራ በማግስቱ መጣች፡፡ የማያርፈው አፏ እኛንም የመናቅ ሆኖ ከሌላ ሰው ጋር ስጋ እና ቢራ በልታ ጠጥታ አድራ እንደመጣች ታወጋን ጀመር፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ የራስ ያልነበር ነገር እንደ ራስ አድርገህ ብትነግረው ሊወሽክትህ ወይም ሊቆጣ ቢሻ እንጂ መስሚያ ጆሮው ተደፍኖ መች የራሱ ያደርግህ እና!! በማንስ ፍቃድ በማንነት ላይ ማንም ላይፈርድ ሆኖ ነገሩ በግልፅ ይፋ ወጣ፡፡

ታድያ በዚህ ጊዜ የተለያዩ አማራጮችን ብፈልግም ላይሳካልኝ ስለቻለ ከማዘን ውጪ ሌላ ምንም መፍትሄ አልነበረኝም፡፡ በ’ርግጥ በዚህ ወቅት ወርልድ-ቪዥንኢትዮጲያ የለገሰኝ ስጦታዎች በእንክብካቤ ጉድለት እና የኔ ነውነት ስሜት እጦት ለሞት አንድ ረብዕ ቀርቷቸው ነበር እና እነሱን ለማንሳት አንዱን ገሎ ሌላውን ማዳን እንዲሉ አድካሚውን ሥራ በመሥራት እታትር ነበር፡፡ ነገር ግን ይባስ ብሎ የቤተሰብ ጥላቻ እየጠነከረብኝ መጥቶ እንዳልቆም መሬት ከድቶ እንዳልተኛ መኝታው እሾህ ሆኖ ትልቁ ችግር በላዬ ላይ እሳተ ጎመራውን ይተፋ ጀመር፡፡

• * *

‹‹ተው ቻለው ሆዴ›› እንደሚሉት ሆኖ ጥቅምት ጠብቶ የሥራ ማስታወቂያ ያኔ በልጅነት ከተማርኩበት ት/ቤት መግቢያ በር ላይ ተለጥፎ አገኘሁት፡፡ እናም የሚያስፈልገው ዶክመንት እኔ ጋር ስለነበረ ከነማመልከቻው ለሚመለከተው አካል ገቢ አደረኩ፡፡ የመጀመሪያው የሥራ ማስታወቂያ የቤተ መፀሐፍት ኃላፊ የሚል ሲሆን በማይለየው የፆታ ምድብ የሚያሳትፍ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ሕጻናትን ከዋና መምህራኖች ጋር በመሆን የማመቻቸት ሥራ የሚያሰራ ሲሆን ቢቻል ሴቶችን የሚያበረታታ መሆኑን ይገልፃል፡፡

ታድያ በራሱ ፍቃድ ያሻውን ሰው እንዲያመጣ የተመሳጠረው የከተማው ነዋሪ ቢን ‹‹በወመህ›› ከዛው ይሰራ ስለነበር የተለያዩ የሰፈሩን ልጆች ለማሳተፍ ቢሞክርም በፍቃዳቸው ሳይሳካለት ቀርቶ ለቤተ መፅሐፍቱ የጓደኛውን ባለቤት ከስምንተኛ ክፍል ት/ቷ ከተለየች ዘመናቶችን ያስቆጠረች እማ-ወራ ለቤተ መፅሐፍቱ የጥያቄውን መልስ በመንገር ከሌላ የፐሪንሲፐል ማሚያ ተወዳዳሪዎች ጋር አሳተፏት፤ ዐይኔ እያየ በፊታቸው መሐይም እየሸለለ ገብቶ በራሳቸው ብቃት በውጤትም በልጠው እሷ ግን አለፈች፡፡ ውስጤ ከሚገባው በላይ በንዴት በግኗል፡፡ ምክንያቱም በዛ ውድድር ላይ በዐይኔ ያየሁትን ማስታወቂያ ቀደው ‹‹ፆታ አይለይም፡፡›› ያሉትን ሥራ ‹‹ሴት ብቻ›› በሚለው ተክተውታል፡፡

ቢን ማለት በማህበረሰቡ ከበሬታ እና ተቀባይነት ያለው ዲያቆን ሰባኪም ጭምር ነው፡፡ በ’ርግጥ ይሄንን ችግር ይፋ ላድርግ ብል የምጎዳው እኔው ነኝ፡፡ ካልሆነ ደግሞ ከሱ በበለጠ እኔን የሚሰማኝ የለም፡፡ በዚህ ሥራ ብቻ ያላቆመው የቢን እና ዳይሬክተሩ አፀያፊ ተግባር እስከ መጨረሻ ያለምንም ይሉኝታ ቀጥሏል፡፡ ሁለተኛው ውድድር በትዕዛዝ ቀጠለ፡፡ ትዕዛዙ እንዲህ የሚል ነበር ‹‹ያው ስራው አሁንም ቢሆን በትልቁን ቦታ ወስዶ ተሳታፊ የሚያደርገው ሴቶችን ነው፡፡ ስለሆነም ወንዶች ከሴቶቹ ውጤት በሀምሳ ፐርሰንት መብለጥ እና ማሸነፍ ካልቻሉ ለሥራው ተሳታፊ መሆን አይችሉም፡፡›› የሚል ነበር፡፡ ይታያችሁ ፈተናውን ሳልፈተን ከፈተናው መጀመሪያ ራሴን እንዳሰግድ የተደረገ ሲሆን ቀጣዩ ግን በመረበሽ የተሰጠኝን ፈተና በአግበባቡ እንዳልሠራ የተደረገ ቅድመ ማደናቀፊያ ነበር፡፡

ይግረማችሁ!!! ፈተናው ሥርዓቱን እና ደንቡን ተከትሎ የተዘጋጀ አለመሆኑ 'ርግጥ ቢሆንም ተወዳዳሪዎች ፈተናውን ስንጨርስ የአካውንት ምሩቅ የሒሳናት መምህርት ውጤቱን ልታርም ከባልደረባዋ የጂኦግራፊ መምህርት ጋር መጣች፡፡ ተመልከቱ አንደኛ ሁለቱም የሒሳናት አያያዝ ስልጠና ያልወሰዱ ብቃቱም የሌላቸው ናቸው፡፡ ሁለተኛ ፈተናቸው በሚመለከተው የሥራ ዘርፍ ላይ የሚያተኩር እስታንዳርዱን ያሟላ አይደለም፡፡ ሶስተኛ የመምህርነት ሥረዓት ያልነበራቸው ናቸው፡፡ ት/ቤቱ በቁሙ ሞቶ ካልሆነ በስተቀር ሊኖር ስለሚችል ማጣራት የእናንተ አንባብያውያን ፋንታ ሆኖ ተወዳዳሪዎቼን በስልሳ ፐርሰንት በልጬ ፈተናውን በድል አጠናቀኩ፡፡

ነገሩ ግን ጥርስ የነከሰ አውሬ የከፈተበትን ባለቀን እንሰሳ ሳይበላው ላይመለስ ሆኖ እኔም እስከመጨረሻው ሁነቱን ልከተለው ራሴን ሳላቦዝን የሚያደርጉትን ለማየት ጊዜ ሰጥቼ መጠበቅ ጀመርኩ፡፡ በዚህ ጊዜ ከተወዳዳሪዎች አንዷ የሆነችውን የቤት አከራያቸውን ልጅ ሥራዓት የጎደላቸው ያልኳችሁ መምህራን ‹‹ምነው ያን ሁሉ ነግረንሽ!›› ሲሉ ያለምንም ህሌና ቢስነት ከአጠገቤ አቁመው ያፋጥጧት ጀመሩ፡፡ ይህን አጀብ ብዬ ሳላበቃ ከቢሮ ተጠርተን በቢን እንዲህ ዓይነት የማስተዛዘኛ መልዕክት ተስወነጨፈ ‹‹እኛ የምንፈልገው ሴት ነው፡፡ በዛ ላይ ከሒሳናት ጋር ስለምትውል ዐይኑ-ምድራቸውንም ልታፀዳ፤ ንፍጣቸውንም ልትጠርግ የምትችል አይመስለኝም!›› ምላሼ የኽልህ ስልነበር ‹‹ከሰው ተፈጥሬ እንዴታ በደንብ እችላለሁ፡፡ አቶ ቢን›› የውስጥ ንዴቱ ከላይ እንደ ፈላ ቡና ሲገነፍል ይታይ ነበር እና በአቋሜ ፀናሁ፡፡

በዚህ ጊዜ ያከራያቸው ልጅ ተጠርታ ሀሳብ እንድትሰጥ ብትጠየቅ እንደማትፈልገው እና ውጤቱን ያገኘው ሰው መስራት እንዳለበት ጭራሽ ጠበቃ ሆናኝ ለኔው ትከራከር ጀመር፡፡ አልሆን ያለው ቢን ግን አግባብቶ አሸናፊ ሊያደርጋት ቢፈልግም ከጅምሩ እሷም ሥራውን ሳትፈልገው ከሱ ምላሽ ሳትጠብቅ ቢሮውን ለቃ ሄደች፡፡

እኔም የመጨረሻውን የክፋታቸውን ቅዳሴ አይቼ ድምዳሜያቸውን ስላገኘሁ ‹‹አቶ ቢን ከዳይሬክተራችሁ ጋር በትርፍ ሰዓታችሁ እየተባበራችሁ በዚህ ሥራ ላይ ራሳችሁን ጨምራችሁ ብትሰሩት የተሻ ነው፡፡›› ብዬ ላፍታ ሳላናግራቸው ግቢውን ጥዬ ወጣሁ፡፡

እውነት ነው ‹‹ባለቤቱን ካልናቁ ለካስ አጥሩን አይነቀንቁት›› የሆነው፡፡ የዚህ ሁሉ መዘዝ መነሻው ራሱን በየቀኑ የሚያዋርደው የህሌና ማንነት እና የኤርሚያስ ወልማጣነት ነበር፡፡ ሰው ሰርቶ በፍቅር ካልተቋደሰው፤ 'ርስ በራስ ተከባብሮ ከመናናቅ ወጥቶ ራሱን አክብሮ እስካላስከበረ ማን የጣለውን ማን ማን ሊያነሳው ይሆን?! ሀቁ ያለቀኑ የተፈጠረን ዜጋ ደቁሶ ሊገል ካልሆነ በስተቀር ማንም ነው፡፡ ታድያ በመጨረሻም መላ ያጣው የቢን ቡድን ከቤሰብ ድረስ አሽከር የሆኑትን ተላላከኪ፤ ያለሞያቸው የገቡ ሞዋርተኞች ላከብኝ፡፡ አሻፈረኝ ብል ህሌና እንደሁ ማን ሆና ሆኖ ነገሩ በብዙ ግልምጫ እና ስድብ ሳልወድ በግድ ወርደት በኔ አይጀመር ሆኖ ወደ ሥራው አመራሁ፡፡

ገራሚ!! አመቻች የተባለው ሰው አሁንም ያለምንም ስልጠናና ሞያዊ ብቃት ተማሪዎችን ከሌሎቹ የሥራው ባልደረቦች እኩል መስራት ግዴታው ሆኖ ክፍያው ግን ሰማይ ከምድር ሆነ፡፡ በዚሁ የተገፋ የቀን ተቀን ውሎ ሥራውን ያለምንም ስልጠና እየጫነ ቢመጣም የቻለውን ከመሥራት ሳይታቀብ ከት/ቢሮ የሥራውን ሁነት የሚመለከት አካል ብቅ አለ፡፡ ለየብቻ በትነን ስናስጠናቸው የነበሩትን ሒሳናት ተማሪዎች በሁለቱ ባለሞያዎች ስር ተይዘው እኔ ግን ከክፍል ክፍል እየዞሩ የአመቻች ሥራ ከዋኝ ተዋናይ ሆኜ አረፍኩት፡፡

በጣም አደገኛ እና መጥፎ ሥራ ነበር እና ነገሩ በጣም ውስጤን አስቆጣኝ፡፡ በዛ ላይ ከቤተሰብ ተለይቼ ራሴን ለማውጣት እያጣርኩ የነበረበት ወቅት ቢሆንም ህሌና ይንን አግዞ ለመርዳት ምንም ቅን እና መልካም አመለካከት የነበራት ስላልነበረች ሌላኛው በሽታ ተደማምሮ ቀጣይ ዓመት ደርሶ ስልጠናውን እስክወስድ ውስጤ ሽፍቶ እጅጉን ቸኩዬ ነበር፡፡ ነገር ግን የቤተሰብ የማይረባ ጫና በላዬ ላይ ምራኑን በጥሶ ችግር መፍጠሩን ተካነበት፡፡

ይህንን ሥራ ሥሰራ ከናስቶሲን ጋር አንዳንዴ ስለምንገናኝ በስልኩ አንዳንድ የበየነ-መረብ አገልግሎቶችን መጠቀም ጀመርኩ፡፡ በዚህ ጊዜ እሱም ሌላ ስልክ ስለነበረው ለጊዜው እንድጠቀመው ሰጠኝ፡፡ ታድያ እኔም ገንዘብ አጠረቃቅሜ የራሴን ስልክ ገዝቼ የበየነ-መረብ አገልግሎቴን ከቀን ቀን እያሰፋሁ መጠቀም የግሌ ሆነ፡፡ ሙዚቃም ከበፊት ጀምሮ በጣም እወድ ስለነበረ ሲያሻኝ ከሬድዮ ካልሆንም በብሉቱዝ ቀድቼ እያሳለፍኩ አዳምጣለሁ፡፡

ታድያ በዚህ መሐል አንደኛው ከሆነው የፌስ-ቡክ በየነ-መረብ ስገባ በሌላ ሰው ሥም የተከፈተ ነገር ግን የኒካውላ ፎቶ የተለጠፈበት ገፅ አየሁ፡፡ ፎቶዋ ትንሽ እሷ ስለመሆኗ ያጠራጥራል፡፡ ያ! ሙሉ ሰውነቷ በሙሉ ተመጧል፤ ውብ ፊቷም ቢሆን ወዘናው ጠፍቶ አመድ ሆኗል፡፡ ብቻ ሰላም እንዳልነበረች በደንብ ያስታውቅ ነበር፡፡ አላናግራት ነገር የተለያየነው ተኮራርፈን ስለነበር ከሌላ ሰው ጋር እያወሩ በየቀኑ ገፁዋን ከማየት ውጪ ሰላምታም ይሁን ሌላ ምልልሶችን ለማድረግ አልደፈርኩም፡፡

ያች በጋ እንደምንም አልፋ እንደሌሎቹ የክረምት ደሞዝ ክፍያ ስላልነበረው ሥራውን ለቅቄ የነበረኝን ነገር ግን ቤተሰብ እንደ ሸንኮራ መጠ የጣላትን ላም እስከነ ጥጃዋ ይዜ ከአባባ ጥበቡ በገዛሁት ግጦሽ መሬት ላይ ሳበላላ ከርሜ ሰውነት አበጅታ ስትሄድ በጋውን ወደ ቤት ተመልሼ ገንዘብ ስላልነበረኝ ት/ት ለመጀመር ብጣጣርም የህሌና ደካማ ወቀሳ ተጨምሮበት ሳይሳካ ወራቶች ነጉደው በብስጭት ራሴን መጉዳት ጀመርኩ፡፡ ያፈሩት ቢኖር ላይሰጡኝ አስቀድሜ ከቤት ስለወጣሁ ጨክነው ዝምታቸው ነገሰብኝ፡፡ ታድያ በዚህ ከጎረቤቶቼ እየተመላለስኩ ቤት ያፈራውን መስራት መቋደስ ብችልም ነገሩ በዚህ ሳይቀጥል ቀርቶ ‹‹ደካማ ሰው የአህያ ርቢ ይወስዳል›› እንዲሉ ሆኖ ለቤተሰብ ካልተመለሰው፤ ሥራቸውን ነቅሎ መቆሚያ ካሳጣው የዊዝ ደም የብድር ገንዘብ በአባቴ ኤርሚያስ አማካኝነት ተጠናወትነው፡፡

ባንኩ የኢንሹራንስ ክፍያ እና አንዳንድ መዋጮዎችን ጨምሮ ከስድስት ሺህ ብር በእጃችን የደረሰው አራት ሺህ ብር ገደማ ነበር፡፡ በዚህ ላይ በየወሩ ከመቶ ሃያ ብር በላይ ወለድ ያለው ሲሆን ከወሩ ካለፈ ከመቶ እና ከዛ በላይ የወለድ ቅጣት ነበረው፡፡ እግሮቼም ሳይደክሙ የሶስት ሰዓት መንገድ ሄደው እየተመለሱ ለመነገድ ቢታደሉም፡፡ ከ*ባት እና ከ*ናት ኪስ ያልወጣው ገንዘብ ግን መዳረሻው አይታወቅም ነበር፡፡

በመጨረሻም ከግብርናው ከአባባ ጥበቡ የጋራ ወስጄ ሸንኩርት ብዘራም እጅ ከዶማ ተዋዶ ወገብ እየረገደ ለወራቶች ደክሞ ነገሩ ያልተሳካለት ሆኖ በትል ተበላ፡፡ መጀመሪያው ያላማረው ብድር መጨረሻውም እንደዛው ሆኖ የነበረውን ድምጥማጡን እያጠፋ ይዞ ሄደ፡፡ በዚህ ቤተሰብ ውስጡ የረካ ቢመስል እንጂ ምንም የመቆርቆር ስሜት አልነበረውም እና በትምክት የሚደረጉ ጥፋቶቻቸውን አምኖ ላለመቀበል በምታትርበት ወቅት ህሌና ከቤት ለቅቄ መሄድ ወዳለብኝ ቦታ እንድሄድ ማስጠንቀቂያ ሰጠችኝ፡፡

የምፈልገውም የምጠብቀውም ይሄንኑ ስለነበር ምንም አማራጭ ሳይኖረኝ ቀርቶ ከአጎቴ ልጅ ኋሉ ጋር ለመሄድ ተገደድኩ፡፡ ኋሉ ማለት ሲበዛ ቀልደኛ እና ነገሮችን ቆራርጦ እየቀጠለ ሲያስቅህ የሚውል ደስተኛ ዓይነት ልጅ ነው፡፡ ሥራው የቤተሰቡን ወፍጮ ቤት መቆጣጠር እና መስራት ነው፡፡ ት/ቱንም የተወው ይህንኑ ሥራ አያቱ በአደራ እንዲይዝለት ስላስገደዱት ነበር፡፡

በወቅቱ አዲስ ያሠራውን ቤት እያሳደሰው ስለነበር የሚተኛበት ቤት ከወፍጮ ጎን በተሠራች ጎጆ ቤት ነበር፡፡ እናም ምሽት ደርሶ ለመተኛት ስንገባ ውስጧ በዱቄት እና በአሰር ኮስኳሽ ቡናኝ ተሞልቶ እናገኘዋለን፡፡ አፀዳድተን ማግስቱን ያው ነው፡፡ ምግብ ከቤተሰብ እያስመጣ ለጥቂት ወራት ከዛው ስንጠቀም ብንሰነብትም አዲሱ ቤት ከሳምንታቶች በኋላ ታድሶ ገባን፡፡ የመጥጥ ሥራ ለጊዜው ቢጀምርም ብዙም ስላላዋጣው ትቶት የቀድሞ ሥራውን አጠናክሮ መሥራቱን ቀጥሎበታል፡፡

እኔም ቀን ቀን ቁጭ ብዬ ከቤት ከአንዳንድ ቦታ አምጥቶ የጣላቸውን መፀሐፎች ሳነብ ውዬ ማታ ማታ ባስ ሲለኝ ለንግድ ገስቶት የነበረውን ጂፓስ ከፍቼ ለብቻዬ ሳዳምጥ አመሻለሁ፡፡ ኋሉ

አንዳንዴ ውጪ ከጓደኞቹ ጋር ስለሚቆይ እስከ መምጫው ድረስ ጂፓሱ ሲጮኽ ይቆየው እና ዘጋግቶ እንቅልፍ እንደያዘኝ ሲያውቅ ላለመረበሽ ቀስ ብሎ ከውስጥ ገብቶ ይተኛል፡፡

ታድያ ማግስቱን ስንነቃ ካጠገባችን ካለች ሻይ ቤት ሻይ ብስኩት እንል እና ከቤተሰብ ምሳ ለመብላት አወላላውን ሥፍራ በለምለሙ ሜዳ አድርገን ራሳችንን እያዝናን አልፈን ከደጃቸው እንደርሳለን፡፡ በአንድ የቀን እለት የጀመረው ጉዟችን ዘወትር ቀጥሎ በኤርሚያስ ውትወታ ወደ ቤት ተመለስኩ፡፡ ነግር ግን የመማር አላማዬ እንዲጨናገፍ በተለያዩ አካላቶች ቢሞክሩም ሳይሳካላቸው ቀርቶ ለአያቴ እትዬ አበባ አማክሬ ከነሱ ጋር የነበረች ጥጃ ሽጬ እንድማር እንድታግዘኝ ለመንኳት፡፡ እሷም በሀሳቤ ተስማምታ ያላትን ካገኘችት ቀንጥራ ልትልክልኝ ቃል ገብታ በጠዋት ጥጃዋን አብልታ አ/ጠ እንድሸጥ ላከችኝ፡፡

ከገበያ ገብቼ ገና ከመቆሜ ህሌና ኤርሚያስን እና ወንድሞቹን ይዛ መጣች፡፡ መልዕክቱ በ'ርግጥ የደረሳት ከእትዬ አበባ ሲሆን አላማው መንጋው ያለዋጋ እንዳይሸጥ እንዲያግዙ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል፡፡ ህሌና አባቷ ጥበቡ እስክንድርን አሳብደው ከሀገር እንዳወጡት እኔንም ለማድረግ በሚመስል መልኩ ‹‹እዩ!! ተመልከቱቱ ዘመድ ወዳጆቹ ከቤት ዘርፎ ሀብት እና ንብረቴን ሲሸጥ!›› እያለች እማኝ ታሳይ ጀመር፡፡ ንብረትነቱ ወርልድ-ቪዥን አስመፅውቶ የሰጠኝ የኔ ታድያ ህሌና የሷን ንብረት ብወስድ ምን ልታደርገኝ ይሆን?! ብቻ ነገርን በአህያ ላልጭነው አላንዛዛው እና ‹‹ከዚህ በኋላ መግቢያህን ፈልግ!! የቀረህ የሬሳ ማውጫህ አንድ ወይፈን ነው፡፡ እሱም በሰዓቱ ይሆናል፡፡›› ብላ እየደነፋች ይዛቸው ከመጣቻቸው ጀሌ አጎቶቼ ጋር ተያይዛ ሄደች፡፡

ታድያ ውስጤ ነዶት እንባ እያቃተተኝ ስለነበር የያዝኳትን ጥጃ ከተገዛችበት ስድስት መቶ ብር በመወረድ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር የመጀመሪያ ጠያቂ ሳገኝ ሽጬ ወጣሁ፡፡ ጥጇዋን በሌላ ያስገዛቻት እራሷ ህሌና ነበረች፡፡ በርቀት ሆኜ ከገበያው አቅራቢያ ሳይ ከገዢው ጋር ተመሰጋግነው በሌላ ሰው አስነድተው ሲዱ አየሁ፡፡

እኔም ጉዞዬ ወደ ደብረ-ኤባ ሆኖ አጎቴ ነጋድረስን በስልኬ አነጋግሬ ልገናኘው ብፈልግም እሱ ከዛ ሳይኖር ቀርቶ የምሄድበት ጠፍቶኝ የማደርገው ቢታጣኝ አልጋ ይዤ እዛው ደብረ-ኤባ ከከተማው አደርኩ፡፡ ፍላጎቴ ት/ት እና ራሱ አውቆ መገኘት ብቻ ነው፡፡ ከዛ የዘለሉ አማራጮች ከዚህ በፊት እልህ አስጨራሽ በሆኑ መልኩ ለመጠቀም ብሞክርም የተመቻቸ እና የተስተካከለ ነገር ሊገጥመኝ አልቻለም፡፡

የነጋድረስ ከዛ አለመኖር ውስጤን አስጨንቆት ለሊቱን ሲያባንነኝ አድሯል፡፡ ይሁን እንጂ ለራሴ እንዲህ ስል ራሴን ሰበኩት ‹‹አንተ ከሌላው የተለየም ሆነ የበለጠ ነገር የለህም አብኔ በዚች 'ምድር ላይ ሰው ሁሌም በሰው ፍቃድ እና ምርኩዝ መኖር አይቻለውም፡፡ መውደቅም ካለበት ራሱን ችሎ ዓለምን ጥሏት እንደሚሄድ ሁሉ በመነሳቱም ጊዜ ራሱን ለራሱ ደግፎ ሊቆም ይገባዋል፡፡ ካልሆነ ግን እመነኝ አብኔ አንተ በወደክ ቁጥር ከንፈር መጦ በግልምጫው ዱዲት ሳንቲም እየደለለ ከማኖር ውጪ ሌላው ስላንተ ተጨንቆ አንተን አያቀናም፡፡ ኦፐ.. አንድ ብለህ አሳየኛ?! … አብኔ ጠንክራ!!…..››

ራሴ ልላ ሰው እሲኪመስለኝ በደንብ አናገርኩት፡፡ ጠዋት ላይ ካንድ ሻይ ቤት ገብቼ ቁርሴን እንደነገሩ ቀማምሼ ቀበሌ 07 ከሚባለው ሥፍራ ቤት መፈለጉን ተያያዝኩት፡፡ ከብዙ ልፋት እና ድካም በኋላ በሁለት መቶ ብር ከውጪ በቆርቆሮ የተመታ ከውስጥ በማዳበሪያ ተጠርዞ የመሬቱ ወለል ግን ድልድል እና መስተካከል የቀረው ቤት አገኘሁ፡፡

ከሰ.መ ከመውጣቴ በፊት እለብሳት የነበረችኝን የተበጣጠሰች ብርድ-ልብስ፤ ፎጣ፤ ቡታጋዝ እና ብረት ዲስት ይዤ ነበር፡፡ መኝታ ከበፊቱኑ ከሜዳ ታጭዶ በተዘጋጀ የሳር ፍራሽ ሲሆን እሱን ይዞ ለመሄድ አንድም ውስጡ ደቆ ተባይ የሰራ ሲሆን ሁለትም በርካታ ስለነበር ለትራንስፖርትም አስቸጋሪ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አመሻሽ ላይን ያዝ አድርጎ የመኝታ ሰዓት እየደረሰ ስለነበር በአቅራቢያው ከሚገኝ ሱቅ ጥቂት ካርቶኖች ገዝቼ ውሃ ቋጥሮ ብርዱ በሚያንዘፈዝፈው መሬት ላይ ጋደም አልኩ፡፡

እንቅልፍ ይዞኝ ካሳብ ጭንቀት ትንሽ አረፍ ለማለት ብሻ ያ'ከባቢው አደገኛ ብርድ ተጨምሮ ሲቱን የሲኦል ደጅ አድርጎ አንድም ሲያሳየኝ ሁለትም ሲያስቃየኝ አደረ፡፡ አለምደው ነገር ቀን ቀንን እየወለደ ሲሄድ ግድ ሆኖ መላመዴ 'ርግጥ ሆነ፡፡

የመጀመሪያ ሥራዬ የት/ት አካዳሚዎችን በያሉበት ፈልጎ ማግኘት ነበር፡፡ ቀጥሎም እያንዳንዱን ት/ት ቤት የነፃ የት/ት ዕድሎች ካሏቸው አፈላልጎ መወዳደር ሲሆን ሶስተኛው ሌላ አማራጮችን በመጠቀም ለመማር ቆርጦ መነሳት የሚሉት ናቸው፡፡ ታድያ በእቅድ የጀመረው ዓላማ ከግቡ ሊደርስ የግድ ጥረት እና ድካምን ይጠይቅ ሆኖ በፍለጋ ከእያንዳንዱ ቀበሌ አንዳንዴ በእግሬ ራቅ ሲል ደግሞ በባጃጅ አንዳንዴም በመኪና መዳሰሴን ተካንኩበት፡፡

ከዛው ከ07ስጀምር የግል የሆነውን የቪክትሪን ኮሌጅ አገኘሁ፡፡ የመጀመሪያዎቹን ሁለት አማራጮች ልጠቀም ብሞክር ስላልተሳኩልኝ ፍለጋዬ ቀጥሎ ደብረ-ኤባ ጤና ሳይንስ ኮሌጂ አቀናሁ፡፡ ነገር ግን እንኳን በግቢው በሥራቸው ላያ ያላገኘኋቸው የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ቀናቶችን አመላልሰው መገኘታቸው በመጨረሻው ተሳክቶ እውን ቢሆንም ያነሰ እና ዘምድና ወይም ገንዘብ ያልነበረውን ሰው ማስተናገድ ኃፅያት ሆኖ ሰበብ እና የትዕቢት ትምክት እያሳዩ እኔም በሜዳ ቀርቼ ላይሳካ ነገር መቋጫው ፍላጎታቸው ሆነ፡፡

የዓላማና የህይወት ነገር ሆኖ ላለመውደቅ ለመነሳት ደክሞ ቢያሰለቸኝም ፍለጋዬን ግን ሳላቋርጥ ሁለት ሳምንታት ነጎዱ፡፡ ከሬፊት ቫሊ ውጪ በርከት ያሉ ኮሌጆች በደብረ-ኤባ ባይኖሩም ያሉትን ጠይቄ ለማጣራት ጥረት ባደርግም ቢዝነሳቸውን የሚያጧጡፉ ኮሌጆች ቅበላቸው መልካም ሆኖ ልምምጥ ቢታጀልበትም ክፍያቸው በሴሚስተር ሆኖ እየናረ ከአቅሜ በላይ ሆኖ ተውኳቸው፡፡

ታድያ የነበረኝ አንድ እና የመጨረሻ አማራጭ ከቪክትሪ ኮሌጂ በህክምና ሞያ ወርሃዊ ክፍያ ከፍዬ መማርን የግዴታ ምርጫዬ አደረኩ፡፡ በእጄ ላይ የነበረች ገንዘብ ለምግብ፤ ለቤት ክራይ ስላት ወደ አራት መቶ ገደማ ደርሳለች፡፡ እኔም ከዛችው ላይ የመመዝገቢያ ሀምሳ ብር ከፍዬ የሚጀመረውን ት/ት በጉጉት መጠበቅ ብጀምርም ይህኛው ት/ቤትም እንደሌሎቹ ካንፓሶች ከተቻለ የግማሽ ሴሚስተር ካልሆነ እና ካልተቻለ ግን የሁለት ወር ማስከፈል እንዳለባቸው በማስታወቂያቸው ት/ት ከመጀመሩ ሶስት ቀን በፊት አሳወቁ፡፡

በጣም የሚያሳዝን ነበር፡፡ ለዛ የሚሆን ክፍያ በጄ ላይ አልነበረም፡፡ የተገኘውን ሥራ ሰርቼ ለመማር ቁርጠኛ ብሆንም የሥራውም ሁኔታ ከህዝቡ ብዛት እና እንግልት አንፃር አስፈሪ እና አስጊ ነበር፡፡በ'ርግጥ የኮሌጁ ባለቤት የሆኑትን ዶክተር ፈልጌ አፈላልጌ ብጠይቃቸው እነሱም ከዛው ስላደጉ ችግርን ሳይቀምሱት አላለፉም እና መሳካቱ እሙን ነበር፡፡ ነገር ግን ውስጤ በክፍያው እና በነገው የህይወት ኑሮ ባክኖ ምንም ሳይፈይድ የክፍያውም ቀን አልፎ ት/ት ተጀመረ፡፡

ከሁለት የተበደለ ሰው በመንታ መንገድ ላይ ሁሌም ሲንከራተት አደገኛ አውሬ ያጋጥመዋል፡፡ ያውም ስጋን ብቻ ሳይሆን ነብስያን በጣጥሎ የሚገነጣጥል፡፡ የፍራቻ እና የማያባራው የመከፋት ለቅሶ የሆነው መራሩ ሕይወት ነው፡፡

በዚህ ጊዜ ከበረራ የተሻለ ቢሆን ብዬ ለነጋድረስ ደውዬ ካለበት ደረስኩ፡፡ ነገር ግን የበረራን ኑሮ ቀድሞ ስለሚያውቅ የተለያዩ አማራጮችን እንድጠቀም ምሽቱን በምክር ዘልቀን እኩለ ለሊት ላይ ጋደም ብለን ሳስብበት አደርኩ፡፡ ጠዋት ማለዳ ከመስኮቱ በስተ-ምዕራብ በኩል ወፎች ሲንጫጩ ከእንቅልፌ ነቅቼ ከተኛሁበት በዐይኖቼ ነጋድረስን ካልጋው ብፈልገው አጣሁት፡፡ ታድያ በዚህ ጊዜ የዘወትር ሥራው አትሌቲክስ ስለነበር ብዙም አልተረበሽኩም ነበር፡፡

ካላጋው ላይ ፈንጠር ብዬ እየተነሳሁ ከሽንት ቤት መውጫው መንገድ ጠፍቶኝ ግቢውን ስቃኝ ሰውነቱ በላብ ተጠምቆ ልብሱ ላብ ላብ እያለ አጠገቤ ደረሰ፡፡ ‹‹ለምን ተነሳህ ትንሽ አትተኛም ነበር!!›› ሲል በቁጣ መልክ እንድተኛ ፈለገ፡፡ እኔ ግን አሻፈረኝ ብዬ ለሰውነቱ መታጠቢያ እንዲሆን ውሃ በባሊ

ባመጣለት ማምጣት እንደሌለብኝ ማሰብ በሆነ አመለካከት ዳግም ተቆጣኝ። እኔ ግን ከዛም ከዚህም እያልኩ ለመሯሯጥ ብሞክር መቀመጫ ዱካ ከቤት አውጥቶ ተቀምጬ ፀሐይ እንድሞቅ አስጠነቀቀኝ።

እኔም ቁጭ ብዬ በአስተጣጠቡ እና በቅልጥፍናው እየተደመምኩ ሳለሁ ልብሶቼን አውልቄ እንድሰጠው ጠየቀኝ አመል ሆኖ ብግደረደርም የልብሴ ጠረን ጥሩ ሳይሆን ቀርቶ እራሴ ለማጠብ ባወልቀውም ሳይሆን ቀርቶ ራሱ አጥቦ አሰጣልኝ። የሥራ ሰዓት ረፋፍዶበት ስለነበር አዳዲስ ልብሶቹን አልብሶኝ ከሲፓራ ሽሮ ቤት ይዞኝ ሄደ።

ነጋድረስ ከበር ከመግባቱ ሲፓራ እና እህቷ ከመላ ሠራተኞቹ ጋር ‹‹እስኬ የጠፋ ሰው›› እያሉ ናፍቆት በሚመስል መልኩ ካንገቱ እየተጠመጠሙ ሳላምታው ጦፈ። ወድያው ምግብ ታዞ ሳቁ እየቀለጠ ጨዋታው ደራ። እስኬ ከሚገባው በላይ ይወደኝም ስለነበር ወንድምነቴን ለመጣው ሁሉ ፊቱ እየፈካ ውስጡ ሀሴት እያደረገ ያስተዋውቅ ነበር። እኔ ግን ከሰላምታ የዘለለ ስቆ መጫወት ልምዴም ባህሪዬም ስላልነበረ እንደ ተለጎመች የጭራ ገረድ በዝምታ መዐበል ውስጥ ዝም ብዬ ከራሴ ጋር አንዴ በደስታው ሌላ ጊዜ በሀዘኑ አወራለሁ።

በዚህ መሐል ምግብ ቀርቦ ቁርሳችንን ከበላን በኋላ እኔን እነ ሲፓራ ጋር እንድጠብቀው ካልሆነ ቦታው ካልጠፋኝ ከቤት ሄጄ አረፍ እንድል ቁልፍ ሰጥቶኝ ሄደ። ትንሽ ለመቀመጥ ፍላጎቴ ቢሆንም ብዙ ደንበኛ እየመጣ ቤት እያጣበብኩ በዛ ላይ ጭንቀት ተደርቦ ስለነበር ከቤት ተነስቼ ወጣሁ። ለጋ-ሲዮን ቦታዋ እፅዋት ዙሪያዋን የከበባት ስለነበረች ውበቷ ያስደምማል። በ'ርግጥ በወቅቱ አደባባዩ እና የውስጥ ለውስጥ መንገዶች እየተሰሩ ነበር።

እኔ ግን ቀልቡ የተሰረቀበት የመንገድ ዳር ጓዘኛ ሆኜ እይታው አታላይ ቢመስለኝም የሚያስጨንቀኝ ነገር ድንገት ብልጭ ብሎ ት/ቤቶችን መፈለግ ተያያዝኩት። በለጋ-ሲዮን አደባባይ ወደ ጉራራ የጀመርኩት ጉዞ በበፊቱ የሓ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ዩንቨርስቲ ኮሌጅ ሲሆን ባሁኑ TURKYE MRIF VAKFI ከሚባል የኮሌጅ ት/ቤት አደረሰኝ። መልካም ሆኖ ከዘብ ጋር ንግግሬ ቢቀጥልም ሳላውቀው ቀርቼ የሀብታም ልጆች የሚማሩበት የውጪ የግል ድርጅት ያቋቋመው ት/ቤት እንደሆነ እና ክፍያው አይደለም ቀን ሥራ ተሰርቶ መኪናም ገልብጦ እንደማይቻል ነገረኝ።

ከዛ በላይ ለሆነ ጉዞ ቦታውም አዲስ ስለነበረ ሊመጡ ይችላሉ ብዬ ካሰብኳቸው የዘረፋ እና ጥቃት ሰለባ መሆንን በመፍራት ተመለስኩ። ቀኑ በዛው የለጋ-ሲዮን መንደር የጉብኝት ጉዞ ተጠናቆ አመሻሽ ላይ ነጋድረስ ከሥራው ተመልሶ ሲመጣ ከሲፓራ ሽሮ ቤት ተገናኝተን ቤት ያፈራውን ተቋድሰን ስንጫወት ቆይተን ወደ ቤት ሄድን።

ማግስቱ ሰንበት ስለነበር አንዳንድ ት/ቤቶችን ስንቃኝ ውለን ምክር እና ሀሳብ በመለዋወጥ ሌላኛው ሰንበት ተገባዶ ከስድስት ኪሎ ወደ አርባ አንድ (እየሱስ) መሄጃ ከሚገኝ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ተመዝግቤ ስመለስ ከአትሌቲክስ አሰልጣኙ ጋር ተገናኝተን ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ነጋድረስ የተሻለውን ሀሳብ እግረ መንገዱን አማከረው። እሱም እንደ አማራጭ ያቀረበው የደብረ-ኤባ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ መሆኑን በመጠቆም ለኔም ቢሆን ለኑሮ ከዛ እንደሚሻል በመመካከር በራስህ ላይ እንጂ በሰው ላይ አትወስን ሆኖ ያለማቅማማት በስምምነታቸው ተስማማሁ።

ታድያ የተከራየሁት ቤት እንዳልተለቀቀ ቢሆንም ከደብረ-ኤባ ተመልሼ ከቤተሰብ የነበረኝ ንብረት በነጋድረስ አማካኝነት በኤርሚያስ ተሸጦ እስኪላክልኝ እጠብቅ ነበር። ቀን በቀን ላይ እየነጋ ሄዶ ነገሮች የበጎ ባይመስሉም ለበጎ ሆነው አምስት መቶ ብር በባንክ ተላከልኝ። ከበረራ ከተመለስኩ ጀምሮ ከቤት የሚላስ የሚቀመስ አልነበረኝም ነበር። ታድያ የተላከችልኝ ብር ማታውን በኢቲኤም አውጥቼ ልጠቀማት ብሻ ያለ ሰዓት ከቦታው ደርሼ ኤቲኤሙ ከማሽኑ ቀረ።

ከማታውቀው ማህበረሰብ ጋር መኖር እስካልተግባባኃቸው ድረስ የባህር ውቅያኖስ ውስጥ ድንጋይ ነህ። ማንም ዞር ብሎ አያይህም አንተም ብትሆን እንደዛው። ቀናቶች አልቀው የቤት ክራይም ደርሶ አንድ ሳምንት አልፏል። በዛ ላይ ይሄንን የተዝለፈለፈ ሰውነት አከራዮች ቢያዩት ምንሊፈጠር

እንደሚችል ባላውቅም ምንም እንዳይሆን በመስጋት ግቢውን አልፌ ከቤት እስክደርስ ሁለት እጆቼን ከኪሴ ሸጉሬ ደረቴን ነፋፍቼ ከገባሁ በኋላ እስትንፋስ እጥሮኝ ካነጠፍኳት ካርቶን ላይ ጋደም አላለሁ፡፡

ሆድ እያከኩ ሌት ቢበረታም መንጋቱ አይቀር ሆኖ ከባንክ ደርሼ አስካወጣ ቸኮልኩ፡፡ የለበስኩት ልብስ ያኔ ለት/ቤት ላመቻችነት መስሪያ ቤት የገዛሁትን ጂንስ ነበር፡፡ የዜሮ ሰባት የንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ብደርስም ሰዓት ሳይደርስ ለካስ በጠዋቱ ሄጄ መጠበቁ አሰለቸኝ፡፡ በዚህ ጊዜ የደከሙ እግሮቼን አስልቼ በበሬሳ ድልድይ ላይ አድርጌ ማዞሪያ ከሚገኘው ንግድ ባንክ ደረስኩ፡፡ ነገር ግን ሰው በአሸኑ ካስፋልቱ በድርበብ ሞልቶ ከመጨረሳው ተሰለፍኩኝ፡፡

ሰዓት ስጠይቅ ለሁለት ሃያ ጉዳይ እንደሆነ ከፊቴ ተሰልፈው የነበሩትን አዛውንት ከእይታቸው ያተረፉትን ነገሩኝ፡፡ ነገር ግን ሰዓቱ እሳቸው እሲኪመስለኝ ኩስትር ብዬ ተመለከትኳቸው፡፡ እሳቸውም አስተያየቴ ብዙም ስላልተመቻቸው ፊታቸውን ወደ ፊት አዙረው ቆሙ፡፡ ከሃያ ደቂቃ በኋላ ያስገቡናል ብለን ብንጠብቅም ‹‹ብር ላስተናጋጅ እስኪበተን ነው፡፡›› የሚል ሌላ ትዕዛዝ መጥቶ ሰልፈኛውን አናጫጫው፡፡ አንዳንዱ ሰልፉን ትቶ ሲሄድ ሌላው ደግሞ ያጉረመርም ጀመር፡፡ በዚህ መሐል ለካስ ከውስጥ እልህ ተጋብተው ሲዝረከረኩ ሁለት ሰዓት ከአርባ ሆኖ ሰልፉ በየተራው መግባት ጀመረ፡፡

ያልፈጠነው መስተንግዷቸው ሰዓታትን እያስቆጠረ ከኔ ፊት ካሉ አዛውንት ሲደርስ ሲስተም ተቋረጠ፡፡ ከጠዋቱ አራት ሰዓት፡፡ የኔቶዎርክ ሲስተም ተስተካክሎ ጀምሮ እኔም አምስት መቶ ብሬን አውጥቼ የሚበላ ነገር ካፌ እስከምል ተንገብግቤ ወጣሁ፡፡

አንድ አጠር ብሎ ጠቆር ያለ፤ ቦርጩ ዘርገፍ ብሎ ሌዘር የለበሰ ጎልማሳ የመስታወት አወራጅ ሠራተኛ እንደሚፈልግ ጠየቀኝ፤ እኔም ካገኘሁ ብጨምርብ ብዬ ደስ ብሎኝ እከተለው ጀመር፡፡ ከመንገዳችን መሐል ላይ ሌላ ጎርመስ ብሎ ልብሱ የተበጣጠለ ወጣት ቆሞ ፀጉሩን ሲያሽ ከኔ ጋር የነበረው ጎልማሳ እሱንም አሳምኖ ተከታትለን ወሬያችንን እየደሰኮርን መንገዳችንን አጧጧፍ ነው፡፡

ወጣቱ ካለባበሱ ስላሳዘነኝ ምክንያቱን ከመጠየቅ አልተቆጠብኩም እና ጥያቄየም በርትቶ አሳዛኝ ምላሹ ጠንክሮ የምንሄድበት ሳይታወቀን ከአንድ ኮረብታማ ደባቃ ቦታ ደረስን፡፡ በ'ርግጥ ብዙ ሰው የሚሄድበት ስለሆነ መንገዱ የሰው ነው፡፡ ታድያ በዚህ መሐል አሠሪያችን ከኮረብታው ቆሞ ቁማር ሲያጫውት ከነበረ ልጅ እግር ወጣት ጋር ቀርቦ ለመጫወት እጁን ከኪሱ አዋዶ በመቶ ብር አስጀመረው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ቢበላም በተከታታይ ሁለቴ ተበላ፡፡ ሶስተኛው ላይ ሲደርስ ያለው አማራጭ ሠራተኞቹን ጠይቆ የሥራ ቦታ መመለስ ስለነበር ለአላቃ ሆኖ ሆዴ ሸፍቶ እየጮኸ በጉልበቴ ከመሬት ተንበርክኬ መቶ ብር ሰጠሁት፡፡

በቁማሩ ተሸነፈ፡፡ ሁለተኛ ደገምኩት፡፡ ዳግም ችሎ አለመቻልን በማስመሰል ሊያሳይ ሲፈልግ ተረታ፡፡ ታድያ በዚህ ቅፅበት ምን ከዚህ ሁሉ ማጥ ውስጥ እንደማስኝ ሳላውቀው ከቁማሩ ገብቼ መቶ ብር ተበላሁ፡፡ የቀረኝ ሁለት መቶ ብር ነው፡፡ ሁለት መቶ ብር እንደሚመለስልኝ ተስፈኛ ብሆንም በመቶ ብሯ መበላት ስለደነገጥኩ ካለሁበት ፈዝዤ ቀረሁ፡፡ በዚህ ጊዜ አልጠግብ ያለው አሠሪያችን ከሥራው ቦታ ከዚህ የበለጠ ብር እንደማገኝ ነግሮ አበረታታኝ፡፡

ሌላኛው ተስፋ መጥቶ እንዲያስመልስልኝ መቶ ብር ከኪሴ አውጥቼ ሰጠሁት፡፡ ነገር ግን ተወናውን የተካነበት አሰሪዬ በቁማሩ ተረታ፡፡ እኔም ከመሬት ያረፉ ጉልበቶቼ ቀንተው እየቆሙ ሰውነቴ በላብ ተጠመቀ፡፡ አሰሪዬ ግን ውትወታው ቀጥሎ የመጨረሻዋ መቶ ብር በእሱ እጅ ተይዛ ላምስተኛ ጊዜ ሲረታ የማስተማመኛ እና የማስተዛዘኛ ቁመራውን በራሱ የተሰባበረች የበተን ስልክ ላይ አደረገ፡፡ ለስድስተኛ ጊዜ ተረታ፡፡

እኔ ግን አጫዋቹን እጆቼ ሊፋቱት አልችል ብለው ከሰውነቱ ላይ ተከመርኩ፤ በዚህ ጊዜ የአሰሪነት ካራክተሩን ሲጫወት የነበረው ሌዘር ለባሽ ጎልማሳ ‹‹እኔንም አስበላህ!!!.....›› ሲል ቁጣው በሱ ግኖ አካላዊ መተናኮስ ተፈጠረ፡፡ በስለት ያማሩ ጩቢያቸው አንዱ ከወገቡ ሲመዘው ሌላው ከእግሩ ካልሲ እየመነቀረ አወጣው፡፡ የአሳዛኝ ገፀባህሪን የተላበሰው ሠራተኛ ባለበት ትወናውን ቀጥሏል፡፡

‹‹ልታስወጋኝ ነው እንሂድ!! ወይኔ ጉዴ!! ለምን ከዚህ ጉድ ውስጥ ይዘሽኝ መጣህ!!›› ብቻ ደራሲያኑ እና ተዋኒያኑ ተገገናኝተው በብቃት ቢወጡትም ተሳፋ የቆረጠ እኔነቴ በሰውነቱ ቆርጦ ካጫዋቹ ላይለይ ወሰነ፡፡ በመጨረሻም ውትወታዬ በትህትና ሆኖ እነሱም አዝነው አምስት መቶ ብሬን መልሰው በሰላም አሰናበቱኝ፡፡

• * *

04 ቀበሌ ከፖሊስ ጣቢያው ፊት ለፊት ከምትገኝ ምግብ ቤት ገብቼ ሚኑ ያቀረበልኝን በምርጫ ተጠቅሜ መምህራን ኬሌጁን እያጠያየኩ ከቦታው ደረስኩ፡፡ የምዝገባ ክፍሎች በተለያዪ ሥራዎች ተጨናንቀው ስለነበር ማስታወቂያ እንድጠብቅ አንድ ምላሽ ብቻ ሰጡኝ፡፡ ሌላ መረጃዎችን ግን ጠይቆ ለመረዳት ከሥራውም ባሻገር ቅን ስላልነበሩ ሊያስተናግዱኝ ፍቃዳቸው አልነበረም እና የተባልኩትን ከመጠበቅ ውጪ ምንም ማድረግ አልቻልኩም ነበር፡፡

በተከታታይ ቀናት ከኮሎጁ ጠፍቼ አላውቅም ነበር፡፡ በዛ ላይ ያለ ት/ቤቱ የመታወቂያ ደብተር መመሳለሴ የሰለቻቸው ዘቦች አንዳንዴ ላለማስገባት ይታገሉኛል፡፡ በመጨረሻም የመጓዜ ዋጋ ከንቱ ሳይሆን ቀርቶ የምዝገባ ቀን በማስታወቂያ ቦርዱ ተለጥፎ የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች ጭምር ለመረዳት ስሞክር ያለኝ ውጤት ከበቂ በላይ ቢሆንም አንድ የኮመን ኮርስ ውጤት ግን ‹‹D›› ሆኖ የምፈልጋቸውን ት/ቶች ከመማር የሚገድብ ነበር፡፡ የሰው ልጅ በመጀመሪያ ጊዜ ሀዘኑን በልባዊ ድማት በድንጋጤ ሲገልፅ ከፋ ብሎ ሲያይልበት ደግሞ እንባውን እየረጨ ሊወጣው ይሞክራል የመጨረሻው የሚሆነው ግን እብደት ስለሚሆን ሀዘኑን በሳቅ ከመወጣት እና ቆሽቱን ከማሳረር ውጪ ለሞት ካልሆነ በቀር ምንም ዋጋ የለውም፡፡

መሳተፍ የምችለው ምንም አማራጭ በሌለው አንድ እና አንድ በአፀደ ሕጻናት የት/ት ጥናት ዘርፍ ብቻ ነው፡፡ ሞራሌ ደቆ ሰውቴን ቢያንኮታኩተውም ለመሞከር ስል ብቻ ምዝገባውን ሀምሳ ብር ከፍዬ ተቀላቀልኩ፡፡ አንዳንድ ተመዝጋቢዎች ምክንያቱን በቅጡ ባላውቀውም ሁለት ኮመን ኮርሶችን ‹‹D›› አምጥተው የፈለጉትን ዲፓርትመንት መርጠው ሲመዘገቡ ተመልክቼ ለመጠየቅ ብሞክርም ነገሩ የጀርባ ጨዋታ ሆኖ እንቆቅልሹ ሳይፈታልኝ በግልምጫቸው እና ቅንነት በጎደለው መስተንግዷቸው ምክንያት ትቼው ሄድኩ፡፡

ሁሉም የኮሌጁ የትምህርት ጥናቶች የሚተገበሩት በመግቢያ መፈተና ነው፡፡ ይህም የሚደረገው ኮሌጁ በሚያወጣው የቅድመ መግቢያ ፈተና ስለነበረ ቀን ተቆርጦለት በዛ ትልቅ የግቢው አስፋልት ላይ አሸን የሆነው ተመዝጋቢ እየተመመ ወደየ ተቀጣጠረበት ክፍል ገባ፡፡

የመገቢያ ጥያቄው ለኔ አዲስ እና የተለየ ነገር ስላልነበረው ብዙም ሳያስቸግረኝ አርባውንም ጥያቄ ሰርቼው ወጣሁ፡፡ ግቢው አጠር ባሉ የፅድ ዛፎች የተዋበ ስለነበር በጣም ያምራል፡፡ በዛ ላይ ደግሞ ከጥላው ስር ድፍት ብለው የሚያጠኑ ተማሪዎች ይባስ አስውብተዋታል፡፡ ፅዶቹን አለፍ ብዬ የኮሌጁ ዳርቻ ስደርስ ከበሬሳ ድልድይ ስር የሚመጣውን ኩልል ያለ ውሃ በዳክዬዎች ዋና ሲምሸቀሸቅ አየሁት፡፡ በዚህ ጉብኝት ላይ እያለሁ ተፈታኝ ከፈተናው እየወጣ የግቢውን ዙሪያ ገባ መልሶ ሞላው፡፡

በመጨረሻም የቀሩት ተፈታኞች አጠናቀው ሲገባደድ ወደ ክፍል ተጠርተን የቃል ፈተናው ላይ ስምንት ሰዓት ደርሰን መሳተፍ የማንችል ከሆነ የመግቢያ መፈተናውን እንዳላለፍን ተደርጎ ስልጠናውን መሳተፍ እንደማንችል በማስጠንቂያ ተነገረን፡፡ ሁሉም በትዕዛዙ ተስማምቶ ለምሳ ወደየ ቤቱ ሲሄድ እኔ ከዛው ከወንዝ ዳርቻ ሆኜ በሀሳብ እየተብከነከንኩ ሰዓቱ ደርሶ ፈተናው ተጀመረ፡፡

አንዳንዱ ተማሪ እውቀት እና ብቃቱ እያለው ከዛ ሁሉ ተማሪ ፊት ሆኖ የተጠየቀውን ለመመለስ እየተርበተበተ ሲመለስ ድፍረቱ ኖሮት እውቀቱ የሌለው ደግሞ አፉ ያመጣለትን ተንብዮ ሲወርድ እኔም ተራዬ ደርሶ ለጥየቃው ተዘጋጀሁ፡፡ በርግጥ በጣም ያስፈራ 'ና ያስጨንቅ ነበር እና ጥያቂያቸው ቀጠለ፡፡

ጥያቄ ቁጥር 1. የአፀደ ሕጻናት መምህር ለመሆን ምን አነሳሳህ?

መልስ ፡- አንድኛ የሞያው ክብር ስላለኝ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ቀጣዩ ትውልድ አሁን ካለው በተሻለ የትምህርት ጥራት ብሎም በየቦታው የትምህቱ ተደራሽነት እንዲኖረው ለማድረግ ነው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 2. መምህር ለተማሪዎቹ ምን ሊሆን ይገባዋል?

መልስ ፡- መምህር ለተማሪዎቹ የቀለም አባት ወይም እናት እንደመሆኑ መጠን በአለባበስ፤ በአነጋገር እንዲሁም በተግባር አርዕያው ሊሆን ይገባል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 3. አንድ ተማሪ የጤና ችግር ቢያጋጥመው ምን ልታደረግ ትችላለህ?

መልስ ፡- ቅድሚያ የመጀመሪያ እርዳታ አደርጋለሁ፤ በመቀጠል ተማሪው በዚህ እርዳታ የማያገግም እና የሚከብድበት ከሆነ ወደ ጤና ጣብያ እንዲሄድ በማድረግ ለቤተሰብ የማሳወቅ ሥራ እሰራለሁ፡፡

ጥያቄ ቁጥር 4. በኮሌጁ ውስጥ ሊከበሩ የሚገባቸው ሦስት የደንብ ስርዓቶችን ጥቀስ?

መልስ፡- በት/ቤቱ ውስጥ አለመረበሽ፤ አለማርፈድ፤ ንፅህናን መጠበቅ እና የመግቢያ መታወቂያዎችን ሳይዙ ከት/ቤቱ አለመገኘት ናቸው፡፡

አሐዱ ብሎ የጀመረው የቃል ጥያቄ በዚህ አላበቃም፤ አንድም የእጅ ፅሑፍን ለመገምገም ሲሆን ሁለትም ከቃላት ’ና ከፊደሎች ጋር ያለውን ትክክለኛ የመልዕት አግባብነት ለማወቅ እስኪርቢቶ እና ብጫቂ ወረቀቴ ላይ የሚናገሩትን መፃፍ ጀመረኩ፡፡

‹‹**ፖሊስ፤ ኃይለማርያም፤ ’ርግብ፤ ’ርጥብ፤ ቀ/ኃ/ሥ፤ ’ስፖርት**›› ይሄንን እንደጨረስኩ ባለ አንድ እግሯን ‹‹**ጎ**›› እንድጽፍ አዘዙኝ፡፡

‹‹**ጎ ጉ ጊ ጋ ጌ ኅ ኆ**››

ይህ ፊደል በ’ርግጥ የተለያየ ቅርፅ ስለነበረው ብዙዎቹ ከ ‹‹ጎ-ጌ›› ለመፃፍ ቢታደሉም የ ‹‹ኅ ና ኆ›› ነገር ግን እንዲህ በቀላሉ የሚታሰብ ሆኖ በጊዜው የመፈተኛ ፊደል ሆኖ የቃል ጥያቄው ተጠናቆ ሁላችንም ግቢውን ጥለን ወጣን፡፡

•   *   *

ፈተናውን ልፈተነው እንጂ ለመማር ያለኝ ፍላጎት ካላሰብኩት የጥናት ክፍል መሆኑ ትንሽ ውስጤን ሸርሸሮት ፍላጎቱም ተቀዛቅዟል፡፡ በዚህ መሐል ውጤት ከማስታወቂያ ቦርዱ ባሻገር ከሚገኘው የክፍል ግርግዳ ላይ ተለጥፎ ተማሪዎች ይራኮቱበት ይዘዋል፡፡ ያለፈው ሲደሰት ስሙ የሌለው እና የወደቀው አዝኖ በእንባ ይመላለሳል፡፡ እኔ አልፌም ወድቄም ለማየት ጉጉቱ ስላላደረብኝ ያ! ሁሉ ተፈታኝ አይቶ እስኪበቃው ከሰንደቃላማ መስቀያ እንጨት ስር ቁጭ ብዬ የሀሳብ ቁዘማዬን አበርትቼ ከቦታው በነንኩ፡፡‹‹ፈጣሪዬ ስለምን በማታኖረኝ ’ምድር ፈጥረህ የፀሐይ ’ና የጨረቃ መዘባበቻ ታደርገኛ? እኔንስ እንደ ሌሎቹ ልጆችህ አትወደኝ ይሆን? ካልሆነስ ለምን? ለምን? በ’ርግጥ ያን ሁሉ የልጅነት ዘመን አሳልፈህ ለዛሬ ቀን አድርሰኸኛል!! ግን አባቴ አሁን እነኛን የምጥ ቀንበሮች መሸከም አልችልም

እና ከወደድከኝ አንሳኝ ከጠላኸኝ ግን አልሞት እንደሁ ልሙት.......›› በዚህ መሐል ዘቡ ባንዲራ (ሸንደቅ አላማ) ሊያወርድ ከእንጨቱ ሲደርስ ከሰመመኔ ነቅቼ ቆምኩ፡፡

በስፍራው ከአንዳንድ ተማሪዎች ውጪ ምንም ሰው አልነበረም፡፡ የሚተራመሰውም እንዲህ ባዶ ሆኖ የደብረ-ኤባ ብርድ ሊሞቀው ትቶት ሄዷል፡፡ እኔም ውስጤ ሆኖ ለማይት ባልሻም እንደ ነገሩ እግሬ አድርሶኝ ውጤቴን አየሁት፡፡ ከመጀመሪያው ከፍተኛ 74% ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ ላይ የኔ 69% መሆኑን በደንብ ደጋግሜ እያየሁ አረጋገጥኩ፡፡ በውጤቱ የተወነዣበረ ስሜት ቢፈጠርብኝም የውስጤ ጉትጎታ ግን ወደ ሌላ ሄዶ ከምንም ሳልቆጥረው ከራሴ ጋር እየተጨቃጨኩ ወደቤቴ ተመለስኩ፡፡

ራሴን አረጋግቼ ምንም አማራጭ ሳይኖረኝ ዕድሜን በከንቱ ባቃጥል ተሰምቶ ቢቆጨኝ በሶስተኛው ቀን ከት/ቤት ተመልሼ ስለ ትምህርቱ የሚመለከታቸውን አካላት ጠየኩ፡፡ ነገር ግን በመንግስት እየተከፈለኝ ልማረው ያሻሁት ትምህርት በክፍያ ሆኖ ሌላ መናወጥ ውስጥ እንድገባ አደረገኝ፡፡ አልከፍላቸው ነገር ለክፍያው የሚሆን ገንዘብ የለኝ፡፡ ቤተሰብ እና ዘመዱ-አዝማድ አልጠይቅ ነገር ያሁሉ የሕይወት ወጣ ውረድ አላስማማ ብሎ ለያይቶ ምደረ በዳ አድርጎናል፡፡

የጥናት ት/ቱ መንፈቃዊ ክፍያ ዘጠኝ መቶ ብር ነበር፡፡ ታድያ ስላልነበረኝ በጠመመው ዕድሌ እያዘንኩ ትቼ ከግቢው ልወጣ ከቢሮው በራፍ ዳር ሳኮበኩብ አንዲት ሁኔታዬን አይተው የተረዱ እናት ወደ እኔ ተጠግተው ሁነቴን ጠየቁኝ፡፡ እኔም ጭንቀቴን የምተነፍስበት ሰው ስላጣሁ እሳቸውን እንዳገኘሁ ሁሉንመም አንድ በአንድ ዘርግፌ ነገርኳቸው፡፡

እሳቸውም ብዙ ነገር አካፍለውኝ ዛሬ ባለመማራቸው የሚንቁትን ነገር ግን ለመኖር ሲሉ አክብረው የሚሰሩትን የፅዳት ሥራ እንደ ምሳሌ እያነሱ ውስጤን ረብ አደረጉት፡፡ ምን ያሻል ብላቸው ት/ቤቱ ይህንን የማድረግ አቅም ስላለለው ት/ቢሮውን አናግሮ የተሻለውን ቢያደርግ ቅን ከሆነ እንደሚቻል አስረዱኝ፡፡ እኔም በሰጡኝ ፍንጭ መሠረት ጥየቃዬን አጠናክሬ ቀጠለኩ፡፡

ብዙኃኑ እንደተባለው ቀና ባይሆኑም አንዳንድ መልካም መካሮች ግን ቦታ እየጠቆሙ እንዳናግር እርዳታቸውን ቢለግሱኝም ከቢሯቸው በር ዘግተው ስልክ ሲጎረጉሩ፣ አዲስ በተገጠመላቸው የኮምፒውተር ስክሪን ፖለቲካን፣ ፊልምን እና ሙዚቃን ሲኮመኩሙ የሚውሉ ዘብናኞች ለኔ ዓይነቱ ጥያቄ ምላሽ ሳይኖራቸው መኮሰታተርም እያማራቸው ከቢሯቸው እንኳን ለቀቁ እስክወጣ ጭንቀታቸው ከፊታው ላይ ይነበብ ነበር፡፡ ከኮሌጁ በዚህ ጉዳይ ምንም የተለየ ነገር ማግኘት ስለማልችል ሳልፈልገው የነበረ ት/ት ይባስ ብሎ እልህ ውስጥ ከተተኝ፡፡

አንድ የሺዋስ የሚባሉ መምህር አሰልቺ በሆነ ድግግሞሽ ስለተጫንኳቸው ከቀበሌ ድጋፍ ላገኝ የምችልበትን ፍንጭ ሰጡኝ፡፡ የተራድኦ ድርጅቶች ’ና አንዳንድ መንግስታዊ የሆኑ ተቋሞችን በተባለው መሠረት ጠየኩን፡፡ አ/ጠ አስተዳደር ቢሮ እንዳመራሁ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ መምህራችንን አገኘኋቸው ሁሉንም ነገር አንድ በአንደ ምንም ሳላስቀር ተረኩላቸው፡፡ ለብዙ ሰዓት ከተጨነቁ በኋላ ከዛው ከአስተዳደር ቢሮዎች እየዞሩ ማጠያየቅ ጀመሩ፡፡ በምላሻቸው ምንም ነገር ያጡ እና ሲመለሱ እኔን ተስፋ ላለማስቆረጥ ሲሉ ‹‹ብቻ ችግር የለውም እየተመላለስክ ጠይቀኝ!!›› ብለው ሊሸኙኝ ሲሉ አንድ ሀሳብ ውል ስላለኝ አወጋኋቸው፡፡ በሀሳቤ እሳቸውም ተስማምተው ጥሩ አማራጭ መሆኑን ነግረውኝ ወደዛው ላኩኝ፡፡ ወርልድ-ቪዥን ኢትዮጲያ ዋና ኋላፊ የሆኑትን አቶ አቤሜሌክ ከገጠራማው ቦታ ደርሼ ብጠብቃቸውም ለስልጠና ወደ ናዝሬት እንደሄዱ ነገሩኝ፡፡ ከደ/ብርሃን-አ/ጠ በተደጋጋሚ ብመላለስም ምንም መፍትሄ ላገኝ አልቻልኩም፡፡

መምህር የሺዋስ በጣም አዝኜ እና ተቦሳቁዬ ሲያዩኝ አዝነው ስለሁሉም አማከሩኝ፡፡ ውጣ ውረዱ በዝቶ ላይሳካ ቢመስል እሳቸውም ደብዳቤ ባመጣሁት ውጤት ላይ ተመስርተው እንዲፃፍልኝ ያደረጉትም ራሳቸው ነበሩ፡፡ በአራተኛው ቀን አቶ አቤሜሌክ ከስልጠና ተመልሰው ኖሮ ከቢሯቸው ስደርስ አንዱ ቢሮ ወደ ሌላው እንደ ፌንጣ ሲዘሉ ደረሼ ሁሉንም አስራዳኋቸው፡፡ አቶ አቤሜሌክ ሰምተው አዝነው የድርጅታቸውን መታወቂያዬን አገላብጠው ከተመለከቱት በኋላ ከድርጅቱ ምንም

ዓይነት አገልግሎት ማግኘት እንደማልችል እና ዕድሜዬ ከመራጃው የድርጅታቸው መስፈርት በላይ መሆኑን አስረድተው መማሪያ ደብተር 'ና የኮት እና ሱሬ ቱታ ሰጥተውኝ መልሰው መ/ሬ ጋር ሸኙኝ።

እሳቸውም ሲያጠያይቁ ቆይተው ከከተማው አስተዳዳሪ ዘንድ ላኩኝ። አስተዳዳሪውም የሰማውን መረጃ ከኔ ደግሞ ካረጋገጠ በኋላ የሴቶች እና ሕጻናት ድርጅት ይሄንን ማድረግ እንደሚቻለው በማሰብ ኃላፊዋን ጠርተው አማከሯት። እሷም ለጊዜው በጀት እንደሌለ እና አቅማቸው እንደማይፈቅድ በማስረዳት ቀበሌዬን ጠየቀችኝ። እኔም ስናገር እንደውም ቀበሌያችን ዳጎስ ያለ ብር እንዳለው በቁጭት ትናገር ጀመረ።

በዚሁ ክርክር ውስጥ እያለን የቀበሌው አስተዳዳሪ አቶ ማቱሳላ ከቢሮው ሰተት ብለው ገቡ። በጣም ተሳቅቄ ነበር። አስተዳደሩ ይሄንን ባየ ጊዜ እንድወጣ ትዕዛዝ ሰጥቶኝ ካማከረው በኋላ አብሬው ሄጄ ከቀበሌው የሴቶች ማህበር ጋር ጉዳዬን እንድከታተል መክሮ ሰደደኝ። ተያይዘን ከቦታው ስንደርስ ሥራ-አስኪያጇ ከቢሮ ስለነበረች ሁሉንም ስሰማ አዝና የሚጠበቅባትን ለማድረግ ወሰነች።

በማግስቱ ጠዋት የመጀመሪያ ቀን የኮሌጅ ክፍያው ተጠናቆ ት/ት የሚጀመርበት ቀን ነው። እኔ ግን ያለሁት አዛው ከራሱ ከት/ቤቱ አጠገብ ረሃብ እንደነገሰበት ጥማተኛ ስንሰፈሰፍ እውላለሁ። አንድ ቀን ያለኝን ሁሉ ልእልና አሟጥጬ ባከበሩኝ እና ፈርተው አብረው በኖርኳቸው ማህበረሰብ ስር በጉልበቴ እንብርክክ ወድቄ ተማፀንኩ። እነሱም እድገቴን ከሀ-ፖ ያውቁታል እና ከሰፈር የተሰቀለውን ባዶ ቆርቆሮ አይተው ሳይታመኩ ዘመድ የተባሉት እንደ ኤርታሌ ጎመራ በመሐላቸው ሲፈነዱ፤ በትዕግስት አሳልፈው በውሳኔ ተስማምተው እንድማር ወስነው የአንደኛ ሴሚስተር ክፍያ በአባላቸው አስይዘው ላኩኝ።

አባላቸው በጣም የማውቃቸው እና አያቴን በቀብራራ 'ና በቸርነቱ የሚያውቁት ናቸው። ቄስ እና መምህር ነበሩ። ምንም ነገር አላስቻለኝም የቀበሌው ሊቀመንበር በነገሩ አኳሁኔ ግልፅ ስለነበር ንግግር 'ና ሌላ ጉሸጣ ሳናበዛ ከፍለው እንዲመጡ ከክፍያው ጋር አስይዘው ሸኙን። እኔም የነበረችኝን ብር ለትራንስፖርት እየከፈልኩ ከኮሌጆ ስንደርስ ክፍያው በቀጣት መሆኑን ነገሩን። እኔም ያለችኝ ከዛ ሁሉ ወጣ ውረድ የተረፈችኝ የቅጣቷ ብቻ ስለነበረች እሷውኑ ሞልቼ በ'ርሳቸው ብርታት ተከፍሎ ያንን ሁሉ ሰዓት አብረውኝ ሲዳረቁ ቆይተው ሻይ እንኳን ሳልለላቸው እነሱም ወደ ቀያቸው እኔም ወደ ቤቴ በርጋታ አቀናሁ።

• * *

# ምዕራፍ አምስት

## ቢጎድልም ላይጨረስ ያልተጀመረ ባህር!!

አሁን ላይ የነበረችኝን አምስት መቶ ብር ከዛም ከዚህም ስል አጠናቅቂያለሁ፡፡ ያለችኝ አንድ የጋዝ ቡታጋዝ እና ብረት-ዲስት ብቻ ናት፡፡ ኪሶቼን ከግራ ወደ ቀኝ እያገላበጥኩ ስፈትሽ አስራ ሁለት ብር አገኘሁ፡፡ በወቅቱ ሩዝ ኪሎ አስራ ሁለት ብር ስለነበር ገዝቼ በዛ ብረት-ድስት እየቀናነስኩ መስራት ጀመርኩ፡፡ ዘይት ቀድሞ የተገዛ ስለነበር በሱ ያለማጣፈጫ ሞርሞር ሲያደርገኝ እቀማምሳለሁ፡፡ አንድ ሳምንት በዚሁ ሁኔታ ቆይቼ ለመማር ብችልም የሩዟም ነገር ወደ ማለቁ ደርሳ ረሃብ በሁለተኛው ሳምን መአቀቡን ጣለብኝ፡፡

ቀን ሥራ ለመሥራት ከትምህርት መልስ በየከተማው እየዞርኩ ብጠይቅም ከማነሴ እና ከሰውነቴ መልተት የተነሳ ማንም ወደ ሥራው ጋብዞ ሊያሠራኝ አልቻለም፡፡ ሁለተኛው ሳምንት ሊገባደድ የሁለት ቀን ዕድሜ ብቻ ነው የቀረው፡፡ ላለፉት በርካታ ቀናት በመኝታ ለማስታገስ ብታትርም ሳይሆን ቀርቶ ከሰውነቴ ውስጥ ፍም እሳቱን ለኩሶ እያነደደ ማጥፊያ የለው ማረሚያ ብቻ መጥፎ ህመም ውስጤን ይረብሸዋል፡፡ እለቱ ቅዳሜ ነው ጠባሴ ከሚባለው ስፍራ በጣም ብዙ የሚሰሩ አዳዲስ ቤቶች እና ፋብሪካዎች አሉ፡፡ መናቂ ገብቶኝ መጠየቅ በማጣት ላይ ውርደት ጭምር መስሎ በምስሉ ሰንኮፍ እያስፈራራኝ እንዳልጠይቅ አሸማቀ መለሰኝ፡፡ እግር ግን ችሎ እንኳንስ ለኪሎ ሜትር ለረጅም ማይል የማይቃተው ሰውነት ለቶ መቶ ሜትሮችን ተራምዶ መሄድን አልችል ብሎ ለገመ፡፡

በሀሳብ ቃጠሎ ታጭቆ ሊፈነዳ የደረሰው ራሴ ራሱን በእንባ ቢያፅናና ከዐይኑ ጎርፍ እያዘነበ መፈጠሩን ዳግም ደጋግሞ እስኪጠላ አናባው፡፡ ከደ/ኤባ ዩኒቨርሲቲ ፊት ለፊት አስፋልቱን ተሻግሮ ማዶ ላይ የሚገኘው ተራራማ ስፍራ ከውስጡ ተገኝቼ ማንባቴ የሳቀብኝ ሲመስለኝ እግሬን ሄድ ቆም እያደረኩ አመሻሽም ደርሶ ወደ ቤት ገባሁ፡፡ አከራዮቼ ችግሬን አይተው በግቢ ውስጥ መቆሚያ ማግደሚያ እንዳያሳጡኝ ስለምፈራ ሥራ ውሎ እንደመጣ ሰው ቤቴን ከፍቼ እስክገባ ድረስ እንደተለመደው ጀነን ብዬ አልፋለሁ፡፡

እሁድ ዕለት ሰንበት እንደመሆኑ መጠን በጠዋት ተነስቼ ወደ አቦ ቤተክርስትያን ሄድኩ፡፡ ሰዉ ግቢውን ሞልቶ ግማሹ ሲፀልይ የተቀረው ከቂሶቹ እየተቀበለ በቅዳሴ ፈጣሪውን ያመሰግናል፡፡ ትልልቅ ሰዎች በስተ-ምሥራቁ በኩል ማቋሚያቸውን ይዘው ወገባው ረግዶ ሰውነታቸው እስኪዝል ወዳሴ ማርያም እና መፀሐፍ ቅዱስ እያነበቡ ይረግዳሉ፡፡ እኔ ስደርስ ቅዳሴው ወደ መገባደዱ ላይ ደርሶ ነበር እና እኔም ፈጣሪዬን በምሬት እየለምንኩ ሳለሁ ደቂቃዎች ነጉደው ፍትሃት ተደርጎ ቅዳሶው ተጠናቀቀ፡፡

ከሰሜኑ በኩል ከአንድ ወንበር ላይ አረፍ ብዬ ስብከት ተጀምሮ ጆሮዬ የሚባለውን ወደ አዕምሮ ክፍል እያስተላለፈ በመደመም እንዳዳምጥ አደረገኝ፡፡ ታሪኩ ዓለም እና መልካም ጠይዎቸዋ በረጋቢ ስለቀጣቸው የመፀሐፍ ቅዱስ ሰው ኤርሚያስ የሚያወጋ ነበር፡፡ በ'ርግጥ አስተምህሮቱ ፈጣሪ ለኔ ሲል ያቀረበው ነው ብዬ ራሴን በኤርሚያስ አፅናናሁ፡፡ ነገር ግን በጣም ርቦኝ ስለነበር እንደ ኤርሚያስ በአሞራ መናን ቢመገበኝ ከልብ ተመኘሁ፡፡ ግን ምን ያደርጋል እኔ የሱን ያህል ፅናት እና እምነቱም ጭምር አልነበረኝም፡፡

ስብከቱ አልቆ ፍትሃት በአባቶች ተደርጎ ሁሉም ሰው ወደየ ቤቱ መጉረፍ ጀመረ፡፡ ታድያ ሁሉም ከስጋ ወደሙ መቋደስ ስላለበት ከውሃውም፤ ካሹቁም፤ ከዳቤውም ቤት ካፈራው ሁሉ ነገር በትንሽ በትንሹ ሁሉም በእጁ እየተቋሰ ይሄዳል፡፡ እኔም እሱን አግቼ እስክቀምሰው ቸኩያለሁ እና በሰው ውስጥ አልፌ አሳላፊው ጋር እስክደርስ ድረስ ነብሴን አላውቅም፡፡ ይቅርታ ባንተ ላይ የዘመተው 57/77 ነው

ብላችሁ ግራ እንዳትጋቡ ምክንያቱም እኔ ሁለቱንም በዚህ ሳምንት ውስጥ በደንብ አድርጌ አይቻቸዋለሁ።

በመጨረሻም ካሳላፊው ደርሼ ከስጋው አንድ ቁርጥ ዳቦ፤ አንድ እፍኝ አሹቅ እና ከደሙ አንድ ብርጭቆ ውሃ ይገፍ ካንድ ጥግ በውሃው እያማከ ያለ ሥርዓቱ በልቼ ጨረስኩ። ሆዴ ዘማቾች ምሽግ ይዘው የሚዋጉበት የጦር ሜዳ ይመስል ካራንባ እና ቆቦ ይንጋጋል። ከበድ ሲልም ሚሳኤል እንደ የተፈጠረቀበት ምድር ይመስል በመቀመጫዬ ይበርቃል። በ'ርግጥ ማስተዋል ይከልለናል እንጂ ፈጣሪ ለኔ ካደረገው የተለየ ለኤርሚያስ ያደረገው ነገርስ ይኖር ይሆን?

ያቺን ቀማምሼ ሌላ ጊዜ አገር ቢከሽን የማይበቃው ሆዴ ለካስ ራሱን አውቆ ገርገብ ብሎ አደካክሞኝ ከአራት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ሰውነቴን በላብ ነክሮ እስትንፋሴን እያነቀ ሸለብ አደረገኝ። ወዲያውኑ በህልም አልም ውስጥ ከቶኝ መባተት ጀመርኩ።

‹‹ በጣም ብዙ ሰዎች ያሉበት የለቅሶ ቦታ ነው። በውስጣቸው በርካታ ዘመዶቻችን አሉ። እኔም ከውስጣቸው አንዱ ነኝ። ቀብሩ እየገሰገሰ ከማላውቀው ስፍራ ተፈፅሞ ሁሉም በምላሹ ላይ የአብዮት ዘማች መስሏል። ከፊታችን አባጣ ጎባጣ የነበረው መንገድ በአንዴ የማይወጣ ተራራ ሆኖ ከፊታችን ተከመረ። ሰዉ እንደ አሸን እየተመመ ከጋራው ሲጎርፍ እኔም በፍራቻ መዐበል ውስጥ ሰምጬ ተራራውን በእንፉቅቄ ወጣሁ። ከዚህ በኋላ ነበር ተከትዬ የተከተሉኝን ሰዎች አጥቼ ብቻዬን ከተራራው መሻገሪያ ገደል ከተለየው የማላውቀው ፍጥረት ጋር የተገኘኅሁት። ሁለት ክንፍ አለው። ክንፎቹ ጥቋቁር ሲሆኑ ከፊቱ አከባቢ የሰው ፊት ያለው መስሎ ልክ እንደ ንስር አፉ ሲበዛ ሹል ነው። የሰው እጅ በሚመስላው መዳፉ ላይ በብረት የተሳለ ጦር ይዟል። በቅፅበት ሳላስበው መጠናቸው እየሰፋ ሰውነቴ እንደ እንዝርት ሲሾር ይታወቀኛል። ሮጬ አላመልጥ ከፊት እንደነሱ የሚያስፈራው ገደል ሊበላኝ ጥርሶቹን አስግጓል። ጩኸቴ በርትቶ ፍጡራኑ ወደ እኔ እየተጠጉ ሲሄዱ እኔም ሁለት እጆቼን እንደ አሞራ እያራገብኩ ላመልጣቸው አታትር ተያያዝኩት። በጣም ያስፈራል በረራውን ከየት እንደጀመርኩት ባላውቀውም በመክነፌ መሐል ክንዶቹ ዝለው ሰገሌ ከሚባለው ዋሻ አፋፍ ቆሜ ዋሻው በገደላ ገደል ተውጦ አሁንም ከዛው ዋሻ ውስጥ ቀስተኞቹ ፍጡራን ሲተሙብኝ አንደኛው ክንዴ ዛለ። በምንም ቅድሚያ እንደ ነስር ራሴን እያደስኩ በረራዬን ቀጠልኩ። በስተመጨረሻም ከዋሻው ራቅ እንዳልኩ በርቀት ሆኜ ከንፋማው ፍጥረት ቀርቦ ታየኝ። ግራ እና ቀኝ ስመለከት ምንም ነገር ስላልነበረ አረፍ ከማለቴ አንደኛው ከአጠገቤ በአውላላው ፀሐያማ ሜዳ ላይ ደርሶ በአንደኛው ከንፋማው ክንዴ ላይ ሲንጃበብ ወድቆ የሰውነት ባህሪ እየተላበስኩ መብረር አቅቶኝ ሰው እና ከዛፍ ውጪ ተፈጥሮ በሌለበት የብርሃን ጭለማ ውስጥ በፍራቻ እየናኘሁ ሳለሁ›› ብንን ስል አማተብኩ።

ቤቱ ትንሽ ጨለምለም ያለ ስለነበር ቢያንስ ለሶስት ደቂቃ ያለሁበትን በቅጡ አላውቅም ነበር። ከተኛሁበት ተነስቼ ፊቴን በውሃ ለቅለቅ አድርጌ የተሰጠንን አዲስ ሞጁል ማንበብ ጀመርኩ። ልክ አስራ ሁለት ሰዓት አከባቢ ራሴን ክፉኛ ያዞረኝ ጀመር። የሰው፤ የእንስሳ …… ብቻ የምንም ድምፅ መስማትም ሆነ ማዳመጥ አልፈልግም። እያደር ወደ ማቅለሽለሽ ቀይሮት ነብስ ግቢ ነብስ ውጪ በራሴ ላይ ነግሶ ያስቃትተኝ ጀመር።

ጣቶቹን ከጎሮሮዬ ሰድጄ የገባችውን እንኳን እንድትወጣ ብጥርም ህመሙ እጥፍ ድርብ ሆኖ ላያናግር ድምፅ፤ ላያሳይ አይታዬን ነፍጎ በቃተታ የሰዓት እርዝማኔ ውስጥ እንቅልፍ በመከራ ተጠምቆ አዳር በመኝታ መካን ሆና ስትጠጣ አደርኩ። ማግስቱን ተስፋ ካልቆረጠበት የቀን ሥራ መሥሪያ ሳይት ሄጄ ከማንኛውም የሰው የውሎ ክፍያ በታች እንደምሠራ ለአሠሪዎች በተማፅኖ ጠየኳቸው። አሠሪዎች

እንደዚህ ዓይነት ነገር ሲያገኙ ከሚከፋላቸው የኮንትራክተር ክፍያ በላይ መላ ሰውነታቸው እየሳቀ ደስ ይላቸዋል፡፡

በወቅቱ አንድ የቀን ሠራተኛ የሚቀጠረው በሀምሳ ብር ሲሆን ግፋ ቢል እሱም አርማታ ከሆነ ስልሳ ብር ይከፈለዋል፡፡ እኔም እቅዴ ይሄንን አግኝቼ ለመሥራት ቢሆንም የአሰሪው ፍቃድ ካልሆነ ያለሁበት ሁኔታ አይደለም በቀን ውሎ የአንድ አንባሻ መግዢያ ባገኝ እንደማላፈገፍግ በደንብ አውቃለሁ፡፡ አሠሪው ግን ከነበረው ቀንሶ ቀን ሞሉ የአርማታ ሥራ በአርባ ብር ከቻልኩ እና ከጠነከርኩ መሥራት እንደምችል በማስጠንቀቂያ ነግሮ አስገባኝ፡፡ በ'ርግጥ እንኳንስ ቁርስ ራትም ከየት ተገኝቶ ነው እና በባዶ አንጀቴ ሳጥን ይዤ አሸዋ ማፈስ ጀመርኩ፡፡ አሠሪው በእኔ አርባ ብር እያሳበበ ሌላውን አርባ አምስት፤ ሀምሳ 'ና ሀምሳ አምስት ብር እያስማማ ከስራው ዶላቸው፡፡

እኔም ጠጠሩን አፍሼ ሳጥኑን ለመሸከም ጎንበስ እንዳልኩ ወገቤን ጨምደድ እጆቹን ፍልቅቅ አድርጎ በአስጨናቂ መታትር ተነስቶ ወደ ሚክሰሩ ጉዞ ተጀመረ፡፡ ከሚክሰሩ አፍ ላያ አድርሶ መገልበጡን ማንስ ይሞክረው! በኦፕሬተሩ አጠገብ ስለነበርኩ ተቀብሎ ገለበጠልኝ፡፡ ‹‹አሸዋ፤ ጠጠር›› በየተራ እነሱን እያመጡ በምጠት ሸክም ከወጣው የከረጢት ሲሚንቶ ጋር እያዋሐዱ በሰንኬሎ ከፊት ከተቆለለው ፎቅ በሸክም ማውጣት ነው፡፡

የጠጠር አፈሳው ትንሽ አስቸጋሪ ነበር፡፡ ደጋግሜ ስሞክረው ደከምከም ብሎ ክንዴ ቢዝልም ለምጄዋለሁ፡፡ እንዲህ እንዲህ እያልን ልብሳችን በሲሚንቶ ደክርቶ ድካም አቅል አሳጥቶ ጉልበት እያለገመ ግማሹ ሊወድቅ ከፎቅ ሲንገዳገድ ከቀኑ ስምንት ሰዓት ላይ ለምሳ ወጣን፡፡ የሠራሁት የለ! አልጠይቀው ነገር አሠሪው ከወጣ ስድስት ሰዓታቶችን አስቆጥሯል፡፡ ኦፕሬተሩን ከሌሎቹ እየተሸሸኩ ልጠይቀው ብሞክር ከትዕቢቱ የተነሳ ይኑረው አይኑረውም ባላውቅ እያናናቀ እንደ ሌለው ነገረኝ፡፡ መጠየቄን ጠልቼ ከዮኃንስ ተራራ ግርጌ አረፍ ለማለት መንገድ ልጀምር ስል ቃንጃዬ ለምሳ መሄድ እንዳለብን ወትውቶ እና አስገድዶ በግራ በኩል ከምትገኝ ዳስ ውስጥ ተያይዘን ገባን፡፡

አንድ ሽሮ አዞ ሁለት ሙልሙል አንባሻ ዳቦ አስጨምሮ ከላይ እየቆራረሰ በሽሮው ዙሪያ አደረገው፡፡ ሁለታችንም 'ርቦን ስለነበር የሌለብኝ አመል ድንገት ተከስቶ እየተሻማን በልተን እሱ ቡና ለራሱ ሲያዝ ለኔ ሻይ አዘዝኩ፡፡ ትንሽ ወሬ ስለመጣንበት እና ስለምንኖርበት አወራርተን ሰዓታችን ደርሶ ለመነሳት ስናኮበኩብ እንዳለው ሰው ካልከፍለኩ ብዬ አስቸግረው ጀመር፡፡ ፈጣሪ ነገሮትስ መሰለኝ አስገድዶ ያመጣኝ እራሱ ከፍሎ ወደ ሥራ ተመለስን፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ ሰው አላውቀው አያውቀኝ አጋጣሚ ሆኖ ሥራ አገናኝቶን እንጂ ክፈል ቢለኝ ከየት ላመጣ እደሆን ሳስበው ነገሩ አልፎ ነብስ ስዘራ ከሥራው ስፍራ ሆኜ እጅጉን ገረመኝ፡፡

የአርማታው ሥራ ከአመሻሹ አስራ አንድ ሰዓት አከባቢ ተጠናቆ ኮንትራክተሩን ለደመ-ወዝዛችን ብንጠብቅ ብንጠብቅ የውሃ ሽታ ሆኖ አመሻሹ ጨለምለም ብሎ አሠሪያችን በማግስቱ እንድንመለስ በልመና ጭምር አሰናበተን፡፡ እኔም ከበፊቱ ጥቂት ሰውነቴ ረጋ ስላለ የ'ራትም ባይኖረኝ መስጠቱን ተስፋ እያደረኩ ወደ ቤቴ ሄድኩ፡፡ ከቤት ገብቼ ትንሽ መፀሐፍ እና የማስታወሻ ደብተሬን ካገላበጥኩኝ በኂላ የተሰጠኝን የቡድን ሥራ ሠራርቼ በተቀመጥኩበት ጋደም እንዳልኩ አነጋግ ወገግ አለች፡፡

ክላሳችን ማክሰኞ፤ ሐሙስ፤ አርብ ማታ ከአስራ ሁለት እስከ ሶስት ሰዓት እንዲሁም አንዳንዴ መ/ራኖቹ ከተመቻቸው ቅዳሜ 'ና እሁድ ከሁለት እስከ ስምነት ሰዓት ድረስ ነው፡፡ ነጋቱ እለተ ማክሰኞ ነበር ሥራ ቦታ ሁለት ሰዓት ላይ መገናኘት ካልቻልን ከአሠሪያችን ጋር ተነጋግረን የጨረስንበት ጉዳይ ስለነበር በወቅቱ ከቦታው ተገኝቼ ሥራዬን ቀጠልኩ፡፡

*አካፋ፤ ሳጥን እና ሰንኬሎ የያዝኩበት እጄ በጣም ቆስሎ እየፈነዳ ነው። ትከሻዬም ከሚገባው በላይ ቆስሎ እየቆጠቆጠኝ ነው። መላ ሰውነቴ በስትራፖ 'ስርስር ብሏል። ትንሽ እንቅስቃሴ ሳደርግ ስትራፖው ቢለቀኝም ቁስላ ቁስሉ ግን ፈፅሞ ሊያሰራኝ አልቻለም ነበር። ነገሩ ያለ ውሎ አዳር፤ ያለሥራ ኖሮ ሆነና ህመሜን ቆንጥጬ ይዤ ሥራዉን አስራ አንድ ሰዓት ላይ አጠናቅቄ ወደ ክላስ አመራሁ። ከት/ቤት እስከ መኖሪያዬ ያለው ርቀት 1500ሜትር ይሆናል። ከዛ በሶስት ሰዓት ተመልሰህ ለመግባት ከሚወስደው ሰዓት በላይ በፃድቃኔ ፎቅ ስር እና አለፍ ብሎ ከገዳሙ በሚወስደው መንገድ ላይ ያለው ማፍያ እጅጉን የሚያስፈራ ነበር።*

*መምህራኖቹ ካለፉት የዘመናት አስተማሪዎች ጋር በምንም የሚወዳደሩ ባይሆኑም ለቦታው ግን በቂ ናቸው ብሎ መናገር አያስደፍርም። በዙኃኑ በተለይ በመቅረት እና በፀባይ ጉዳየ ኢንኮፕሌትን እንዴት እንደሚወዷት ልነግራችሁ አልችልም። እነሱ ሲያስተምሩ በሁሉም ነገር ለእነሱ በገባቸው ልክ 'ና ልክ ናቸው። ከሌላው የሚመጣው ሀሳብ ግን በማባረር እና ግሬድ እንደ ግራይንደር በመሰባበር የተወሰነች ነች።*

*ብዙኂኑ በሚገርም ሁኔታ ራሳቸው ካላቸው እውቀት ጋር ሳይሆን ራሳቸውን የሚያኖሩት ሆነው ካላግባብ ከተሰጣቸው የራሳቸው ፍላጎት ጋር ነው። እነሱ በቃ ከምንም በላይ በ'ምድር ላይ ያልተፈጠሩ ምሁራኖቹ ዩፎዎች እና ኤሊያንሶች ናቸው። በእውቀት ለሆነ ነገር ምንም ቢሆኑ በ'ርግጥም ከዚህ በላይ ቢሆኑ እንጂ አያንሱም። አንዳንዱ ቀን ላይ ጥቂት ክሬዲት ሐወር ይሰራ እና ማታ ላይ የዱካኩ መዘርገፊያ መደበሪያ ማሽኑ ያደርገናል። ብቻ ችግሩ ከእንደሱ ዓይነቶቹ ብቻ ሳይሆን ያለ ዓላማ እና ያለ እቅድ ከመጣውም የግፊት ተማሪም ጭምር ነው።*

*‹‹ሰርተ-ፍኬት .......›› የሁሉም ተማሪ ጭንቅላት ውስጥም የሚያቃጭለው ይሄ እንጂ የእውነት እና የአስተውሎት እወቀት ካረገች ራሳቸው መምህራኖች ከሚያደርጉት የድርጊት ምስክርነት መረዳት ይቻላል። ጠንክረው እና ተግተው የሚያስተምሩ መምህራኖች ለእንደዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች ፋሮች ናቸው። እነሱ ግን እንደ እህል ዘር ያንን ሁሉ እውቀት በማህላችን ሲበትኑት እንደዛኞቹ መምህራኖች ካልሆንኩ ሞቼ እገኛለሁ የሚልም የባቱ ወይም የናቱ ልጅ ተማሪም ሌላው እንቅፋት ነው።*

*የመላክም ዘር ዘሪዎች ፈሬ ምስላቸው እንኳን እስከነ ቁመናዋ አትረሳም። መልካም ያልሆነ ግን መልካም አለመሆኑን ማስታወስ ቢቻልም አድራጊውን ግን ከነምስሉ ለፍሬው ማስታወስ ሊቻል አይችልም። ይህ የሚሆነው ግን መልካም እና ቀና በሆኑ ሰዎች ውስጥ 'ና በተቃራኒው ለሆኑ የእናት እና አባቱ ልጆች አይደለም።*

*ት/ት 'ና ሥራ አደካክሞ ተስፋ የሚያስቆርጥ ቢሆንም ህይወት እንዳት ሞት መቆሚያ እንዳትነሳ መጣያ የሆነውን የተሰበረ እርካብ አጥብቆ ከመያዝ ውጪ ምንም ዓይነት አማራጭ አላነበራትም። በዚሁ ሁነት አንዳንዴ የሳይት አሠሪዎች ገንዘብ እየወሰዱብን ሲሄዱ ሌላኛው እያዘነ አስጠግቶ ያሰራናል። የሚገርመው ነገር አንዳንዱ የቤቱን አመል ይዞ መጥቶ በሥራ ውስጥ ለመበጥበጥ የሚፈልግም የምች ጓደኛ ተምችም አይጠፋም። ቀኝ ስትለው ግራ፤ ግራ ስትለው ቀኝ ብቻ በጣም ባህሪያቸው መጥፎ የሆኑ አሉ።*

*በዚህ መሐል በሁለተኛው ወር አካባቢ ወንድ አያቴ በሴት አያቴ አማካኝነት ከዘመዶቻቸው እንዲያስተዋውቁኝ ላኳቸው። እሳቸው በጣም ከመድከማቸው የተነሳ የወንድሞቻቸውን ልጆች በተዓምር ጠይቀው አያወረቁም ነበር። ዛሬ ግን ለኔ ሲሉ እዛ ድረስ በማያይ ዐይናቸው ምርኩዝ ተደግፈው መጡ። እኔም ተቀብዬ ከሻቸው አደረሳኳቸው።*

እሳቸውም ለሦስት ቀን የወንድማቸውን ልጆች እየጠየቁ እኤን አደራ ብለው ከዛው የምትገኘውንም የእህታቸውን ልጅ እንዲያስተዋውቁኝ አደራ ሰጥተው ሄዱ፡፡ እኤ ግን ከጠዋቱ ከሰው በመቅረብ የታደልኩ ስላልነበርኩ ትንንሽዬ ሰበቦችን እየፈለኩ 'ራቃቸው ጀመር፡፡ እነሱም በስልክ እየደወሉ ከአክስቴ እንድገናኝ ወትውተው ጠሩኝ፡፡ እኤም በሀሳባቸው ተስማምቼ ቦታውን በርቀት አይቼ ተመለስኩ፡፡

በዚህ መሐል ትንሽ ቸገር ይለኝ እና ከተሸጠችው ላም የተወሰደ ጥጃ ተሸጦ ለቤት ክራይ እንዲከፍሉልኝ በአጎቴ ነጋድረስ አስጠየኳቸው፡፡ እነሱም ምክንያቱ ባይገባኝም አዝነው እናቴ ከታናሽ ወንድሜ አላዛር ጋር እኤ ከዛው ሆኜ ስቀልበው ሶስት ሺህ ብር የተሰጠ ወይፈን በአንድ ሺህ ሶስት መቶ ሸጠው የቤት ክራይ ልከው የቀረውን ከዛው በግ ገዝተው አስቀሩት፡፡

እናቴ በዚህ መሐል ምን እንደታያት ባላውቅም ስልክ እየደወለች ታዋራኝ ጀመረች፡፡ ‹‹ የት ነው ያለሽው? ት/ትህስ እንዴት ነው? ልምጣ ልጠይቅህ ወይ? ዘመዶቼንስ አወቀኃቸዋል እንዴ? ……….›› ለኔ ያሁሉ ነገር ካለፈ በኋላ ይህ መፈጠሩ በጣም የሚገርም ነበር፡፡ እኤም እሺ.ታዬን በሰላሙ ችሬ ልትመጣ መቀበያ የሚሆነውን የቤት ድግስ ባለችኝ አዘጋጅቻለሁ፡፡

ቤት በዋጋ ምክንያት ከቀየርኩ ሁለት ሳምንት ሆኖኛል፡፡ የገባሁት በአውለላ ሜዳ ላይ የተሰራች ቤት ነው፡፡ አጥር እና መከለያ የሚሆን ምንም ነገር የላትም፡፡ ቤቷ ጠባብ እንደመሆኗ መጠን መንገደኛው እስከ ውስጠኛው ክፍል ድረስ እንዳሻው እንዲያይ የሚያደርግ ነው፡፡ ውስጧ ፅድት ያለ ሲሆን ኮርኒሷ ግን የማዳበሪያ እና ከጎን በኩል ሽንት ቤት ላይ የተሰራች የሽንት ቤት ትራፊ ነች፡፡ በሶስተኛው ሳምነት ባለቤቱ ባለችበት ከበብ አድርጎ በቆርቆሮ አጥር ሰርቶ ለራሱም ከጎን በኩል ሲያስውበው ከነበረው ቤቱ ገባ፡፡

እናቴ በአራተኛው ሳምንት ስትመጣ ከዛው ከጎረቤቴ አንዳንድ እቃዎችን ተበድሬ ቡና አፍልቼ በደስታ ተቀበልኳት፡፡ እሷም እሷም ከዚህ ቀደም እንደተለመደው ከጥሮሾው፤ ከእንጀራው፤ ከበሶው እና ከሽሮው አዘጋጅታው መጥታ ስለነበር፡፡ በጥሮሾው ጎረቤት ጠርቼ ያለፍኩትም ታሪክ በራሴ ላይ ይስከን ብዬ በሰላም ጠጥተን ከጨረስን በኋላ ለአፍታ ከቤት ብወጣ አከራዬ መምህር ስለነበሩ እንዲረዱኝ እና እገዛ እንዲያደርጉልኝ መክረው እና በኃዘኔታ አዋዝተው ሥራ ስለነበረባቸው ከቤት ሄደው ህሌንን ብቻዋን አገኘኋት፡፡ እኤ በበኩሌ እንጀራ እንዲበሉ ፈልጌ ነበር ሳይሳካ ቀርቶ ግን ቀድመውኝ ወጡ፡፡

እናቴ እንደ ሌላው ጊዜ ዘንተል ቀብረር ብላ አልነበረም የለበሰችው፡፡ በቃ ብስቁል ብላለች በዛ ላይ የተነገራትን ሌላኛውን ታሪክ ስትሰማ ውስጧ እንደተጎዳ በጣም ያስታውቃል፡፡ ሲቀጥል ከቤት ውስጥ አራት ልጆች አሉ፡፡ እነሱን ማብላት፤ ማጠጣት፤ ማልበስ ብቻ ውስጤ የሆነ ነገር መጥቶ እየረባበሸኝ ቤት ባፈራው አቀማምሼ ተመልሳ ብስቁል ፊቷን እያየሁት የሻይ ገንዘብ ሰጥታኝ ሄደች፡፡

ከዛ በኋላ የኔ ህመም እና ስቃይ ተረስቶ እነሱን ለማፅናናት ስል በውሸት የሌለኝን ‹‹አሁን ገንዘብ አግኝቼ እቁብ መጣል ጀምሪያለሁ፡፡ ችግር የለውም›› እያልኩ ባልነበረኝ ማንነት 'ራሴን በችግር እየቆላሁ መልካሙን ለማሳየት ታናሽ ወንድሜን ጠርቼ በጋጣሚ ከተዋወኳቸው አሠሪዎቼ ለመጀመሪያ ጊዜ በኮንትራት የተቀበልኳትን ሥራ አብረን እንድንሰራ በስልክ ነገርኳቸው፡፡ እሱም ከዛ ገንዘብ ተበድሮ ተሳፍሮ ሲመጣ ሰውነቱ እጅጉን ሳስቷል፤ እንኳን ሥራ ልታሰራው ይቅር እና አይተህ በወንድምነት ራርተህ ቢኖርህ ለሱ የምትኖርለት ምስኪን ልጅ ነው፡፡ አንባሻ ገዝቼ ብላ ብለውም መብል ላይ ብዙም አይደለም እና እንቢ ብሎኝ ወደ ሥራ ተሰማራን፡፡ ሥራውን አጠናቀን አመሻሽ ከእኔ ጋር አድሮ ሙሉ ገንዘቡን ይዞ ይሄዳል ብዬ ባስብም ሳይሳካ ቀርቶ ‹‹እንቢ›› ብሎ ያለችኝን ስልሳ ብር ሰጥቼው ሸኘሁት፡፡

በጥላቻ የጀመርኩት ክላስ እያደር የሚያባባ እና መልካም እየሆነ መጣ፡፡ ይህ የሆነው መፀሐፎችን አብዝቼ ማንበብ ከጀመርኩ በኂላ ነው፡፡ በ'ርግጠጥ ከዛ በፊትም ሰመመን፣ ስደተኞቹ ፣ አሮማይ እና ባልጨርሳቸውም አልፎ አልፎ አንዳድ መፀሐፎችን አነባብብ ነበር፡፡ ከኮሌጁ የጀመርኩት የፍቅር እስከ መቃብር መፀሐፉ በልዞ ትንሽ ጠቆር ቢልም ለሶስት ቀን ያለምንም እረፍት ሁለት ሰዓት ገብቼ አስራ ሁለት ሰዓት እያወጣሁ ጨረስኩ፡፡ ከዛ በኂላ የአእምሮ ንጉስ ጥንታዊ የኢትዮጲያ ሰራዊት፣ የይስማዕክ ወርቁ ዣንቶ ዣራ፣ ዴርቶ ጋዳ ፣ ራማቶ ሐራ፣ የኢትዮጲያ ታሪክ ከመጀመሪያው እስከ አሁን፣ የመምህር ግርም የእምነት መፀሐፎች፣ THE MODERN HISTORY OF ETHIOPIA፣ አስራ አንደኛው እዝ፣ የአብዮቱ መባቻ፣ የአብዮቱ ዋዜማ፣ THE RIMENDERS OF ANNA FERANK፣ ሞሳድ ተልዕኮ፣ ሁቱ እና ቱትሲ፣ የቴድሮስ እንባ፣ የባሩዱ በርሜል፣ የተቆለፈበት ቁልፍ፣ ሰበዝ፣ ዛጉራ፣ መርብብ ……….. ብቻ ማቆሚያ አልነበረኝም፡፡

መምርነት ማለት የሞያዎች ሁሉ ታላቅ ንጉስ ነው፡፡ ሌሎቹን ፈቶ፣ የተዛባውን አስተካክሎ፣ የጎበጠውን አቅንቶ በእውቀት እና በጥበብ መሥራት የሚችል የእውቀቶች ሁሉ ኃያል አባት ነው፡፡ ዶክተሩ፣ ኢንጂነሩ፣ ፓይሌተሩ፣ ሳይንሲስቱ፣ ሲናተሩ፣ መካኒኩ፣ ቴክኖሎጂው፣ አርክ-ቴክቸሩ ብቻ የሁሉም መፍለቂያ ካንፓስ ውስጥ እንደመገኘት የሚያስደስት ምን ነገር አለ?! ምንም ነው ወንድሜ/እህቴ፡፡ ውስጤ ገነፈለ፡፡ ሁሉንም አቅሜ በቻለው መጠን ለመከታተል እና ለመስራት መወደድ አስገደደኝ፡፡

ረሃብም በንባብ ተረቶ የስዕሉ መምህር ለስዕል ያልነበረንን ጥበብ ከጉያው ፈትፍቶ በቀላል መንገድ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ለአንድ ሴሚስተር መገበን፡፡ የሳይኮሎጂው ጠቢብ ሳይኮሎጂን በብዕሩ ዐይኑ ቀልቶ ከጥቅም ወጪ እስኪሆን የአእምሮን ማንነት እና የሰው ምንነትን በታትኖ አሰጣጥቶ ጉድ እስኪመስል መገቡን፡፡ በጤናው ዘርፍ ሲሰጥ የነበረውም የኸልዝ ኒውትሬሽን ት/ትም ያቅማቸውን ችረው መልካሙን ሊመግቡን ጥረዋል፡፡ ጨዋታን አስናፍቀው በእውነት ተጫውተን ትውልድንም በቁም-ነገር አንፀን እንድናፈልቀው መጠነኛውን የጨዋታ ስልት ጥቂቶች አሳይተውናል፡፡

የነገሮችን ስያሚ እና ውክልና ምንም በማይናገር አለት ላይ አቁመው እንደ ፈጠሩት ጠቢባኖች እነዚህም በጥቂቱ አስታውሰው ሊያሳዩን ለሌላው እስከነ ጥቅሙ ማሻገር እንድንችል ያቅማቸውን አድርገዋል፡፡ አደራጅተን የተደራጀውን እንዴት አድርገን ማስተዳደር እንዳለብንም የተቀሩት ፊዝን አባታቸው አድርገው ለመቀለድ ቢሞክሩም አቅም በፈቀደ እና በኛው ጥረት ተመግበንዋል፡፡ የይቻላልን መንፈስ ሰጥተው መቻልን ለማሳየት ሌላውን አለም እንድናይበት የመጀመሪያዬ የሆነውን እና መሠረት የተሆነውን ቋንቋም ንጉሱ ሆነው ባይመሩትም በሚችሉት አቅም እና ችሎታ መጠን ለመዝራት ሞክረዋል፡፡

ሙዚቃውን ከፒያኖ 'ና ከሙዚቃ መሳሪያዎች ጋር እያዋደዱ ኖታዎች እንደ ፅሑፍ ተጽፈው እንደ ንባብ ትርጉም እንዲሰጡ ተደርሰው በተቻለ መጠን ለመዋሃድ ተሞክሯል፡፡ በግል ጥረታችንም ቢሆን የሰው ልጆች እርዳታ እና እገዛ ምን ዓይነት ቦታ ማድረስ እንደሚችል ልዩ በሆነው የልዩነት እገዛ እና ድጋፍ ላይ በተቻለ መጠን ለማየት ታድለናል፡፡

ከሥነ-ምግባሩ ምህዳር ብዙ መልካም እና የተሻለ ነገር እንዳለ እና የአለም መግባቢያ ቋንቋ መሆኑንም በተቻለ መጠን ለማሳየት ከሞከሩት ባለሞያው መምህራኖች ለማየት ችለን ለራሳችን

እስቀርተን ለሌላውም እንድንበጅ አድርጎናል፡፡ ክፋት እና ደግነትንም እስከ ጥግ አይተን ደጉንም አድንቀን ክፋቱንም ኮንነን እንድናልፍ ረድቶናል፡፡

ምንም ነግር የመውጫ እና የመውረጃ መንገድ ሳይኖረው እዳልተፈጠረ እንደ ከታብያን እና ፈጣሪ የቀባቸው ልሂቃን ያፃፉት መጸሐፎች ዘፍቀው እያነከሩ፤ ነክረውም እያወጡ አሳይተውናል፡፡ ላንፈራ ዓለምንም መጋፈጥ እንዳለብን በሰነፍ ረፍደኞች የረፈዳ  እና የትጉዎችን የህይወት መስታወት ምስል አድርገው እስከነ ነብሱ አሳይተውናል፡፡

በዚህ ውስጥ ግን አልጋ ላይ ብቻ የሆነ ነገር ምንም የለም፡፡ እንዳንዴ ወገብ ሲቆረቁር እንኳን መገላበጥ እንደሚያስፈልገው እግርም በርትቶ መውረድ ካልቻለ ህመሙም ሌላውም ተኳኛ ችግር ጠንክሮ ከተኛህመት ላያስቀርህ ምንም ዋስትና የለህም፡፡ ያለኸው ዓለም ላይ እንጂ ገነት ወይም ሲኦል አይደለህም፡፡

ዓለም የገነት እና የሲኦል ምሳሌ ናት፡፡ ከላይኛው ግን የሚለየው ይህኛው በሰው እና በሰው ልጅ የሚመራ ሆኖ ከሁለቱ አንዱን በፍላጎቱ መውሰዱ ነው፡፡ የላይኛውን ግን ይቅርታ አድርጉልኝ እና የቤታችሁን አመል በቤታችሁ ብቻ ነው፡፡

ግለኝነቴ በተቻለ መጠን በክፍል ጓደኞቼ እና በሥራ ባልደረቦቼ እየተሻሻለ ነው፡፡ ከእነሱ ጋር ለቡድናዊ ሥራ እየተወያየን በጋራ መወሰን ባለባቸው ነገሮች ላይ መወሰን እየቻልን መጣን፡፡ ታድያ በባህሪዬ ዝም ብሎ ሳቅ እና ፌዝ የሚያበዛ ሰው አይመቸኝም፡፡ ህይወት ህይወት ነው፡፡ ቀልድም በቦታው እንደዘው፡፡ አንዳንድ የሴት ጓደኞች በጣም ጠንካራ ከመሆናቸው የተነሳ ሥራ ቦታ ከት/ቤት እና ከምግብ ቤት እንጨዋወታለን፡፡ አብዛኞቹ የጤና፤ የቴከተኒክ እንዲሁም በአጠቃላዩ ከዩንቨርሲቲው በግላቸው ከፍለው የሚማሩ ናቸው፡፡ ከወንዶቹ ጋር ምንም ነገር ማውራት ነብሴ ነው፡፡ በቃ ሴቶችን ባልጠላም ከእናቶች ቀጥሎ ለወንድ ልጅ ያለኝ ክብር ግን ወደር የለውም፡፡

ወንዶች ሕይወትህን የምትቀይርበትን እና ከሰው ልጅ ጋር እንዴት በብልኂት እና በጥበብ መኖር እንዳለብህ በሥራ እና መተሞክሯቸው ሊያሳዩህ ይጥራሉ፡፡ ሴቶች ውስጠኔውን ሴት ሆኜ ባላየውም በተለይ ሚኒስትሪ ሳይክል በሚከሰትበት ወቅት እናቶችን ጨምሮ የዱር አውሬ ሲሆኑብኝ ከነሱ መፈጠሬንም እጠራጠራለሁ፡፡ በድንገት ስህተት ካጣኂት ፍቅረኛዬ በስተቀር በባህሪዬ ሴት ልጅን ማነጋገር የምፈልገው ልክ ወንድን ቀርቤ እንደማናግረው ነው፡፡ ከዛ የዘለለ ግን ሌላው እያለ እንደሚያስበው የለሁብትም፡፡ ጉረኛ ብትሉ ተቃራኒዬ ለሆናችሁ ሰዎች ይገባችኂል፡፡ ምክንያቱም ስሜት ከምንም በላይ መጥፎ ሊሆን ይችላል፡፡ ላንተ ወይም ላቺ ከብዶ ሀፅያት እና ሀራም ካልሆነ ሌላ አማራጭችን መጠቀም ይቻላል፡፡ ይህ ግን ከምንም በላይ አንተንም አንቺንም ፈፅሞ አይጠቅምም ከፈጣሪ ዘንድም ትጣላበታለህ፡፡ ከሆነ ግን አንዳንዶቻችን ከሰው ተፈጥረን የሰው ለሆነው የኛ ፍልቃቂ ሰውነት የእንስሳ ባህሪያትን ባንላበስ ለሁለቱም ፆታ መልካም ነው፡፡

በክላሴ ብዙ የምወዳቸው እና የማከብራቸው ሴት የክፍል ጓደኞቼ አሉ፡፡ ደስ ብለውኝም ከነሱ ጋር ለመዝለቅ የበቃሁት ከሌላው በተለየ ሁኔታ እህታዊ እና ወንድማዊ በሆነ ማንነት ተግባብተን ስለሁሉም ነገር በአግባቡ መነጋገር መቻላችን ነው፡፡ ሴቶች በባህሪያቸው የሚሉትን ብቻ ይፈልጋሉ፡፡ ያ! የማይሆንበት ደግሞ በጣም ብዙ ምክንያቶች  ይኖሩ እና ከተቃራኒያቸው ጋር ወደ አላስፈላጊ ግጭት ውስጥ ይገባሉ፡፡ ወንድ ደግሞ ተፈጥሮ የሰጠችውን ስጦታ ተጠቅሞ ያሻውን ማድረግም ይሁን ማስደረግ ይፈልጋል፡፡ በዚህ መሐል ጠብ አትጥሩብኝ እንጂ ወንድ ያሸንፋል ሴት ፈጣሪ የረዳው ነው፡፡ እንደኔ ግን በምንም ነገር መግባባት ካልቻልን ሴት እህቶቻችንን ባናስጨንቅ ምርጫዬ ነው፡፡

## እኛ!! የጨንቅ ዘመናቶች

ከዚህ ኮሌጅ በሚያስደስት በእውቀት ላይ የተመሰረተውን የመጀመሪያውን ውጤት አገኘሁ፡፡ በአንደኛ ሴሚስተር ከከፍሉ በሁለተኛነት ለትንሽ ተቀድሜ አጠናቀኩ፡፡ በ'ርግጥ ከሁሉም ሴክሽን በውጤት ከፍተኛው የኛ ነበር፡፡ አንደኛውም ሁለተኛውም እኛው ጋር ነበር፡፡ የዚህ ሁሉ ውጤት ምንጭ አብረውኝ የነበሩ ጓደኞቼ ቀናነት እና መልካም የሆነ ስብዕና ነው፡፡ ያልገባኝ እኔም እስካሁን እረገምበታለሁ ብዬ የማስበው ባልሰሩት የተሰራ ውጤት እንዲሰጣቸው እና እነሱ ሳይረዱ የተረዱ በማስመሰል ማቅረቤ፡፡

የአንደኛ ሴሚስተር ትምህርታችን በዚህ ተጠናቆ እኔም ከተጣላሁት ቤት ዘንድ ለመጀመሪያ ጊዜ ሄድኩኝ፡፡ ጥምቀት ነበር፡፡ ቤቱ ሞቅ ደመቅ ብሏል፡፡ ብዙ ጊዜ ሙዚቃ አንዳንድ ነገሮችን ለማስታወስ ስለሚረዳኝ ከአጎቴ ልጅ ጓሉ ጋር ሄጄ በጂፓስ እሲኪያሻኝ አዳምጣለሁ፡፡ እሱ ሲመጣ ከጓደኞቹ ጋር ይዞኝ ይሄድ እና ቀልድ 'ና አንዳንድ ቁም-ነገር አዘል ንግግሮቹ ትንሹ አለቃ ገብረ-ሃና ቢባል የሚጋነን አይደለም፡፡

ሀገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ማጠንጠን የጀመርኩት ገና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እያለሁ ነበር፡፡ አንዳንድ ባለስልጣናት ከስራ ባልደረቦች ጋር ሳይሻረኩ ይቀሩ እና በመርዝ እንዲሁም በተለያዩ ጥቃቶች ይሞታሉ፡፡ ከዛ ውስጥ አንደኛው የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳት አለማየሁ አቶምሳ ናቸው፡፡ ከዛ በፊት በታሪካቸው የማውቃቸው ታላቁ ሰው ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ እና በሽፍታነት ተፈርጀው እየታደኑ የተገደሉ ዘመዱ-አዝማዶቼንም ጭምር አስታውሳለሁ፡፡

ሀገራችን የምትተዳደረው በዲሞክራሲው ሥራ-ዓት ቢሆንም ከአፍ የዘለለ እንኳንስ ለዚህ ሥርዓት ይቅር እና ለሰበዓዊነትም አዳጋች የሆነች ሀገር ነበረች፡፡ በ'ርግጥ አንዳንድ ሚዲያዎችን በአግባቡ ስለምከታተል ኢትዮጲያ ከትናንቱ ዛሬ ላይ ዘመን ብላ የተሻለ እድገት ላይ ነች፡፡ ይሁን እንጂ በአንድ ሀገር ውስጥ የሰው ልጅ ተከባብሮ እና ተዋዶ የሚባባሉትን ተሰማምቶ መኖር ካልተቻለ በጣም የከፋ ችግር ውስጥ ነው ያለችው ማለት ነው፡፡

ሙዚቃ እና ታሪክ ይሄንን በሥነ-ሥርዓቱ ፍንትው አድርጎ ያሳየን ሲሆን ሌላኛው አቀጣጣይ በየነ-መረብ ውስጣችንን ይረብሽው ነበር፡፡ የኦሮሞ የሙዚቃ አቀንቃኞች በተለይ ሀጫሉ፤ ጃንቦ፤ ጫላ ቡልቱ፤.... የኢትዮጲያን ህዝብ ህመም እየጎረጎሩ ከኛው ወስደው ለኛው ያደርሱናል፡፡ የአማራ ሙዚቀኞች ፋሲል፤ ዳኛቸው፤ አንተነህ፤ በለቸው፤ መሐሪ፤ አምሳሉ.... በቁጭት የመቃብሩን ዘመን ፈነቃቅለው ለመውጣት በሚደረገው የማንነት ወኔ ውስጥ ገብተው ቁም አልነበረም ሙት ይቀሰቅሱ ነበር፡፡ ከትግሪኛ ሰለሞን፤ አብርሃም... ያለፈውን የስቃይ ዘመን ሲያስታውሱ ልላኛው አንጀት ቆርጥሞ የሚበላ ሀገራዊ ህመማቸው ነበር፡፡

እነዚህን ሁሉ የማስታውሰው ታላቅ በሆነው የሰው ልጅ ጥበብ ሙዚቃ ነው፡፡ ሲከፋህ ማፅናኛ፤ ስታጣ ማስተዛዘኛ፤ ሲጎልህ ማስተማሪያህ ብቻ አንተ መርጠህ ካዳመጥከው ሁሉንም ከነምስሉ ጠጠር እየለቀመ ቋጥኙን ከምሮ ያሳይኃል፡፡ የጥምቀት ማታም ያደረኩት ይሄንኑ ነበር፡፡

ጥምቀት እንደሚታወቀው ፅላቱ ከቤተ መቅደሱ ራቅ ወዳለ ቦታ ሄዶ የሚያድርበት እና የጌታችን የእየሱስ ክርስቶስ የመጠመቅን ተምሳሌት ምዕመናን ተጠምቀው ድነው የሚመለሱበት ነው፡፡ እንደ ሀገራችን ደግሞ ጎረምሳው ከኮረዳዋ የሚተጫጩበትም ጭምርም ሲሆን ሴት የማትለብሰው ልብስ የለም፤ ወንዱም የማይሽቀረቀርበት ከፈን አይኖርም፡፡ የሽቶው መአዛ፤ የአለባበስ ውበት በዛ ላይ ሳቅ ጨዋታ ተጨምሮበት ገነት ባላጋንናት የውስጡን ባላውቅም የውጪው ግን እዚሁ ጥምቀት ላይ ነው፡፡

ብዛት ያላቸው በሌላ ሀገር የሚኖሩ ተወላጆች በተለይ የዘመኔዋ አለባበሳቸው ሙት ቀስቅሶ ቋሚ ያስደነብራል፡፡ ታድያ አደራ ጉራ አልወድም እንግዴ ሳትዋሹ የነበራችሁ መስክሩ፡፡ ግን እኔ ሎሚውን ሲሉት እንጂ ሲወረውሩት አይቼ አላውቅም፡፡ ግን ማን አውቆ ያው እንግዴ የቤት ልጅ ሆኜ ከኋላ ሲወረወርብኝ ሽሽቼ አምልጬ ገብቼ ይሆናል፡፡ ጥምቀት በወረቡ፤ በዝማሬው እና በቅዳሴው ከቤተ መቅደሱ ተመልሶ ማምሻ ለፕሮግራም ቀጠሮ ተይዞልን ወደ ቤት ተመለስን፡፡

ከቤት እንደደረስኩ ወዳጅ ዘመዱ ተሰባስቦ ቤት ያፈራውን እየተቋደሰ ሳሎኑን በሳቅ ሞልቶ ደስታው ወደር አልነበረውም፡፡ ቀኑ በዚህ ተሸኝቶ አመሻሽ በብርሃኑ ላይ ነግሶ ወደ ቤተ-ክርስትያን አመራን፤ የሞንታርቫው ድምፅ ከቦታው ውበት ጋር ተዳምሮ ገነት አስመስሎታል፡፡ እምነትን ከበዓድ አምልኮ የለየሁት በነዚሁ አባቶች ሲሆን ከቤቱ ውስጥ ለሚደረግ ባዕዳዊ አምልኮት የተለየ ጥላቻ ስለነበረኝ ከቤተሰብ ጋር ከልጅነት እሳካሁን ያለመስማማቴ ትልቁ ችግርም ይሄው ነው፡፡

ጥቁር 'ና ዳለቻ ካባ የለባበሱት አባቶች ቆባቸውን አስተካክለው ማይካቸውን ከአንደበታቸው እያዋደዱ የሚያቀርቡት ፀሎት እና ስብከት አምሮን አንቅቶ ዐይኖች ስለ እውነት እንዲያነቡ ያደርጋል፡፡ መዝሙር እና መስተንግዷዊው ስብከት ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ በፀሎት ተጠናቆ በዛ ቁልቁለት አቀበት መንገድ እንደ ገነት መግቢያ በር እየተመምንበት ሰንበት ተማሪዎች በዝማሪ እጅበው ከተማዋን እያወዱ ሲመለሱ በ'ርግጥም ደሜ የሆነችውን ክርስትና ከልቤ በእውነት እና በምክንያት ወደድኳት፡፡

አዳሩም ቀን በተጀመረው ሽርጉድ ደምቆ ለሊት በሰላማዊ እንቅልፍ ተደቅሳ አነጋግ ወደ ወትሮ ት/ቴ ተመለስኩ፡፡ በቦርሳዬ የጥምቀትን ትርፍራፊ ይዣለሁ፤ እሷን እየቀማመሱ ሌላኛው ቀን ተመልሶ በረሃብ እንዳይቀጣኝ ሥራ ማፈላለግ ጀመርኩ፡፡ ከቤተሰብ ጋር የሚተዋወቅ አንድ የሰፈራችን የመንግስት ቅጥረኛ በአባቴ አማካኝነት አገኘሁት፤ እሱም በዛን ዓይነት ህይወት ውስጥ ይሄንን ማሳለፌ ለበጎ መሆኑን እየነገረኝ ከአከራዩ ባለቤት ጋር ሥራ እንድሠራ ከቤተሰቡ አግባባኝ፡፡ እሱ ከሚገባው በላይ ያዝንልኝ ስለነበር የማልችለውን አዝ አንኳን እንድችል ይችላል እያለ ሥራውንም ለምጄ እንድሠራ እጅጉን መልካምነቱን ችሮኛል፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ ከሥራ ለምሳ ሲመለስ ሥራ ላይ ስላገኘኝ ምሳ መብላት አለመብላቴን ጠይቆ ምሳ ከቤቱ እንድበላ ጋበዘኝ እንደ አውነቱ ከሆነ ምንም ገንዘብ ስላልነበረኝ ጥቂት ብር እስኪሰጡኝ እየጠበኩኝ ነበር፤ ግን እሱ መጣና ሁሉንም መልካም አድርጎ እሱም ወደ ሥራው እኔም ወደ ድርሻዬ ተመለስኩ፡፡ ቀኑ እንደምንም በሥራ ተገባዶ መቶ ብር ለመጀመሪያ ጊዜ እራቴንም እንዳሻኝ ደቁሼ ወደ ቤቴ አመራሁ፡፡

የቤቱ ባለቤት ማክዳ ትባላለች ደ/ኤባ ቀበሌ 05 አከባቢ የሚኖሩ ሲሆኑ አምሳያዬን በሞት እንዳጡት ይነግሩኛል፤ እኔም በጣም አዝኜ ምንም ነገር ሳይቀር በአግባቡ እና በሥርዓቱ ሰርቼ አስረክባቸዋለሁ፡፡ እናም እያደር መግባባት እየተጠናከረ መጥቶ ውሎ ገባዬም ከቤታቸው ሆነ፡፡ የቤት ክራይ የኮሌጁ ሞጅል መግዣ እና የት/ቤት የግል ሥራ ማተምያ እና የመመረቂያ ፅሁፍ ማዘጋጃ ብቻ ምኑ ቅጡ ገንዘቧ መቅኖ የላትም፤ በዚህ አገኘሁ ስል በዛ ጋር ሌላው ቀዳዳ ይዞት ይበናል፡፡

ታላቁ የሳይኮሎጂ መምህራችን አሸናፊ አንዳንድ የግል ፍልስፍናዎቼን እየሰጧቸው በአትኩሮት እያዩ ማለት እና ለማለት የፈለኩትን ከክፍለ ጊዜ ውጪ አብረውኝ በተለይ በሥነ-ባህሪ ላይ ቆም ብለው ያናግሩኛል፡፡ እንደ እሳቸው ቆሞ አንድን ተማሪ በእውነት እና በእውቀት ላይ ለተመሰረተ አስተምህሮት ጊዜ የሚሰጥ ሰው ማግኘት ይከብዳል፡፡ በሳቸው ክፍለ ጊዜ አንድ የግሩፕ ፕረዘንቴሽን ስለነበረብኝ ያዘጋጀሁትን ላቀርብ እጅግ ተርበትብቼ ሌሎቹ እንዲያቀርቡ ተማፀንኳቸው፤ እነሱ ግን ወይ

ፍንክች ብለው ላይሆን ነገር ልምምጤ በዝቶ 'ራሴው ወጣሁ። ለሌላ ጊዜ የሌለብኝ ፍራቻ ዛሬ ላይ በመላው ሰውነቴ ላይ ተደፍድፎ በደንብ ይታያል።

ፕረዘንቴሽኑ ጀመረ። መምህር በአትኩሮት እያዩ ነበር። እይታው አትኩሮት ስለነበረው በጣሙን ያስፈራል። ያ! ጭብጨባ ያስለመደኝም ተማሪ ለዘብ ብሎብኛል፤ ብቻ እንደፈራሁት አልቀረልኝም እና ያልተዘጋው ያለካርቦን ሥራ የጀመረው ቢሮዬ ተከፍቶ ባዶ ወረቀቱ ይታይ ነበር። ተማሪው ችግሬን ስለሚያውቅ ዝም ብሏል። መምህሩም እስክጨርስ ወረቀታቸው ላይ አቀርቅረው ነጥብ እየሰጡ ነው። እኔም ሳወኩት ነገር እነሱም አዝነው ከመተው የዘለለ ምንም ብለው ሊያሸማቅቁኝ አልፈለጉም እና ፕረዘንቴሽኑ አልቆ ከወንበሬ ተመልሼ በሀፍረት እየተሸማቀኩ ተቀመጥኩ።

እንደ ገባሁ ያለ ካርቦን የተሰጣ የወረቀት ቢሮዬን ለመዝጋት በግመል መሹለኪያ እስኪበቃው ከግራ ወደ ቀኝ ከቀኝ ወደ ግራ እያዋደድኩ አስተካክዬ ዘጋሁት። የት/ት ማገባደጃ የመጨረሻው ሴሚስተር እንደ መሆኑ መጠን መምህራኖች ለቀሪ ቻፕተሮች ትርጉም እና ዴንታ እየሰጡ አይደለም። ብቻ እንዳሻቸው ይገባሉ፤ ያሻቸውን ይዘበዝባሉ በቃ ትልቅ ሌላ ፈተና ያዘለ የቀልድ ጨዋታ ነበር። ግዴታ ውጤት ሞልቶ ብቻ ማባረር ስለነበረባቸው ሲላቸው በግል ሥራ፤ ሌላውን በቡድን አንዳንዴም ድንገታዊ በሆነ ፈተና አንዱ ከሌላው እያየ ማጨመላለቁን ተያይዞታል።

አጀብ ይላል ኦሮሞ ብቻ አንድ ቀን በጣም ተናድጄ ስለነበር ባላለቀ ምዕራፍ ላይ የተፈተነውን ኮርስ ከባለቤቱ ጋር በፍጥጫ ተያያዝን። እውነታውን ለማመሳከር ከሌላው ተማሪ ምስክርም ማፈላለግ የባለሞያው ተግባር ነበር እና ሁሉም 'ርግጥ ሆኖ ምንም መላወሻ ጠፋ። አማራጩ በድሮፕ-አወት ሌላኛውን ዓመት እንዲደግሙ እናደርጋለን ብሎ ማስፈራራት ነበር። በራሷ የምትተምመነው የመጀመሪያ ደረጃውን የተጎፀፈችው ተማሪ እውነቱን ላለመካድ መደገሙን ብታምንበትም ሌላው ግን በያለበት ርዕደ መሬት እንደሚውጠው ፍጥረት መንቀጥቀጥ ጀመረ።

በመጨረሻም ጉዳዩ በእኔው ላይ እየከረረ መጥቶ የጓደኞቼ ልመና በረታ። መካድ እና እንደ ተሳሳትኩም ያለ እውነት በውሸት ማመን እንዳለብኝ ተማፀኑኝ። ምንም ምርጫ አልነበረኝም እና ግርግሩን በፊት ለፊቴ እያየሁ እወነትን ቀብሬ ለሌላው ስል ሀሰትን አበሰረኳቸው። እነሱም ደስ አላቸው እኔም ውስጤ እየነደደ ላልዘሩት ዘር ፍሬ መፈለጋቸው እያስገረመኝ ለብቻዬ ተጠራሁ።

በእውነት እስከዛች የመጨረሻ ቀን ድረስ የጠራኝ አካል የክፍላችን አማካሪ መሆኑን አላውቅም ነበር እና እንደ አማካሪ መሆኑን እና የተፈጠረውን ችግር ዳግም ሊያብራራልኝ መሞከር ጀመረ። ያንን ሁሉ ምስኪን የጎዳሁበትን የእውነት ውሸት እንዴት ብዬ መካድ ዳግም ሌላ ክህደት መፈፀም እችላለሁ እና በንዴት አፍልቶ ቢሰጠኝ እንኳን አንደማልጨነቅ ደጋግሜ ዐይኑ እያየ ነግሬው ወጣሁኝ። ይባስ ሌላውን ጥርስ እያስነከሰብኝ ለማጋጨትም ሞከረ። ነገር ግን ከእርሱ ጋርም ሆኖ በቡድን ሥራ፤ በአንዳንድ ፈተና ሊያሳትፉኝ ቢፈልጉም ‹‹B›› ግን ማንም እንደማይነጥቀኝ ደጋግሜ አስረድቻቸው ነበር እና በራሴ እምነት ውስጡ እንደ እሬት የበገነ ከአምሳያው ከ60%ጎማምዶ እና አንዳንዱን ENCOMPLET ብሎም NO GRADE የሚልበት ምክንያት ስላጣ ያለሥራዬ ዜሮ እየሞላ 34% በመስጠት በግሬድ ሊቀጣኝ ያሻውን አደረገ።

ነገር ግን በፋይናል ከ40% ጥያቄ 39.5% በመመለሰስ በአጠቃላይ 73.5% በማምጣት የተናገርኩትን ‹‹B›› በፊቱ አስጠብቄ አሳይቼዋለሁ። እነሱ ግን ወትሮም ከዚህ ስላልተማሩ ያው!! ናቸው እና ት/ቱም ተጠናቆ የመውጫ ክረምት ደረሰ።

## *እኛ!! የጨንቅ ዘመናቶች*

በመፅሄት እና በጋውን ከተንቆጠቆጠ ሰው ውስጥ በደከረተ ልብስ መገኘት ከምንም በላይ ነውር ነው እና ራሴን ከሁሉም ነገር መደበቁ መፍትሄ እንደሆነ በማሰብ ነፈኩት፡፡

እንደ አውነቱ ከሆነ አሁን ላይ ሁሉም ነገር ከእጄ እየተገባደደ ነው፡፡ ክረምትም እየመጣ ስለሆነ የግንብ እና የአርማታ ሥራ እንበዛም አይኖርም ቤት ክራይ ከፍሎ ሆድንም ችሎ ክፉውን ወቅት ማለፍ አይቻልም፡፡ ደግሞ ለምንም እንደሆነ ባላውቅም በጣም ሆድ የሚሞረሙር ወቅት ነው፡፡ እናም ከተለመደው የሥራ ማስታወቂያ ቦታ ማዘውተር የየእለት ውሎዬ ሆነ፡፡ የሁለት ወር የቤት ክራይ ለመክፈል ደግሞ የግድ ማክዳ ሥራ እስክትሰጠኝ በጉጉት መጠበቅ ነበረብኝ እና ከልጇ ጋር ጭቃ አቡክተን አዘጋጅተን አንድ መቶ በር ይገፔ ሄጄ ለአከራዬ ከፈልኩ፡፡ እሳቸውም መምህር እንደመሆናቸው መጠን ሁሉንም ስለሚያውቁ ከምሳውም ከራቱም አቋድሰው አዲስ የሚሰሩት ቤት ስለነበራቸው የቤት ፓድ አስቆፍረው እዳዬን ሰረዙልኝ፡፡ የሥራ ማስታወቂያም እንደ አጋጣሚ ከከተማው የሥራ ማስታወቂያ ቦርድ ተለጥፎ አገኘሁ፡፡

ብዙ ጊዜ አንድ የምመላለስበት መልካም ጓደኛ ስለነበረኝ ለውድድር የአለባበስ ሥርዓት ራስን ለሚቀርቡ ነገሮች በሙሉ ዝግጁ ማድረግ እንዳለብኝ ስለሚነገረኝ ከሱ ዘንድ ሁሉንም አድርጌ ማስታወቂያው ከወጣበት ጅማ-ሰንበቴ አቀናሁ፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

## ተንኮልን ያልተላመደ ፈረስ ጋጣ የለውም!!!

አልዋሽም የሚባለውን ሁሉ ከመስማትም አልፌ በተግባር ሲሆን ስላየሁት የት/ቤቱን ር/መር ለመሳተፍ እንኳን እንድበቃ እንዲያደርገኝ ካልሆነ ግን ጉርሻም አጉርሼ ለመጠየቅ ብፈልግ በጣም ኮስታራ ተቆጪ ስለነበሩ ራሳቸውን በቁጣ ነቀነቁ፡፡ በ'ርግጥ እኔም ካሉ አይቀር ላስመስል ብዬ እንጂ መሳፈሪያውም ከሰማይ ርቆ ምጥ እንደሆነብኝ ማን በነገረልኝ፡፡ የአንድ ዓመት የሥራ ልምዴን እና የክላስ GRADE ሰጥቼ ለውድድር ቀረብኩ፡፡ የመጀመሪያው ፈተናዬ የፅሑፍ ሲሆን በርከት ያለ ነበር፡፡ ከወላጆች ጋር፤ ከተማሪዎች ጋር፤ ከሥራ ባልደረባ ጋር ስንገናኝ ምን ማድረግ እንዳለብኝ እና እንዴት ተጋግዘን ለአንድ ዓላማ መሥራት እንዳለብኝ የሚጠይቅ መጠይቅ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ እንዴት የት/ት መርጃ መሳሪያ ማዘጋጀት እንዳለብኝ እና እቅድ እንዴት ማውጣት እንዳለብኝ በተግባር ከአንድ ርዕስ ጋር የሚጠይቅ ነበር፡፡

ስለ ር/መሩ ከዚህ ቀደም እንደ እርሳቸው ፍትሃዊ እና አግባብ ያለው ሰው ስላላየሁ በጣም ገረመኝ፡፡ የፅሁፍ ፈተናው እንዳለቀ ስለራሴ እንድተርክላቸው አደረጉ፡፡ በርካታ መመዘኛ ፈተናዎችን በቃላቸው አቀረቡልኝ፡፡ እኔም በቻልኩት መጠን የተቻለውን ማብራሪያ ከመስጠት ስላልቦዘንኩ ሥራ በፍጥነት መጀመር እንዳለብኝ ከሄድኩኝ በኋላ ከት/ቱ መምህራን ጋር ተወያይተው እንደ ነበር በስልክ አበሰሩኝ፡፡ እኔም የሌላኛው ወር ክፍያ ቤተሰብንም ሆነ ሌላውን ጠይቄ ማግኘት እንደማይቻለኝ ስላወኩኝ የለተተች ብልድርብሴን እና ፎጣዬን ይዤ ከጅማ ሰንበቴ ከተምኩ፡፡ ቤት ክራይ ከደ/ኤባው ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም ከቤተሰብ ለመጠየቅ ግን በጉራ የታጀለው ማንነቴ ላያስችል አስሮ አስቀመጠኝ፡፡

የተከራየሁት እንደ ቀድሞው ከሸንት ቤት ጎን እንደመሆኑ መጠን ሙሉ ጉርጓዱ ያለው እኔው ቤት ውስጥ ነው፡፡ ፍራሽ የለም፡፡ ከዛ ተገዝቶ የነበረው የገለባ ፍራሽ እንዳላመጣው እንኳን እንደተለመደው በተባይ ተወሯል፡፡ እናም ከዛው ስለጣልኩት አንድ ማዳበሪያ ከስር አንጥፌ በላው ላይ ያቺን የለተተች ብርድ-ልብስ ደርቤ ፎጣዋን ከላይ ለብሼ ልተኛ ስል የሚነሳው ብርድ ሰውነቴን ያንዘፈዝፈው እና ከአካፋዩ ንጣይ መሐል ገብቼ እየቆረቆረኝ እንቅልፍ አይሉት መኝታ ሆኖ ከሦሥት ቀን በኋላ እንቁጣጣሽ ደርሶ ወደ ቤተሰቤ ሄድኩኝ፡፡ ያ! የእነሱ በትኳን የሞላ ቤታቸው ለኔ የገነት ቤት ነበር እና ዓመት በዓልን አሳልፈን የቤት ክራይ አስይዘው ላኩኝ፡፡

ቀናቶች እየነጎዱ የወር ደሞዝ ሊደርስ ከሥራዬ መገኘትን ብካንበትም እቀምሰው መከራ ሆኖ ምንም ስላልነበረኝ ቤተሰብን የመስቀል ማግስት ምግብ እንዲልኩልኝ አደረኩ፡፡ ፍትፍቱን እና ትልቁን ጉርማጅ ዳቦ እየቀማመስኩ የወር-ደሞዝ ደርሶ አንድ ሺህ አራት መቶ ለመጀመሪያ ጊዜ ተቀበልኩ፡፡ ለእንደኔ ዓይነት ደሀ በሚገርም ሁኔታ ትልቅ ብር ነበር ማለት ይቻላል፡፡ አንዳንድ ወጪዎችን አወጣጥቼ በጥቂቱ አስቤዛ ገበየሁ፡፡ በዛ ላይ ከጎረቤት ተግባብቶ መኖር የሚባለው ነገር አለ እና ከኔ ጎንም የገባው ተከራይ ቀለል ያለ የሚመስል ነገረ ሥራው በመልካምነት ላይ የተካነ ይመስላል፡፡ ብቻ ከቀረብኩት ሰንበትበት ብዬ ስለነበር ቤቱ ቤቴ መሆኑ 'ርግጥ ነው፡፡ ግን ወደ እኔ ቤት ይህንን ሰው ቤትህ ቤቴ ነው ብሎ ማስገባት ከምንም በላይ ከባድ ነው፡፡

በዛ ላይ በጣም እየተላመድኩት ስመጣ የሚያደርገውም ሆነ ሆኖ የሚያሳየኝ ነገሮች በሙሉ ከፊት አስጥቶ ከኋላ የሚወጋ ዓይነት ነበር፡፡ አንደበቱ እንደ ችኩል ሴት የተጣደፈ ነው፡፡ በጣም ማውራት ይወዳል፡፡ በዛው ልክም ደግ ለመምሰል ይሞካክራል፡፡ ግን ድብቅ መድፍ እንደሆነ በአንድ

ወቅት በቤተሰቡ ላይ ባደረገው ጥቃት ላውቀው ችያለሁ፡፡ ብዙ ጊዜ ቤተ-ክርስትያን ያዘወትራል፡፡ ነገር ግን እሱም ሆነ ጓደኞቹ እውነትን በውስጣቸው አምቀው ለማስመሰል ከመሳቅ ውጪ ምንም ቁም-ነገር አልነበራቸውም፡፡ ብቻ ግን ለራሳቸው ጎበዞች ናቸው፡፡

እኔ ደግሞ ለእንደዚህ ዓይነቱ ማንነት የታደልኩኝ ስላልሆንኩኝ ጭንቅ ብሎ አንገቴንም ቀና አድርጎ እነሱን ማየቱ እንብዛም አያስደስተኝም፡፡ ከቀን ቀን ህይወት እየተሳለጠች ውበቷን አሳምራ ወደ እኔው እየገሰገሰች ነው፡፡ በዛው ልክም እንደ እባብ የሚናደፉ ጊንጦቿን ከኋላዬ እያስከተለች እጅጉን እየተፈታተነችኝ ነው፡፡ ጠዋት የምወጣው ሁለት ሰዓት ነው፡፡ የግል ት/ቤት እንደ መሆኑ መጠን አብዝተህ የምትለፋበት መስሪያ ቤት ስለሆነ እስከ አስር ሰዓት ወጥሬ እሰራለሁ፡፡ አስራ አንደኛዋን ደግሞ ለጥናት ወገቤ እስኪረግድ እሰራለሁ፡፡ ደግነቱ እንደ ሌላው ት/ቤት አስራ ፐርሰንቷን ጨምሮ የጥናት የሚካፈለን አልነበረም፡፡ ርዕስ መምህሩ ከዚህ በፊት በከተማው ላይ ብዙ የአስተዳደር ሥራ ሰርተዋል፡፡ በጣም ቆራጥ ናቸው፡፡ 1+1= 3/2/ን በደንብ ያውቃሉ፡፡

እንደ እርጅናቸው ነገሮችን የሚዘነጉ አይደሉም፡፡ መጠምዘዙንም ማቅናቱንም ባስፈላጊው ቦታ በደንብ ይችሉበታል፡፡ ከሥራዬ እወጣለሁ፤ ባለሀብት እንዳሻው እፈነጫል፤ ምንም ቢል ቁልፉን አስረክበው ለመሳቅ ዝግጁ ናቸው፡፡ ባለሀብቱም እሳቸውን የመቅጠሩ ትልቁ ቁም ነገር ይሄው ነው፡፡ በራስ መተማመናቸው እና በሁሉም ሰው ያላቸው ተቀባይነት ወደር አልነበረውም፡፡

ማታ ላይ ወደ ቤት ስመለስ ሰውነቴ ለቶ የእለት እቅዴን ካሰናዳሁ በኋላ እንቅልፍ ተጫጭኖኝ ምንም ሳልሰማ ንጋት ወከክ ብሎ ወፎች እየተንጫጩ ይቀሰቅሱኛል፡፡ አንዳንዴ ተቀያሪ ሸሚዞችን ስላልገዛሁ ከጋዎን ስር የምለብሰውን ነጭ ሸሚዝ ሁሌም አጥቤው ከዛው አሰጣው እና ጠዋት ደርቆ ልብሼው እሄዳለሁ፡፡ በ*ርግጥ የምተኛበት ፍራሽ ገንዘቡም በቅቶኝ ለመግዛት አልቻልኩም፡፡ ሆድ ጠገብ ካለ ሰውነት ሁሉንም ይችላል እና እኔም ሰነፍ ብዬ ገንዘብ ሳላጠረቃቅም የአስቤዛው ወጪ እና የአንዳንድ ጉዞ እና ክፍያዎች ተዳምረው ወርም በደሞዝ ለመደረስ አስቸጋሪ ሆነብኝ፡፡

እኔ የምንም ሱስ የለብኝም፡፡ መብልም ቢሆን ከተገናኘን እንጂ ካልተዋደድን ችግር የለብኝም፡፡ ግን ማምሻ ላይ የወጉ ነው እና ሳልቀምስ ማደሩ ትንሽ ከውስጥ የማቃጠል ስሜት ስለሚፈጥርብኝ ግድ ነው፡፡ ከዛሬ ነገ ከገንዘብ አጠረቃቅሜ አንዳንድ ነገሮችን ለቤት መገልገያ ብገዛም ከዛ ተርፎ ግን ለአልጋ እና ፍራሽ የሚሆን ገቢ ማግኘት አልተቻለኝም፡፡

ት/ቤት በተለይ ሰኞ አከባቢ ሕጻናት እንደ መሆናቸው መጠን ደብተራቸው የቤተሰብ ማንነታቸውን ያለፈውን የማስተወስ እና ወደ ቀጣዩ ለማለፍ ደግሞ የነሱን በቤተሰባቸው ውስጥ ያለውን ችግር በደንብ ያሳያል፡፡ ለኔ ደግሞ እንደዛ ዓይነት የደከረቱ እና የተበጫጨቁ ወረቀቶች ት/ቤት እንደመሆኑ መጠን ተቀባይነት ያሳጣኛል እና ዳግም የተበላሸውን ደብተር ከቤተሰቡ ጋር ተነጋግሮ ለማስተካከል ጥረት አደርጋለሁ፡፡ በ*ርግጥ ለንባብ እና ለመለማመጃ የሚቆሽሽ ደብተር አለ፤ ለሱ ግን ኃላፊነቱን ራሴ ስለምወስድ እነዛ ተማሪዎችም የሚያሳዩት አቅም በጣም የሚያረካ ስለነበር እጅግ ደስ ብሎኝ እቀበላለሁ፡፡

ሕጻናቱ እጅግ በጣም ጎበዝ ናቸው፡፡ ነገር ግን ባልተቀረፀ ቤተሰብ ውስጥ የተፈጠረን ንፁ ወረቀት እንዳያበላሹት ከመታገል ውጪ በመንግስትም ደረጃ የሚሰጠው ትኩረት አናሳ እንደመሆኑ መጠን ከባድ ነው፡፡ ግማሹ ልቅ በሚባለው የልጆች አስተዳደግ የመጣ ነው፤ ሌላው አንባገነን በሆነ ሲሆን የተቀረው ምደባ ለመስጠትም የሚያስቸግር ነው፡፡ ማዕከላዊ የልጆች አስተዳደግን እዛ ውስጥ ማየት ግኝ የማይቻል እዳ ነው፡፡

*በሕጻናት ላይ መልካሙን ነገር ከዘራህ መልካሙን ታገኛለህ። ካልሆነ ግን እጅግ ከባድ የሆነውን ግድያ በትውልድ ላይ ታዘምታለህ። አንዳንዱ ወላጅ ከልጁ በላይ መማር ያለበት ሲሆን ይህንን ተቀብሎ ባለሞያው በሚመራው መልኩ የተሻለውን ለውጥ ለማምጣት ፍቃደኛ አይደለም። በተለይ በኬ.ጂ ላይ ያሉ ህፃናት 80% ከወላጆቻቸው ጋር ስለሚውሉ ትልቁን ማንነት የሚወርሱት ከቤተሰባቸው ነው። ከት/ቤት ሲቀሩ፤ ትምህርታቸውን በአግባቡ መከታተል ሳይችሉ ሲቀሩ የሚፈጠረውን አደጋ ማሰብ የሚያዳግት አይመስለኝም።*

*ምክንያታቸውን አጣርተን ልንረዳቸው በምንሞክርበት ወቅት እንኳን ሲሰጡን የሚፈልጉት ምላሽ ሆድ እና ጀርባ ይሆን እና ምክንያቶችን ደርድረው ለማምለጥ ይሞክራሉ። አንዳንዱም ለመሳደብ የሚቃጣው እና የሚያደርገውም የትዬለሌ ነው። አመስግኖ መርቆም የሚሰናበተው በዛው ልክ ነው። ሕጻናቱ ምንም ስለማይደብቁ ሁሉንም ለኛ በቃል፤ በተግዳሮት እና በተለያዩ አካላዊ ችግሮቻቸውን ያስረዳሉ። ያንን ሰምቶ ወላጅ ከማስተካከል ይልቅ ሕጻን ላይ እያፈጠጡ መምህሩን እና ትምህርቱን እንዲያስጠላው የሚያደርጉም አልጠፉም ነበር። የራሳቸውንም ጭንቀት ለሌላው አጋርቶ ከመፍታት ይልቅ ነገርን ደፍድፈው የሚከምሩም አልታጡም ነበር። ነገሩ ግን ፍየል እና ቅዝምዝም ወዲህ እና ወዲያ ሆኖ ላይጥ የገንዳ ውሃ መውጫ ታጥቷት ይቋጫል።*

*በማማከር እና አስተዳደር ሥራ ላይ ኅበዝ ነበርኩኝ። በዛ ላይ የተለያዩ ቋንቋዎችን መቻሌ ትልቅ ጥቅም ስለነበረው። የአመራር ሥራዎችን ከነሱ ጎን በተጓዳኝ ሁኔታ በጥንካሬ እሰራ ነበር። የተለያዩ የስልጠና አውደ-ረዕዮችን ት/ቤቱን ወክዬ እሳተፋለሁ። ተርጉሜም በአማርኛ ለሌሎቹ አቋድሳለሁ። ተግባራዊነቱ ሁላችንም የምናውቀው ሆኖ ግን ምንም ሳይቀር በተቻለ መጠን በኔ እና በስልጠናው መሐል የሚደረገውን ልምድ አካፍላለሁ። የተለያዩ የክበብ ሥራዎችን በመሪነት አስፈፅማለሁ። ቀና የሆነ ይሰራል ቀና ያልሆነ ለመላተምም የተለያዩ ግብብ ለመፍጠር ይሞክራል ግን በማቻቻል እና በማሳዘን እንዲሰራ ይሆናል።*

*የሚገርመው አንዳንዱ ለምን ወደ መስሪያ ቤት እንደሚመጣ የሚዘነጋም አለ። ሥራውንም ረስቶ ሥራም የሚጠይቅ ገራሚ ሰው አለ። እሱ ሁል ጊዜ ሥራው እንደሚያዘው ሊነግርህ ያሻል። ነገር ግን ሥራው አንደበት አጥቶ እስኪጠራው ይጠብቃል። ብቻ ትንሽ ከባድ ህይወት ውስጥ የገባሁበት ወቅት ነበር። አንዳንዱ ወላጅ ደግሞ ልጄ ቢያውቅ ብሎ በእግሩ ረጅም መንገድ እየተጓዘ ምንም በሌለው ገንዘብ ለጥናት እና ወርሃዊ ሲከፍል ውስጥን አድምቶ መኖርን ያስረግማል። አንዳንዱ በሥራህ ረክቶ ከቤቱ እንድትመጣለት ጎንበስ ቀና ሲል ራሱን መቀበል ያቀተው ከራሱ የተጣላው ግን ካርድ እንኳን ወስዶ እስከሚሄድ በጎሪጥ ያይሃል።*

*አንድ ዓመት በእንዲህ መልኩ ተጠናቀ። ህሌና ብዙ ጊዜ ካልመጣሁ ስለምትለኝ በዚሁ ጊዜ የጓሳ ፍራሽ ገዝቼ ልጠራት ስላሻሁ እንደነገ ልትመጣ ፍራሽ እንደዛሬ ልገዛ ገንዘብ ከአስቤዛ ተርፎ ስላልበቃኝ ከጠራኋት በኋላ እንድትቀር ደውዬ ነገርኳት። ነገር ግን አሷ ተዘጋጅታ ስለነበር መቅረት እንደማትችል ነግራኝ መጣች። በጣም ሰነፍ መሆኔን አወኩ። ከጓደኛዬ ቤት በተደጋጋሚ ጊዜ እገባለሁ። እሱ ግን ቤቴ እንዲገባ ስለማልፈቅድለት ከበር እመልሰዋለሁ። እናም ከመምጣት ያልታቀበችውን እናቴን በካፌ ላሰናብታት ብፈልግም ሳይሆን ቀርቶ ከቤቴ ካልሄደች እንደማትመለስ አሳወቀችኝ። አስቤዛ ሁሉም ተሟልቷል ግን መኝታ የለም።*

*ከፈለገች ደስ ብሏት ሁሉንም ካሻችው ብዬ ከቤቴ ይዣት ስገባ ከት ብላ ሳቀችብኝ። ምንም አላልኩም በወሬ እያቃለድኩ የውስጧ ንዴት በፊቷ እየታየ ከቡናው፤ ቤት ያፈራውን ብዬ ከሰፈር ድረስ አድርሻት ተመለስኩ። ስንመለስ ብዙም ልታዋራኝ አልፈለገችም። ባጭሩ የዘነጋሁት ነገር ነበረኝ*

አገልግል ሰው ጋር ሄዶ ባዶውን አይመለስም እና እኔ ግን ትልቅ ጥፋት ሰራሁ። ልጅ ሳለን መንገድ ሄደው ሲመጡ አገልግላቸው ትፈተሻለች። እናም ወይ ከፍትፍቱ ካልሆነም ከዱቄታ ዱቄቱ ክላዘጋጁም ከፍሬው እናገኛለን። እኔ ግን ነገሩ ከቤት ከደረስን በኋላ ቢገባኝም ምንም ማድረግ ስላልቻልኩ ከዝምታ በቀር ትነፈሳም አልነበረኝም ክረምትን መሰረታዊ የኮንፒውተር አጭር ኮርስ ግንቦት ጀምሬ ከደ/ሌባስ ስወስድ መስከረም ጠባ።

ኒካውላ የዛሬ ሁለት ዓመት በፌስቡክ በየነ-መረብ ባገኛትም ላላወራት ብወስንም የኢሞ በየነ-መረብ ስከፍት ብዛት ያላቸው የሰፈሬ ልጆች ጓደኝነት ጠየቁኝ። ከዛ ውስጥ እሷ አንዷ ነበረች። እንዳላወቀ ሰው ለበርካት ቀናቶች ስታናግረኝ ብትቆይም በመጨረሻም ራሴን እንደ አዲስ አስተዋውቄ ዳግም ማዋራት ጀመርኩ። እንደ እውነቱ ከሆነ አሁን እኔ ጋር አይደለም ለሌላው ለእሷም የሚሆን ቅንጣት ቦታ የለኝም። ምክንያቱም ቀድማ ስራዋን በአግባቡ ተወጥታለች። እኔ ግን ከጀመርኩ አይቀር ላስጨርስ ብዬ ጉዞዬን ቀጠልኩ።

ያለፍኩትን ዘመን ሁሉ በእውነቱ አጫወትኳት እሷም እንደዛው አደረገች። ነገር ግን በመፃፍ እና በቃለ ምልልስ ያላቆመው ንግግራችን ሳላስበው ወደ ጋብቻ ህይወት ጥየቃ ገባች። እኔም ክፉ ባላስብባትም የዋዛ አልነበርኩም እና ከአካሄዷ እስከ አድራሻዋ በሌላ ሰው እየመሰልኩ አጫወትኳት። በ*ርግጥ የታሪኩን ባለቤት እስክታውቅ በጣም ብትቸኩለም ቀናቶችን አርዝሜ እሷው መሆኗን ስነግራት ደነገጠች።

እኔም ያልሆነ ስሜት እንደ አዲስ ሊያገረሽብኝ ቢሞክርም ራሴን እየገዛሁ ማስጨነቁን ተካንኩበት። ነገር ግን ካሳብ የዘለለ ሌላኛወን የፍቅር ጥያቄ ሊዋጥላት አልቻለም። የኔም ንዝነዛ በርትቶ ለበርካታ ሰዓታቶች ብናወራም የሚቀየር ነገር ሳይኖር የኔም የሙከራ ፈተና በዚህ ላይ ተደምድሞ በእህት እና ወንድም በአስፈላጊው ጊዜ እንገናኛለን።

• * *

የተማሪዎች ምዝገባ ነሀሴ መሐል ላይ ስለነበር ለምዝገባ ወደ ስፍራው ዕረፍት በሆነ ወቅት እመላለስ ነበር። ምዝገባው ተጠናቆ መስከረም 21 ት/ት ስንጀምር ባለፈው ዓመት 36 የነበረው ከሁለት እጥፍ በላይ ጨምሮ ወደ 100 ተማሪዎችን አስመዘገብን። ነገር ግን ማህበረሰቡ እና ት/ቢሮው ካስተዳደሩ ጋር መልካም የሆነ ግንኙነት ስላልነበራቸው ይህ ዓመት የነቀፏ ሆኖ መምህራንም እርስ በእርስ እየተጎሻሸሙ ሌላ ችግር ተፈጠረ።

ከራሱ የተጣላ ሰው አስታራቂ የለውም እና ለማጅ መምህራንን መገራት አባይን ተሸክሞ እስከነ ጉዱ መንገላታት ነው። ምክንያታም በእጅ ይዘህ ልታስቀረው ብትሻ በእግሮችህ መሐል አልፎ ሲሄድ ታየዋለህ። በመላ ሰውነትህ ከጭቃው ተኝተህ አታስቀረው ጎርፍ ሆኖ ይወስድህ እና መከራው መዓት ነው። ብቻ እንደዛ ዓይነት ሆኖ በጣም የምታስጨንቅ አንዲት ሴት ተከሰተችብኝ። መነሻው የቋንቋ መቻል አለመቻል ነው። ፈጣሪ ላንተ ሊሰጥህ የሚችለው ላንተ የሚጠቅምህን ነገር ብቻ ነው። ያንንም ልታዳብረው የምትችለው እስከ አስራ ስምንት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው። እንደዛም ሆኖ የሰው ልጅ ነህ እና ላትሰጥ የምትችለው ብዙ ነገር አለ እና ያልተሰጠህን ነገር በመልካም ነገር ተቀብሎ መኖርን የሚያህል ምንም መልካም ነገር የለም።

ልጅቷ እኔን በዲፕሎማ እና በጀመረችው የድግሪ ማኔጅመት ደረጃ ት/ት ትበልጠኛለች። እናም በሌላ ቋንቋ የማወራው ነገር በጣም ውስጧን ስለረበሸው ሰላሟን አጥታለች። ይቺ ልጅ በዚህ ብቻ ያለ

ምክንያት እንዲህ ልትሆን አልቻለችም። እናም ነገሮችን በአንክሮ ሳጣራ ጎረቤቴ የወንድሙ ልጅ ከዛው ስለሚማር በአንድ ዲፓርትመት ላይ ችግር እንደነበረ አማክሮኝ ነበር። እናም የሚመለከተውን አካል ጠቁሜ እንዲያናግረው መራሁት። ስህተትን መቀበል ያልቻለው ማንነት መሳሳቱ ሞት መስሎ ስለታየው እና ያለበትን ጫና ጭምር ከሌላው ስለሰማ ክፉኛ ተጎድታለች።

እውነቱን አረጋግጬ ሁሉንም በራሴ ችዬ ለማረጋጋት ብሞክርም የከራስ በራቀ ምንነት የተጎደፈረው አስተሳሰቧ ገኖ ብቅላን በየቦታው ትፈልገኝ ተያይዛለች። በሰዓት ጉዳይ፤ ሰርተ ፍኬት የለውም፤ የአስተዳደሩ የዘመድ ልጅ ነው፤ ይሄንንም ለሷ ካስደሰታት እንዳሻት ትሁን ብልም። የጀመረችው በቀል በእንባዋ ገኖ ይባስ ካስተዳደሩ እሰጣገባ ውስጥ ገብታ ላትችው ራሷን ጎዳች። ስለ እውነት በጣም ስላሳዘነችኝ የኔን በደል ትቼ ሁለቱን አሸማገልኩ። እሳቸውም እንደ እህት እና ወንድም ስለሚያዩን የኔን ትህትንና እይተው ለይቅርታ እጃቸውን ሲዘረጉ ከራሱ ያልታረቀው ማንነቷ አስመስሎ ወጣ። እንደ እውነቱ ከሆነ ጓደኛ ካልኩት ጎረቤቴ ጋር ኃይለኛ ችግር የነበረ ይመስለኛል። ሲበዛ ሥራም ጭምር ቶሎ ቶሎ አግኝቶ የሚሰራ ስላልሆነ ለኔ ቅን አመለካከት የለውም። ምክንያቱ ሁሉም ነገሮቹ በእውነት እና በአትኩሮት ላይ የተመሰረቱ አይደሉም። ብቻ ማስመሰልን ከልቡ የተካነ ነው።

በዛ ላይ ከቤተሰብ ሳይስማማ ቀርቶ ለብቻው ተከራይቶ የሚኖር ሲሆን ብዙ ጊዜ እየሄደ ይጋጫቸዋል። ሲያሻው የተቦካ ሊጥ ይደፋባቸዋል፤ የኤሌትሪክ ምጣድ ይሰብርባቸዋል። ብቻ ሰው መስሎ ባህሪው ወጣ ያለ ስለነበር አስቸጋሪ ነው። በቻልኩት መጠን መልካም እንዳልሆነ የበኩሌን በምክር አጋራዋለሁ። በሥራም ጭምር ሳይት ድረስ እየሄድኩ አግዘዋለሁ። ዕድሜውም በጣም እየሄደ ስለነበረ ማግባት እንዳለበትም በጎን ሸንቆር አደርግለታለሁ። ታድያ ሲመስለኝ ማስተዋልን ያልተካነው መግባባቱ ‹‹ለአወኩሽ ናኩሽ›› ዓይነት ሁነት ሳይጋብዘው አይቀርም። በግልፅም ላናግረው እና ልግባባው ብሞክርም ከተረት ተረት የዘለለ ሌላ መልክም ቁምነገር አልነበረውም። ብቻ እንስቃለን እንጫወታለን። የወመህ አካል እንደመሆኑ መጠን በሥራ ጉዳይ ያሉ አንዳንድ ድክመቶችንም እናወጋለን። ይህ ግን ለኔ ለማጠናከሪያ እንዲሆነኝ እንጂ ከሌላው ጋር የሚያጠራምስ አጀንዳ እንዳለው የሚያሳብቅ (የሚገልፅ) ነገር አልነበረውም።

መምህርቷ ግን ካለባት ጫና አንፃር ሌላውም መምህር ሊያግዛት ቃል ቢገባም በሸንፈት ማሸነፍን ያልፈለገው ማንነቷ ጭራሽ ከሁሉም ያናክሳት ጀመር። ክላስ በአግባቡ አትጠቀምም። ሲያሻት ለሰራችው ጥፋት በይቅርታ ምትክ ድርብ ጥፋቶችን እንደ እንቁላል ትፈለፍላለች። እዚህ ጋር እኔ ትልቁ ጥፋት በ*ርግጥም ከማላውቀው ሰው ለልምድ ብዬ እንደ ህግም አንድም ድክመት እና የመንስኤ ሀሳብ መጠየቅ አልነበረብኝም። የኔ ትልቁ የጥፋት ውድቀቴ እሱ ጋር ነበር። ብቻ ሴቶች ለብቻቸው ቡድን ያዙ። እኔም ወደ ሥራዬ ስለማተኩር ብዙም በሥራ ምክንያት እንኳ የምንነጋገርበት ጊዜ እንዳይኖር አድርገን በሥራ ዘጋነው።

ይህም ሆኖ በቡድን የተቋደሱትን ተባእት እና እንስት በዛም አለ በዚህ በኔው የአንድ ማድረግ ሀሳብ ይገቡ እና ዳግም ወደ ነበሩበት በማስመለስ እተጋለሁ። ነገሩ በዚህ ቀጥሎ ለራሱ እንኳን ራሱ መኖር ያቃተው ማንነት ሥራ ለመልቀቅ ወስኖ ተነሳ። ነግር ግን ስሙ ከአንዳንድ ሥራው ጋር እንደ ሸማ የተበጣጠለው ር/መር እስከ በሽታዋ እያስታመመ ሥራዋን እንድታጠናቅቅ አባታዊ በሆነ ምክር መክሮ ወደ ሥራዋ መለሳት። በስተመጨረሻም ችግሩ ራሱን ያገጠጠው የእንግሊዘኛ ቋንቋ ሆኖ ተገኘ። በርግጥ በዚህ ቋንቋ እንኳን ያለዲፓርትመንቱ ያለ ለማጅ ይቅር እና በሥራው ላይ አቅሙ አለኝ የሚሉት ምሁራኖት ብዙም አይደሉበትም። ብዙኃኑ የኢትዮጲያ ተመራቂዎች እናም አስመራቂዎች ጭምር የዚህ ቋንቋ ችግር አለባቸው። ይህ ደግሞ በት/ት ካሪኩለሙ ውስጥ ምንም ዓይነት ሥራ

አለመሰራቱን ራሳቸው ምስክር ናቸው። በተለይ በዚህ የቋንቋ ሞያ የሚሰለጥኑ ባለሞያተኞች ብዙ ጊዜ ለሌላው ለማስረዳት ብዙ ይለፋሉ። እሱም በፎርምላ መልክ የያዙትን እንጂ በእውቀት ላይ ተመስርቶ እወነት የሆነውን አይደለም።

የእሷ ጭነቀት እና ፍራቻም ይሄው ነበር እና በ*ርግጥም ተናግራ ር/መሩ እንዲያግዟት አደረገች። እሱም ሌላ ስንፈት ስለነበር በራሷ ተቋቁማ ሁሉን ነገር ማድረግ ስላልቻለች  የመስሪያ ቤት ዘመዶቿን በመኪና አሰባስባ የሥራ ውል እና የዋስትና ዶክመንቶችን እንዲሰጧት ተማፅኖዋን ቀጠለች። ር/መሩ ግን ለዚህ የሚበገር አልነበረም እና በህጉ መሰረት የፈረመችውን የኮንትራት ውል ማጠናቀቅ እንዳለባት ካልሆነ እና አሳማኝ ሁኔታዎች ከተፈጠሩ ለአንድ ወር ሌላ ባለሞያ እስኪተካ መቆየት እንዳለባት በፈረመችው ውል መሰረት አረጋግጠው መለሷቸው።

ስለ እውነት በጣም ታሳዝናለች። በዛ ላይ ሲበዛ ቂመኛ እና እንደ ነበር መኮፈስ የሚቀናት ነች። ከሴቶች መስርታ ስትመራው የነበረውም ቡድን ከአንገት በላይ እየሆነት መጣች። ደብዳቤውም ሳይገባ ሌላ መምህርም ሳይቀጠር ፍንጭ የሆናት አሳምኝ ምክንያት በባለቤቷ የሥራ ስምሪት ተሳክቶላት እንደ ታመመች በማስመሰል ለት/ቤቱ ሪፖርት ተደረገ። እውነት የመሰለው መስሪያ ቤታችን ሶስት ሳምንት እየሸፈኑ ለመስራት ቢሞከርም ሳይቻል ቀርቶ ወር በሳምንታቶች ነግሶ የቅጥር ማስታወቂያ በየቦታው ተሰራጭቶ ሌላ ቅጥር ተደረገ።

‹‹በደሞዝ ጨምሩ›› ክርክር ላይ የነበረው የመምህራን ጥያቄ በአዲሱ ተቀጣሪ የቅጥር ሁኔታ እጅጉን ተበሳጭተው ስለነበር መታመሟን ማስመሰሉን ተክነውበታል። *ርግጥ ነው እኛን ገንዘብ እንደሌለ ሲነግረን የነበረ ድርጅት ከዛሬ ነገ የተሻለ ከአንድ ሺህ ብር ደሞዝ ተጨማሪ ይከፍላል ተብሎ በሚጠበቅበት ት/ቤት ውስጥ አዲስ ቅጥረኛ አራት ሺህ ብር መቀጠር ማለት እኛንም ከሥራው እንደ ማባረር ይቆጠራል። ‹‹ነገሩ ዳመናው ዝናብ አርግዞ›› እንደሚባለው ሆኖ እርስ በእርስ መፈራራቱ ነግሶ ክረምት በግቢያው ደረሰ። ሁላችንም ለመውጣት ወስነን ስለነበር ሌላ ኮንትራት እንዳንፈራረም ስንጠብቅ ቅጥረጠኛው ጆሮ ጠቢ መረጃው አዳቁሶ የክረምት ክፍያ እንደማይከፈለን በማስፈራሪያ እንድንፈርም ሲያደርጉ በሀሳቡ ያልተስማማች የሥራ ባልደረባችን ነገሩን በግልፅ አስረድታ ስራዋን ለቀቀች።

ከአንድ ሁለቴ በደሞዝ ጭማሪ ላይ ስላታለሉን እኔም ማካካሻ ላደርግ እንጂ ትክክለኛው ቴንፖ እነሱ ጋር ስላልነበረ ጥሎ ለመውጣት ወስኛለሁ። በዛ ላይ ከአራት ዓመት በፊት የጀመርኩት የፅሁፍ ሥራ በበተን ስልክ ኢሜል ውስጥ ስለነበር አውጥቼ እስካሳትመው ቸኩያለሁ። አንደኛው ዓመት ከሥራ በተንዳኝ መረጃውን የሚያወጣልኝን የሶፍት ዌር ባለሞያ ስፈልግ ነበር። መገናኛ የቴክኖ ካንፓኒ፤ ቦሌ መደሃንያለም፤ ሴኔት፤ ይርጋ ሃይሌ ቶፕ ቴን …… ብቻ ያልሄድኩበት የለም፤ ምንም ነገር ሊሳካ አልቻለም። በዚህ መሐል ወደ በረራ ስመላለስ ነበር የደላላ ሥራ አግኝቼ በአምስት ሺህ ብር ላይ የሁለት ወር ደሞዜን ጨምሬ አልጋ እና ፍራሽ ነበር የገዛሁት።

አዲሱ ቅጥረኛ አመጣጡ ሞጆ ላይ መዘረፉን ለኛ በማብሰር ነበር የተቀላቀለን። እኔም ለዚህ ዓይነት ሰው የሚጨክን አንጀት ስላልነበረኝ ያለኝን በሙሉ እያወጣሁ ወር እንኳን መድረስ እስኪያቅተኝ እጋብዘው ነበር። ንግግሩ የጥንቆላ ጥበብን መሠረት ያደረገ ነው። እኔ ደግሞ ጥሎብኝ ከቤተሰብ የመጣያ አንዱ ችግሬ ስለነበር ፊፅሞ እንዳያወራብኝ አጀንዳ አስቀይረዋለሁ። ብቻ እንደሱ ክፍለ ሀገራትን መጥቀስ አልፈልግም እና ከዚህ እዚህ እያለ የሚያወራቸው ወሬዎች አልተመቹኝም ነበር።

በዛ ላይ የልጅ እና የአባት ያህል ዕድሜም እንራራቃለን። የመጀመሪያው ወር ደሞዝ ሲደርስ የሚተኛበት ምንም ነገር ስላልነበረው የራሴን ችግር እያስታወስኩ እንዲገዛ አደፋፍሬ ያሻውን አደረገ።

ብቻ የኔ ልገሳ አላቆመም፡፡ ሜዳውን ተራራውን ሳስቃኘው እሁድ እና ቅዳሜን አብረን እንሰነብታለን፡፡ ታድያ ከለታት አንድ ቀን ከቤቴ ባደርሰው ባልታሰበ አመለካከት ፊቱ ተቆጥቶ ጅማቱ ሲቆላለፍ አየሁት፡፡ ግን ነገሩን ላለማስነቃት በሰላም ሸኘሁት፡፡

የፈራሁት እውነት አልቀረ በማግስቱ ከሰፈር ሄጄ ስለሰላሙ ልጠይቅ ብሻም ወጥቶ ሊያናግረኝ አልፈቀደም፡፡ ብዙ ጠበኩት ነገር ግን ምንም መውጣት እንደማይችል በሰው መልዕክት ላከብኝ፡፡ ውስጤ ተጨንቋል፤ ማድረግ ያለብኝን ነገር አላወኩም፡፡ ከቤቱ ከሰሞኑ ሽሮ ነገር መሰራራት ስለጀመረ ቀማምሼ ነበር፤ ግን ብዙም ገንዘብ በእጄ ላይ አይበረክትም፡፡ በዛ ላይ አንዳንድ የእዳ ክፍያዎችም ልከፍላቸው የማልችልበት ሁኔታ ላይ ደርሻለሁ፡፡ ደሞዝ አለ ግን ህይወት ባልታወቀ ሁኔታ ተናግቷል፡፡

እሁድን ብቻዬን አሳልፌ ሰኞ ወደ ሥራ ቦታ ሳመራ ያልጠበኩት ነገር ዘነበ፡፡ ስልክ እንደተወሰደበት ይባስ ብሎ ካልተመለሰለት ጫት እንደሚያስቅም በአንደበቱ እየተናዘዘ ግቢውን ይሽከረከር ጀመረ፡፡ ስለ እውነት አሁንም ያው ነበርኩ እና ከሁለት ስልኬ መሐል እኔ የበተኑን ይገፍ እሱ የእስክሪኑን እንዲጠቀም እንዲወስድ ተለማመጥኩት፡፡ እሱ ግን አይሆንም አለ፡፡ ሳላየው ራዳሩ ወደ እኔ ዞሮ ነበር እና ወሬ ከሥራ ባልደረባዬ በሹክሹክታ ሰማሁ፡፡ ሌባውም አዘራፊውም እኔው ነበርኩ፡፡

በ*ርግጥ ያቺ ክረምት ደርሳ ከዛ ትምህርት ቤት እስክሄድ እንደዛም ሆኖ ስሜን እያቆላመጠ ከመጥራት የተቆጠበ አልነበረም፡፡ ማጣፈጡን ተክኖበታል፡፡ እኔም ብሆን ያለፈውን ረስቼ አብሬው ከመሆን የዘለለ ምንም ነገር አስቤ አላውቅም ነበር፡፡ ነገር ግን ያሻውን በሚችለው በስውር አደረገ፡፡ በእምነቴም የማልደራደር ንፁህ ኦርቶዶክስ ነገር ግን ሁሉንም በደንብ አክብሬ እንደምወድ አስገንዝቤዋለሁ፡፡ እሱ ግን ላይመስል ወሽክቶ እሱ ለእምነቱ እምነቱም ለእሱ ምንም እናዳልሆነ አሳየኝ፡፡

ቅጥረኛው መ/ር ብቻ አይደለም በእምነት ስም የሚነግድ ክፉ የአውሬው መንፈስ የተጠናወተው የጠንቋዬች አባት ማማ ነው፡፡ እኔ የሰመዐቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ አምላክ ከኔ ጋር ስለነበር አዞ ስንበላው ከነበረው ምግብ ውሥጥ ሻይ የሚመስል የቅመም ዓይነት ብናኝ ሲምስበት አየሁ፡፡ በፊቱ አማትቤ ከመብላት የዘለለ ምንም አላደረኩም፡፡

እውነት ነው በዕምድር ላይ ሰነፍ ስትሆን *ምድርን ሊገዛት የሚችለው የገሃነሙ አባት አንተን ሊገዛህ ይችላል፡፡ ከዛ በበለጠ ግን ምንም አድርጎ ስጋህን እንደ አቤል ቢያንገላታውም ነብስህን ግን በምኑም ሽምቶም ሆነ አርሶ አይገዛህም፡፡ ነገር ግን እንደዚህ ዓይነት የሰው ቆዳ የለበሳችሁ የአውሬ ማንነት የተከናነባችሁ እባቦች በስንቱ ቦታ ትሆኑ? ምንስ ማሕፀን እናንተን ተሸክማ ይሆን? ስለምንስ ዓለም እናንተን ተሸከመቻችሁ? አጀብ!!! አጀማመሩ ያላማረው ቅጥረኛው አነፍናፊዬ በዚህ ስለማልበገር በሚሰጠኝ የሥራ ውጤት እርከን እንደ ሻማ ጧፍ ውስጡ እስኪከስል ድረስ በፊቱ ላይ ያንፀባርቅ ነበር፡፡

ለክረምት ት/ት ፍቃድ ወስጄ ስሄድ ለቡዙ ጊዜ ያልተገናኘሁት አጎቴ እስክንድር በጎዳና ላይ ታሞ እንደጠፋ ነገሩኝ፡፡ ከሶስት አራት ቀን በኂላ ተመልሼ ለመግባት በሀሳብ ላይ ሳለሁ ሳይገኝ ቀርቶ ለስምንት ቀን ከጓደኛው ጋር አልጋ ላምበረት አከባቢ ይዘን ስንፈልገው ያጠራቀምኩትም የክፍያ ብር አልቆ እሱንም በወቅቱ ሳላገኘው ተመልሼ ክረምትን ከቤተሰብ ጋር እየተመላለስኩ ከት/ቤቱም ሳልለይ ስልክ ከበረራ ተደወለልኝ፡፡

እኔም የተደወለውን ስልክ አንስቼ ለብዙ ሰዓት አወራሁ፡፡ የት/ቤቱ ባለይዞታ ነበር፡፡ ከር/መሩ ከወላጅ በተነሳው አስተያየት መሰረት ስምምነት ስላልነበራቸው መስሪያ ቤቱን መልቀቃቸውን እና እኔ ተክቼ ብሰራ የተሻለ መሆኑን አማከረኝ፡፡ እኔም የሰውነት ይሉኝታ ስላለብኝ ር/መሩንም ላለመጋፋት

በሀሳቡ ላለመስማማት ደግሜ እንደምደውል አሳውቄው ስልኩን ዘጋሁ። ዕድሉን ለራሱ አይሆን ነገር መጠቀም ያልቻለው መ/ር ከሌላ ቦታ ሰው እንደሚያመጣለት ቃል ገብቶ ከሴክሬተሪያሏ ጋር ተሻርከው እኔ ከጎልባ ተነስቼ ከቦታው ሳልደርስ ከሞጆ ጅማሰንበቴ ሌላ ሰው አምጥተው ጠበቁኝ።

ከበፊቱ ልቤ መንገደኛ ነበር። ምንም ሳልል የጀመርኩትን የመልቀቂያ ደብዳቤ አስገብቼ በንዴት የቆዘሙ ፊቶች ላይ እያዘንኩ በረራ ዳግም ከአጎቴ ነጋደረስ ዘንድ አስቀድሜ ነግሬው ስለነበር ዶክመንቶቼን እና ሸቀጤን ይዤ ወደ እሱው ተጠጋሁ።

# ምዕራፍ ሰባተት

## ለሁለት ዓመትያልነጋው ለሊት በበረራ!!

በረራ መምጣት የፈለኩት የመጀመሪያ እና ዋናው እቅዴ የጀመርኩትን ት/ርት ለማስቀጠል ሲሆን ሌላኛው እና አንገብጋቢው ጉዳይ የመፀሐፍ ሕትመት ነበር፡፡ ለእሱም ማስኪጃ እንዲሆነኝ ዘንድም ከአጎቴ ጋር ሆኜ ስመላለስ በነበረበት ወቅት ያስገባሁትን የሥራ ማመልከቻ እና የተጠናቀቀውን ፈተና መሰረት አድርጌ ነው፡፡ አራት ኪሎ ከቦርዱ ብዙ የሥራ ማስታወቂያዎች ይለጠፋሉ ነገር ግን በአንዱም ከተወዳዳሪዎች ውስጥ ሲገባ አይታይም፡፡ ይባስ የሚያስጠላው የግል ኤጀንቶች የውሸት ቅጥር እና ብዝበዛ ሲበዛ አስጠሊታ ነበር፡፡

የበረራ የመብራት ፖሎች በንግድ ሥራ ማስታወቂያ ታጭቀዋል፡፡ ከዛሬ ነገ ጠርቶ ይቀጥረኛል ያልኩት መስሪያቤትም የውሃ ሽታ ሆኖ ከቀረ ወሩን ደፍኗል፡፡ በዛ ላይ አንዳንድ ት/ቤቶች ሕጻናትን በመዝሙር እና ወንዝ በማያሻግር የተዘበራረቀ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ይፈላሰፉባቸዋል፡፡ ሌላው ደንበኛ ሲወጣ የሚረሳ የመግባቢያ ቋንቋ ተረስቶ መላላጫው የራሳቸው አማርኛ ይታደል እና ዓለም አስር ትሆናለች፡፡ ከዚች ከተማ በርካታው ት/ቤቶች የግል እንደመሆናቸው መጠን የሚፈለገው ትውልድ ሳይሆን ገንዘብ ነው፡፡ የት/ት አሰጣጡም ሆነ የሕጻናት አያያዙ በጥናት እና በፍላጎታቸው ላይ የተመሠረተ አይደለም፡፡ ቀጥሮ ማሰራት የሚፈልገውም ት/ቤቱ በሚፈልገው ካሪኩለም እንጂ ሞያው በሚፈቅደው አይደለም፡፡

በ*ርግጥ ለወርክሾፕ መብራት ኃይል <<---->> የሚባል ት/ት ለሁለት ቀን ብቆይም ሕጻናቱን ለማናገር የሚሞክሩት በእንግሊዘኛ ሲሆን የውጪ ዜጋ ከሆኑት የእንግሊዘኛ ቋንቋን መግባቢያቸው ካደረጉት በስተቀር ሁሉም የሚባሉትንም ሆነ መመለስ ያለባቸውን አያውቁም፡፡ ይሄንን ስላችሁ ቋንቋ ይጎዳል ወይም የእውቀት መለኪያ ነው ብዬ ሳይሆን ሕጻናት የወደፊት ህይወታቸውን እያጣጣሙ ሊማሩ የሚችሉት ከገሀዱ ዓለም ጋር በሚችሉት እና በሚገባቸው ቋንቋ መረዳት ሲችሉ ነው፡፡ ይህም እንዲሆን የኮሌጆችንም ስልጠና ካሪኩለሙን ጨምሮ ሕጻናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ ያስገድዳል፡፡ እንደ ሞያው ሲታይ ደግሞ እነዛን ሕጻናት እያሰለጠኑ የሚገኙት ባለሞያዎች በሞያው በበሩ ዳር ያላለፉ ሲሆኑ አንዳንዱ የህክምና ባለሞያ፤ ሌላው የማኔጅመንት ባለሞያ እና የኢንጂነሪንግ ባለሞያ እንዲሁም የተለያዩ የት/ት ዘርፍ ሰልጣኖች ያሉበት ነበር፡፡

አስቡት እነዚህ ሰዎች በዚህ ሞያ ውስጥ በቂ ስልጠና ስላልወሰዱ ከነኚህ አንቦቃቅላ የተሻለም ይሁን ቁብ የያዘ ልምዱ የላቸውም፡፡ ስለዚህ ይህ ማለት የፒዚክስ ኪት አምጥተህ አንድን ሰው አይ! ያመጣሁት የጤና ኪት ነው እና ዝም ብለህ ታከም እንደማለት ነው፡፡ እጅግ በጣም አደገኛ ነበር፡፡ ብዙውን ጉድኝታችንን አጠናቀን የህፃናቱን ወርሃዊ ክፍያ ስንጠይቅ ይባስ ጭንቅላት ያሲዛል፡፡ በአንድ ህፃን 1700 (አንድ ሺህ ሰባት መቶ) ብር ነበር፡፡ እንደ አውነቱ ከሆነ ይሄንን የሚከፍሉ ወላጆች እንደ ሥራው ገንዘቡ በቂ ሆኖ ሳይሆን እንደሰሪው አደገኛ ስለነበር በጣም ከባድ ነው፡፡

ጉብኝታችንን በዚህ ብቻ አላበቃንም አንደኛ ደረጃ ወደ ሆነው ሌላኛው ት/ቤት ሄደን ነበር፡፡ ነገር ግን ተማሪዎች በጣም ከመታፈናቸው የተነሳ ራስ የመግዛት መንፈሱ በጭራሽ አልነበራቸውም፡፡ የ5ኛ፤ የ6ኛ፤የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ት/ቤቱ ከግቢው ጀምሮ ጠባብ ሲሆን በዚህ ውስጥ ከተፈጥሮ ጋር ተላምደው እውቀት ይገበያሉ ማለት ሌላኛው ችግር ነው፡፡ በ*ርግጥ ከዚህኛው ት/ቤት ባለሞያዎች ቢኖሩም አንዳንድ ያለሞያቸው የሚሰሩ አካላትም አልጠፉም፡፡ በተቻለ መጠን ሁሉንም በተግባር ለማስተማር የተለያዩ አዝዕርቶችን፤ ከእንሰሳት ጥንቸል እና ለገበያ የሚውሉ ርግቦች አሉ፡፡

ወደ ተማሪዎችም ቀርበን አንዳንድ ጥያቄዎችን አቀረብንላቸው፤ ነገር ግን የግንዛቤ እውቀት ስላልነበራቸው ተፈጥሮን በይመስለኛል የሚያውቁ ናቸው፡፡ እንዲህ ዓይነት ትውልድ ደግሞ ከፍ እያለ በሄደ ቁጥር ተጠራጣሪ፤ ፈሪ፤ ውሳኔ አልባ ሆኖ ዓለምን በስጋት እንዳይኖራት ያደርገዋል፡፡ ብቻ ከዚህም አንፃር አስቀድሜ የበረራን ት/ቤት ከሞላ ጎደል ስለማውቅ ለውድድር በምሄድበት ወቅት ምንም

*ሊሳካልኝ አልቻለም። አብዛኛው ከት/ቤት ውጪም ያሉ መስሪያ ቤቶች የሥራ ቅጥር ማስታወቂያ የሚያወጡት ለፕሪንሲፕል ማሚያ እንጂ የሚቀጥሩት በገንዘብ እና በዝምድና የሚደልላቸው ቅጥረኛ አጥተው እንዳይደለ በተግባር ያየሁበት ነው።*

*አንዳንዱ ምክንያት ያለቀበት ይመስል ቀን እየቀጠረ ተስፋ እስኪቆርጥ ያንገላታዋል። በዚህ ዓይነት ድርጊት ግን ምንም ሊሳካለት ካልቻለ የበፊት የሥራው ባለሞያ ዳግም ወደ ሥራው እንደተመለሰ ያለምንም ሀፍረት እና ራሳቸው ሊጠየቁበት ስለሚችሉት ህግ እንኳን መናቅ በሚመስል መልኩ ይናገራሉ። በተለይ በአመራር ላይ ያሉ አንዳንድ ሴቶች ከመስተንግዷቸው ጀምሮ ለቦታው የማይመጥኑ አመጣጣቸውም በጥቅማ ጥቅም እና በወንድ አመራር ፍላጎት የመጡ መሆናቸውን የድርጊት ሁነታቸው ከሚገባው በላይ ያሳብቅባቸዋል።*

*እኔ ብቻ በተጓዳኝ ሁኔታ የመፅሁፍ ሥራው ስለነበረኝ በስልኬ ኢሜል ውስጥ ሳይወጣ ሲያስቸግረኝ የነበረውን አድካሚ ዶክመንት በአርታይኔ ሀሳብ ወደ ኮንፒውተር ቀይሮ ለመጨረስ ከዛሬ ነገ እያልኩ ሙሉ አትኩሮቴ ወደዛው ሆነ። ከመቀጠር የሥራ ሀሳብ ጋር ከተለያየን ሁለት ወር ሆኖታል። አጎቴ ነጋድረስ ስለኔ ሥራ ማግኘት ሁሌም ስለሚጨነቅ ያያቸውን ማስታወቂያዎች ሁሉ ስልካቸውን ይዞ እየመጣ እንዳናግራቸው ይሰጠኛል። እኔም ከማናገር አልፌ እስከ መስሪያ ቦታቸው ከለጋሲዮን እስከ አራት ኪሎ - ከለጋሲዮን እስከ መገናኛ - ከለጋሲዮን እስከ መሪ፤ አያት፤ ገርጂ፤ አዲሱ ገበያ፤ ሽሮ-ሜዳ፤ ካዛንቺስ፤ ለገ-ሀር፤ ሜክሲኮ፤ ሃያሁለት፤ ቦሌ፤ ልደታ፤ ጦር-ኃይሎች ብቻ በእግሬ እንክክ እስኪለኝ ለሥራ ያልዞርኩበት የበረራ ከተማ አልነበረም ማለት ይቻላል።*

*እስክንድር ለበርካታ ወራቶች ብፈልገውም ሳይገኝ ቀርቶ በዚህ የፈተና ጊዜ ደወለልኝ። እናም ካለበት ደርሼ ሳገኘው ብሞክር ከጴጥሮስ ሆስፒታል መተንፈስ አቅቶት ኦክሲጅን ከአፉ ላይ ተገጥሞ ክፍተኛ ማገገሚያ ክፍል ውስጥ ተኝቶ አገኘሁት። በጣም ያሳዝናል በዛ ህመም ውስጥ እንኳን ሆኖ የአፍ መሸፈኛ እንዳላደረኩ ሲያይ ከተኛበት ቀና ብሎ ፊቱን እያኮሳተረ በምልክት እንዳጠልቅ ነገረኝ። ያ! ለምንም እና ለማንም የማይበገር ሰውነቱ ለቶ ቀይ ፊቱ ወደ ንጣት ተቀይሮ ሰውነቱ በሙሉ ከስቷል። ውስጤ አዝኖ የማደርገው ቢጠፋኝም ካለችኝ ጥቂት ነገር ውጪ ግን ምንም ላደርግለት አልቻልኩም ነበር። ቀኑን ከዛው ሳጫውተው ውዬ ጨለምለም ብሎ ስለነበር ፍቃዱን ጠይቄ እያሳዘነኝ በእግሬ ከሽሮ ሜዳ ወደ ለጋሲዮን በሚወስደው የቀበና ወንዝ ጫካ አልፌ ከነጋድረስ ቤት ገባሁ።*

*አጎቴ ነጋድረስ የሚሰራው ሥራ የመንግስት ቢሆንም ደሞዟ ከቤት ክራይ አልፋ ለሌላ ጥቅም የምትውል ነገር አይደለችም። እሱ ግን ጠንካራ ሠራተኛ ስለሆነ ያገኘውን ሥራ ሁሉ በትርፍ ጊዜው ይሰራል። ረፍት፤ ቁጭ ብሎ ማውራት በቃ ለሱ ያልተሰጠው ነው። በጣም ለማግኘት ይጥራል። እኔም ከአንባ-ሳደር ወመዘክር ቤተ-መፀሐፍት ስመለሰ አንዳንድ አደፍ ያሉ ልብሶች ካሉ አጥባለሁ። እሱም ሁለትም አንድም በሥራው ያፈራውን ገንዘብ ይሰጠኛል።*

*በ*ርግጥ ከዛ ተንኮል ካረገዘበት መስሪያ ቤት ወጥቼ ከእሱ ጋር ማረፌን ወድጄዋለሁ ነገር ግን ህይወት መሆኑን እየኖርኩት ያለሁት ስረዳ ያለምንም ነገር ከሰው ህይወት ውሥት ገብቶ መዳከር ሌላኛው ህመም ነበር። በዚህ መሐል የትዳር መያዢያውን ወቅት እያሳለፍኩበት መሆኔ ሲገባኝ ሌላው ጭንቀት መከራን እየወለደ ራሴን እንድጠላ አደረገኝ።*

*በወጣ በገባ ቁጥር ከጓደኞቼ ጋር ሥራ ስለሆንኩበት ስለ እኔ እየተጨነቀ ያወራቸዋል። ልደታ ተግባረ-ዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በዳታ ማኔጅመት ክላስ ጀምሪያለሁ። ይህም የሆነው ለኤጀንቶች ከፍዬ ሥራ እንዳፈላልግበት በሰጠኝ አራት መቶ ብር ነበር። ኤጀንቶች አራት መቶውን ወስደው ያለሥራ ለተከታታይ ሶስት ሳምንታት ካንገላቱኝ በኋላ የኮሚሽናቸውን ቆርጠው በመለሱት ሶስት መቶ ብር ነበር። ጠዋት ከወጣሁ የምገባው ከምሽቱ አራት ሰዓት ነው። አንዳንዴም የፅሑፉ ሥራ ቶሎ ስለማይጠናቀቅ ከዛውም የማድርበት ወቅት ነበር።*

*መፅሐፉ ከተጀመረ አራት ዓመታትን አስቆጥሯል። በርካታ የደራሲያን ስራዎችን በፒዲፍ ከዚህ ቀደምም ሳነብ ስለነበር። እኔም ፈጥኜ በማጠናቀቅ የራሴን በአውነት እስካየው ቸኩያለሁ። እያደር*

እየሻከረ የመጣው የነጋድረስ ንግግር ውስጤን ቢያነደውም እየሰራሁ ያለሁት ሥራ ጥላ ስለነበር ከመስማት የዘለለ አድምጦት ግን አልነበረኝም፡፡ አንዳንዴ ምንም ሳይኖረው ገንዘብ ከራሱ አስበልጦ ቢሰጠኝ ላለመቀበል እፈልግ እና ሲለየኝ ያላቻለው ሆድ ማግስቱን አድሮ ከሆነ አላስችል ብሉኝ ከምግብ ቤት ገብቼ እስክቀማምስበት ቸኩዬ እቀበለዋለሁ፡፡

በዛ ላይ በየሳምንቱ ከእስክንድር ጋር ገንዘብ እየሰጠ የሚያስፈልገውን እንድገዛለት ይለክኛል፡፡ በ*ርግጥ እስክንድር በበጎ አድራጊያን ኢትዮጲያኖች እየተረዳ ስለሆነ የሚታከመው ቤተሰብ ስለመኖሩ ድርጅቱ ከሰማ በሚል ይጨነቅ ነበር፡፡ በዛ ላይ ከዚህ ከመግባቱ አስቀድሞ አረቄ፣ ኮረፌ፣ የጠዋት በነፃ የሚታደል ጠጅ ቀርተውበታል፡፡ እሱም ለሱ ሌላ ጭንቀት ነው፡፡ በ*ርግጥ ይሄንን የሚያደርጉ ሰዎች ፈጣሪ ዕድሜያቸውን ያርዝመው እና ከቲቪ በሽታ ህመሙ በመጠኑ እያገገመ ይመስላል፡፡ በኤም ቢረካ እያልኩ አንዳንድ ስራዬን አሳየው ነበር፡፡ በሳምንት ውስጥ ቢያንስ አንድ ጊዜ ከእስኬ አልቀርም፡፡ ብዙ ጊዜ መዳኒቱ እንደከበደው እና አገግሞ ለመነሳት ተጨማሪ የተመጣጠነ ምግብ እንደሚያስፈልገው ቢያወጋኝም እኔ ግን ከነጋድረስ የማገኘውን ገንዘብ ከመስጠት ውጪ ምንም ያደረኩለት ነገር አልነበረም፡፡ ይሁን እንጂ አላዛር ስራ ስለነበረው ስነግረው ከሚሰራበት ቦታ ያማረውን ሁሉ እያስቋጠረ ይዞለት ይሄዳል፡፡

ነጋድረስ በጣም ቢወደውም ፊት ለፊት ሲገናኙ ብዙም ደስ አይላቸውም፡፡ ወይነጋድረስ አስቀድሞ ይቆጣል ካልሆነ ደግሞ በእስክንድር ይብስ እና እየተነፋፈቁ ሊተያዩ ሳይችሉ ተለያይተው ይሄዳሉ፡፡ በ*ርግጥ እስክንድር አሁን ከጓደኞቹ ጋር ወደ ውጪ እየወጣ መጫወት ጀምሯል፡፡ ሁሌም ሲስቅ በዛ የፈካ ፊቱ ላይ ሙሉ የደስታ ብርሃን ማዓዛውን በሱ ላይ ይላበሳል፡፡

አንዳንዴ ስለመኖር አንስተን እናወራ እና ምሬቴን ስነግረው ከዛው እንደ አስታማሚ ሆኜ አንዱን ፍራሽ ለቀልኝ፣ ከምግቡም ቢሆን የሚመጣለትን አቃምሶን አብረን ከሆንን ምንም ችግር እንደሌለው ያወጋኛል፡፡ አንዳንዴ ከሱ ደርሼ ባዶ እጄን መሆኔን ሲያውቅ ካለችው ከሱም ብሶ ለኔ ካልሰጠ ሰላም ነስቶት ተቆጣትቶ በእጄ ላይ አድርጎ ይመለሳል፡፡ እሁድ እሁድ ሁሌም ጳጥሮስ ነኝ፡፡ ግቢው በጣም ስለሚያምር በውስጡ እየተንሸራሸርን ከጓደኞቹ ጋር ፎቶ እንነሳለን፡፡ የፊት ጥርሱ በመጠኑ ብትበለዝም ውበቱን ግን ልትነጥቀው አልቻለም ነበር፡፡ ቀኑን አብረን ውለን አመሻሽ ሊያሳድረኝ ቢፈልግም ከነጋድረስ ቤት ይሄ እንደማይሻል በማሰብ አዝኖ ይሸኘኛል፡፡

ነጋድረስ የቤት አከራዩዋ የቤት ክራይ በየወሩ እየጨመረች ስላማረረችው ብሎም የኔ መፍትሄ አልባ ጉዞ አሁን ላይ እንዲሰለቸኝ ስላደረገው እኔን ለማየት እንኳን በጣም እየጠላ ነው፡፡ መወደዱ ግን አስችሎ አላስለየውም፡፡ እኔም ከዛው ውዬ ከዛው ቤተ-መፅሐፍት የማድረው ይሄንኑ ሰቆቃ ሽሽት ነበር፡፡ እሱ ግን ከቤት ስጠፋ ደውሎ ውሎዬን በቁጣ ይጠይቃል፡፡ እውነቱንም ብነግረው ግን እኔን ስለማያምን ጓደኞቼን ጠይቆ የመሽታ ቤተ-መፀሐፍት ቤት መኖሩን በአግራሞት ይጠይቃል፡፡ በ*ርግጥ እንደ ሀገር ይኖራል ብሎ ማሰቡ በጣም ከባድ ነው፡፡ ወመዘክር ግን ይሄንን አድርጎ ከሳምንት እስከ ሳምንት የሚዘልቅ ታላቅ ቤተ መፀሐፍት ነው፡፡

ከአራት ዓመት በፊት የጀመርኩት የመፀሐፍ ስራ ‹‹አርቦሄሮያ›› ይባላል፡፡ እኔ ከኮርነር ላይ አንድ በየነ-መረብ የማትሰራ ፒሲ (ኮምፒውተር) ስለነበረች ከዛ ቁጭ ብዬ ወርድ ብቻ ነበር የምጠቀመው፡፡ አንዳድ ሰው ተጠቃሚ ሲመጣ ዶክመንት ላይ አስቀምጪ አውጣለሁ፡፡ ግን ስመለስ ሪ-ሳይክሉ ቢን (RECYCLE BIN} ውስጥ እንኳን ሳይቀመጥ ጠፍቶ አገኘዋለሁ፡፡ 15፣ 20፣ 30 ገፆች በሳምንት ውስጥ ሶስት አራቴ ሳይጠፉብኝ ሳምንት በሰላም ተሰናብታኝ አታውቅም፡፡ ኬብል ከቤት ይገፔ ብመጣም ያም ያም ስለሚጠይቅ ሳያስችለኝ ይቀር እና እሰጣቸዋለሁ፡፡ ነገር ግን ሳይመልሱት እንደዛ በተደቀነ ካሜራ ፊት ይዘውት ይሄዳሉ፡፡ እኔም አንዴ መ..ፍ ስጀምር የሰጠሁትን ሳላየው እቀር እና እዛውም ተቀምጦ የሚሽመጥጥ የእትዬለሌ ነው፡፡

ታድያ በዚህ መሐል ከቁርሱም ከምሳውም ሳልል እቆይና ሁለተኛዋን ቀን መንገድ መራመድ ሲያቅተኝ ስልኬን ወይም ልብሴን አሲዤ የነጋዴው ቤት ያፈራውን ቀማምሼ ጉዞዬን እቀጥላለሁ፡፡ ገንዘብ ላላገኝ ስለምችል ወንድሜ ከዛው ለጋሲዮን በዌተርነት ይሰራ ስለነበር አንዳንዴ ገንዘብ እንዲሰጠኝ

እየሄድኩ አስቸግረው ጀመር፡፡ የካፌው ባለቤት የሚያውቀኝ ከዚህ በፊት በስራዬ እና በክፍያ አገልግሎቴ እንጂ በእንዲሕ ያለው የምፅዋት ጥየቃ አልነበርም፡፡ ግፋ ቢል እሱንም የምጠይቀው በአራት ቀን እና በአምስት ቀን ልዩነት ነው፡፡ እሱንም ሃያ እና አንዳንዴም ምናልባት ከሆነ ሀምሳ ብር ነው፡፡

በዚህ መሐል ተስፋዬን በአንድ አቅጣጫ ብቻ አድርጌ የት/ቤት እንኳን የምከፍለው ሳላዘጋጅ ሶስት ወር አለፈ፡፡ ማንንም አልጠይቅ ነገር ሁሉም ‹‹የለኝም›› ስለሚለኝ እና ለራሴም መጠየቅ ስለሚከብደኝ ያለኝ አማራጭ የክፍል አድቫይዘሬን ማናገር ነበር፡፡ እሱም ከዚህ በፊት ያለውን ነገር እንድነግራቸው ከዛምበተቻለ መጠን ሊያግዙኝ እንደሚችሉ ነግሮ ወደ ሚመለከተው አካል ጋር መራኝ፡፡ አንድ ሳምንት ከቢሮው በራፍ ላይ እየደረስኩ ተስፋ በመቁረጥ እየተመለስኩ እሄድ ነበር፡፡ ነገሩ በዚህ የማይቀጥል ሆኖ ክፍያ ሳይከፍሉ የሚማሩ ልጆች ክፍያ መክፈል የማይችሉ ከሆነ መምጣት እንደሌለባቸው ማስጠንቀቂያ ተነገረ፡፡

ምንም አማራጭ አልነበረኝም፡፡ ሁሌም እየለመኑ ከመማር ጠንክሮ ሰርቶ መማሩን በማሰብ ት/ቱን ትቼ ፅሁፍ ስራዬን አጠናክሬ ቀጠልኩ፡፡ መፃፍ፤ ፊደል መልቀም፤ሀረግ፤ ዐ.ነገር ማስተካከል፤ ርዕስ መስጠት፤ ሀሳብን በተገቢው ቦታ መቋጨት፤ ግጥም በድርሰቱ ውስጥ መቀመር፤ የማይጣጣሙ ሀሳቦችን ማሶገድ፤ የነገሮችን አውንታዊ ትርጉማዊ ፍቺ አግኝቶ ለማረጋገጥ የሚደረግ ዳሰሳ እንዲህ ተፅፎ እንደሚነበበው ወይም ተዘርቶ እንደሚመጣው የእህል ፍሬ ቀላል እና ትንሽ አልነበረም፡፡

በዛ ላይ እንደ ጀማሪ ይሆንስ ይሆን አይሆን?! ማንስ ሊቀበለኝ?! ከእኔስ፤ ቀድሞ በኑሮው ራሱን ካልቀየረ ሰው እንዴት ሊማር?! ብቻ ከገባህበት እንዲህ በቀላል የምትወጣው የገነት መና አይደለም፡፡ ከዛ በፊት ያገኘሁት አርታይን በራሱ ሞያ ነፃ ነው የሰራልኝ ብል ማጋነን አይሆንም እና ይሄንን ስራ ዳግም ኢዲት ለማስደረግ በሌላ ባለሞያ ብሞክር በአንድ ገፅ ሁለት መቶ ሀምሳ ብር መክፈል እንዳለብኝ ነገሩኝ፡፡

በ*ርግጥ የመጀመሪያ አርታይን ያገኘሁት በሬድዮ ዝግጅት የበጎ አድራጎት ወጣቶች መልክም የበጎ አድራጎት ሥራ ላይ ነበር፡፡ በጣም ቀና ከመሆኑ የተነሳ ስራዎቹን በተደጋጋሚ እንደ ነባር ባለሞያ ለማየት ጥረት አድርጎ ሞክሯል፡፡ ሊታተም የሚችሉባቸውን መንገዶችም በተቻለ መጠን አሳይቶ ለማገናኘትም ሞክሯል፡፡ ነገር ግን በአንድ ወቅት ቸልተኝነቴ እና በነገሮች ላይ ቆራጥ ወሳኝ ሰው አለመሆኔ አናደደው መሰል ምክር አዘል ቁጣውን አበሰረኝ፡፡ እኔም መቼ እንደሚሆን ባላውቅም ከእሺታዬ የዘለለ ምንም ምላሽ አልነበረኝም እና ስራዬ ከነድካሙ በዛው ቀጥሎ ፋሲካ ደረሰ፡፡

ከዓመት በዓል መልስ ከመስከረም ጀምሮ ለድጋፍ ስጠይቃቸው የነበሩትን መስሪያ ቤቶች ውትወታ ጀመርኩ፡፡ ነገር ግን አጎቴ እና አከራይ ወርሃዊ ክፍያ ላይ ሊጣጣሙ እና ሊግባቡ አልቻሉም፡፡ አከራይ ሁለት ናችሁ በሚል አንድ መቶም ሁለት መቶም በየወሩ ትጨምር እንደ ነበር፡፡ በጣም እያዘንኩኝ ክረምት እየደረሰ እንደመሆኑ መጠን ከቤተሰብ ጋር ለማሳለፍ ወስኜ ተነሳሁ፡፡ ግን ከቤተሰብ ብሄድም ሁሉም ለኔ መልካማዊ አመለካከት አልነበረውም እና አልጋ እና ፍራሼን ሸጬ አንድ ሺሕ ብር ‹‹ሐማን-ዳብ›› ለተሰኘው ስራዬ ለአርታይኔ ስከፍል የተቀረውን ከፈረንሳይ ጫካ ሰፈር ውስጥ ቤት ተከራየሁበት፡፡ አጎቴም ጋብቻውን አድርጎ ትዳር ስለጀመረ ውስጤ አንድ እዳ ከራሱ ላይ እንዳወረደ ቅልል አለኝ፡፡ ምክንያቱም ጋብቻው እስከዛሬ ድረስ በኔ ምክንያት ይሆናል ብዬ ስላሰብኩ ነበር እና ሆኖም ስላሳለፈው ውስጤ ሀሴት አደረገ፡፡

ምግብ ከመስከረም ጀምሮ የምጠቀመው ከሲፓራ ሽሮ ቤት ነበር፡፡ በገባሁ በወጣሁ ቁጥር እንደ ቤቴ ቤት ያፈራውን ለአንጀቴ ብዬ እወጣለሁ፡፡ ከእሷ ጋር የተዋወቅነው በነጋድረስ አማካኝነት ነው፡፡ በጣም ከመግባባታቸው የተነሳ እንደ ቤተሰብም ናቸው፡፡ እኔም ወደ አንባ-ሳደር ወመዘክር ከመምጣቴ በፊት ከቤት የሚወጣ እቃ አወጣጥቼ፤ ስጋ ከትፌ፤ ቡና ለቅሜ እና አንዳንዴም ሽንኩርት እንዲሁም ድንች ልጬ ከትፌ ሰውም በርከት የሚል ከሆነ ከዛው ሳስተናግድ አውላለሁ፡፡

እሷ ሲበዛ ስለሰው ልጆች የምትጨነቅ ሩህሩህ እና አዛኝ ናት፡፡ ይሄም በቀላል የመጣ አንዳይደለ ስትሰራ ከነበረበት የአክስቷ ቤት አንስታ ሰው ቤት ከደረሰባት ግፍ እና ካየችው የሰው ሀገር የመከራ

ኑሮ እንዲሁም የስቃይ ህመም ነው፡፡ ረሃብን በአግባቡ ታወቃታለች፡፡ እኔም ከዛሬ ነገ ሁሉም አልቆ ህልሜ እውን እስኪሆን ያንን ደግነቷን የምመልስበት አንዳች ጊዜ እየጠበኩ ነው፡፡ የፅሑፍ ሥረዬን በወረቀት ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ስታየው ትይዘው ትጨብጠው የራሷ እስኪመስላት በደስታ ተፍነከነከች፡፡ በጣም አዘንኩ በጣም ከምንም በላይ ትጨነቅልኛለች፡፡

አላማዋ ሁሉ የእማማ አበበች ኀበናን ሥራ መሥራት ብትችል ደስተኛ ነች፡፡ ከምታተርፈው ለሰው በነፃ የምትለግሰው ይበልጣል፡፡ በተለይ አንድ የኤሌትሪካል ኢንጂነር ምሩቅ ሥራ ስላላገኘ ከዛ ቤት አይወጣም፡፡ ልጁ በነብይነትም ጭምር የሚያገለግል ሲሆን አንዳንዴ ስሜታዊ ይሆን እና ሲጮህ ጎረቤት ጭምር ይመረረዋል፡፡ ለሱ እሱ የሚያውቀው እና የመሰለው እውነት ነው፡፡ ካልመሰለው ግን አውነቱም ለሱ ውሸት ብቻ ነው፡፡ ፖለቲካነክ፤ ሀይማኖትነክ እና ወቅታዊ ጉዳዮች ሁሉም በተረዳው አንግል ከምግቡ እኩል ፈትፍቶ ይጎርሳል፡፡ ከነሱ ጋርም ይሄው ልጅ በሀይማኖት ዙሪያ ስለሚያተኩር አታካራ ውስጥ ገበቶ መሀንዲሱ ሆኖ ታገኘዋለህ፡፡

አንዳንድ መፀሐፎች ስለሚያነብ የፅሑፉ ይዘት ካማረው እና ከጣመው በቃ የፃፈው ጴንጤ ነው፡፡ ከዛ ውጪ በሱ አስተሳሰብ ማንም ሊፅፈው አይችልም፡፡ አመለካከቱ አንድ አቅጫን ብቻ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ እምነት እና እምነት ብቻ፡፡ በ*ርግጥ መልካም ነው፡፡ ነገር ግን ሌላውን የማያማክል ነገር ለማመሳሰል ማስመሰል መሞከሩ መልካም አልነበረም፡፡ እናም እየተቆጣ ምግብ የሚያዝበት ወቅት በትህትና ከሚጠይቅበት ጊዜ የላቀ ነበር፡፡ እሷ ግን በመርዳትም ስላደረገችው ያለምንም መቃወም ገንዘቡን ከፍሎ እንደሚገለገል ደበንበኛ አስተናግዳ አፅናንታ ትሸኘዋለች፡፡ ብቻ የመጣው ሁሉ ለእሷ ዘመዷ ነበር፡፡

እኔም ከዛው ሰፈር ወሎ እና ቆይታዬ የበረታ ቢሆንም በተጓዳኝ ሁኔታ ከየመሥሪያ ቤቱ ደብዳቤ ይገኙ እርዳታ መጠየቄን ሳላቆም ሥራዬን ከችግሬ ጋር ተሸክሜ ቀጥያለሁ፡፡

በሰው ቤት የሰው የሆነን ነገር ያለምንም ልፋት እንደመጠቀም የሚከብድ ሸክም ይኖር ይሆን? ብቻ የሲፓራ በጎ ፍቃድ ቢሆንም ለእኔ ግን የማይቻል ሁል ጊዜ አንገት እያስተፋ በሰቀቀን ጸጸት ማንነትን ዝቅ አድርጎ እንዳልነበርክ አድርጎ የሚገድል ሌላኛው መጥፎ በሽታ ነው፡፡

• * *

## *ልደርስ ስል ጣሬን አበዘብኝ!!*

አሁን ላይ ያለኝ ተስፋ ብዙም የሚያረካ አይደለም ለመኖርም የሚያስመኝ አይደለም፡፡ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሰው ግድያ፤ ረብሻ እና መፈናቀል ሰውን ከሰውነት ያወጣ ርካሽ ዘመን እየሆነ ነው፡፡ ደብዳቢዎቹም ‹‹ድሮም ድሮ ነሽ እንኳንስ ዘንቦብሽ›› እንደሚሉት ሆኖ ከአንዳንድ ግለሰቦች ብሄድ ምክንያት በሀገራዊ ጉዳይ እየደረደሩ ይመልሱኛል፡፡ በ*ርግጥ በብሄር እና በጎሰኝነት የሚጠመቀው የሞት ድግስ ከየብሄሩ ተንሰራፍቷል፡፡ እናም ከውጭ እንሰማው የነበረ ሰበር እና ዘግናኝ ዜናዎች ህልም በሚመስል መልኩ ተበራክተዋል፡፡ በተለይ አማራ በሚባለው ብሄር ላይ የሚደረገው የዘር ጭፍጨፋ እጅጉን የሚያስጠላ እና መደረግ የሌለበት ነበር፡፡

ይህ ብሔር ባመራር ደረጃ በቂ እና አቅም ያለው አይደለም፡፡ ሌላው በቻለው መጠን ከሌላው ሀገር ጋር ዲፕሎማሲ እየፈጠረ አቅሙን ያዳበረ ነበር፡፡ ታድያ ከታሪኩም እንደምንረዳው ይሄ ብሄር ያለፉ በርካታ ዘመናትን ኢትዮጲያን በመምራት እና ሀገር በማስጠበቅ ከየትኛውም በፊት ትልቁን ድርሻ የሚወስድ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት እንደዚህ ዓይነት የብሄርተኝነት በሽታ ሳይፈጠር በየስፍራው ከሁሉም ብሄሮች ጋር ተከባብሮ እና ተፋቅሮ የሚኖር እንደመሆኑ መጠን አንዳንድ የውጪ ተልዕኮ ያዘሉ የዘመኑ ሂትለራውያን አስተሳሰብ የተሸከሙ መጥፎ ሰዎች በያሉበት እያሳደዱ እርጉዞችን በገጀራ

ሆድ በመቅደድ፤ አሮጊቶችን እና ወጣቶችን በመድፈር ወንዶቹን የስለት መጫወቻ የሚያደርጉበት ዘመን ነበር፡፡

በ*ርግጥ ይሄ በብሔሩ ስም የተደራጀ ቡድን ያደርገው የነበረ እንጂ የማህበረሰቡ ፍላጎት እና ፍቃድ አለመሆኑን ማህበረሰቡ ደብቆ በማዳን ትልቁን ድርሻ ወስዶ ሲሰራ የነበረ የተከበረ ህዝብ ሆኖ እንደነበር በዚሁ አጋጣሚ የድርሻውን ተወጥቶ ለማሳየት ሞክሯል፡፡ በእንዲህ ዓይነቱ በሽታ ሀገሪቷ ተንኮታኩታ እያለች ሌላኛው ወረርሽኝ ተከስቶ ‹‹በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ›› ሆኖ ከዛ በፊት እና በኋላ የተለያዩ ድርጅቶችን ለመጠየቅ ሞክሪያለሁ፡፡

አደራ ጉዳዩን ወደ ሌላ መጥፎ ትርጓሜ እንዳትወስዱት ምክንያቱም እውነት እና ዐይኔ ያየውን ላወጋችሁ ብሻ ነው እና ራሴንም በዚሁ አጋጣሚ ላስተዋውቃችሁ፡፡ የዘር ግንዴ በህሊና በኩል የእስራኤል፤ የአማራ፤የትግራይ እንዲሁም የኦሮሞ ደም ዘር ውጤት ስሆን በኤርሚያስ በኩል ደግሞ አማራ እና ኦሮሞ ሲያዛራኝ በአባቱ ዮቶር በኩል ደግሞ ከታላቁ ንጉስ ሚኒሊክ ሁለተኛ ጋር የስጋ ዘመድ ነው፡፡ ስለዚህ በኔ በኩል በህይወት ሀገሬ ውስጥም ሆነ ከዛውጪ እስከኖርኩ ድረስ ማንም ማንንም እያስቃየ እና እያወደመ ቢኖር ትርፌ ህመም እንጂ ደስታ አይኖረውም፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ የሄድኩት ጃፋር የመፀሐፍ ማከፋፈያ ነበር፡፡ እሱ ከወቅቱ አንፃር ለሌላ ወቅት አዛውሮ ቢሸኘኝም በቃሉ ሳይገኝ ተመልሼ ስሄድ እዳላወቀኝ ሆኖ ሌላ ቀጠሮ ሰጠኝ፡፡ ቀጣይ ወደ ሜጋ መፀሐፍ ማተሚያ በተደጋጋሚ እየሄድኩ ስጠይቅ ቆይቼ በመጨረሻም ደብዳቤ ይገፔላቸው ስቀርብ ምንም ዓይነት ድጋፍ ማድረግ እንደማይችሉ ከአቅማቸው በላይ መሆኑን ነግረው አሰናበቱኝ፡፡

መዳረሻ ያልነበረው ጥያቄዬ በዛው ቀጥሎ ወደ ብርሃን እና ሰላም ማተሚያ ቤት አቀናሁ፡፡ እነሱም ከ…ምስት መቶ እና ከአንድ ሺህ በታች ገፆችን እንደማያትሙ ተናግረው ሸኙኝ፡፡ በዚህ ተስፋ አልቆረጥኩም ሆዴ እየነደደ ሰው አቃቂር እንደ መርዝ እየተፋብኝ ተስፋ ገብረ ስላሴ ማተሚያ ቤት ሄጄ ሁሉንም ለዋናው አስተዳዳሪ ነግሪያቸው ደብዳቤዬን ገቢ አደረኩ፡፡ ትልቅ ተስፋ ቢሰጡኝም የጥቂት ማህበሩ አባላት አለመስማማት እና የበጀት እጥረት ምክንያት እንዳልሆነ በተደጋጋሚ በጠየኳቸው መረጃ መሠረት አስረድተው አሰናበቱኝ፡፡

መች ይሄ ብቻ ጅምር እንጂ ማገባደጃ እንዳልሆነ በማወቅ ወደ ደራሲያን ማህበር ሄጄ ጉዳዬን በዝርዝር አስረዳሁ፡፡ እነሱም የአባልነት ክፍያ እና መታወቂ እንዳመጣ ጠየቁኝ፡፡ ሳንግባባ ቀርተን ነበር እና በሌላኛው ወቅት ስመለስ የስራዬን ሀርድ ኮፒ ጠየቁኝ፡፡ በ*ርግጥ ከለገሀር ለጋሲዮን የታክሲ ያጣን ሰው የአባልነት ክፍያ በዛ ላይ ችግር ተነግሮ የታደሰ መታወቂያ ከሰ.መ እንዲመጣ ማስደረግ ብቻ ግድ ስሆነ ነገር መስዕዋት ለመክፍል በመጀመሪያ ሀርድ ኮፒውን ከደብዳቤ ጋር አደረስኩላቸው፡፡ ለድጋፍ መሆኑ የገባቸው የምፀት ደብዳቤዬ ሲነበብ ነበር፡፡ ምላሹ በጣም የሚያበሳጭ የሚያዝናናም ጭምር ነበረው፡፡ ‹‹ብዙ ደራሲያን ድጋፍ አድርገንላቸው አልመለሱልንም፡፡ እናም ወደ ሌላ እንኳን እንዳንፅፍልህ ለመህበሩ ስምም ጥሩ አይሆነም፡፡ በዛ ላይ አሁን ያለንበትም ሁኔታ የምታየው ነው፡፡›› የሚል እንቆቅልሽ መሰል ንግግር ያዘለ ነው፡፡

‹‹ልፋ ያለው ቆዳ ከበሮ ያሆናል›› አይደለም ምላሹ ሌላኛውን ዳብዳቤ አሰናድቼ ቅድስ ጊዮርጊስ ፋብሪካ በሰው ጥቆማ ሄድኩኝ፡፡ በተባልኩት መሠረት ደብዳቤዬን ለሚመለከተው አካል ገቢ አድርጌ አንድ ወር፤ ሁለት ሶስት እያልኩ ስጠብቅ ከርሜ በመጨረሻም በመሰላቸት የቢሮ ስልካቸው ላይ ደውዬ ወደ ቢሯቸው አመራሁ፡፡ የደብዳቤውን ቁጥር ለአስተናጋጇ ሳስረክባት ለምን እንደ ቆየሁ ስትጠይቀኝ ቀጠሮዬን አክብሬ ስመጣ ቀጠሮ እንደተሰጠኝ ሳሳውቃት ለፀሐፊዋ ደወለች፡፡ ፀሐፊዋም ከላይ እየተምዘገዘገች መጥታ የሌሎቹን ጉዳይ ስታስተናግድ ቆይታ በደንብ ካጤነችኝ በኋላ ከቢሮዋ ተመልሳ በስልክ ለአስተናጋጇ በበየነ-መረብ ኦንላይን እያየች በጀት እንደሌለ አስተጋባች፡፡ ደስ የሚል ኮሚክ ቀልድ ነበር፡፡ ኦንላይን ከዓመት ዓመት በቅንጠጡት የሚያዋራ ድርጅት በጀት ሲያጣ ማየት ለመርዳትም መችገር ሆኖ እንጂ ነበረ ጉዳዩ፡፡

በዚህ አሁንም አዝሎ ቢደክመኝም ተስፋዬ ቢላሽቅም ድጋፍ ከማፈላለግ አልቦዘንኩም፡፡ ሌላኛው ወደ ሆነው ድርጀት አዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር አመራሁ፡፡ የያዝኩትን ደብዳቤ ለደንበኛ አስተናጋጆቹ ለማሰረከብ ጥረት ባደርግም ከራሳቸው ላይ ላማራገፍ በሚመስል መልኩ ለፃፊዋ እንድሰጥ ወደ ውስጠኛው ክፍል መሩኝ፡፡ ፀሐፊዋ እንደፈራሁት አልቀረም እና አስተናጋጆቹ ውስጥ የተላከችው አንዲት ሴት ስትወጣ ለኃላፊዎቹ ብሰጥ የተሻለ እንደሚሆን አማክራ ትንሽ እንድጠብቃቸው ካልሆነ ግን ተመልሼ በሌላ ጊዜ እንድመለስ ምክረ ሀሳቧን ለገሰችኝ፡፡ እኔም እሺታዬን ከመልካም ምኞት ጋር ችሪያት በሌላ ጊዜ ልመለሰ ቀጠሮ ይዤ ተመለስኩ፡፡

• * *

የቤት ክራይ ከፍያ እንደ በረከት በርከትከት ብሏል፡፡ የምወጣው ከጠዋቱ አስራ ሁለት ሰዓት ሲሆን የምገባው ከቀኑ አስር እና አስራ አንድ ሰዓት ነው፡፡ የቀን ሥራ እንኳን አፈላልገን ለመግባት ብታትር ሳይሳካ ቀርቶ ከማቆሚያ ቀርቼ ሌላው ሰርቶ ይመለሳል፡፡ በ*ርግጥ ከዛ በፊት ውስጤ ሰላም ስለነሳኝ የሥራ ተነሳሽነቱም አልነበረኝም እንጂ ያች እናት የሆነች ሴት ምግብ ሊመገቡ ከሚመጡ ሰራተኞች ጋር እንድሰራ ብዙ ለራሴ ስትል ተማፅናኝ ነበር፡፡ እኔ ግን ያለ ዛሬ ነገን ተመኝቼ ቀኑ ድፍንፍን አለብኝ፡፡

ቀጠሮዬ ደርሶ ከአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር ስመለስ ምክትል አስተዳደሩን አገኘሁት፡፡ እሱም የነበርኩበትን ስነግረው ፕሮፖዛል ነድፌ እንዳመጣለት ጠየቀኝ፡፡ እኔም ሁሉን አድርጌ አስረክቤው ዳግም በቀጠሮ ተለያየን፡፡ ስለ እውነት ከሆነ ያንን ፕሮፖዛል ለማዘጋጀት ያልዞርኩበት የአዲስ አበባ ማተሚያ ቤት አልነበረም፡፡ ቀን ሳምንታትን፤ ሳምንታት ወራቶችን እየወለደ ሲሄድ እግሮቼም ሳይለግሙ መመላለሱን ተክነውበት አንድ መመላለሴ የሰለቸው የአስተዳደሩ አካል ወደ አዲስ አበባ ሴቶች እና ሕጻናት መራኝ፡፡

ለበርካታ ቀናት ከቢሯቸው ብመላለስም የሚፈለገው አካል ሊገኝ ስላልቻለ ተመልሼ ወደ ላከኝ የአዲስ አበባ ወጣጦች ማህበር ሄድኩኝ፡፡ እነሱም ምንም በጀት እንደሌላቸው እና አቅማቸውም እንደማይፈቅድ ብሎም የምርጫ ወቅት እየደረሰ መሆኑን መሠረት በማድረግ ሊያሳትሙት እንደማይችሉ አሳወቁኝ፡፡ ቆይ ግን ለመሞኑ የነዚህን ድርጅቶች ሥራ የሚነግረኝ አካል ቢኖር ለኢትዮጲያ ህዝብ ስል ከፊቱ ተንበርክኬ አናግረው ነበር፡፡

በዚህም ያቆምኩኝ መስሏችሁ ይሆን ይሆን? አልቦዘንኩም ነበር እና በተለያዩ የማተሚያ ቤቶች እየዞርኩ ጠየኩኝ፡፡ ነገር ግን ሁሉም በኑሮው ውድነት እና ጊዜያዊ ሁኔታ ላይ እያላከኩ እንደማይችሉ ነገሩኝ፡፡ አሁን ከሚገባው በላይ ሰልችቶኛል፤ አይመጣ ሆኖ እንጂ ከሞት ሺህ ጊዜ መዛመዴን ወደድኩት፡፡ ከአዲሱ-ገበያ በጎርጊስ አድርጌ ከአንድ የመፀሐፎች መደብር ስደርስ እንድ አዛውንት መፀሐፍ በሀምሳ ብር እየተከራዩ ሲሄዱ አየሁ፡፡ እናም የመፀሐፍ መደብሩን ልጠይቅ ነበረውን ጥያቄ ይዤላቸው ሄድኩኝ፡፡

እሳቸውም የመፀሐፉን ከበር ፔጅ አይተው ‹‹ልጄ ከዚህ በፊት ያሳተምከው መፀሐፍ ወይም እውቅና ያገኘህበት ሥራ አለህ?›› ሲሉ ጠየቁኝ፡፡ እኔም በማስተዛዘን እንደሌለ ነገርኳቸው፡፡ ትንሽ ጺማቸው አጎጥጉጣ ስለነበር በእጃቸው እያሻሹ በአትኩሮት በሀዘኔታ እያዩኝ ‹‹አዬ ልጄ ምንም እውቅና ወይም ገንዘብ ከሌለህ እንዳትሞክረው፡፡ ምክንያቱም በአፉ እየሸነገለ በህይወትህ ሲጫወት የሚሻው ጥቅመኛ ብቻ ተፈጥሯል፡፡ አንተ ተነሳህ ወደክ ለማንም ዴንታው አይደለም፡፡ በ*ርግጥ ይህ መፀሐፍ

የዶክተር እከሌ ነው ቢባል ሻጮች እንኳን ተረባርበው ለማሳተም ከጎርጓዱ ውስጥ ይፈልጉኃል፡፡ በል ተስፋ አላስቆርጥህ እና አሁን ትንሽ ስራ ብጤ ካለህ ወይም ዘመድ እንዲረዱህ አድርገህ ከማውጣት የዘለለ ሌላ አማራጭ የሚኖርህ አይመስለኝም፡፡ …….›› ብለው እያፅናኑ አስፋልቱ ድረስ ሸኝተውኝ ተመለሱ፡፡

የሁለት ሺህ አስራ ሶስት አዲሱ ዘመን ከረምቱ ሊያለፈ ተቃርቧል፡፡ ከዛችው ሽሮ ቤት ደፍ ደፍ ስል መስከረም ጠብቶ የመስቀል በዓል መዳረሻ ላይ በአስራ ሁለት የቤቱ ባለቤት ቤቱን ቆልፋ ጠበቀችኝ፡፡ ጥፋቴን አምኜ ያለፈውንም ማስጠንቀቂያቸውን በማስረዳት እንድገባ በልመና ጭምር ብጠይቅም ሳይሳካ ቀርቶ በዛ በጭለማ ያንን ጫካ እያቋረጥኩ አልፌ በአመሻሽ መኪና ከአክስቶቼ ዘንድ ወደ መሪ ሄድኩ፡፡ አዳር ከዛው አንግቼ ማግስቱን ከሽሮ ቤት ባለቤቷ ላይ አንድ መቶ ብር ተበድሬ ወደ ቤተሰብ አቀናሁ፡፡ በ*ርግጥ ከዛ በፊት የስራ ዶክመንቴን በወቅቱ በርካታ መምህራንን መንግስት በኮቪድ ምክንያት ይፈልግ ስለነበር ከየካ ከተማ አስተዳደር በስተጀርባ ከሚገኘው ት/ቤት አስገብቼ ብሄድም በትራንስፖርት ችግር ሳልደረስ ቀርቼ እስከ ጥቅምት ከዛው ሆኜ ሌላ ሥራ እንኳን ሳልሳተፍ ቀርቼ ቤተሰብን ያማረረው የጎረቤት ሮሮ ሰምሮ የትራንስፖርት ተቀብዬ ተመለስኩ፡፡

ከጥቅምት መባቻ በኂላ ወደ መሪ በመመለስ ከአክስቶቼ ጋር ለበርካታ ወራት አብረን ዘለቅን፡፡ ስራ ከመፈለግ አልቦዘንኩም ነበር፡፡ ለዐይናቸው የታከቱኝ ሰዎች እንብዛም ሊያናግሩኝ ቀርቶ ለሰላምትም ግድ ሲሆንባቸው ካልሆነ በስተቀር አይተው እንዳላየ አልፈውኝ ይሄዳሉ፡፡ በ*ርግጥ ከበፊቱ ራሴን ስለናኩት ከሚገባው በላይ ማንነቴን አርቄ ጥዬዋለሁ፡፡ አንዳንድ ውስጤን እና እኔን የተረዱ ሰዎቸ ደግሞ አንዳንድ የመፍትሄ ሀሳብ ከማቅረብ አልቦዘኑም ነበር እና ያዋጣኛል ያልኩትን ከማድረግ አልተቆጠብኩም ነበር፡፡ ነገር ግን ከልፍት በስተቀር ምንም አማራጭ አልነበረኝም፡፡

የመጨረሻው አማራጩ ስራዬን ከሌላ አካል ጋር በፐርሰንት መስራት ካልተቻለ እና የከረረ መራራ ከሆነ ለአንድ የደራሲ አካል በነፃ ለመስጠት ወሰንኩኝ፡፡ ይህንን ከማድረጌ በፊት ብዙ የበየነ-መረብ ዌብ-ሳይቶችን ተጠቅሜ ጋዜጠኞችን፤ ደራሲዎችን እንዲሁም አክቲቪስቶችን ለማናገር ትልቅ ጥረት አደረኩኝ፡፡ አንዳንዱ ለመመለሰ ባይቻለውም የተቀሩት ግን በተስፋ እንድቆይ ምክረ ሀሳባቸውን እና አማራጫቸውን ሰጥተውኛል፡፡

ባጋጣሚ በደንብ ሊያናግረኝ የወደዱት የሚኒሊክ ቲቪ ና የኦቢኤን ቲቪ ጋዜጠኞ የተለያዩ አቅጣጫዎችን በመጠቆም የሚያግዘኝ ሰው ጭምር እስከማገናኘት ድረስ ድጋፍ አድርገውልኛል፡፡ እንደተፈለገው ሆኖ ባይሰምርም ካንደኛው ጋዜጠኛ ጋር ባደረግነው ቆይታ ስለሥራው ጥልቅ ሀሳብ በመጠየቅ መጀመሪያ ስነ-አዕምሮ ክፍል ማስመዝገብ እንዳለብኝ በአንክሮ አስረድቶ በፐርሰንት ሊያሳትሙ ከሚችሉ አካላት ጋር በጥቆማ ላከኝ፡፡ ነገር ግን የተገናኘኂቸው የሥራው አካላቶች ከሥራቸው ደፋ ቀና ሲሉ ሥራዬን ተቀብለው ወራቶችን አስጋልበው ዓመት መገባደጃ ድረስ በምክንያት ምንም ማድረግ እንዳልቻሉ አወጉኝ፡፡

• * *

# ምዕራፍ ስምንት

## ለጠዋት ያልተቃና ህይወት አመሻሹ አያምርም!!

በአንድ የሰፈሩ ጓደኛዬ ምክንያት የመፅሔት እና የጋዜጣ ሥራ ጀምሪያለሁ፡፡ በ*ርግጥ ይሄንን ትልቅ ሞያዊ ተግዳሮት ስጀምር በጥንቃቄ እና ሀገራዊ በሆነ ወቅታዊ አጀንዳ ነበር፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ይህንን ሥራ ለማውጣት የመፅሔቱን ባለቤት እስካገኘው ድረስ በፍለጋ ብዙ ተንገላትቻያለሁ፡፡ በስተመጨረሻም ከቀየረው አዲስ ቢሮ ባስተዋወቀኝ ጓደኛዬ አማካኝትነት ላገኘው ቻልኩ፡፡ ወጥቶ እስካየው ቸኩዬ ስለነበር ለተከታታይ ሶስት ሳምንታት ብጠብቀውም ሳይሳካ ቀርቶ ደውዬ ጠየኩት፡፡ እሱም ሌላ የቆየ ሥራ እንዳለው እና በቀጣዩ ሳምንት ሊያወጣው እንደሚችል ተነጋግረን በመገባደጃው ሥራው ወጣ፡፡

አንድ ሁለት ሳምንት የልፋቴን ውጤት በቴሌግርም ብልክም ከባለቤቱ ግን ተቀብሎ ከማውጣት የዘለለ ምንም ስለሥራው የክፍያ ሀሳብ ሊያነሳ አልቻለም፡፡ እኔም ሥራዬን ቀጥዬ አራተኛ ሳምንት በተደጋጋሚ አንድ እና ከዛ በላይ ሥራዎችን እየሰራሁ ወደ ህዝብ መድረሳቸውንም ማረጋገጥ ቻልኩ፡፡ ነገር ግን ከመሪ መገናኛ በእግር እየተመላለስኩ የራሴውኑ ሥራ ከአላዛር ና ከአክስቶቼ በምቀበለው በሃያ ብር እየገዛሁ ከመመለስ ያለፈ ለውሃ መውቀጫ አጥንት ላገኝ አላቻልኩም፡፡ ታድያ በዚህ መሐል አምስተኛ ሥራዬን ከመላኬ በፊት ችግሬን በንግግር እያዋዛሁ ለመግለፅ ስታተር እሱም ቁም-ነገር ጉዳዩ ገብቶት ከመወሰን እና ከማሳተም እንዲሁም ከድርጅቱ ፍቃድ ውጪ ምንም ማድረግ እንደማይችል ንዴት በሚመስል አነጋገር አወጋኝ፡፡

በዚህም ሳልሰላች የመጨረሻውን ሥራ ሳደርሰው በሌላ ሰው ሥም ታትሞ አገኘሁት፡፡ ውስጤ ከሚገባው በላይ አዘነ የሚገርመው ነገር የኔ ብቻ ሳይሆን የሌላውም ሰው ሥራ በዛ ስም ሁሌም እንደሚወጣ በአግባቡ አይ እና እናደድ ነበር፡፡ በኔ ላይ ሲደርስ ግን ሥራውን ወዲያው አቁሜ ከባለቤቱ ጋር ለመነጋገር ከቤሮው ብደርስ ያሉባልታ እና የቤተመንግስቱን ውሎ እያወጉ ደርሼ በርጋታ እውነቱን ዳግም እያዋዛሁ ልጠይቀው አቅማማሁ፡፡ እሱም ራሱን ኮፍሶ ማሽሟጠጥ በሚመስል አተያይ እየተመለከተኝ እንደ ሀሳብ ሀሳቡን ሊያስተናግድልኝ እንደሚችል ካልሆነ ግን ምንም ማድረግ እንደማችል ሀሳቤን እንኳን በቅጡ ሳይሰማ ውስጤን ነደድ አድርጎኝ ስለነበር ጥዬው ወጣሁ፡፡

ይሄም ሆኖ ቀናቶች አረጋግተውኝ ሳምንት ንዴቴን ሲያስረሳኝ በተለመደው ወቅት እና ሰዓት ለመላክ ብችልም ከሌላኛው ጋዜጣ ላይ ተነጋግሬ ሌላኛው ሥራዬ ሲወጣ የዛኛው ግን በዛው ተኖ ቀረ፡፡ ከሌላኛው የመፅሔት እና የጋዜጣ አምድ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰጠሁትን የልፋት ውጤት ትቼ ሌላኛውን በመስጠት ክፍያ ለመጠየቅ ብሄድም ሳይሳካ ቀርቶ ከዛው ሊቀጥረኝ እና በሞያዬ እንድሰራለት ጠየቀኝ፡፡ እኔ ግን ያላለቀውን የት/ት መስክ ለማገባደድ ስለፈለኩ ወደ ባህርዳር ለተጓዳኝ ስልጠና እንዲሁም ተጨማሪ በርካታ የፅሑፍ ሥራዎቼ ለኤም ጌዜ የማይሰጡኝ መሆኑን ነግሬው የኪስ ብሎ አምስት መቶ ብር ሰጥቶ ሸኘኝ፡፡

ከዛሬ ነገ፤ ከነገ ተነገወድያ እያልኩ መሄዴን እየተጠባበኩ ነው፡፡ እስክንድር በዘመኑ የበሽታ ወረርሽኝ ምክንያት ትንሽ አገግሞ ስለነበር ወደ ቀበሌው በመመለስ ካለበት እገዛ እንዲያደርስት የጴጥሮስ በጎ አድራጊ አካላቶች ወስነው ሸኝተውታል፡፡ ከቤተሰብ በተለያዩ ጊዜያት ብመላለስም አዘውትሮ መጠጥ

ቤት እንደሚውል እና መዳኒቱን እንዳቋረጠው ሰማሁ። እንዲጠቀም ለማድረግ የተለያዩ የማበረታቻ ቃላቶችን ብሰነዝርም ላይሆን ነገር ሆኖ እኔም አላማዬ ከግቡ ደርሶ ባይ ብዬ ከበረራ ከተምኩ።

ነገር ግን እሱም ብዙ ከሲ.መ ሳይቆይ ወደ በረራ መምጣቱ አልቀረም ነበር እና የተለያዩ ሥራዎችን እየሰራ ለመኖር ቢታትርም ሳሉ እየበረታ፤ ሰውነቱም እያባበጠ ሄዶ ምንም ዓይነት ሰው ካጠገቡ ደርሶ ዕርዳታ ሊያደርግለት አልችል አለ። ቤተሰብ የሱን ችግር እንዳይሰማ ስለሚፈልግ ተጨንቆ ማሰብ በሚመስል መልኩ ለጓደኞቹ ደውሎ ጳውሎስ መግባቱን ይናገራል። ጳውሎስ ያለሰው የገባው መንገደኛው እስክንድር ባልታሰበ ዕድሜ እና ባልታሰበ አጣብቂኝ ሕይወት ውስጥ ከፓውሎስ ሆስፒታል ሰውነቱ በመቀስ ከደረት እስከ ሆድ እቃው ተቀዶ በሥነ-ሥርዓቱ እንኳን ሊሰፉት ሳይችሉ ነጋድረስ ደርሶ ከሆስፒታሉ አስከሬኑን ለቤተሰቡ ካልደላችው በረራ ወስዶ ከሲ.መ አስረከባቸው።

አስቀያሚውን መርዶ እንደሰማሁ ውስጤን ልቆጣጠረው አልቻልኩም ወድያውኑ ራሴን ጠልቼ በወጣሁ በገባሁ ቁጥር በየመንገዱ ማንባት መጥፎው የመናፈቅ ስሜት እየወዘወዘኝ ውስጤን አደፈራረሰው። ጃል ሜዳ፤ የለጋስዬን ጫካዎች እና የለጋሲዮን ታክሲዎች አንደበት አውጥተው እስኪያባብሉኝ አነባሁ። በ*ርግጥ የቀብሩ ለታ ለመገኘት አልፈቀድኩም ነበር። ምክንያቱም የምወደውን እና ያሳደገኝን ያዛኔው ትንሽ ልጅ የዛሬ ጎረምሳ አጎቴን እያየሁ መቅበር ሌላው የማልችለው ህመም ስለሆነብኝ ነው። በሶስተኛው ቀን ራሴን አረጋግቼ ለመሄድ አኮበኮብኩ ጉዞውም ቀንቶ ከዛው የመቃብሩ ቦታ ብደርስም ላያስችለኝ ውስጤ ከሚገባው በላይ ተጎዳ። ከሰልስቱ መልስ ወደ ቤት አምርቼ ወደ አባባ ጥበቡ ጋር ብሄድም ከደጁ ባርፍ ‹‹የት አደረስከው አምጣው ልጃችንን›› ያለኝ ይመስል እያንዳንዷ ተቀምጠን ስንጫወትባት የነበሩት ቦታዎች በድምፃቸውን አጥፍተው ሲጮኹ እጅግ ይሰቀጥጥ ነበር።

እስክንድር ላይመለስ ይቺን ዓለም ጥሏት ሄዷል። በ*ርግጥ ዛሬን አድረን ነገን ላንደግማት ቀን ብዙም መጨነቅ የማይጠቅም ከንቱ ልፋት ሆኖ እኔንም ልትክደኝ አንድ ቀን የማትሰጠው የሆድ ሰለኔ ሆኖብኝ የእዳ መስፈሪያ ሰይፍ ዳግም ወደ በራራ ተመለስኩ።

አሁን ላይ ያለሁት ከፍተኛ ግራ መጋባት ላይ ነኝ። በዛ ላይ የምይዘው የምጨብጠው እየጠፋኝ በልቶ ከመንገዱም ለመተኛት እጅግ እየተቸገርኩ ነው። ይባስ ብሎ የማየውም የምሰማውም ነገር በጎነት ስለሌለው ሰው ሁሉ ያቅለሸልሸኝ ይዟል። የራሱ ቀዳዳ እየፈሰሰበት ስለሌላው የሚጨነቅ የሚመስል አስመሳይ ሆኗል።

• * *

አንዱ አቋድሶ ሕይወትህን ስላኖራት ሌላው ዐይኖቹ ደም ለብሰው ዐይኖቻቸው ቀምተው ሁሉን ነገር በያደርጉ ደስታቸው ወደር የለውም። ሰው በሰው ሊቀና ይችላል ነገር ግን በችግር መቅናቱ እጅግ ያበሳጫል። *ርግጥ ሆኖ ሲፖራም የበፊት ባህሪዋ ከተቀየረ ወራቶች ተቆጥረዋል። ብቻ ጭንቅ ጥብብ ይለኝ ጀምሯል። ነጋድረስ ምክንያቱን ባውቀውም እኔን ለማየት እንደማይፈልግ ካወኩት ፀሐይ ሞቆት ቀናቶች እያጨበጨቡ አንድ ዓመት ከአራት ወር ሆኖታል፤ እኔም እሱ ከጠላኝ ስለምን የጠላኝን ሰው መለማመጥ ብሎም ሁሌም እየተለማመጡ ለማትሆን መንደር መሸነፍ አንገሽግሾኛል። አሸናፊነት የሌለው ሽንፈት ሲበዛ እንኳንስ ለሰው ካበዙበት መከራ ብረትም ይጨንቀዋል።

በለጋ-ሲዮን የሚያውቅህም የማያውቅህም ሥራ ሰርቶ የማያቅ ጣቱን እየዘረጋ መጠቋቆሚያ ሲያርግህ ይውላል። ሰፈሩም ለምዶ ተግባባኝ መሰለኝ መመላለሴን ሁሌም በምሬት ሲያስጨንቀው የተንኮል ፉጨቱ እግሬም እንኳ መሮት እስኪሰለቸው በህመሙ ወግሮ ያስጨንቀኛል። በርግጥ ስለ

ባህርዳር የኑሮ ሁኔታ መረጃዎችን ለማሰባሰብ እንደሞከርኩት በጣም ውብ እና ለኑሮ አመቺ ሁሉም ነገር የተሟላ አንደሆነ ነበር፡፡ እኔም ከሰው ዐይን ተሰውሬ ትምህርቴን ከዛው ለማገባደድ ብሄድም ባህርዳርን እንዳሰብኳት እና እንዳቀድኳት ሆና ላገኛት አልቻልኩም ነበር፡፡

ወቅቱ ክረምት እንደ መሆኑ መጠን ከበረራ ተነስተን ሞጣ እስክንደርስ ድረስ ምንም ዝናብ ኡልነበረም ነበር፡፡ ነገር ግን ጋራ ጎርባጣውን አልፈን አዴት ስንድረስ ላይን በያዘው ምሽት ላይ ባህርዳር እስክንደርስ ድረስ ዝናቡን አበርክቶ አረበረበው፡፡ ጠዋት አስራ ሁለት ሰዓት የጀመርነው መንገድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተጠናቆ ባህርዳር ብንደርስም ለስለስ ብሎ የጀመረው ዝናብ ማቆሚያ አጥቶ ከዛው ቆመን የአስፋልቱ ጎዳና በውሃ ተጥለቀለቀ፡፡ መፋሰሻ ቱቦዎቹ በቂ ሆነው ጥንቃቄ ባይደረግላቸውም ባሉትም የሚጎርፈውን የዝናብ ውሃ እንኳን የማስተንፈሻ አቅም አልነበረውም፡፡ የያዝኩት ኮተት ከአንድ የሽሮ ቤት በአደራ አስቀምጬ ያንን በጎርፍ የተጥለቀለቀ ውሃ በመላ ሰውነቴ ተነክሬ እየዋኘሁ ካናደኛው ኮብልስቶን ወደ ሌላኛው ተሻገርኩት፡፡

የአመጣጥ እቅዴ ከባህርዳር አምስት ሰዓት በመድረስ ቤት ፈልጌ ተከራይቼ አረፍ ብዬ በማግስቱ ሥራ ማፈላለግ ነበር፡፡ ነገር ግን አገባባችን እንኳን ሳያምር ቀርቶ አልጋ መያዝ ግድ ሆነብኝ፡፡ በጄ ላይ ቀን እንኳን ገብረ ጉራቻ ላይ ለምሳ መብያ የሚመሆን ገንዘብ አጥቼ እንደዛው ስንዝ ነበር ከዚህ የደረስኩት፡፡ <<አልጋ አልጋ>> ከሚሉ ጎልማሳ ሴት ደርሼ ስለአመጣጤ ትንሽ ካወጋኋቸው በኋላ በማግስቱ ልከፍላቸው መታወቂያዩን  አስይዤ ከመኝታ ክፍሌ ገባሁ፡፡

የቀን ጉዞው በረሃብ ላይ ተጨምሮ ከክፍሉ እንደገባሁ እንቅልፍ ይዞኝ ነጎደ፡፡ ማግስቱን ጠዋት ለህሌና ደውዬ ገንዘብ እንድትልክልኝ በስልክ እወተውታት ጀመር፡፡ በ*ርግጥ የት እንደነበርኩ ስላላወቀች ገንዘቡን ለመላክ ፍቃደኛ አልነበረችም ነበር፡፡ በመጨረሻም ጉዞዬን ስነግራት ያልነበር ትህትናዋ በላዬ ላይ ዘነበ፡፡ ውስጤን እጅጉን ተሰማኝ፡፡ እኔ ከሆነ መሄዴ በመሥራት ለመማር ካልሆነ ግን ለዓመታት ስታገልበት የነበረውን የድርሰት ሥራዬን ሊያሳትሙ የሚችሉ አካላትን ማፈላለግ ነበር፡፡

ጓዜን ከአዲሱ መናኸሪያ አድርጌ በስታድየሙ ቀጥታ በፓፒረስ ወጥቼ ትልቁን ሀይቅ በመደመም እየዞርኩ አየሁት፡፡ በርግጥ ለኔ እንደዚህ ዓይነት ነገሮች ጊዚያዊ ደስታን ይፍጠሩብኝ እንጂ ውስጤ ቆይተው በስቃይ የተረበሸውን ማንነቴን መለወጥ አልተቻላቸውም፡፡ ከአሁን አሁን ተልኮልኝ ይሆን እያልኩ ስጠብቀው የነበረው ገንዘብ ጣናን ትቼ ወደ ጊዮርጊስ ስመለስ በስልኬ መግባቱን የሚያመለክት መልዕክት ደረሰኝ፡፡

ፍራቻዬ ያንን ያልጋ ሳልከፍል ቀርቼ በማላውቀው ሀገር ሌላ ችግር ባስተናግድ የሚለው ነው፡፡ ታድያ ገንዘቡ መግባቱን እንዳወኩ ሦስት መቶ ብር አውጥቼ አንድ መቶ ሀምሳ ብሩን ከፍዬ አንድ መቶ ሀምሳ ብር ይዤ ወደ ምግብ ቤት ስገባ ነገሩ እንደ በረራ ሳይሆን ቀርቶ በጣም ከባድ እና አስቸጋሪ ነበር፡፡ ምግቡ ለእንስሳ እንኳን የማያቀርቡት ሲሆን መጠኑም በጣም ያነሰ ነበር፡፡ ሀገሩ እኮ ምዕራብ ጎጃም ነው፡፡ ነገር ግን መጠን እና ጥራቱ  ሲገርመን ዋጋው ከበረራ የግብይት ዋጋ በአምስት ብር የጨመረ ነበር፡፡

ይህም እየገረመኝ ከተማዋን ለመቃኘት ስወጣ በርግጥ በረራን ከባህርዳር ላገኛት አልቻልኩም፡፡ ጣና ዙሪያ፤ ገበያ፤ አባይ ማዶ፤ ልደታ፤ የሰላም በር እና ቅል ጎጥ በትንሹ ያየኋቸው ሲሆኑ ብዙም ከከተማነት ትርጉም አንዓር አላረኩኝም፡፡ ህይወት ነው እና መቀጠል ስለነበረባት ራሴን አሳምኜ የምከራየው ቤት ብፈልግም ዋጋው አይቀመስ ሆኖ ከበረራ የጫፍ ሰፈር ዋጋ ጋር ሲነጻፀር ናር ያለ ነበር፡፡ ወደ ገጠራማው ቦታ ፍለጋዬ ቢበረታም የክረምቱ ዝናብ ታክሎበት ከበድ ያለ ሆነ፡፡

*ታድያ ቀኑ ምንም ሳይሳካ ተጠናቆ ማታው ከያዝኳት አልጋ ቤት ለሊቱ ተደምድሞ ያስላኳት ብር ወደ መደምደሚያው ደረሰች፡፡ በማግስቱ የምይዘው የምጨብጠው ጠፍቶኝ ሀሳቤ ከሥራውም ከቤት ፍለጋውም ተበታትኖ ሰዓት ከዛው ከመኝታ ቤት ደረሰ፡፡ የመኝታ ሀምሳ ብር ይቀርብኛል ዳግም በዚህ ላይ ሌላኛው ምሽት እየመጣ ስለነበር ሌላ ክፍያ ያስፈልጋል፡፡ የማስታወቂያ ሥራዎችን ጎርጊስ አከባቢ እየዞርኩ ብመለከት እኔን የሚያሳትፍ ሥራ ምንም እንደሌለ አረጋገጥኩ፡፡ በበረራ በፖል ላይ ተለጥፎ ለዐይን የተመረርኩበት የማስታወቂያ መአት ከዚህ ሰፈር ካንዳች ቦርድ ውጪ ሌላ ቦታ ማግኘት አልተቻለኝም፡፡*

*በየመንገዱ የሚለጠፉ ነገሮች እንኳን እንዳጋጣሚ ቢገኙ እርዳታ የሚሹ እንጂ ድጋፍ የሚለግሱ የሥራ ማስታወቂያዎች አልነበሩም፡፡ የመጨረሻ አማራጩ የነበረው የቀን ሥራ ፈልጎ መሥራት ነበር እና ያንንም ሥራ ለመጠየቅ ከሳይት ሠራተኞች ጎራ ብል የቀን ውሎው አንድ መቶ ብር እንደነበር ነገሩኝ፡፡ በጣም ራሴን ከሚገባው በላይ ነቄ ጠላሁት፡፡ ቤት አልተከራየሁ የአልጋ እንኳን ለመክፈል አትበቃ፤ ይብዛ ሲለው ደግሞ የሰው ልጅ ምንም ነገር ሳይቀምስ አይደለም የቀን ሥራ ሲሰራ ቀርቶ ለመንቀሳቀስም ምንያሓል አዳጋች እንደሆነ ያለፈችሁበት ታውቁታላችሁ፡፡ ላላለፋችሁበት ግን መርዶ ነጋሪ አልሁን እና ሰውነትን ከውስጥ እንደ እሳት ረመጥ እያቃጠለ ዐይን አጨልሞ እግር እያንቀጠቀጠ ከሰውነት ጎዳና አውጥቶ እንደ እቶን ይባላል፡፡*

*በሶስተኛው ያዳር ቀን የተላከችው አምስት መቶ ብር ተጠናቃ እንደ ወላድ እርጉዝ ሴት በምሄድበት በምቆምበት ሁሉ መቃተት ጀመርኩ፡፡ በአንድ መቶ ብር እንኳን ሊያስገቡኝ የፈለጉትን ሥራ በአራተኛው ቀን ብጠይቅ ከበረራ ወደ ባህርዳር መግቢያ ጎዳናው ላይ የቆሙት የቀን ሠራተኞች እንደተቀራመቱት ያላገኙትም አዝነው ከዛው ተመልሰው ቆመው እንደሚጠብቁ የሳይቱ ኃላፊ አረዳኝ፡፡ በ*ርግጥ ከቦታው ደርሼ ሳይ የተቃውሞ ሰልፈኛ መስለው በአሸኑ ከአደባባዩ ይራኮታሉ፡፡ ሲበዛ አደገኛ ችግር ውስጥ ገብቻለሁ፡፡ እና ያለኝ አማራጭ ወደ በረራ እየደወልኩ ከማውቃቸው ሰዎች ላይ በየምክንያት ገንዘብ መቀበል ነበር፡፡ መጀመሪያ የደወልኩት በቅርብ ከምተዋወቀው ከበረራ የከተማ አስተዳደር ውስጥ ከሚሰራ እንጂነር ነበር፡፡ ከዚህ ቀደም ወስጄ ያልመለስኩት ገንዘብ ቢኖርም ዳግም መጠየቁ እስትንፋሴ ለደቂቃዎች መተንፈስ አቅቶኝ እየቃተትኩ በመንተባተብ ነገርኩት፡፡ ነገሩ እሱም በፕሮግራም ላይ ስለነበር እንደማይሆን ነገረኝ፡፡ ቀጥዬ ከአክስቴ ጋር ስደውል የጠየኳትን ሁለት መቶ ብር ላከችልኝ፡፡*

*ይሁን እንጂ ከአራተኛ ቀን የአልጋ ክፍያ እና የራት መብያ ሳታልፍ ቀርታ ከመውጣቷ አለቀች፡፡ ዳግም ወደ ኢንጂነሩ ብደውል የማይሆን ይሆን እና አጉል እንቀያየም ይሆንል ብዬ በመልዕክት ሶስት መቶ ብር እንዲልክልኝ ላኩለት፡፡ እሱም ሳያቅማማ በሁለተኛው ቀን ካለበት ሆኖ ላከልኝ፡፡ ሶስት መቶ ብር በእጄ ቢገባም አምስተኛው ቀን ተጨምሮ በእጄ ላይ አንድ መቶ ሀምሳ ብር ቀረች፡፡ በሰላሳ አምስት ብር ራቴን በልቼ አንድ መቶ ሃያ ብር ቀረችኝ፡፡ መቼስ ያላዩት ሀገር ሲናፍቅ እንዲህ ነው እና በረራ እስክደርስ ውስጤ በፍርሃት ተናጠ፡፡ በአምስተኛው ቀን ከወንድሜ አላዛር ደውዬ ሁለት መቶ ሀምሳ ብር እንዲልክልኝ ደጋግሜ እየደወልኩ አጣደፍኩት ከቀኑ ስምት ሰዓት የጠየኩት ገንዘብ ገባልኝ፡፡*

*የማደሪያ ለአምስተኛ ጊዜ አንድ መቶ ሀምሳ ብር ስከፍል ከእጄ ላይ የቀረችው ሁለት መቶ ሃያ ብር ብቻ ነበረች፡፡ አስር ብር ትኬት ቆራጩ ጨምሮልኝ ቀርጦ እንዲያሳፍረኝ የደከመ ሰውነቴን እያሳየሁት እንዲረዳኝ በጉትጎታ ብበረታም ይባስ ብሎ ሀገራዊ የእርስ በእርስ የጦርነት ሰበቃ ላይ ስለነበሩ በዘቦቹ የቅዝምዝም ዱላ ሊያቧቅሰኝ ፈለገው፡፡ ወደ በረራ ከባህርዳር በየቀኑ የሚጎርፈው ሰው*

ኖሮዉን ጣራ አስነክቶት ምርር ይል ነበር፡፡ በረራ ደብረ ኤባ ለካ ብዙ ጉድ እንደተሸከሙ ሳላውቅ የማላውቀውን ሀገር ተመኝቼ ባለኝ ችግር ላይ ችግር አቆፋዳውን እንዲከፍትብኝ ሳላውቀው ፈቀድኩለት፡፡

እለታ ቀንን እየወለደ ሊሳካ ሳይችል ቀርቶ የያዝኳትን የሕዋዊ ስልክ ለመሸጥ ስድስተኛውን ቀን ሳስማማ ሁለት መቶ ሃያ ብሯ ከዛው አለቀች፡፡ ሰባተኛው ቀን ተደግሞ የምደውልበት ባጣ ስልኬን ለማዳን ከነጋድረስ ብደውል ‹‹ድሮውም ድሮ ነሽ እንኳንም ዘንቦብሽ›› ሆኖ ላይሳካ ነገር ስልኬን ዘግቼ ከየመንገደኛው እየዘረጋሁ አስማማ ጀመር፡፡ አንዳንዱ ከደጁ ዛፍ እርፍ እንደሚጎትተው ሁሉ ስልኩንም ራሱ አምርቶ ያውቅ ይመስል ‹‹እንደዚህ ዓይነት ስልክ እማ ቢበዛ ሁለት መቶ፤ እንደው ሀዘኔታ ከታከለበት ሶስት መቶ ብር ነው፡፡ በርግጥ የሰው ሀገር ሰው ነህ ማንም የሚገዛህ ስለሌለ እኔ በሶስት መቶ ብር ልግዛህ!›› ብቻ ወሽመጤ ቁርጥ ይልና ምንም ሳልመለስ ጥዬው እሄዳለው፡፡

ከዛም ከዚህም ብዞር ከሥስት መቶ ብር የተለየ ክፍያ ያለው የስልክ ቤቶችም ሆነ ገዢዎች ሊመጡ አልቻሉም፡፡ ምሽት እየመጣ ነው የሰው እዳ ደግሞ በራስ ላይ ከምሮ ገብቶ ለመተኛት ማሰብ ሞኝነት ነው፡፡ በሰጡኝ ዋጋ ልሸጠው ከአዲሱ መናኸሪያ ሆኜ ከአንድ ተራ እስከባሪ ጋር ብገናኝም ሚሞሪ ከሌለው በዛም ላይገዛኝ እንደሚችል አስጠንቅቆ መለሰልኝ፡፡ ሚሞሪውንም አብሬ ብሸጥለት ምንኛ እድለኛ ነበርኩ ነገር ግን በውስጡ ከዛሬ ነገ ይወጡልኝ ይሆን ያልኳቸው ‹‹**አርቦሄሮያ ቁጥር አንድ፤ ሐማንዳብ፤ እኛ! የጭንቅ ዘመናቶች እና የዓለም ጣጣ**›› የተሰኘው የግጥም ሥራ ታክሎበት አራት መፀሐፎች ተከምረውበታል፡፡ በተለዋጭ ቦታም ከሚሞሪዬ በስተቀር ያስቀመጥኩበት ቦታ አልነበረኝም ነበር፡፡ ሰውነቴን ቆርጠህ ስጠኝ ያለኝ ይመስል እየነዘረኝ ስልኩን ከእጁ መንጭቄ ከቦታው ጥዬው ሄድኩኝ፡፡ የአልጋ የምከፍለው ብር ስላልነበር አመሻሽ መሆኑ እና ወቅታዊ ግርግሩ ስላሰጋኝ ‹‹ወለል›› ከሚሉት ሰፈር መታወቂያዬን አስይዤ ማግስቱን ልከፍል ብሄድ አስቀድማ ከሦስት ቀን በፊት መታወቂያ ያለችኝ ባልቴት ቅድሚያ ገንዘብ ካልሆነ ሞቼ እገኛለሁ አለች፡፡ በሁነቴ መሮኝ እያዘንኩ ከመናኸሪያው ካሳደሩኝ ለአዳር ከግቢው ስገባ ግዳጁን አጠናቀ ከቆመ የባስ ሹፌር ጋር ተገናኘን፡፡ መመላለሴን ያየው ትኬተር ከለበስኩት የትግራይ ልዩ-ኃይል ጫማ ቢጠራጠረኝም ስልኬን የሚገዛ ሰው ካለ እንዲያሻሽጠኝ ስነግረው አምኖ ለሹፌሩ አምስት መቶ ብር ሸጦ የሁለት መቶ ሰላሳ ብር ሁለተኛ ደረጃ ባስ ቆርጦ ለሊት አስራ አንድ ሰዓት መምጣት እንዳለብኝ አስጠንቅቆ ሸኘኝ፡፡

ቀኑን ቁርስ እና ምሳ የበላሁባት ኮማሪት ከመጣሁ ጀምሮ የተለያዩ ነገሮችን እያደረገች ብታግዘኝም ክፍያ ስላልከፈልኳት ራቴን በልቼ አንድ ላይ አንድ መቶ አስራ አምስት ብር ከፍዬ በሀምሳ አምስት ብር ካንድ ደሰስ ካለች ጎጆ ገብቼ ለሊቱ እስኪነጋ በእንስፍስፍ መጠበቁን ተካንኩበት፡፡ ከለሊቱ ስምንት ሰዓት ስነሳ ባልቴቷ ተነስታ ሰዓቱ ሲደርስ እንደምትቀሰቅሰኝ ነግራ መለሰችኝ፡፡ ትንሽ ጋደም እንዳልኩኝ ከለሊቱ አስራ አንድ ሰዓት ደርሶ መኪናው ከመናኸሪያ ክላክሱን እያሸፈተረ ምልክት መስጠት ሲጀምር ባልቴቷ ቀስቅሳ ሸኘችኝ፡፡

ውስጤ ትንሽ እርካታ አግኝቶ መንገዴ አነጋግ አስራ ሁለት ሰዓት ሲጀምር አዴትን አልፎ ያንን ገደላ ገደል ወጥተን ሞጣ ስንደርስ መኪናው ተበላሽቶ ትክ መኪና እንኳን ማግኘት ሳይቻል ከዛው ቆመን ቀረን፡፡ በመጨረሻም ሹፌሩ ምንም አማራጭ ስላልነበረው ልዬ በሚባሉት ባሶች እንድንሄድ መቶ ሰባ ብር ለተቀሩት ሲመልስ እኔ ግን ምንም አማራጭ ስላልነበረኝ ከነሱው የሙጥኝ አልኩ፡፡ ልዩ ባሱ ከሞጣ በረራ 350ብር ስለነበረ እኔ ያው አነሳሴን ደግሜ አልነግራችሁም እና ከትኬተሮች ዘንድ አዳሪውን እዲቆርጡልኝ ከቢሮ ቢሮ እየተሯሯጥኩኝ መማፀኔን ቀጠልኩ፡፡

በመጨረሻም ተሳክቶ አዳሪውን በአንድ መቶ ሰማንያ ብር ቆርጬ ሌላኛውን አስራ አንደኛ ሰዓት መጠበቅ ግድ ሆነ፡፡ መሄጃ መንቀሳቀሻውን አላውቀው ነገር ሀገሩን ከመናኸሪያው ከተራ አስከባሪዎች ጋር ውዬ ማታ ላይ በነገርኳቸው ስንብቴ አዝነው ከየመንገዱ፤ ከየመኪናው መቶ ሰባ ብር ለቅመው የሚያውቁት ወለል ቤት የቀረው ገንዘብ ለምሳ እንዲሆነኝ በማሰብ አሳደሩኝ፡፡

ከበረራው ጎዳና ባይለይም ያ! ለሊት በጣም ከባድ ነበር፡፡ የመኝታ ቦታ፤ ፍራሽ እንዲሁም ጣል ተደርጎ ብርዱን የሚከላከሉበት ፎጣ እንኳን የለውም ነበር እና ቁጭ ብሎ ከመደብ ላይ በብርድ እየተቀጠቀጡ ማደር ከባድ ነበር፡፡ የሸከፍኩትን እቃ አስር ሰዓት ተኩል ላይ ይዤ ስውጣ መናኸሪያው ላይ ከተሳፋሪ ሰልፈኞች ውጪ የግቢው ሠራተኞች አልነበሩም፡፡ ሰዓቱ ደርሶ ቢያልፍም የመናኸሪው በር ግን እስከ አስራ አንድ ተኩል ሊከፈት ሳይችል ሰልፈኛው ጨኸት ጀመረ፡፡ ሊቀሰቅሰኝ ቀጠሮ ይዞልኝ የነበረው ተራ አስከባሪ ከሰው ሁሉ ውስጥ እቃ ይዤ ስለነበር በሩን ከፍቶ ቢያስገባኝም ዳግም ቀጠሮ የተያዘለት መኪና ደጀን ላይ ተበላሽቶ እንደቀረ አሳወቀን፡፡ በርግጥ ከውስጥ ከፍቶ ያስገባኝ ተራ አስከባሪ በጣም አዝኖ በፐርሰንት ክፍያ እንድሄድ ትኬት ቆራጩን አዳር እና ውሎዬን ጭምር ነግሮ ለማሳመን ሞከረ፡፡

እኔም ከትኬት ቆራጩ ሳልለይ ማታ ከሰበሰቡልኝ ብር ላይ ዘጠና ብር ጨምሬ ‹‹ሀገሬ ባስ አጣሽ ወይ›› እያልኩ ተሳፋሪዉን በሳቅ እያምሸቀሸኩ ጉዟችንን ከሞጣ ጀመርን፡፡ ያንን አድካሚ መንገድ እንደምንም ጨርሰን ከበረራ የአውቶቢስ ተራ ስንደርስ መሽቶ ይዤው የነበረውን ጓዝ ከለመድኩት ሰፈር ለጋሲዮን አድርጌ ከማድርበት የመኪና ዘብ መጠበቂያ ስፍራ ስሄድ የቀድሞ ጓደኞቼን አገኘኋቸው፡፡ ባጋጣሚ በወቅቱ የሚጠብቀው ተረኛ ስላልነበረ ብርድ አንገሽግሾ መቆሜን እስክጠላ ድረስ ለሊቱን ዝናቡ እንዳጠመቀኝ አደርኩ፡፡

ማግስቱን ከነሲፓራ ቤት ሄጄ ቁርስ ብበላም የእንቅልፍ ነገር በብርድ ላይ ተጨምሮ በቁሜ ያንቀላፋኝ ጀመር፡፡ ከነጋድረስ ቤት አልሄድ ነገር ያ! እኔን ሲያይ የሚጨነቅ ፊቱ እጅግ አስጨንቆ የማይሆን ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ምንም አማራጭ ስላልነበረኝ በለጋሲዮን አቦ መሄጃ መንገድ አድርጌ ፀበሉ ከሚገኝበት ጫካ ውስጥ ገብቼ ኮቴን ከፊቴ ላይ ደርቤ ተኛሁ፡፡

በጣም ኃይለኛ እንቅልፍ ይዞኝ ነበር፡፡ አንድ ሴት እና ሁለት ወንዶች ዙሪያዬን ከበው አንደኛው ‹‹ማነህ አንተ?›› ሲል ያለሁበት ቦታ በእንቅልፍ ተዘንግቶኝ ደካክመው የነበሩ ዐይኖቼን በእጄ እየጠራረኩ በድንጋጤ ተነሳሁ፡፡ በ*ርግጥ እነሱም የአራት ዓመት ልጅ ጠፍቶባቸው ስለነበር ነብሳቸውን አጥተው ነበር ነገር ግን ሆኖ ሁኔታዬን ሲያዩ ‹‹ምን ታደርጋለህ ከዚህ ጫካ?›› ብለው ትንሽ ካፋጠጡኝ በኋላ እኔም ያለውን እውነት ሳልደብቅ ነግሬያቸው ልጅ ፍለጋውን ተቀላቀልኩ፡፡

ልጅ በየመንደሩ ቢታሰስ ሊገኝ አልቻለም፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ከዚህ በኋላ የሚመጣውን ነገር ባላውቅም ውስጤ ግን ክፉኛ ተጨንቋል፡፡ ከብዙ የሜዳ ዳሰሳ በኋላ ግን ከቤቱ ልጁን በደንብ አጣርቶ ያላየው ባለቤት ቢጨንቀው ሆኖ ከየስርቻው ሲፈልግ ከቁቦ ውስጥ ሆኖ ሲጫወት አገኘው፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጤ በመጠኑ ተረጋግቶ ከቦታው ብሄድም ያላጣጣምኩት እንቅልፍ ግን ሊለቀኝ አልቻለም ነበር፡፡

አመሻሽ ላይ ተረኛ ስላልነበርኩ ከመኪናው ገብቼ ጋደም ስል ያለምንም አልባስ ጥቂት ቢወስደኝም በዛ የክረምት ዝናብ ላይ ብርድ ተጨምሮ ያንዘፈዝፈኝ ጀመር፡፡ ይህ ህይወት ብቻ አስጨናቂ ሆኖ ጥበቃ እና ጤንነቱን ያልጠበቀ ስላሙ የደፈረሰ ማንነቴ በማይናቀው ተንቆ ተደፍሮ ከግልምጫም ስድብን እየተጋተ ቢቀጥልም ራሱን ሳያስከብር ቀርቶ በዛ በክረምት ከሥራው ለመሰናበት ግድ ሆኖ ተከሰተ፡፡

ዛሬ ከሲፓራ ጋር ስናወራ ስለነበር በሯን አዛግቼ ሌላኛው የጥበቃ ዘቦች ጋር ሄጄ ለማደር ብሞክርም ሳይሳካ ቀርቶ መርዘኛው የሌቦች መናኸሪያ ወደ ሆነው ሸለቋማው ኬላ ለመኝታ የሚሆን አልጋ ባገኝ ብዬ ሲፓራ በሰጠችኝ ብር ለማደር ተፍ ተፍስል ሰባት ጥቋቁር የለበሱ ቦዘኔ ዘራፊዎች ተከመሩብኝ። መፈናፈኛ አልነበረኝም ሰባቱም ቁልፍ የሚባሉ አደገኛ ቦታዎች ላይ ይዘውኛል። ያ! ሰባት ዓመት ደምስሬ እስኪበጠስ የሰራሁት፤ ሰዎች ዐይኖቻቸውን አድምተው የተጠላሁበት፤ አንደበታቸው በመልካም ፋንታ እሬት እየተፋ ከዛሬ ነገ እያልኩ የተጨነኩበት የልፋት ውጤቴ በነዚሁ ሥራ አልባ የመንግስት ፍቃደኞች ተበላ። ከሥፍራው ፖሊሶችን ብፈልግም ላገኛቸው ስለቻልኩ ተከላክዬ አንኳን ዶክመንቴን ማስመለስ የምችልበት መንገድ ጠፈኝ። በመጨረሻም በአከባቢው በቆሙ የመኪና ዘቦች ጥቆማ አማካኝነት ከማዞሪያው ይገኘ ብመጣም በሌባ እና ፖሊስ መሐል ሮጫ ተይዞ ሳይሳካ ሌባውም እንዲያመልጥ አግዘውት ተመለሱ።

ተጨማሪ ሁለት ኃይሎች መገናኛ ስልክ የያዙ በቦታው ቢደርሱም ይባስ ብለው ሦስቱን በዐይናቸው ጠቅሰው ከሸኙ በኋላ የዘራፊዎቹን ማንነት በፊታቸው መልክ እና ቁመና ሳስረዳቸው አውቀውት ሪፖርት እንዳደርግ ብጠይቃቸውም ችግር እንደሌለው ነግረው አሰናበቱኝ። በ*ርግጥ በጣም ተደናግጬያለሁ። በዛ ላይ የጠፋው ተራ ስልክ ቢሆንም ሚሞሪዋ ግን ለኢትዮጲያ እና ለእኔ ትልቅ ዋጋ ነበራት፤ በዛ ሁሉ አስቀያሚ ዶፍ ላይ ይሄ ሲጨመር አይደለም የሰው ልጅ ሆነህ ብረት እንኳን አንዴ ተሸክሞ ለሚኖረው አለት ሲጨንቀው እንባውን በዝገት ይገልፃል።

ከፖሊሶቹ ተለይቼ ለማመልከት ብፈልግም ፖሊስ ጣብያው ያለው ኃይለኛ ከሚባሉት ሌቦች ሰፈር አልፎ ስለሆነ በአካል ላይ ሌላ መዘዝ ይዞ መምጣት ነበር። ፖሊሶቹም ከነዚሁ አካላት ጋር ስለሚግባቡ ቦታውን መካን አድርገውታል። ስለዚህ ቀድሞ የደንብ ልብስ ያለበሰ ሰራዊት ይሄንን ካደረገ አላውቀው ሰፈር በዛ ላልፍ ብሞክር የደንብ ልብስ የለበሰው ወንበዴ የመንግስት ቅጥረኛ ሌላው ስጋቴ ነበር።

ተስፋ ላለመቁረጥ ምሽቱን ከዛው የመኪና ጥበቃዎች በልመና አድሬ ማግስቱን ለፖሊስ ላመለክት ብሄድ ግማሹ ከሌባ ጋር ሽርከኛ ሆኖ ሌላም በሩ ተገንጥሎ ንበረት የተወሰደበት ባለንብረት ከዛው ተገኝቶ በድርድር ለማስመለስ ቢሞከርም የሌብነት ሞያው አሰማሪ ባለቤት ከፖሊሶች ጋር ሳይስማማ በመቅረቱ ወደ ፍርድ ቤት የሚመራለትን ደብዳቤ መርተው ሲያስተላልፉ አየሁ።

የሀገር ሰው ማጣትን ማየት እዚህ ጋር ነው። እኔም ብሆን ይህን እያየሁ ሌላ መዘዝ ከምፈልግ የሰረቀኝን ሰው አጥፍቼ ከተያዝኩም ሞቴን በፀጋ ልቀበል ካልተያዝኩም አምልጬ ለመሄድ አቀድኩ። ነገር ግን ወንድሜ አላዛር የሚሰራው ከዛው ሰፈር ነው። አጎቴም ነጋድረስ ሲዘዋወር የሚውለው ከዛው ስለሆነ አጣርተው ደርሰው በእነሱ ላይም ጥቃረት ያደርሳሉ የሚል ስጋት በአዕምሮዬ ተደግኖ ቀን ቆርጬ መጠበቁን መካን ሌላው ጉዳይ ሆነ።

ታድያ ተስፋ ያልቆረጠው ተስፈኝነቴ ቢሆን ብዬ የመብት ከለላ ላይሆነኝ ክስ አስጀመርኩ። ጉዳዬን የያዘው ሰው ክሱን ሲያደራጅ ተከሳሹ እኔ እንጂ ከሳሽ መሆኔም የተዘነጋ ይመስል ስለግል ህይወት እና ኑሮዬም ጭምር እየፈተፈተ ከፊቱ ባቀረባት ወረቀት ላይ ይቦጫጭር ጀመር። በመጨረሻም ‹‹ፖሊሶች ተመድበው ሌባውን ይይዛሉ›› ብዬ በክሱ ላይ ብፈርምም ነገሩ ሳይሆን ቀርቶ ሲያሰራኝ የነበረውን ሰው ማምጣት ካልቻልኩ ለዛሬው ወደ ማፈላለግ ሥራው እንደማይገቡ በግዳጅ አሳወቁኝ።

‹‹ጅብ ከሄደ የውሻ ጩኸት ምንስ ሊሰራ›› ሆኖ ከሌሎቹ ጋር እየተነጋገርኩ ጉዳዬን ለማስፈፀም ብጥርም ሳይሳካ ቀርቶ በእልህ ውስጥ ወደ መካረር ገብተን ከግቢው ወጥቼ ሄድኩኝ፡፡ በአንዳንድ አካላት የጠፉትን ሌቦች ለማፈላለግ ብሞክርም እውነቱ ተደብቆ አንድ በአትኩሮት ያየሁትን ሰው አጣሁት፡፡ ጓደኞቹ ናቸው በሚባሉ አካልቶች በድብቅ እንዲያደራድሩን ብፈልግም ቀድሞ ከፖሊስ ጣብያ የተጀመረው ክስ ሪፖርት ተደርጎላቸው ስለነበር እምጥ የገባ ስምጥ ሲገኝ ሳይችል ቀርቶ በዛው ጠፋ፡፡

ከኔ ጋር የነበሩ የማውቃቸው የሰፈሩ ወጣቶች አፈላልገው ለማግኘት ቢሞከርም አይሆንም የተባለው ነገር ሳይሆን እና እኔን በዛ ጥናት መሰረት ሊያጠቃኝ የመጣ ሌላ አካል መኖሩ ይፋ ባይሆንልኝም *ርግጥ ሆኖ ተስፋን በተስፋ መቁረጥ እድቋጨው ሚሞሪው የሌባ ሰራው ከተያዘ ችሩ ሌላ ነው እና መደምሰሱን (ፎርማት) መደረጉን ነገሩኝ፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ ከዚህ በላይ የጭለማ ዘመን የለም፡፡ ኢትዮጲያ ፈጣሪዋ ይጠብቃታል ሲባል ብዙዎቻችን አምነን ባንቀበለውም እውቱ ግን የሱ ጥበቃ ብቻ ሆኖ ይኸው እየኖርን ነው፡፡ ግን ምንም አይምጣብን!! አንዳች ነገር ቢከሰት ለኛ እኛው በጋራ ዘብ ካልቆምን በስተቀር ፈጣሪ ታክሎበት ከልረዳን እንደወጣ ቀረ መባባሉ ቢቀጥል እንጂ አያቆምም፡፡ ማንንም በራስህ ላይ አታንግሰው ምክንያቱም አንተ ለራስህ አቅም ያለህ ንጉስ ነህ፡፡ ማንም ያንተን መኖር እንዲጋፈጥህ አታድርገው ምክንያቱም ወጥቶ ለመግባትም እስትንፋስ እስኪያጥርህ እንደ ሽቀጥ ይጫወትብኃል እና፣ የጎረቤትህ ውሻ በጅብ ሲበላ ከሳክ ነገም ያንተው ነው እና ነገሮችን ከመራዳት በሌላ መልኩ የምታሳልፍ ከሆነ በቃ በየተራ ከመጮህ የዘለለ አክብሮ አንተን የሚጠብቅህም ሆነ የሚያስጠብቅህ የለም፡፡

# ታሞ ያልዳነ ሠው!!

ህመም እንኳን  አሞኝ
ለሰው አልናገር፤
ይባስ ይወጋጋኛል
ካሳር እና ምንቃር፤
ቢዳንልኝ መስሎኝ
ምርቃዜን ብሰጠው፤
በምርምር እጦት በኮፈኑ ብሶ
ልቤን አቆሰለው፤

አነጋግቶ ውሎ አመሻሽ ላይደግም
ፊና በጥሪኝ እያሳፋ፤
በጠራራ ፀሐይ በምሽት ታውሮ
ቀን እያዋለው ሲያናፋ፤
ባልሰማው ጆሮ ባልኖረው አዱኛ
ውል ቋጥሮ እየገመደ፤
ስንቴ አስጨነቀኝ ህመም
እንኳን ታሞ እያነደደ፤

አልተወው ነገር ምኞት
ካሳብ ሰምሮ፤
ወኔዬም አስገምግሞ በጠጠር
ቋጥኝ ከምሮ፤
እርካቡን ብጫነው
እሬት አርግዞ፤
ደግሞ ያንሸራትታል
እንባ ና ጥርስ ታዝሎ ባዞ፤

በተፈጥሮ ሰማይ አየር
ንስር ካሞራ እያጣላ፤
ነብር ንኳ አዝኖ ለጎሽ
ሆድ ቆርሶ እንዳያዳላ፤
አበሳስቶ ሊያጋምድ መርፌ
ከክሩ እየተዋደቀ፤
መች ይሞቀው ነበር
ካንጀት የተላቀቀ፤

አይጋልቡት ነገር የቆሙበት
ድንጋይ፤
አይበሩ አይዋኙት ልጓሙ
ተንጠልጣይ፤
በክህደት ለሊት ቀኑ ዳምኖ
በውነት ያልተረታ፤
እረ ይሄስ ከየት ይሆን
ምልጃው የተፈታ፤

ማረሻው እንደሁ ካልተዋደደ
ከሞፈሩ፤
ላይበጅ ሆኖ ከበሮች ማነቆ
ማሰሩ፤
ላይታረስ መሬትን ከሰማይ
አስታከው ካልጎመጎሙ፤
ታድያ ምን ያደርጋል ቀንበር
ጢጣ መሸከሙ

ውሃም በንፋሳት ህይወት

ዘርቶ ነፍስ ካላዳነ፤

እሳትም ነዶ ንዶ ብርድ

ካላሰከነ፤

ዋልታ ከፍርግርግ ካልያዘ

የምሰሶ መቆም፤

ድሮውንስ ምን ሊበጅ

የንፋሳት ዓለም፤

ባመሻሽ ባነጋጉ ወፎች እየዘመሩ

ካልነጋ ለሊቱ፤

ፀሐይ ስቃ በቋር ከባሰ

ግለቱ፤

ቃር አላስችል ብሎ ምስር

ከገባ ከቤቱ፤

ካበቃ ዓለሜ አልሞት

እንደሁ ልሙት፤

ስለ እኔ ከጠየቃችሁኝ ስለሁሉም ፈጣሪዬ ይመስገን እና ‹‹***ሐማንዳብ***›› የተሰኘውን ሥራ በሀርድ ኮፒ ከሰው ጋር ስላገኘሁት በመጠኑ ለመረጋጋት ሞክሪያለሁ፡፡ በዛ ላይ ይህንን ‹‹***እኛ! የጭንቅ ዘመናቶች***›› የተሰኘውን ሥራ ፅፌ እስክጨርስ ውስጤ በረሃብ፤ ንዴት እና እግሮቼ በክረምቱ እግረ መንገድ ጉዞ ተሰላችቶ ቢያመኝም ዛሬም ተስፋ ስላለኝ ምንም ሳልሆን አለሁ፡፡ *ለትንሽ ቀን ውድቀት ብዬም ትልቁን ማንነቴን ለማንም ሰጥቼ ማለፍ ስለሌለብኝ ዛሬም እንደ ትናንትናው ሁሉንም ነገር ተሸክሜ ወገቤ ረግዶ እግሮቼ መንገላታትን ቢሰለቹም ነገ ሌላ ቀን ይሆን ይሆናል እና እሱ እስከፈቀደ ድረስ ሕይወትን በለሊት አንግቼ ቀንን ለማየት ይኸው ዛሬም አለሁ፤* ነገም ኖሬ ላላየኝ ሁሉ ራሴን አኑሬ አሳያለሁ፡፡

ዓለም ላይ ምንም ሙሉ እና ጎዶሎ ነገር የለም፡፡ እስቲ ዓለም ጎዶሎ ነች የሚል ካለ የሱ ሙሉነት እንኳን የሚኖርበትን ንፋሳት ቢያጣ ለአፍታ የሚቆይ አለ? ሳይመገብ እና ሳይጠጣ ሳምንታትን ችሎ የሚቆይ አንጀትስ ይኖረው ይሆን? ተፈጥሮ አግዛ ካላጀበችው ከቦታ ቦታስ የሚንቀሳቀስ ይሆን ይሆንን? እሺ አለም ሙሉ ነች ያልከኝስ ክምር ከሆነው የሙሉነት መንፈስ አንተን ሳፍታ የማያስጨንቅህ ነገር ኖሮህ ይሆን? ሙሉ አድርጎኛል ያልከው ሙሉነትስ ምንያክል

ትተማመንበት ይሆን ይሆንን? በጎዶሎነት ያገኘኃቸውንስ ሙሉነት ምንያህል ታውቃቸው ይሆን? ብቻ ስላልኩህ ራስህን ጥለህ እንደኔ ተንከርፈፍ እያልኩህ አይደልም። ነገር ግን በጎዶሎው ውስጥም ሆነ በሙሉነት ውስጥ ፀንቶ እና ተለውጦ የሚኖር ማንነት ብቻ ይኑርህ እያልኩህ ነው።

*ሙሉነት ፀጋ ከሌለው ጎዶሎነት ትህትና ከሌለው የሁለቱም ድምር ውጤት ባዶነት ብቻ ነው።* ዓለምንም ልክ እንዳዚሁ አርክሶ ሰው በሌለው ፈረስ ቢዶ ሜዳን ሲጋልቡ መኖር ድምር ውጤቱ ልፋት እንጂ ድካም ሆኖ ወደ ስኬት አያስገዝም። መልካሙን ሁሉ ለመሆን አስብ ነግር ግን እያንዳንዱ ቦታ ያለምንም መፈተኛ የሚወጣ ጋራ ተራራ ወይም መሰላል የለም እና ሁሉም ገፍትረው ሊጥሉህ ሲቃጣቸው አጥብቀህ ያዛቸው። በ*ርግጥ አንተ ስታልፍባቸው ይፋሩ ይሆናል እንጂ አንተ ቀለህ አትወድቅም።

አንተ በ*ምድር ላይ ካሉ ፍጥረታት ሰው ሆነህ በመፈጠርህ የተለየህ እና አስደማሚው ፍጥረት ነህ። በዚህ ስለምንም ልትኮራ ይገባኃል። ባንተ ላይ ካንተ ውጪ እንደሌላው ተፈጥሮ ማዘዝ የሚችል ምንም የለም። የሜዳ አህያን አይተኃታል? በሷ ላይ ማዘዝ የሚችለው ሌላው እንስሳ ግን እሷስ እንዳልሆነች ታውቅ ይሆን? አንበሳስ ቢሆን በእሱ ላይ ማዘዝ የሚቻለው ሌላው እንስሳት ግን እሱ እንዳልሆነ ታውቅ ይሆን? እመን ግን አንተ ሰው በመሆንህ ብቻ ትልቁ ማንነት ሀሳብ ካንተ ጋር ስላለለ አንተን ነክሶም ሆነ አባሮ ሊያዝብህ የሚችል ፍጥረት የለም። ምክንያቱም አንተ የፈጣሪ ሀምሳሉ ኃያል ንጉስ ነህ።

• * *

*~~~~~~~~~~~~~~~› ‹‹ እኔ ልኖር እንጂ ልሞት አልተወለድኩም!!›› ‹~~~~~~~~~~~~~~~*

